# 2023-24

# የተማሪዎች የሥነ ምግባር ደንብ፥

# ክፍል ፡ ኬ-12

የተማሪዎች፣ የቤተሰቦች እና የሥራ ባልደረቦች መመሪያ ደንብ



Alexandria City Public Schools

# ማውጫ


ስለኤሲፒኤስ ...... 1

ውድ የ ACPS ቤተሰቦች ...... 2

የወላጅ/አሳዳጊ እንዲፈርሙ መጠየቅ...... 3

አስፈላጊ የ ACPS ዕውቂያ፣ አድራሻ መረጃ...... 4

የተማሪዎች፣ ወላጆች/ሞግዚቶች እና ሥራ ባልደረቦች የሚጠብቋቸው ሁኔታዎች ...... 5

መብቶችዎን ማወቅ እና ሃላፊነትዎን መወጣት...... 6

ለመጀመሪያ-ደረጃ ተማሪዎች፤ ቴክኖሎጂ (Technology)ን - ኃላፊነት-ባለው ሁኔታ የመጠቀም-ስምምነት...... 6

ለሁለተኛ-ደረጃ ተማሪዎች፤ ቴክኖሎጂ (Technology)ን - ኃላፊነት-ባለው ሁኔታ የመጠቀም-ስምምነት...... 8

በትምህርት ላይ መገኘት ...... 10

የተማሪዎች አለባበስ...... 11

የተማሪ መብቶች...... 11

የጣልቃ ገብ እርምጃዎች እና የስነ ምግባር ሥነ ሥርዓቶች ...... 13

በትምህርት ቤት ውስጥ ያሉአሳሳቢሁኔታዎችን ማስወገድ ...... 22

ፍተሻና ህገወጥ ንብረቶችን መያዝ...... 22

የስነምግባር እርምጃ መስጣት ሂደቶች...... 23

የስነ ምግባር ቃላት ትርጓሜ ...... 24

እግድ ...... 27

ከአካል ጉዳት ጋር የሚኖረ ተማሪዎች ስነ ምግባር ...... 31

ፀብአጫሪነትን መከላከል...... 35

አባሪዎች...... 37

አባሪ A፡ የትምህርት ልሕቀትና ፍትሃዊነት ...... 38

አባሪ B፡ ትክክለኛ የኮምፒውተር ሲስተም አጠቃቀም ፖሊሲ ...... 38

አባሪ C፡ የተማሪዎች የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ...... 39

አባሪ D፡ የክብር ኮድ ...... 40

አባሪ E፡ የተማሪ ስነ ምግባር ደረጃ ...... 42

አባሪ F፡ የተማሪ እገዳና ስንብት ...... 45

አባሪ G፡ ከህግ አስፈጻሚዎች ጋር ያለው ግንኙነት ...... 46

አባሪ H፡ እኩል የትምህርት ዕድሎች/ከአድሎ የጸዳ እና የተማሪ መዛግብት/FERPA...... 46

አባሪ I፡ የተማሪ ሕትመቶች ...... 47

አባሪ J: የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎችን ስነ ምግባር ማስያዝ...... 48

አባሪ K፡ ፍተሻ እና በቁጥጥር ስር ማዋል...... 50

አባሪ L፡ ለተማሪዎች መድሃኒት መስጠት...... 51

አባሪ M፡ የተማሪ ድርጅቶች (ሁለተኛ ደረጃ)...... 52

አባሪ N፡ ሐይማኖት በትምህርት ቤቶች ውስጥ...... 53

አባሪ O፡ ስለ አወዛጋቢ ጉዳዮች ማስተማር...... 53

አባሪ P፡ የውሲብ መደፈር/ በዘር ፣ ብሄራዊ ማንነት፣ የአካል ጉዳት፣ ሐይማኖት፣ እድሜ ፣ ፃታ፣ የፃታ ማንነት፣ የፃታ መገለጫ እና የውሲብ ምርጫ፣ / አስጨናቂ የስራ አካባቢ... 54

አባሪ Q፡ በትምህርት ቤቶች አልኮል እና ሌላ ድራግ...... 56

# ስለኤሲፒኤስ

## ተልእኳችን

ተማሪዎችን በማነሳሳት እና ለትምህርቱ እንቅፋቶችን በማቃለል ስኬትን ማረጋገጥ።

## ራዕያችን

ሁሉም ተማሪዎች በተለየ እና በሚለዋወጥ ዓለም ውስጥ እንዲበለጽጉ ኃይል መስጠት።

## ዋና እሴቶቻችን

**በምናደርገው ሁሉ፣ የ ACPS ትምህርት ማህበረሰብ እነዚህን መሠረታዊ እሴቶች ለመኖር ይጥራል። እኛ...**

**የምናስተናግደው፡** ሁሉም ባለድርሻ አካላት በት/ቤቶች ተቀባይነት ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ ንቁ እርምጃዎችን እንወስዳለን። በኛ በኩል የሚመጣውን ሁሉ እንቀበላለን እንዲሁም ልዩነቶቻችንን እናከብራለን ምክንያቱም ልዩነታችን ታላቁ ጥንካሬያችን ነው ብለን እናምናለን።

**የምናጠናክረው፡** እያንዳንዱ ተማሪ እና የሰራተኛ አባል በተቻላቸው አቅም ችሎታቸው እንዲዳብር እናበረታታለን።

**ፍትሃዊ-ተኮር:** ለትምህርታዊ ተደራሽነት እንቅፋቶችን ለማስወገድ በንቃት እንሰራለን።

**ፈጠራ፡** በመማሪያ ክፍል እና በስርዓቱ ውስጥ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት ተነሳሽነትን እንወስዳለን።

**ውጤት-ተኮር፡** በከፍተኛ ደረጃ ለመማር፣ ለማደግ እና ለማሳካት የታሰበ ግቦችን አውጥተናል።

## ግቦች

**ስልታዊ አሰላለፍ**
ACPS ለት/ቤት እና ለትምህርታዊ ማሻሻል ቀጣይነት ያለው መሻሻል እና ዲዛይን ፍትሃዊ ሥርዓቶችን ይቀርጻል።

**የመመሪያ ልቀት**

ACPS ሁሉም ተማሪዎች ጥራት ያለው ትምህርት ማግኘት እና መሳተፍ መቻላቸውን ያረጋግጣል።

**የተማሪ ተደራሽነት እና ድጋፍ**
ACPS ተማሪዎች የትምህርት እንቅፋቶችን የሚቀንሱ መርሃግብሮችን እና ድጋፎችን በእኩል ደረጃ ማግኘታቸውን እና ተሳትፎ ማድረጋቸውን ያረጋግጣል።

**ስልታዊ የግብዓት አመዳደብ**
ACPS ለት/ቤቶችና ለክፍሎች የተለያዩ ሀብቶችን እና ድጋፎችን ስልታዊ በሆነ መንገድ ያቀርባል።

**የቤተሰብና ማህበረሰብ ተሳትፎ**
ACPS ሁሉም ቤተሰቦች እና የህብረተሰቡ አባላት ተቀባይነት ያላቸው፣ የተከበሩ፣ እና ዋጋ ያላቸው እንደሆኑ እንዲሰማቸው ያደርጋል።

**የትምህርት ቤቶች ቁጥር**
1፣ Pre-K
12፣ የመጀመሪያ-ደረጃ/Elementary
2፣ ከK-8
2፣ መካከለኛ-ደረጃ (Middle)
1፣ ከፍተኛ-ደረጃ/High School (4 ካምፓሶች)
አጠቃላይ/Total 18

**የተማሪ ምዝገባ: 15,732***

* እስከ ሴፕቴምበር 30፣ 2022



እስያውያን/Asian: 6.6%
ጥቁር: 25.0%
ሂስፓኒክ/Hispanic: 37.7%
ነጭ: 26.6%
ተወላጅ ሃዋይዋን (Native Hawaiian)/ፓስፊክ አይላንቸር (Pacific Islander): 0.3%
ተወላጅ አሜሪካውያን/Native American: 0.1%
ባለብዙ-የዘር ድብልቅ (Multi-racial): 3.7%
የትውልድ አገሮች: 119
የአፍ-መፍቻ ቋንቋዎች/Native languages: 124

# ውድ የ ACPS ቤተሰቦች

ተማሪዎቻችንን ወደ ትምህርት ቤት መልሰን-በመቀበላችሁ ደስታ-ይሰማናል! የ2023-24 የትምህርት ዓመት፣ ለሁሉም ተማሪዎች - የተለያዩ-ነገሮች በመማሪያ-ክፍሎቻቸው፣ በትምህርት ቤቶች፣ በማህበረሰብ እና ሁልጊዜ-በሚቀያየረው ዓለማችን ውስጥ ያሉትን ለውጦች የሚያስተናግዱበትን-አቅም ይዘው የበለጠ ዝግጁ-ሆነው እንዲገኙ-ለማድረግ፤ ቃል-የሚገባበት-ዓመት ነው። የተማሪዎችን ተሳትፎ የሚንከባከብ፣ የባለቤትነት-ስሜት እና ግንኙነት-ያላቸው ዓይነት ስሜት-ያለው ጠንካራ-የትምህርት ቤት ባህልን ለመገንባት ትኩረት-እናደርጋለን፤ ተማሪዎች ያላቸውን የግል ታሪኮች እንዲያጋሩ ዕድሎችን እንሰጣለን፣ እና የሁሉንም ድምፆች ለማዳመጥ ዝግጁ-ነን። የእያንዳንዱን ተማሪ የየግል ገጽታዎችን ለመገንባት-የምንጠይቅ እና በእያንዳንዱ ተማሪ አዎንታዊ-የሆነ ባህሪይዎችን መገንባት ጠቃሚ-መሆኑን እውቅና-እንሰጣለን። በእያንዳንዱ-ቀን፤ እንደ የትምህርት ቤት ክፍል/school division ሆነን - ማህበራዊ ስሜታዊ ትምህርት (Social Emotional Learning (SEL))ን በማስፈጸም-ላይ ትኩረት መስጠታችንን እንቀጥላለን። 'SEL'፣ ልጆች እና አዋቂዎች - በሂደቱ አማካኝነት፣ ስሜቶችን የሚገነዘቡበት እና የሚቆጣጠሩበት እና አዎንታዊ የሆነ ግንኙነት/positive relationship እና የውሳኔ-አሰጣጥ ችሎታዎችን የሚያገኙበት ነው (CASEL, 2017)። በACPS ውስጥ፤ የቀለም-ትምህርትን ወደ 'SEL' ፕሮግራም እንከን-የለሽ በሆነ-መንገድ በማጣመር ከተማሪዎቻችን ጋር እንሰራለን። የምንሰራው-ስራ፣ 'SEAL' ተብሎም-ይታወቃል። የ'SEAL' ፕሮግራም የተቀረጸው፣ ትምህርትን-ለማበረታታት፤ ቀውስን-ጠቋሚ ከሆኑ ልምምዶች ጋር የአዕምሮ-ጤናን በሚደግፍ፣ መልሶ-መቋቋም የሚችል ጠንካራ የትምህርት ቤት ማህበረሰቦችን በመገንባት፣ እና በሁሉም የተማሪዎች ቁጥር-ዙሪያ ተገቢ-የሆነ እና እኩል-በሆነ ሁሉን-የሚመለከት አሰራርን በማቅረብ - አዎታዊ-የሆኑ ባህሪያቶች (positive behaviors)ን እያንዳንዱ ተማሪ እንዲያዳብሩ ለመርዳት የተቀረጸ-ነው።




በመማሪያ-ክፍሎቻችን እና በትምህርት ቤት ህንፃዎቻችን ውስጥ ፍትሃዊ-እኩልነትን ለሁሉም (equity for all) ላይ ትኩረት-በምናደርግበት ጊዜ፤ በየግል-ሁኔታ እና ሁሉን ባካተተ መልኩ፣ እያንዳንዱ ተማሪ ወደ መማሪያ-ክፍል የሚያመጣውን - ሰፊ-የሆነ ባህልን እና ስብጥር-ያለውን ተሞክሮዎች በሚያከብር-ሁኔታ፣ ጠንካራ ግንኙነቶችን ለመገንባት፣ ከእያንዳንዱ ተማሪ ጋር እንሰራለን። በዚህ የተማሪ፣ የሥነ-ምግባር ደንብ የመመሪያ-መጽሐፍ (Code of Conduct handbook) ውስጥ፣ አዎንታዊ-ባህሪይዎች (positive behaviors) ን ለማስተማር እና ዳግም-ለማስተማር የሚያግዙትን በዘርፍ-የተመደቡ ዘዴዎችን እንዴት እንደምንጠቀም ላይ ትኩረቶችን-ያደረገ መረጃዎች አሉት። በዕድገታዊ-ሁኔታ እና በባህላዊ-ጉዳዮች ላይ ምላሽ-ሰጪ የሆነውን፤ እርዳታ የምንሰጥበትን ዘርፍ-ያለውን ስርዓት (tiered system) ለመገንባት - የመከላከል ስልቶችን እንጠቀማለን። አዎንታዊ-የሆኑ ባህሪያቶች (positive behaviors)ን ለመማር ተጨማሪ እርዳታዎች እንደሚያስፈልጋቸው ላሳዩ-ተማሪዎች - እርዳታን-በመስጠት ላይ፤ በትምህርት ቤት ማህበረሰቦችን ውስጥ መልሶ-ወደነበረበት የመመለስ ልምዶች (restorative practices) ላይ ቁርጠኝነት-እየሰራን፤ እና ተማሪን እና ሠራተኛን በደህንነት በመማሪያ-ክፍሎቻቸው እና በትምህርት ቤት መጠበቅን - ዋነኛ-ተቀዳሚነትን በመስጠት ላይ እያለን - ከእገዳ/suspension ሌላ ያሉ አማራጮችን እንመለከታለን።

## የቨርጂኒያ ምሩቅ መገለጫ




የተማሪ ባህሪይ (Student behavior)፣ ተማሪዎች የሚያስፈልጓቸውን ነገሮችን፣ ለእኛ-የሚነግሩበት አንደኛው-መንገድ ነው። ትክክለኛውን ጣልቃ-ገብነት በመጠቀም እና በመገንዘብ - የተማሪዎቻችንን ፍላጎቶ ማሟላት፤ በትምህርት ቤት ውስጥ እንዲቀጥሉ የሚያደርጋቸው እና በቀለም-ትምህርት አካሄዳቸው እና በባህሪያዊ-ክንውናቸው እየበለጸጉ እንዲሄዱ የሚረዳቸው ነው። ይህ የተማሪ፣ የሥነ-ምግባር ደንብ የመመሪያ-መጽሐፍ (Code of Conduct handbook)፤ ተማሪዎች የማህበራዊ ችሎታዎችን ለማግኘት እና የሚጠበቅባቸውን ባህሪያቶች ለማሳየት ተጨማሪ-ጊዜ የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች በመርዳት-ላይ፤ የሚጠቀሟቸውን በጣም-የተለመዱ ዘርፍ-የተሰጣቸውን ጣልቃ-ገብነቶችን፣ ይዘረዝራል። አዎንታዊ የሆነ የባህሪይ-ለውጥን ለማበረታታት ከተሰጡት ጣልቃ-ገብነቶች ጎን-ለጎን ሆኖ የተወሰነ የስነ-ስርዓት እርምጃዎች (disciplinary actions)ን ሊያስከትሉ-የሚችሉትን - የማንጓጠጥ/bullying ባህሪያቶችን እና አላስፈላጊ-የሆኑ ፀባይን ሪፖርት-የማድረጊያ ሂደቶችንም አጋርተናችኋል።

ከልጃቸው (ጆቻቸው) ጋር ወላጆች ቁጭ-ብለው በዚህ የተማሪ፣ የሥነ-ምግባር ደንብ (Code of Conduct) ውስጥ ያሉትን ነገሮች በጥንቃቄ አብረው በማንበብ - ከእኛ-ጋር አጋርነትን እንዲፈጥሩ እንጠይቃለን። በባህሪያቸው የሚጠበቁባቸውን ነገሮች - ቤተሰቦች ከተማሪዎች ጋር ማጋራት-መቻላቸው - ወጥነት ያለው የሚጠበቅባቸውን አዎንታዊ-የሆነ ባህሪይን-ለማስቀመጥ የሚረዳ ሲሆን፤ ይህም - ወደ አዎንታዊ የቀለም ትምህርት ውጤታማነት ሊመራቸውን የሚችለው - በትምህርት ገበታ ላይ መገኘት (school attendance) ን ያካተተ-ነው። ይህን መረጃ ካነበባችሁ እና ከተወያያችሁበት በኋላ፤ በትምህርት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ በተሰጠው የ'Back to School' ቅጾች ውስጥ - እናንተ እና ልጃችሁ የ'ACPS Signature Form'ን መፈረማችሁን እባካችሁ እርግጠኛ-ሁኑ።

ተማሪዎቻችንን በተቻለ-መጠን ግሩም የሆነ ማንነታቸውን ጠብቀው-እንዲጓዙ ለመርዳት፤ እኛ በዚህ ጉዞ ውስጥ ከእናንተ ጋር አጋሮች-ነን፤ እና ደህንነቱ-የተጠበቀ እና ስርዓት ያለው የመማሪያ አካባቢዎችን ለሁሉም-መቅረቡን ለማረጋገጥ፣ ከእናንተ-ጋር በትብብር ለመስራት በጉጉት እንጠባበቃለን። ደህንነቱ-የተጠበቀ እና ስኬታማ የሆነ የትምህርት ዓመት ሆኖልን-ሁላችንም አብረን እንደሰት!

# የወላጅ/አሳዳጊ እንዲፈርሙ መጠየቅ

በ ACPS አቀባበል እሽግ ውስጥ የሚገኘውን የ **ACPS ፊርማ ቅጽ** በመፈረም እና በመመለስ፣ ወላጅ(ዎች)/አሳደጊ(ዎች) መብታቸውን በሕገ መንግስቱ ወይም በአሜሪካ ሕግ እና/ወይም የቨርጂኒያ ኮመንዌልዝ በህግ በተጠበቁ መልኩ በትምህርት ቤቱ ክፍል ፖሊሲዎች ወይም ውሳኔዎች ላይ አለመስማማትን የመግለጽ መብታቸውን ሳያነሱ በደንብ መግለጽ ይችላሉ። በሕጉ የሚጠየቀው፣ ይህ ቡክሌት፣ የሚከተሉትን ይይዛል፡

- ለተማሪዎች ኃላፊነት የሚሰማው የኮምፒውተር ስርዓት አጠቃቀም ፖሊሲ
- ግዴታ የትምህርት ቤት የአቴንዳንስ መረጃ
- የተማሪ ሥነ ምግባር መስፈርቶች
- ፍትሃዊነት እና ልቀት ፖሊሲ
- የክብር ኮድ

የተማሪ ሥነ ምግባርን እና የግዴታ ትምህርት ቤት መገኘትን ለማስፈፀም ወላጆች/አሳዳጊዎች የ ACPS ትምህርት ቤቶችን የመርዳት ግዴታ አለባቸው። ወላጆች/አሳዳጊዎች የስነምግባር ደንቡን የመረዳት፣ ተገቢ የተማሪን ስነምግባር የማሳደግ፣ ትምህርት ቤቱ የተማሪን ስነምግባር ሲያስጠብቅ ማገዝ፣ እና ከስነስርዓት እና ከት/ቤት የመገኘት ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ለመወያየት ከተጠየቁ፣ ከት/ቤት ባለስልጣናት ጋር የመገናኘት ሃላፊነት አለባቸው። ሕጉ በተጨማሪም ወላጆች/አሳዳጊዎች ኃላፊነቶቻቸውን እንደሚያውቁ የሚያሳይ መግለጫ እንዲፈርሙ ይጠይቃል። የሥነ ምግባር ደንቡን እንዳነበቡ እና እንደተረዱት በሚገልጸው በልጅዎ ወደ-ት/ቤት-መመለስ (Back-to-School) ቅጽ ፓኬት በሚገልጸው በ ACPS ፊርማ ቅጽ ላይ እባክዎን ይፈርሙ።

# አስፈላጊ የ ACPS ዕውቂያ፣ አድራሻ መረጃ

| ቢሮ | ስልክ | አስተዳዳሪ |
|---|---|---|
| የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች አገልግሎቶች | 703-619-8022 | የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች ዋና ዳይሬክተር |
| የቤተሰብ እና የማህበረሰብ ተሳትፎ ማዕከል (FACE፣ የቤተሰብና ማህበረሰብ ተሳትፎ ማዕከል) | 703-619-8055 | የማህበረሰብ አጋርነትና ተሳትፎ ዋና ዳይሬክተር |
| የትምህርት ቤት አመራር ቢሮ | 703-619-8020 | የት/ቤት አመራር ዋና ዳይሬክተር |
| የልዩ መመሪያ ቢሮ | 703-619-8023 | የልዩ ትምህርት ዋና ዳይሬክተር |
| የት/ቤት የተመጣጠነ ምግብ አገልግሎቶች ቢሮ | 703-619-8048 | የት/ቤት ስነ ምግብ ዳይሬክተር |
| የተማሪ አገልግሎቶች እና ፍትሃዊነት ዲፓርትመንት | 703-619-8036 | የተማሪዎች አገልግሎቶች ዋና ዳይሬክተር |
| የት/ቤት የማማከር አገልግሎቶች | 703-619-8157 | የተማሪዎች ድጋፍ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር |
| የት/ቤት የሳይኮሎጂ አገልግሎቶች | 703-619-8159 | የት/ቤት ስነ ልቦና ዳይሬክተር |
| የት/ቤት የማህበራዊ ስራ አገልግሎቶች | 703-619-8156 | የት/ቤት ማህበራዊ ስራ ዳይሬክተር |
| የቤት አልባ ትምህርት ግንኙነት/ የቤት ውስጥ አገልግሎቶች | 703-619-8134 | የቤት አልባ ግንኙነት/የቤት ውስጥ አገልግሎት አስተባባሪ |
| Truancy ጣልቃ ገብነት እና ድጋፍ | 703-619-8358 | ያለ በቂ ምክንያት ከት/ቤት መቅረትን የሚመለከት የአውትሪች ስፔሻሊስት |
| የት/ቤት የጤና አገልግሎቶች ቢሮ | 703-619-8162 | የት/ቤት ጤና አገልግሎቶች ዳይሬክተር |
| የ FACE ማእከል የሁለት ቋንቋ ወላጅ የመረጃ መስመር፣ ሰኞ - አርብ፣ 9 a.m - 1 p.m. | ለ ስፓኒሽ/እንግሊዝኛ፡ 571-775-9719<br>ለ አማርኛ/እንግሊዝኛ፡ 703-927-6866<br>ለ አረብኛ/እንግሊዝኛ፡ 703-927-7095 | |

# የተማሪዎች፣ ወላጆች/ሞግዚቶች እና ሥራ ባልደረቦች የሚጠብቋቸው ሁኔታዎች

የ ACPS ራዕይ እያንዳንዱ ተማሪ ለስኬት የሚያበቃውን እኩል እድል ያገኛል የሚለው ነው። እያንዳንዱ ተማሪ እንዲሳካለት፣ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ሥርዓታማ አካባቢን ጠብቆ ለማቆየት ሁላችንም አብረን መሥራት አለብን። የባህሪ ችሎታዎችን በግልፅ በመለየት እና በማስተማር እና በት/ቤታችን እና በማህበረሰባችን ውስጥ ተማሪዎች ተገቢ ባህሪያትን እንዲለማመዱ በርካታ እድሎችን በመስጠት በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ደጋፊ አካባቢን እንከባከባለን።

## ተማሪዎች፡-

ተማሪዎች ሙሉ የአስተውሎታዊ እምቅ አቅም ለማሳካት የሚጥሩበትን የትምህርት አካባቢ እንደሚያገኙ የመጠበቅ መብት አላቸው።

እያንዳንዱ ተማሪ፡-

- በእያንዳንዱ ቀን ለመማር ዝግጁ ሆነው ትምህርት ገበታቸው ላይ በሰዓቱ ይገኛሉ፣ እንዲሁም የትምህርት መሳሪያዎቻቸውን ይይዛሉ።
- ባለፈው ቀን በክፍል ውስጥ የተማሩትን ትምህርት ይከልሳሉ እንዲሁም ያልገባቸው ነገር ካለ ጥያቄ ይጠይቃሉ።
- የተማሪ የትምህርት እድሎችን ለማስፋፋት ከትምህርት ቤቱ ሰራተኛዎች ጋር አብረው ይሰራሉ።
- ችግሮች እንዳይፈጠሩ ለመከላከልና አንዳንድ ጊዜ ከተፈጠሩ ደግሞ በሰላማዊ መንገድና በትብብር ለመፍታት ትሁት፣ በአክብሮት የተሞሉና ተባባሪ ይሆናሉ።
- ከአዋቂዎች እርዳታ በመጠየቅ የክፍሉ ተማሪዎችና ጓደኛች ችግር እንዲርቁ ይጠብቃሉ።
- የተማሪዎችን፣ የሰራተኛዎችን ወይም የትምህርት ቤቱን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥሉ ስጋቶችን ወይም እክሎችን በትምህርት ቤት ወይም በቤት ላሉ ለሚታመኑ አዋዊች ይነግራሉ።

**የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ትራንስፖርት በመጠቀም ላይ ባሉበት ወቅት፤**

ተማሪዎች በትክክል ሃሳባቸውን ይገልፃሉ።

ተማሪዎች ሁሉንም የደህንነት አሰራሮች እና መመሪያዎችን ይከተላሉ፤

1. ከመነሻቸው ሰዓት በፊት በአውቶብስ ፌርማታ ላይ መገኘት
2. ስርዓት ባለው መልኩ ወደ አውቶቡስ መሳፈርና መውረድ
3. ከአውቶቡሱ ፊት ለፊት መንገዱን ማቋረጥ
4. መቀመጫቸውን በፍጥነት ማግኘት እና ምንጊዜም ተቀምጠው መቆየት
5. የሰውነት ክፍሎቻቸውን እና ሁሉንም እቃዎቻቸውን በራሳቸው መያዝና በአውቶቡስ ውስጥ ማድረግ
6. ሁሉንም መመሪያዎች በመከተል እና ተገቢ ቋንቋን በማንኛውም ጊዜ በመጠቀም ለአዋቂዎች፣ ለተማሪዎች እና ለራሳቸው አክብሮት ማሳየት።

## ወላጆችና አሳዳጊዎች

ተማሪዎቻችንን በት/ቤት ውስጥ እና በቤት ውስጥ ተገቢ ባህሪያትን ለማሳየት እንዲመርጡ ለመርዳት ወላጆች/አሳዳጊዎች የእኛ በጣም አስፈላጊ አጋሮች ናቸው።

ወላጆች የሚከተለውን በማድረግ ተማሪዎቻችንን እና ትምህርት ቤቶችን ማገዝ ይችላሉ፡-

- አዎንታዊ የሆነ የትምህርት አካባቢ እንዲኖር የሚያስችሉ መልካም ባህሪያትን ከተማሪዎች ጋር በመወያየት።
- ከትምህርት ቤቱ ሰራተኛዎች እና አስተዳደር ጋር በመደበኝነት በመገናኘት።
- ተማሪዎች በእያንዳንዱ ቀን ለመማር ዝግጁ ሆነው ትምህርት ገበታቸው ላይ በሰዓቱ እንዲገኙና የትምህርት መሳሪያዎቻቸውን እንዲይዙ በመጠበቅ።
- በትምህርት ቤት ውስጥ ተማሪዎች ላይ ተጽዕኖ የሚፈጥሩ ችግሮች ሲከሰቱ ከትምህርት ቤት ሰራተኛዎች ጋር በመመካከር።
- የተማሪዎችን፣ የሰራተኛዎችን ወይም የትምህርት ቤቱን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥሉ ስጋቶችን ወይም እክሎችን የሚመለከቱ ማንኛቸውም መረጃዎች ለትምህርት ቤቱ ሰራተኛዎች ሪፖርት በማድረግ።

## መምህራን እና ሰራተኞች

መምህራን እና ሠራተኞች በመማሪያ ክፍሎቻቸው ውስጥ ጠንካራ ተማሪ ማህበረሰቦችን የመገንባት ኃላፊነት አለባቸው። መምህራን እና ሰራተኞች አዎንታዊ የት/ቤት ባህርያት እንዲኖሩ ማገዝ ይችላሉ።

እያንዳንዱ መምህር/ሰራኛ የሚከተሉትን ማድረግ አለበት፡-

- ለመማር ማስተማር ሥራ ምቹ የሆነ አዎንታዊ የትምህርት ቤት አካባቢን ማጎልበት እና ማበረታታት።
- ለትምህርት ክፍል ከተማሪዎች የሚጠበቁ መልካም ሥነ ምግባሮችን ማቋቋም፣ ማሳተም፣ ማስተማር እና በወጥነት ማስፈፀም።
- ወደማይፈለጉ ባህሪያት ትኩረትን ከመሳብ ይልቅ በሚፈለጉ ባህሪያት ላይ ማተኮር።
- የስነ ምግባር ጉድለትን ለመከላከል እና በአዎንታዊ መልኩ ለመቅረፍ እርምጃ መውሰድ።
- በተደጋጋሚ የስነ ምግባር ጉድለት ሲያጋጥም ከትምህርት ቤቱ አማካሪ ጋር ወይም ከተማሪ ድጋፍ ቡድን (Student Support Team (SST)) ሌሎች አባላት ጋር መወያየት።
- ሁኔታው እንደዚህ ዓይነት እርምጃ የሚያስወስድ ከሆነ፣ አንድ ተማሪ ድጋፍ እና ጣልቃ ገብነት እርምጃ እንዲሰጠው ወደ ትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪ ያቅርቡ።

## አስተዳዳሪዎች

አስተዳዳሪዎች የትምህርት ቤቱን ህጎች እና ይህንን የተማሪዎች የስነምግባር ደንብ የማስተማር እና የማስፈጸም ኃላፊነት እና ስልጣን አላቸው። የሚወሰደውን የዲሲፕሊን እርምጃ ለመወሰን ተገቢውን ፍርድ መስጠት እና ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው።

የትምህርት ቤት አስተዳደር ቡድኑ የሚከተሉትን ማድረግ አለበት፡-

- አዎንታዊ ባህሪያት የሚማሩበት፣ የሚቀረፁበት እና የሚጠበቁበት አካባቢን መፍጠር።
- አዎንታዊ የትምህርት ቤት አካባቢን ለማሰደግ እና ለማስጠበቅ የትምህርት ቤቱን ሰተኞች መርዳት።
- ለሰራኞች፣ ተማሪዎች እና ቤተሰቦች የሚጠበቅባቸውን ነገር በግልጽ ማሳወቅ።
- የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ማንኛውንም የሥነ ምግባር እርምጃ ቢወስድም ባይወስድም አንድ ተማሪ ከትምህርት ቤት የሚሳግድ መልኩ የትምህርት ቤቱን ቦርድ ፖሊሲ ከጣሰ ይህንኑ ለተማሪው ወላጆችን/አሳዳጊዎች ማሳወቅ።
- አንድ ተማሪ ለትምህርት ቤቱ ዋና ኃላፊና ለቨርጂኒያ የትምህርት ቦርድ (Virginia Board of Education)ሪፖርት መደረግ የሚያስፈልገው ማንኛውም ችግር ላይ ከተሳተፈ ለተማሪው ወላጅ/አሳዳጊ ማስታወቅ።

አመቺ የሆነ የትራንስፖርት አሰራር መኖሩን ለማረጋገጥ የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ትራንስፖርት ከቤተሰቦችና ከትምህርት ቤቶች ጋር በሚከተሉት አማካኝነት ይተባበራሉ ፤

1. ግንኙነት መፍጠር
2. ደህንነት
3. ማክበር

***ግንኙነት መፍጠር፤*** *ደህንነትን በሚመለከት የሚጠበቁትን ባህሪዎች ግልፅ የሆኑ መመሪያዎችን እኛ እናሳውቃለን።*

***ደህንነት፤*** *ሁሉንም የደህንነት አሰራሮች እና መመሪያዎችን እኛ እንከተላለን።*

***ማክበር፤*** *በግንኙነታቻን እና በተግባራችን መያዊ ባህሪ በማሳየት ለሁሉም አዋቂዎች፣ ተማሪዎች እና ራሳችንን እኛ እናከብራለን ።*

# መብቶችዎን ማወቅ እና ሃላፊነትዎን መወጣት

ሁሉም የአሌክሳንድሪያ ከተማ የህዝብ ትምህርት ቤት (ACPS) ተማሪዎች በዩናይቲድ ስቴትስ እና በቨርጂኒያ የጋራ ብልጽግና ሕገ መንግስት እና ሕጎች ስር ሕጋዊ መብቶች እና ግለሰባዊ ነጻነቶች አሏቸው። የACPS ትምህርት ቤት ቦርድ ፖሊሲዎች እና ደንቦች እነዚህን መብቶች ይደግፋሉ። ተማሪዎች የሌሎችን መብት እስካልነኩ ወይም በትምህርት ቤቱ ደህንነቱ የተጠበቀ የትምህርት አካባቢ እና የትምህርት እድሎችን የማቅረብ ችሎታ ላይ ጣልቃ እስካልገቡ ድረስ እነዚህን መብቶች መጠቀም ይችላሉ። እንደ ተማሪ ከነዚህ መብቶች ተያይዘው ሃላፊነቶችም ይመጣሉ። ይህ ዝርዝር ምንም እንኳን የተሟላ ባይሆንም፣ በትምህርት/ት/ቤት ቅንብር ውስጥ ተፈጻሚ የሆኑትን አብዛኛዎቹን መብቶች አጉልቶ ያሳያል።

ለተማሪው የሥነ ምግባር ደንብ፣ የትምህርት/ትምህርት ቤት ቅንብር ወይም ክልል የሚያካትተው፡ በትምህርት ቤት ውስጥ ወይም በትምህርት ቤቱ ይዞታ ላይ ሲኮን፣ በትምህርት ቤቱ ተሽከርካሪ ላይ፣ በትምህርት ቤቱ ድጋፍ የተዘጋጀ ተግባር ወይም ጉዞ ላይ በሚሳተፉበት ወይም በሚካፈሉበት ወቅት፣ ወደ ት/ቤት እና ከት/ቤት ጉዞ ላይ፣ እንዲሁም ከትምህርት ቤቱ ይዞታ ውጪ ሆኖ ባህሪው ወይም ድርጊቱ በወንጀል መጠየቅን ሲያስከትል ( Va. Code - 16.1-305.1. ይመልከቱ)

ከታች የተዘረዘሩት የትምህርት ቤት ቦርድ ፖሊሲዎች ሁሉንም ተፈጻሚ ፖሊሲዎች ላይወክሉ ይችላሉ። በተጨማሪም፣ የመብት ጥሰቶች በተማሪው የሥነ ምግባር ደንብ ውስጥ ለተዘረዘሩት የጣልቃ ገብነት እርምጃዎች እና/ወይም የሥነ ምግባር ቅጣቶች ሊዳርጉ ይችላሉ።

# ለመጀመሪያ-ደረጃ ተማሪዎች፤ ቴክኖሎጂ (Technology)ን - ኃላፊነት-ባለው ሁኔታ የመጠቀም-ስምምነት

በአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ውስጥ የሚገኙ-ተማሪዎች፤ ለመማር፣ ለመፍጠር፣ እና በተለያዩ ዓይነት እንቅስቃሴዎች ውስጥ መሳተፍ እንዲችሉ፤ የACPS-ባለቤትነት ያላቸውን ዲቫይሶች (ACPS-owned devices) ተውሰው-እንዲጠቀሙበት ተሰጥቷቸዋል። ስኬታማ-ለመሆን - እነዚህን ዲቫይሶች ማግኘት-መቻላቸው፣ ለተማሪዎች በጣም-ጠቃሚ ነው። በሚጠቀሙባቸውም-ጊዜ፤ ኃላፊነት-የሚወስዱ እና ክብር-የሚሰጡ - የዲጂታል ዜጎች (digital citizens) መሆን-አለባቸው።

የACPSን ደንቦች (ፖሊሲዎችን፣ ክንውኖች፣ እና መመሪያዎችን) የማይከተሉ-ተማሪዎች፤ የተለያዩ-ዓይነት የሚያስከትሉ ቅጣቶች (consequences)ን ያገኛሉ። እነዚህ ቅጣቶችን የሚያስከትሉ-ነገሮች (consequences) ሊያካትቱ-የሚችሉት፤ እንደ ከርዕሰ-መምህር/ረዳት ርዕሰ መምህር ጋር መሰብሰብ፣ የወላጅ ስብሰባ፣ ዲቫይሶችን ውሱን-በሆነ ሁኔታ መጠቀም፣ ዲቪይሱ እንዲቀማ-ማድረግ፣ የሕግ-አስከባሪ (law enforcement)ን ማነጋገር፣ ወዘተ... ሊሆን ይችላል።

**እኔ የሚከተሉትን አደርጋለሁ:**

- ቴክኖሎጂን በመጠቀም-ጊዜ፣ ሁሉንም የACPS እና የመማሪያ-ክፍል ደንቦችን፣ ፖሊሲዎችን፣ ክንውኖችን እና መመሪያዎችን፤ መከተል።
- ሁሉንም የACPS ቴክኖሎጂን - ከትምህርት-ጋር ግንኙነት ያላቸውን ስራዎች በፋይሎች እና ፕሮጀክቶች ለማስቀመጥ፣ ምርምር/research ለማካሄድ፣ እና መተግበሪያዎች/applications ("apps")ን በክሌቨር/Clever አማካኝነት ለማግኘት እጠቀማለሁ።
- የመጠቀሚያ-ስሞቼን (usernames) እና የሚስጢር መግቢያ-ኮዶቼን (passwords) - የእኔን የጉግል የመጠቀሚያ-ስም (username) እና የመግቢያ-ኮድ (password)ን ጨምሮ - ለግሌ-ብቻ ጠብቄ-እይዛለሁ።
- የእኔን ዲቫይስ፤ እንደ ለመማሪያ መሣሪያ አድርጌ እጠቀማለሁ። መጫወቻ/toy እንዳልሆነ የተገነዘብኩ እና፣ አስተማሪዬ - ዲቪይሶቹን ለመጠቀም እና በስራዬ-ላይ ለመቆየት የሚሰጡኝን-ትዕዛዞች እከተላለሁ።
- ከዲቫይሴ፤ ምግብ እና መጠጦች - እንዳያበላሸው አርቄ-እጠብቃለሁ።
- ዲቫይሴን በምይዝበት-ጊዜ ጥንቃቄ አደርጋለሁ።
- ሌሎችን በተገቢው-ሁኔታ በመንከባከብ ከአክብሮት እና ተገቢ-የሆነ ቋንቋን - ከሌሎች ጋር በማደርገው - በሁሉም የዲጂታል የእርስ-በርስ ግንኙነቶች ውስጥ እጠቀማለሁ።
- ያልተመቻቸ-ስሜት የሚፈጥርብኝ ወይም የሚያሳዝን-ስሜት የሚፈጥርብኝ - የዲጂታል አስተያየት ወይም ግንኙነት-ማድረጊያ/communication ከተቀበልኩኝ፤ ወይም ተገቢ-ያልሆኑ ቁሳቁሶችን/materials፣ ምስሎችን/pictures፣ ቪዲዮዎችን ወይም ድህረ-ገጾችን ሳላውቅ-ከከፈትኩኝ፤ ወዲያውኑ ለማምነው-አዋቂ ሰው እነግራለሁ።

**እኔ የሚከተሉትን አላደርግም:**

- የዲቫይስ ቴክኖሎጂ የመገኛ-ምንጮችን፤ አወዛጋቢ-የሆኑ መረጃዎችን ወይም ለማግኘት፣ ለመፍጠር፣ ወይም መረጃዎችን-በመላክ ለማሰራጨት፤ ወይም ለመተንኮስ፣ ለመጉዳት፣ ለማንጓጠጥ ወይም አንዱን-ከሌላው አድልዎ-በሚያሳዩ መጠቀም።

- ፈቃድ-የሌለውን ወይም ተገቢ ያልሆኑ የክፍሉን የቴክኖሎጂ የመረጃ-ምንጮች (Division technology resources)ን ለማግኘት - ቴክኖሎጂን መጠቀም። (ለምሳሌ: የሌላ-ተጠቃሚ - አካውንቶች-ውስጥ መግባት)
- ተገቢ-ያልሆነ ቋንቋ (inappropriate language)ን፣ ምስሎች/pictures፣ ወይም ሌላ ዲጂታል ይዘትን - መጠቀም፣ መውጣት፣ ማስቀመጥ ወይም መላክ።
- በትምህርት ቤት ንብረት-ውስጥ - በትምህርት-ሰዓታት ውስጥ እያሉ፤ የግል ዋይፋይ/personal wifi አካውንቶችን በመጠቀም-ወይም በሌላ-ማንኛውም መንገድን በመጠቀም፤ ተገቢ-ያልሆኑ ነገሮችን ማግኘት ወይም የታገዱ-የመረጃ ምንጮችን (blocked resources)ን መጠቀም።
- ጽሁፍን ኮፒ-ማድረግ እና/ወይም ምስሎችን ካለፈቃድ መልሶ-መጠቀም (የቅጂ-መብት/copyright ሕጎችን መጣስ)።
- ዲቫይሴን ሌሎች-ሰው እንዲጠቀምበት መፍቀድ፤ ጓደኞችን እና ወንድና-እህቶችን ጨምሮ።
- የሌሎች ተማሪዎችን የመጠቀሚያ-ስሞች (usernames) እና የመግቢያ-ኮዶች (passwords)ን መጠቀም፣ እና/ወይም ወደ ሌላ-ተማሪ አካውንቶች ውስጥ መግባት (log in ማድረግ)።
- በኦንላይን-ላይ፣ የግል-መረጃዎችን ማጋራት (ሙሉ-ስም፣ አድራሻ፣ የልደት-ቀን፣ ትምህርት ቤት፣ ስልክ-ቁጥር)።
- የሌሎችን ስራ፣ ትምህርት ቤት ወይም የግል አካውንቶችን ወይም ፋይሎችን - መተላለፍ (Trespass) እና/ወይም ማምታታት (manipulate)።
- ከACPS የቴክኖሎጂ አገልግሎቶች - ግልጽ-የሆነ ፈቃድ ሳላገኝ - ከአሜሪካ አገር ውጪ ዲቫይሴን ይዤ መሄድ።

**እኔ፣ የሚከተሉትን ተረድቻለሁ:**

- የACPS ቴክኖሎጂን መጠቀም የተሰጠኝ-ዕድል ነው፤ እና ደንቦቹን ካልተከተልኩኝ - ግደባ-የሚደረግብኝ ወይም የተሰጠኝ-ዕድል ሊወሰድብኝ-ይችላል።
- ACPS ቴክኖሎጂውን - በመቆጣጠር እና የተማሪውችን አጠቃቀም በመገደብ ቁጥጥር-የማድረግ መብት አለው። ACPS፤ ማንኛውንም ለተማሪ የተመደበውን ዲቫይስ ለመፈተሽ እና ለመውሰድ፣ ለውጥ-ለማድረግ ወይም በተማሪው የተፈጠሩትን፣ የተቀበሏቸውን ወይም የተጠቀሟቸውን የመረጃ-ስብስብ/data (መረጃ)ን - ሊያጠፋው ይችላል።
- ማንኛውንም ስራዬን ለመስራት ዲቫይሴን በምጠቀምበት ጊዜ፤ በመማሪያ-ክፍል ቦታ ውስጥ እንዳለሁ-አድርጌ አከናውናለሁ። በመማሪያ-ክፍል ውስጥ የማንጠቀመው የባህሪይ እና ቋንቋ ደንቦች፤ ዲቫይሶችን በምንጠቀምበትም-ጊዜ - በማንኛውም በቀኑ-ሰዓት ላይ ቢሆንም-እንኳን፣ እነዚህ ደንቦችን ተከትሎ የማንጠቀም-ይሆናል።
- በኦንላይን የመማሪያ ቦታዎች የሚሰጡ የቤት/የክፍል ስራዎች (Assignments) ልክ-እንደ ማንኛውም በትምህርት ቤት የሚሰጡ የቤት/የክፍል ስራዎች ናቸው፤ እና በተማሪ የሥነ-ምግባር ደንብ የመመሪያ-መጽሐፍ (Code of Conduct Handbook) ውስጥ-እንዳለው-ሁሉ፣ ፖሊሲዎችን እና ክንውኖችን መከተል - ሁሉንም ፖሊሲዎች ማጭበርበር/cheating፣ የሰውን-ሃሳብ መውሰድ/plagiarism፣ እና ቴክኖሎጂን ኃላፊነት-ወስዶ መጠቀምን-በተመለከተ ጨምሮ መከተል-ይጠበቅባቸዋል።
- የትምህርት ቤቱ ክፍሉ/school Division፤ ወደ ትምህርት ቤት ንብረቱ-ውስጥ ስለመጡ ማንኛውም የግል የኤሌክትሮኒክ ዲቫይሶች ኃላፊነት አይኖረውም።
- በዚህ ስምምነት ውስጥ የተጠቀሱን ደንቦች ባለመከተል እና ሌሎች የACPS ፖሊሲዎች፣ ክንውኖች፣ መመሪያዎች፣ እና የተማሪ፣ የሥነ-ምግባር ደንብ (Code of Conduct)ን ባለመከተል፤ ሊገጥመኝ የሚችሉ ቅጣቶች (consequences) አሉ።

ከዚህ በታች-በመፈረም፤ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools)ን - ለመጀመሪያ-ደረጃ ተማሪዎች፤ ቴክኖሎጂን - ኃላፊነት-ባለው ሁኔታ የመጠቀም-ስምምነት (Responsible Use of Technology Agreement for Elementary Students)ን ለመከተል፤ ተስማምቻለሁ። የክፍሉን የቴክኖሎጂ የመረጃ-ምንጮች (Division technology resources)ን መጠቀሜ - ለእኔ የተሰጠኝ ዕድል የሆነ እና፣ ደንቦቹን በመከተል ጥሩ የዲጂታል ዜጋ (digital citizen) መሆን እንደሚያስፈልገኝ፤ ተገንዝቤአለሁ።

የተማሪ ስም:

የተማሪ የጉግል የተጠቃሚ-ስም (Google Username):

የተማሪ ፊርማ:

ቀን:

**የወላጅ/አሳዳጊ ማስታወቂያ እና ፈቃድ-መስጫ**

**ፊልተር/Filter**

ክፍሉ/The Division፤ ከበርካታ የቴክኖሎጂ የመገኛ-ምንጮችን ማግኘት እንዲችሉ - ሰፊ-የሆነ ትምህርታዊ የመረጃ-ምንጮችን በኢንተርኔት/internet አማካኝነት ማቅረብን-ጨምሮ፤ ለተማሪዎች ያቀርባል። ክፍሉ/The Division፤ ከ'ልጆች የኢንተርኔት ጥበቃ ድንጋጌ (Children's Internet Protection Act (CIPA)' ጋር አብሮ-በሚሄድ ሁኔታ፤ ኢንተርኔትን ማግኘት የሚችሉ ሁሉም የትምህርት ቤት ኮምፒውተሮች፣ ተቀባይነት ከሌላቸው የድህረ-ገጽ ይዘቶች ለመጠበቅ፤ ይዘቱን የማጣራት-ሂደት/filtering ማካሄጃ ቴክኖሎጂን ይጠቀማል። ሆኖም-ግን፤ ምንም-ዓይነት የድህረ-ገጽ ማጣሪያ (web filtering) ሙቶ-በሙቶ/100% ደህንነቱ-የተጠበቀ ባለመሆኑ ምክንያት፤ ክፍሉ/Division፣ የኦንላይን እንቅስቃሴ ቁጥጥርን ለማድረግ ጥረት-ያደርጋል።

**በመኖሪያ-ቤት ማግኘት እና ቁጥጥር (Home Access and Monitoring)**

ክፍሉ/Division፤ ለወላጆች/አሳዳጊዎች - የተማሪያቸውን የኢንተርኔት አጠቃቀም በትምህርት ቤት በተሰጣቸው ዲቫይስ ላይ፣ ከትምህርት ቤት ውጪ በሚሆኑ ጊዜ ለመቆጣጠር የሚያስችላቸውን መሣሪያ/tool በመስጠት-እያገለገላቸው ባለበት-ጊዜ፤ ልክ-እንደ ሌሎቹ የመረጃ-ምንጮች - እንደ ቴሌቪዥን፣ ራዲዮ፣ ፊልሞች እና ሌላ ሚዲያ/media - ላይ ልክ እንደሚያደርጉት ሁሉ፣ ስለ ኢንተርኔት-አጠቃቀም መመሪያን በመስጠት - ወላጆች/አሳዳጊዎች ኃላፊነት አለባቸው። ወላጆች/አሳዳጊዎች - በልጆቻው የኢንተርኔት አጠቃቀም ላይ ክትትል-የማድረግ እና፣ - የኦንላይን መማሪያ ቦታዎች/online learning spaces፣ የትብብር-ማድረጊያ መሣሪያዎች/collaboration tools፣ እና የትምህርታዊ የመገኛ-ምንጮች/educational resourcesን ጨምሮ - የክፍሉ/Division የቴክኖሎጂ የመገኛ-ምንጮች በማግኘት-ላይ ክትትል-የማድረግ ኃላፊነት-አለባቸው።

**የዲቫይስ መበላሸት (Damage)/መልሶ-መተካት (Replacement)**

ተማሪዎች፤ ከትምህርት ቤት በተሰጧቸው ዲቫይሶች ላይ እንክብካቤ በማድረግ እና በአጠቃቀሙ ላይ ኃላፊነት-አለባቸው። ብልሽት (Damage) እና/ወይም መጥፋት(loss) በሚከሰት-ጊዜ፤ ከዚህ-በታች የተመለከቱትን ክፍያዎች-ጨምሩ ሊያስከትሉ የሚችሉት ቅጣቶች (consequences) አሉት: ክፍያዎች - በአከፋፈል ስምምነት (payment plan) ሊከፈል ይችላል፤ ወይም በትምህርት ቤቱ ውሳኔ

- በአስፈላጊነቱ-ላይ መሠረት አድርጉ አማራጭ-በሆነ የሚያስከትሉ-ቅጣቶች (consequences) አማካኝነት-ሊከናወን ይችላል።

| | በድንገት-የተከሰተ ብልሽት (Accidental Damage) | ሆን-ተብሎ የተደረገ ብልሽት (Intentional Damage)* | መጥፋት/Loss |
|---|---|---|---|
| ክሮምቡክ (Chromebook) | $25 | እስከ $200 | እስከ $200 |
| ታብሌት (Tablet) | $25 | እስከ $100 | እስከ $100 |
| ቻርጀር (Charger) | | | $30 |

*የብልሽት ክፍያዎች የሚወሰኑት፤ በጥገና አድራጊው ቴክኒሺያን ለመስራት-በሚያስፈልገው ተቀያሪ ዕቃዎች/ዲቫይስ መተኪታ (device replacement) ላይ መሠረት-አድርጎ የሚወሰን-ነው።

ከዚህ-በታች በመፈረም፤ በኃላፊነት የመጠቀም-ስምምነቱን መመልከቴን - አረጋግጣለሁ።

የወላጅ/አሳዳጊ ስም:

የወላጅ/አሳዳጊ ፊርማ:

ቀን:

# ለሁለተኛ-ደረጃ ተማሪዎች፤ ቴክኖሎጂ (Technology)ን - ኃላፊነት-ባለው ሁኔታ የመጠቀም-ስምምነት

በአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ውስጥ የሚገኙ-ተማሪዎች፤ የመረጃ-ምንጭን ለማጋራት፣ ለፈጠራ፣ እና በማስተማር እና መማር ውስጥ ግንኙነት/communication በማድረግ-ለማበረታታት እንዲችሉ፤ የACPS-ባለቤትነት ያላቸውን ዲቫይሶች (ACPS-owned devices) ተሰጥቷቸዋል። ኮምፒውተርን ማግኘት እና ኢንተርኔትን ማግኘት፣ ዲጂታል ግንኙነት/digital communication፣ የትብብር-ማድረጊያ መሣሪያዎች/collaboration tools፣ እና የኦንላይን የመማሪያ ቦታዎች - ለመማሪያ-አካባቢ (learning environment) ወሳኝ-ሆኖ የሚያስፈልግ-ነው።

ከዲቫይስ ፖሊሲዎች፣ ከንውኖች፣ እና መመሪያዎች- ተከትሎ - የዲቫይስ የመረጃ-ምንጮችን መጠቀም አለመቻል፤ በትምህርት ቤቱ ውሳኔ - የስነ-ስርዓት እርምጃ (disciplinary action)ን ሊያስከትል-ይችላል። ከክፍሉ የተማሪ የተማሪ፣ የሥነ-ምግባር ደንብ (Code of Conduct) በተጨማሪ-ሆኖ፤ ማንኛውም የኔትወርክ አለአግባብ-መጠቀም (network misuse)፣ ወይም ህገ-ወጥ እንቅስቃሴዎች፤ ከተማሪው ወላጅ/አሳዳጊ ጋር ግንኙነት-ማድረግን ሊያስከትል የሚችል፣ ወይም ሕግን-የመጣስ ሁኔታ ተፈጽሞ-ከሆነ ደግሞ የሕግ-አስከባሪ (law enforcement)ን - ማነጋገርን ሊያስከትል-ይችላል።

**እኔ የሚከተሉትን አደርጋለሁ:**

- ቴክኖሎጂን በመጠቀም-ጊዜ፣ ሁሉንም የክፍል/Division እና የመማሪያ-ክፍል ፖሊሲዎችን፣ ከንውኖችን እና መመሪያዎችን፤ መከተል።
- ሁሉንም የክፍል/Division የቴክኖሎጂ የመረጃ-ምንጮችን - ከትምህርት-ጋር ግንኙነት ያላቸውን ስራዎች በፋይሎች እና ፕሮጀክቶች ውስጥ ለማስቀመጥ፣ ምርምር/research፣ እና የኮሌጅ እና የስራ-መስክ ዕቅድ-ለማውጣት እጠቀማለሁ።
- የመጠቀሚያ-ስሜ (username)ን እና የሚስጢር መግቢያ-ኮዴ (password) ን - ለግሌ-ብቻ ጠብቄ-ማያዝ።
- ሌሎችን በተገቢው-ሁኔታ በመንከባከብ ከአክብሮት እና ተገቢ-የሆነ ቋንቋን - ከሌሎች ጋር በማደርገው - በሁሉም የዲጂታል የእርስ-በርስ ግንኙነቶች ውስጥ እጠቀማለሁ።
- ያልተመቻቸ-ስሜት የሚፈጥርብኝ - የዲጂታል አስተያየት ወይም ግንኙነት-ማድረጊያ/communication ከተቀበልኩኝ፤ ወይም ተገቢ-ያልሆኑ ቁሳቁሶችን/materials፣ ምስሎችን/pictures፣ ቪዲዮዎችን ወይም ድህረ-ገጾችን ሳላውቅ-ከከፈትኩኝ፤ ወዲያውኑ ለACPS የሠራተኝ-አባል፣ እነግራለሁ።

**እኔ የሚከተሉትን አላደርግም:**

- የዲቫይስ ቴክኖሎጂ የመገኛ-ምንጮችን፤ አወዛጋቢ-የሆኑ መረጃዎችን ወይም ለማግኘት፣ ለመፍጠር፣ ወይም መረጃዎችን-በመላክ ለማሰራጨት፤ ወይም ለመተንኮስ፣ ለመጉዳት፣ ለማንጓጠጥ/bully፣ ወይም አንዱን-ከሌላው አድልዎ-በሚያሳዩ መጠቀም።
- ፈቃድ-የሌለውን ወይም ተገቢ ያልሆኑ የክፍሉን የቴክኖሎጂ የመረጃ-ምንጮች (Division technology resources)ን ለማግኘት - ቴክኖሎጂን መጠቀም። (ለምሳሌ: የሌላ-ተጠቃሚ - አካውንቶች-ውስጥ መግባት)
- ተገቢ-ያልሆነ ቋንቋ (inappropriate language)ን፣ ምስሎች/pictures፣ ወይም ሌላ ዲጂታል ይዘትን - መጠቀም፣ መውጣት፣ ማስቀመጥ፣ ወይም መላክ።
- በትምህርት ቤት ንብረት-ውስጥ - በትምህርት-ሰዓታት ውስጥ እያሉ፤ የግል ዋይፋይ/personal wifi አካውንቶችን በመጠቀም-ወይም በሌላ-ማንኛውም መንገድን በመጠቀም፤ ተገቢ-ያልሆኑ ነገሮችን ማግኘት ወይም የታገዱ-የመረጃ ምንጮችን (blocked resources)ን መጠቀም።
- የቅጂ-መብት/copyright ሕጎችን መጣስ (ጽሁፍን ኮፒ-ማድረግ እና/ወይም ምስሎችን ካለፈቃድ መልሶ-መጠቀም)።
- የሌሎች ተማሪዎችን የመጠቀሚያ-ስሞች (usernames) እና የመግቢያ-ኮዶች (passwords)ን መጠቀም፣ እና/ወይም ወደ ሌላ-ተማሪ አካውንቶች ውስጥ መግባት (log in ማድረግ)።

- የሌሎችን ስራ፣ ትምህርት ቤት፣ ወይም የግል አካውንቶችን ወይም ፋይሎችን - መተላለፍ (Trespass) እና/ወይም ማምታታት (manipulate)።
- ከACPS የቴክኖሎጂ አገልግሎቶች - ግልጽ-የሆነ ፈቃድ ሳላገኝ - ከአሜሪካ አገር ውጪ ዲቫይሴን ይዤ መሄድ።

**እኔ፣ የሚከተሉትን ተረድቻለሁ:**

- የክፍሉን የቴክኖሎጂ የመረጃ-ምንጮች (Division technology resources) ን መጠቀም - ኔትወርክስ/networks፣ ኮምፒውተሮች፣ ወይም የሞባይል-ዲቫይሶችን ጨምሮ፤ እና የኢንተርኔት የማግኘት ዕድል፤ በማንኛውም-ጊዜ አለአግባብ-መጠቀም ወይም በደል-ፈፃሚነት ፀባይ በሚታይ-ጊዜ - ሊከለከል፣ ሊሰረዝ፣ ወይም ገደብ-ሊደረግበት ይችላል።
- ክፍሉ/Division፤ ማንኛውን የቴክኖሎጂ የመረጃ-ምንጮቹን ለመቆጣጠር፣ እና የተማሪው የቴክኖሎጂ የመረጃ-ምንጮች ላይ ክትትል-ለማድረግ ወይም ግደባ-ለማድረግ - መብቱን ጠብቆ-ይሠራል። ክፍሉ/The Division፤ ማንኛውንም ለተማሪው የተመደበውን ኮምፒውተር፣ ሞባይል፣ ዲቫይስ፣ ወይም የኤሌክትሮኒች ማጠራቀሚያ ዲቫይስ ሊፈትሽ-የሚችል፤ ወይም በማንኛውም በክፍሉ/Division ኮምፒውተር ወይም ኔትወርክ/network ላይ ጥቅም-ላይ የዋለውን - ለማግኘት፣ ለመቀየር፣ እና ማንኛውንም የተፈጠረውን፣ የተቀበሉትን፣ ወይም በተጠቃሚው የክፍሉ የቴክኖሎጂ የመረጃ-ምንጮች (Division technology resources)ን በመጠቀም ያስቀመጡትን - ሊያጠፋው ይችላል።
- የክፍሉ የቴክኖሎጂ የመረጃ-ምንጮች (Division technology resources) ን በመጠቀም ለሚደርሰው ሁሉ ተጠያቂነቱ የእናንተ-ነው፤ ሲስተም/system የሚቀርበው "እንደተገኘ/as available" በሚለው-የአሰራር መንገድ-ነው፤ ችግሩን-የፈጠረው ምክንያት ምንም-ሆነ ምን በሲስተሙ/system ላይ የተቀመጠው ማንኛውም የመረጃ-ስብስብ (data) ለሚገጥመው ማንኛውም መጥፋት፣ በበላሽት፣ ወይም አለመገኘት - ክፍሉ/Division ኃላፊነት-አይወስድም።
- የኦንላይን የመማሪያ ቦታዎች/Online learning spaces፣ ግንኙነት/communication፣ እና ትብብር-የማድረጊያ መሣሪያዎች/collaboration tools - ልክ እንደ የመማሪያ-ክፍል ቦታ ሆኖ መታየት አለበት፤ እና በአካላዊ-ሁኔታ በሚገኙበት የመማሪያ-ክፍል ውስጥ ተገቢ-ያልሆነ ቋንቋ እና ባህሪይ - በኦንላይን ቦታዎቹ (online spaces) ውስጥም፤ በቀኑ-በየትኛውም ሰዓት ላይ እነዚህን ቦታዎች/spaces ቢጠቀሙም-እንኳን፤ መጠቀም-የለባቸውም።
- በኦንላይን የመማሪያ ቦታዎች የሚሰጡ የቤት/የክፍል ስራዎች (Assignments) ልክ-እንደ ማንኛውም በትምህርት ቤት የሚሰጡ የቤት/የክፍል ስራዎች ናቸው፤ እና በተማሪ የሥነ-ምግባር ደንብ የመመሪያ-መጽሐፍ (Code of Conduct Handbook) ውስጥ-እንዳለው-ሁሉ፣ ፖሊሲዎችን እና ክንውኖችን መከተል - ሁሉንም ፖሊሲዎች ማጭበርበር/cheating፣ የሰውን-ሃሳብ መውሰድ/plagiarism፣ እና ቴክኖሎጂን ኃላፊነት-ወስዶ መጠቀምን-በተመለከተ ጨምሮ መከተል-ይጠበቅባቸዋል።
- የትምህርት ቤቱ ክፍሉ/school Division፤ ወደ ትምህርት ቤት ንብረቱ-ውስጥ ስለመጡ ማንኛውም የግል የኤሌክትሮኒክ ዲቫይሶች ኃላፊነት አይኖረውም።
- የክፍሉ/Division ፖሊሲዎችን፣ ክንውኖችን፣ መመሪያዎችን፣ ወይም የተማሪ፣ የሥነ-ምግባር ደንብ (Code of Conduct) በመጣስ - ቴክኖሎጂን መጠቀሜ፤ ለስነስርዓት እርምጃ (disciplinary action) ተጋላጭ-ሊያደርገኝ ይችላል።

ከዚህ በታች-በመፈረም፤ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools)ን - ለሁለተኛ-ደረጃ ተማሪዎች፤ ቴክኖሎጂን - ኃላፊነት-ባለው ሁኔታ የመጠቀም-ስምምነት (Responsible Use of Technology Agreement for Secondary Students)ን ለመከተል፤ ተስማምቻለሁ። የክፍሉን የቴክኖሎጂ የመረጃ-ምንጮች (Division technology resources) እኔ መጠቀም-መቻሌ የተሰጠኝ ዕድል-የሆነ እና ተገቢ-የሆነ የኦንላይን ባህሪይ (online behavior) መኖር እንዳለበት፤ ተገንዝቤአለሁ።

የተማሪ ስም:

የተማሪ የጉግል የተጠቃሚ-ስም (Google Username):

የተማሪ ፊርማ:

ቀን:

**የወላጅ/አሳዳጊ ማስታወቂያ እና ፈቃድ-መስጫ**

**ፊልተር/Filter**

ክፍሉ/The Division፤ ከበርካታ የቴክኖሎጂ የመገኛ-ምንጮችን ማግኘት እንዲችሉ - ሰፊ-የሆነ ትምህርታዊ የመረጃ-ምንጮችን በኢንተርኔት/internet አማካኝነት ማቅረብን-ጨምሮ፤ ለተማሪዎች ያቀርባል። ክፍሉ/The Division፤ ከ'ልጆች የኢንተርኔት ጥበቃ ድንጋጌ (Children's Internet Protection Act (CIPA)' ጋር አብሮ-በሚሄድ ሁኔታ፤ ኢንተርኔትን ማግኘት የሚችሉ ሁሉም የትምህርት ቤት ኮምፒውተሮች፣ ተቀባይነት ከሌላቸው የድህረ-ገጽ ይዘቶች ለመጠበቅ፤ ይዘቱን የማጣራት-ሂደት/filtering ማካሄጃ ቴክኖሎጂን ይጠቀማል። ሆኖም-ግን፤ ምንም-ዓይነት የድህረ-ገጽ ማጣሪያ (web filtering) ሙቶ-በሙቶ/100% ደህንነቱ-የተጠበቀ ባለመሆኑ ምክንያት፤ ክፍሉ/Division፣ የኦንላይን እንቅስቃሴ ቁጥጥርን ለማድረግ ጥረት-ያደርጋል።

**በመኖሪያ-ቤት ማግኘት እና ቁጥጥር (Home Access and Monitoring)**

ክፍሉ/Division፤ ለወላጆች/አሳዳጊዎች - የተማሪያቸውን የኢንተርኔት አጠቃቀም በትምህርት ቤት በተሰጣቸው ዲቫይስ ላይ፣ ከትምህርት ቤት ውጪ በሚሆኑ ጊዜ ለመቆጣጠር የሚያስችላቸውን መሣሪያ/tool በመስጠት-እያገለገላቸው ባለበት-ጊዜ፤ ልክ-እንደ ሌሎቹ የመረጃ-ምንጮች - እንደ ቴሌቪዥን፣ ራዲዮ፣ ፊልሞች፣ እና ሌላ ሚዲያ/media - ላይ ልክ እንደሚያደርጉት ሁሉ፣ ስለ ኢንተርኔት-አጠቃቀም መመሪያን በመስጠት - ወላጆች/አሳዳጊዎች ኃላፊነት አለባቸው። ወላጆች/አሳዳጊዎች - በልጃቸው የኢንተርኔት አጠቃቀም ላይ ክትትል-የማድረግ እና፣ - የኦንላይን መማሪያ ቦታዎች/online learning spaces፣ የትብብር-ማድረጊያ መሣሪያዎች/collaboration tools፣ እና የትምህርታዊ የመገኛ-ምንጮች/educational resourcesን ጨምሮ - የክፍሉ/Division የቴክኖሎጂ የመገኛ-ምንጮች በማግኘት-ላይ ክትትል-የማድረግ ኃላፊነት-አለባቸው።

**የዲቫይስ መበላሸት (Damage)/መልሶ-መተካት (Replacement)**

ተማሪዎች፤ ከትምህርት ቤታቸው በተሰጧቸው ዲቫይሶች ላይ እንክብካቤ ማድረግ ላይ እና በአጠቃቀሙ-ላይ፤ ኃላፊነት አለባቸው። ብልሽት (Damage) እና/ወይም

መጥፋት(loss) በሚከሰት-ጊዜ፤ ከዚህ-በታች የተመለከቱትን ክፍያዎች-ጨምሩ ሊያስከትሉ የሚችሉት ቅጣቶች (consequences) አሉት: ክፍያዎች - በአከፋፈል ስምምነት (payment plan) ሊከፈል ይችላል፤ ወይም በትምህርት ቤቱ ውሳኔ - በአስፈላጊነቱ-ላይ መሠረት አድርጉ አማራጭ-በሆነ የሚያስከትሉ-ቅጣቶች (consequences) አማካኝነት-ሊከናወን ይችላል።

| | በድንገት-የተከሰተ ብልሽት (Accidental Damage) | ሆን-ተብሎ የተደረገ ብልሽት (Intentional Damage)* | መጥፋት/Loss |
|---|---|---|---|
| ክሮምቡክ (Chromebook) | $25 | እስከ $200 | እስከ $200 |
| ታብሌት (Tablet) | $25 | እስከ $100 | እስከ $100 |
| ቻርጀር (Charger) | | | $30 |

*የብልሽት ክፍያዎች የሚወሰኑት፤ በጥገና አድራጊው ቴክኒሺያን ለመስራት-በሚያስፈልገው ተቀያሪ ዕቃዎች/ዲቫይስ መተኪታ (device replacement) ላይ መሠረት-አድርጎ የሚወሰን-ነው።

ከዚህ-በታች በመፈረም፤ በኃላፊነት የመጠቀም-ስምምነቱን መመልከቴን - አረጋግጣለሁ።

የወላጅ/አሳዳጊ ስም:

የወላጅ/አሳዳጊ ፊርማ:

ቀን:

# በትምህርት ላይ መገኘት

መደበኛ የትምህርት ቤት ክትትል የልጅዎ የትምህርት ስኬት አስፈላጊ ክፍል ብቻ ሳይሆን፣ በቨርጂኒያ ሕግ ቁ. 22.1-254 መሰረት የተቀመጠ ሁኔታም ነው። ተማሪዎችን ሙሉ እምቅ አቅማቸው ላይ እንዲደርሱና አዎንታዊ የአቴንዳንስ ልምዶችን ለመዘርጋት በሚደረገው ጥረት ወላጆች/አሳዳጊዎች ልጆቻቸው በየቀኑ ሰዓቱን አክብረው በትምህርት ቤት ውስጥ መገኘታቸውን እንዲያረጋግጡ እናበረታታለን። ወላጆች ልጆቻቸው ከመዋለ ሕጻናት ጀምሮ አዎንታዊ የአቴንዳንስ ወይም የመገኘት ልምዶችን እንዲዘረጉ ሲያግዙ፣ እነዚህ ልምዶች ልጆቻቸውን በትምህርታቸውም ሆነ የሰራተኛ ኃይልን ሲቀላቀሉ ይጠቅማቸዋል። የአሌክሳንድሪያ ከተማ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ማንኛውም ተማሪ በአንድ የትምህርት ዘመን ውስጥ በአጠቃላይ ለአምስት የትምህርት ቀናት ወይም ከዚያ በላይ ያለበቂ ምክንያት ከትምህርት ቤት በሚቀርበት ጊዜ እና እንደዚህ ያሉ ክስተቶችን ለማረጋገጥ ከወላጅ ወይም አሳዳጊ ምንም ነገር ባልደረሰበት ሁኔታ የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ወላጅን/አሳዳጊን ለማግኘት አጥጋቢ ጥረት እንዲያደርጉ የሚጠይቀውን Commonwealth of Virginia የቨርጂኒያ የግዴታ የትምህርት ክትትል ሕግን አጥብቀው ይከተላሉ። ተማሪዎች ከልክ በላይ ፈቃድ የሌላቸው ወይም ያልተረጋገጡ ቀሪዎች በሚያበዙ ጊዜ፣ የትምህርት ቤቱ ማህበራዊ ሰራተኛ ከወላጅ እና ከሌሎች የት/ቤት ድጋፍ ሰጪ ቡድን አባላት ጋር የተማሪውን መቅረት ለመፍታት እቅድ ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል። የቨርጂኒያ ህግ 22.1-262 የሚያመለክተው የትምህርት ቤት ክትትል ድጋፍ እቅድን አለመከተል ለተማሪዎችና ለወላጆች/አሳዳጊዎች ከባድ ውጤቶችን ሊያስከትል እንደሚችል ይጠቁማል።

እንደዚህ ዓይነቶቹ ውጤቶች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፣ ነገር ግን በእነዚህ ብቻ የተገደቡ አይደሉም፡-

1. ተማሪን ወደ አሌክሳንድሪያ ፍርድ ቤት አገልግሎቶች ክፍል የክትትል ግምገማ ፓነል ማስተላለፍ
2. በቨርጂኒያ ሕግ 22.1-262 መሰረት ለአሌክሳንድሪያ የወጣቶች እና የቤት ውስጥ ግንኙነቶች ፍርድ ቤት በወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ አቤቱታ ማቅረብ
3. በቨርጂኒያ ሕግ § 16.1-228 በተገለጸው እና በ § 16.1-241.2 ፍቃድ በተሰጠው መሰረት በወጣቶች እና የቤት ውስጥ ግንኙነት ፍርድ ቤት CHINS (ቁጥጥር የሚፈልግ ህጻን) አቤቱታ ማስመዝገብ
4. በወጣቶች የአመክሮ ቁጥጥር አገልግሎቶች ውስጥ መሳተፍ
5. የተማሪ የመንጃ ፈቃድን ማጣት

ከቨርጂኒያ አስተዳደራዊ ሕግ 22.1-254 ጋር በተጣጣመ ሁኔታ፣ ለ 15 ተከታታይ ቀናት ያለምንም ማረጋገጫ ከትምህርት ቤት የቀረ ማንኛውም ተማሪ በይፋ ከትምህርት ቤት እንደሚሰናበት እባክዎ ልብ ይበሉ። ርዕሰ መምህሩ ወይም የተገለጸው ተወካዩ፣ አንድ ተማሪ ከትምህርት ቤት መዛግብት በሚወገድበት ጊዜ በጽሑፍ ወላጆችን/አሳዳጊዎችን ያሳውቃሉ። ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች ለመግታት ሲባል፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች ልጃቸው ከትምህርት ቤት በሚቀርበት ጊዜ ሁሉ የቃል እና/ወይም የፅሁፍ ማሳሰቢያ ለትምህርት ቤት ሰራተኞች መስጠታቸው አስፈላጊ ነው።

የተማሪ መቅረቶች አሳዳጊው እና/ወይም ሌላ የተሰየመ ባለሙያ እስኪያረጋግጡ ድረስ ሊታለፉ ይችላሉ። በበቂ ምክንያት ከትምህርት ቤት መቅረት የሚቻለባቸው ምሳሌዎች በአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የአቴንዳንስ ፖሊሲ ደንብ (JEA-R) ውስጥ የተገለጹትን የሚከተሉትን ሁኔታዎች ሊያካትቱ ይችላሉ፡

1. የህክምና በሽታዎች (አካላዊ ወይም የአእምሮ ህመም)። ርዕሰ መምህሩ በአንድ የትምህርት ዘመን ውስጥ ተማሪው ለ3 ተከታታይ ቀናት ወይም በአጠቃላይ 10 ወይም ከዚያ በላይ ቀናት ከቀረ በኋላ የሃኪም ማስረጃ እንዲቀርብለት ሊጠይቅ ይችላል።
2. የህክምና ወይም የጥርስ ምርመራዎች
3. የኃይማኖት በዓላትን ማክበር
4. የተማሪ የፍርድ ችሎቶች
5. ትምህርት ቤቱ ስፖንሰር በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ውስጥ ለመሳተፍ የተፈቀደላቸው ተማሪዎች (ከት/ቤቱ ዉስጥም ሆነ ውጭ)
6. በትምህርት ቤት ውስጥ (ISS)፣ አማራጭ የትምህርት ድጋፍ (AIS) ወይም ከትምህርት ቤት ውጭ የሚፈጸም እገዳ (OSS) የተወሰነባቸው ተማሪዎች
7. የቤተሰብ ድንገተኛ ሁኔታዎች (የወዳጅ ሞት፣ ያልተጠበቁ ከመኖሪያ ቤት መፈናቀሎች፣ በቤተሰብ አባላት ላይ ከባድ ጉዳቶች ወዘተ.)። ወላጆች/አሳዳጊዎች የተራዘሙ የጉዞና የእረፍት ቀናትን በ ACPS ዕረፍት ወቅት እና በፀደቁ በዓላት ዙሪያ ማቀድ ይጠበቅባቸዋል
8. ከ ACPS የመጓጓዣ አገልግሎቶች ጋር የተያያዙ መዘግየቶች

በሰዓት መገኘትም የACPS የተማሪ አቴንዳንስ ፖሊሲ ተፈጥሯዊ የሚጠበቅ ነገር ነው። ወደ ትምህርት ቤት ዘግይቶ መድረስ የተማሪዎችን ጠቅላላ የትምህርት ተሞክሮ እና የተማሪዎች ስኬታማነት ላይ ተፅእኖ ያለው ወሳኝ ነገር ነው። አርፍዶ መምጣት ለትምህርት ቀኑ ወይም የክፍል ጊዜዎች በርዕሰ መምህሩ ከተመዘገበው የጊዜ ገደብ ውጭ የሚሄድን ማንኛውንም የጊዜ ልዩነትን ያካትታል። አንድ ልጅ ትምህርት ቤት በሚያረፍድበት ጊዜ ሁሉ ወላጆች/አሳዳጊዎች የቃልና/ወይም የፅሁፍ ማስታወቂያ ለሚመለከታቸው የትምህርት ቤት ሰራተኞች ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል። ፈቃድ ያላቸው የማርፈድ ምሳሌዎች ከሚያካትቱት መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡-

1. የህክምና በሽታዎች (አካላዊ ወይም የአእምሮ ህመም)። ርዕሰ መምህሩ በአንድ የትምህርት ዘመን ውስጥ ተማሪው 10 ወይም ከዚያ በላይ ጊዜ አርፎ ከመጣ በኋላ የሃኪም ማስረጃ እንዲቀርብለት ሊጠይቅ ይችላል
2. የህክምና ወይም የጥርስ ምርመራዎች
3. የተማሪ የፍርድ ችሎቶች
4. ትምህርት ቤቱ ስፖንሰር በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ውስጥ ለመሳተፍ የተፈቀደላቸው ተማሪዎች (ከት/ቤቱ ዉስጥም ሆነ ውጭ)
5. ከባድ ወይም የተለዩ የቤተሰብ ድንገተኛ ሁኔታዎች (የወዳጅ ሞት፣ ያልተጠበቁ ከመኖሪያ ቤት መፈናቀሎች፣ በቤተሰብ አባላት ላይ ከባድ ጉዳቶች ወዘተ.)። ወላጆች/አሳዳጊዎች የተራዘሙ የጉዞና የእረፍት ቀናትን በ ACPS ዕረፍት ወቅት እና በፀደቁ በዓላት ዙሪያ ማቀድ ይጠበቅባቸዋል
6. ከ ACPS የመጓጓዣ አገልግሎቶች ጋር የተያያዙ መዘግየቶች
7. ከአየር ሁኔታ ጋር የተገናኙ ሁኔታዎች
8. በትምህርት ቀኑ ውስጥ ወደ መማሪያ ክፍል መዘግየቶች በርዕሰ መምህሩ ወይም በተወካዩ የግል ውሳኔ መሰረት የሚታለፉ ይሆናሉ።

ተማሪዎች ከልክ በላይ ያልተፈቀዱ ወይም ያልተረጋገጡ ማርፈዶችን ካበዙ፣ የትምህርት ቤት የማህበራዊ አገልግሎት ሰራተኛ ከወላጁ እና ሌሎች የትምህርት ቤት ድጋፍ ሰጪ ቡድን አባላት ጋር በተቻለ ፍጥነት ችግሩን ለመፍታት እቅድ ሊያወጡ ይችላሉ።

አንድ ተማሪ ከመጠን በላይ የትምህርት ቀናት እና የትምህርት ጊዜ በሚያመልጠው ወይም በሚያመልጣት ጊዜ በት/ቤት ውስጥ ሙሉ በሙሉ መሳተፍ እጅግ በጣም አስቸጋሪ ነው። ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ሲቀሩ፣ የት/ቤቱ ማህበረሰብ አካል የመሆን እድሉን የሚያጡ ሲሆን ብዙውን ጊዜ አካዳሚክ ብቃታቸው ከሌሎች የዘገየ ይሆናል፤ ጥናቶች እንደሚያሳዩት፣ በማንኛውም ምክንያት በአንድ የትምህርት ዘመን ውስጥ አሥር በመቶ የሚሆነውን ጊዜ ከት/ቤት መቅረት ወይም ስር የሰደደ ቀሪነት ወደ ደካማ የትምህርት ውጤት፣ የመገለል እና የመለያየት ስሜት ሊያስከትል እና ተማሪው ትምህርቱን ሙሉ በሙሉ ለማቋረጥ በሚወስነው ውሳኔ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል። ተከታታይነት ያለው የትምህርት ቤት ተሳትፎ ከሌሎች መልካም ባህሪያት እና ግብዓቶች እንደዚሁም የድጋፍ መስጫ መንገዶች ጋር በመጣጣም የተማሪን የትምህርት ተግባርን እና ማህበራዊ ግንዛቤያዊ እና ስሜታዊ እድገታቸውን ለማጠናከር ይረዳል። ወላጆች የት/ቤት አቴንዳንስን ለማሻሻል ከት/ት ሰራተኞች ጋር በሕብረት እንዲሰሩ ይበረታታሉ። መፍትሄዎችን ለመፍጠር በጋራ መስራት ለተማሪዎች የአካዴሚያዊ ስኬት ምርጥ ዕድሎችን ይሰጣቸዋል።

# የተማሪዎች አለባበስ

የተማሪዎች አለባበስ እና ገጽታ መስተጓጎል እንዲፈጠር፣ ሌሎችን ከትምህርቱ ሂደት የሚያዘናጋ ወይም የጤና ወይም የደህንነት ችግርን የሚፈጥር መሆን የለበትም። ተማሪዎች የተወሰኑ የህንፃ ውስጥ አለባበስ ደንቦችን ማክበር አለባቸው እና ስለእነርሱም ተማሪዎች ቅድመ ማስጠንቀቂያ ይሰጣቸዋል።

# የተማሪ መብቶች

**I. ሃሳብን የመግለጽ፣ የመናገር፣ የእምነቶች ወይም አስተያየቶች ነጻነት፡-**
ተማሪዎች በአካልም ይሁን በማህበራዊ ሚዲያ የሚሉት፣ የሚጽፉት፣ የሚለብሱት ወይም የሚገልጹት ሌሎችን ከትምህርት እንደማያስቆም፣ ማንንም ወይም የማንንም ንብረት እንደማይጎዳ እንዲሁም የተማሪውን የስነ ምግባር ደንብ ወይም ሕግን እንደማይጥስ የማረጋገጥ ሃላፊነት አለባቸው። ፖሊሲ IIBEB-1ን ይመልከቱ - የተማሪ የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም (አባሪ C)/ IIBEA/GAB - ሃላፊነት ያለበት የኮምፒዩተር አጠቃቀም (አባሪ B) እና JP - የተማሪ ህትመቶች (አባሪ I) ስለ አለባበስ ኮድ የሚጠበቅብዎትን በተመለከተ የትምህርት ቤትዎን የተማሪ መምሪያ መጽሃፍ ይመልከቱ።

**II. የፕሬስ ነጻነት**
ተማሪዎች ከብዙ የተለያዩ ምንጮች መረጃን የመፍጠር እና/ወይም የማካፈል መብት አላቸው (ተገቢው እውቅና ለምንጩ በተሰጠበት ሁኔታ) ተማሪዎች ግለሰባዊ ጥቃት ያለማድረስ ወይም እውነት ያልሆኑ ወይም አጸያፊ ነገሮችን ያለማተም ሃላፊነት አለባቸው። ተማሪዎች በሚጽፉበት ጊዜ ወይም እንደ የጽሁፍ መልእክት፣ በድረ ገጽ ላይ ጽሁፍ መለጠፍ፣ ስናፕ ቻት፣ ትዊት ማድረግ የመሳሰሉትን የኢንተርኔት ሚዲያ በሚጠቀሙበት ጊዜ፣ የመረጃውን ፍትሃዊነት፣ ሚዛናዊ አመለካከት እና ሃቀኝነት የመመዘን ሃላፊነት አለባቸው። ፖሊሲ IIBEB-1ን ይመልከቱ - የተማሪ የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም/IIBEA/GAB - ሃላፊነት ያለበት የኮምፒዩተር አጠቃቀም፣ JP - የተማሪ ህትመቶች እና የ ACPS የክብር ኮድ (አባሪ D)።

**III. የፍትህ ሂደት (ፍትሀዊ አያያዝ)**
የትምህርት ቤት ሰራተኞች መረጃን ለማግኘት ማስፈራራት ወይም ሃይል ጥቅም ላይ አለመዋሉን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል። የACPS ተማሪዎች አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ የፍትህ ሂደት መብቶችን የመጠቀም መብት አላቸው። ተማሪዎች በምግባራቸው ሌሎችንም ሆነ ንብረታቸውን ያለመረበሽ ሃላፊነትም አላቸው። የአንድ ተማሪ ስነ ምግባር የACPS የተማሪ የስነ ምግባር ደንብን እና ሕጎችን መከተል ይኖርበታል። በትምህርት ቤቶች ውስጥ፣ እያንዳንዱ ተማሪ በፍትሃዊ ሁኔታ መስተናገድ አለበት።

እያንዳንዱ ተማሪ የሚከተሉት መብቶች አሉት፡-

- የሱ/የሷ ምግባር የማይፈቀድ ከሆነ የማወቅ
- ስለተፈጠረው ነገር የመወያየት እድል የማግኘት
- እሱ/እሷ ከመረጡ፣ ያለመናገር

ፖሊስ ከአንድ ተማሪ ጋር መነጋገር ከፈለገ፡-

- የትምህርት ቤቱ ኃላፊ መገኘት ይኖርበታል (ወላጅ/አሳዳጊ የሚገኙ ከሆነ እንጂ)
- ተማሪ(ው/ዋ) ከመናገ(ሩ/ሯ) በፊት የእሱ/የእሷ ወላጅ ወይም አሳዳጊ እንዲጠሩ መጠየቅ ይችላሉ
- ፖሊስ ለተማሪ(ው/ዋ) እሱ/እሷ የሚናገሩት ነገር በነሱ ላይ እንደማስረጃ ሊውል እንደሚችል መግለጽ አለበት (ተጠርጣሪ ከሆኑ)

ፖሊሲ KNAJን ይመልከቱ - ከሕግ አስከባሪ ጋር ያለ ግንኙነት (አባሪ G)፣ JGD/JGE - የተማሪ እገዳ/መባረር (አባሪ F)፣ JGDA - የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎችን ስነ ምግባር ማስያዝ (አባሪ J)።

**IV. ምክንያታዊ ካልሆነ ፍተሻ እና በቁጥጥር ስር ማዋል ያለ ነጻነት፡-**
ተማሪዎች ምክንያታዊ ካልሆነ ፍተሻ እና በቁጥጥር ስር ማዋል በህግ የተጠበቁ ናቸው። ይሁን እንጂ፣ ይህ ለሁሉም ፍተሻዎች እና በቁጥጥር ስር ማዋሎች አለመፈጸም ዋስትና አይደለም። የትምህርት ቤት ኃላፊዎች በስራቸው ያለን አንድ

ተማሪን ለመፈተሽ ማዘዣ ማግኘት አያስፈልጋቸውም፤ ምክንያታዊ የሆነ ጥርጣሬ ብቻ ነው የሚያስፈልጋቸው። የሕግ አስከባሪዎች ፍተሻው በትምህርት ቤቱ ውስጥ ከተፈጠረ ሁናቴ ጋር ያልተያያዘ ሲሆን ወይም ተግባሩ ወዲያውኑ ተማሪዎችን፣ የትምህርት ቤቱን ንብረት ወይም የትምህርት ቤቱን ሰራተኞች ስጋት ላይ የሚይጥል ሲሆን የፍተሻ ማዘዣ ማግኘት ሊያስፈልጋቸው ይችላል። ፖሊሲ JFGን ይመልከቱ - ፍተሻ እና በቁጥጥር ስር ማዋል (አባሪ K)፣ እና ፖሊሲ KNAJ - ከሕግ አስከባሪ ጋር ያለ ግንኙነት (አባሪ G)

**V. የግል ንብረት**
ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት የግል እቃዎችን የማምጣት መብት አላቸው ነገር ግን ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት የሚያመጡቸው እቃዎች በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የተማሪዎች የባህሪ ህግጋት እና ደንቦች ያልተከለከሉ መሆናቸው ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል።

ፖሊሲ JFGን ይመልከቱ - ፍተሻ እና በቁጥጥር ስር ማዋል (አባሪ K) እና JHCD - ለተማሪዎች መድሃኒት መስጠት (አባሪ L)።

**VI. ግላዊነት/የትምህርት መዛግብት ተደራሽነት**
እንደ ተማሪ፣ ትምህርታዊ መዛግብትዎ በሚስጥር የመያዝ እና በመዛግብቱ ውስጥ ያለው መረጃ ትክክል የመሆን መብት አልዎት። ትምህርታዊ መዛግብት የግድ በእነዚህ የማይወሰን ቢሆንም የሚከተሉትን መረጃዎች ያካትታል፦ የውጤት ካርዶች፣ የትምህርት ክትትል መዛግብት፣ የሥነ ምግባር መዛግብት እና ፈተናዎች። እድሜዎ 18 አመት እስኪሆን ድረስ ወላጅዎ ወይም ህጋዊ አሳዳጊዎ በእርስዎ ምትክ መዛግብትዎን የመመርመር ወይም የማየት፣ ትክክል ያልሆኑ ወይም አሳሳች የሆኑ መዛግብት እንዲቀየሩ የመጠየቅ እና በህግ ከሚጠየቀው በስተቀር መረጃዎችን ከትምህርታዊ መዛግብቱ ለሌላ ወገን እንዲሰጡ የጽሑፍ ስምምነት የመስጠት መብት አላቸው። ይፋ ማውጣት በሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ ሊያስፈልግ ይችላል፦

- ምክንያታዊ የሆነ የጉዳት ወይም የቸልተኝነት ጥርጣሬ ሲኖር።
- ልጁ በራሱ/በራሷ ወይም በሌሎች ላይ አደጋን ሲጋርጥ።
- በልጅዎ ወይም በሌላ ሰው ላይ ስላለ አደጋ የሚያመለክት መረጃ ሲገለጽ።
- ይፋ መደረጉ በፍርድ ቤት የታዘዘ ወይም በህግ የሚፈለግ ሲሆን

(ለምሳሌ፦ የቤተሰብ ትምህርታዊ መብቶች እና ግላዊነት ድንጋጌ፣ Family Educational Rights & Privacy Act [FERPA])

ፖሊሲ JB/ACን ይመልከቱ - እኩል የትምህርት ዕድሎች/ከአድሎ የጸዳ እና JO - የተማሪ መዛግብት (አባሪ H)።

**VII. ነፃ እና ተገቢ ትምህርት (FAPE)**
ACPS ነፃ እና ተገቢ የሆነ ትምህርት (FAPE) በአሌክሳንድሪያ ከተማ ውስጥ ለሚኖሩ ለሁሉም እድሜያቸው ለትምህርት ለደረሰ ተማሪዎች ያቀርባል። የተማሪው ዘር፣ ቀለም፣ የትውልድ ዜግነት፣ ዜግነት፣ ፆታ፣ የአካል ጉዳት፣ እድሜ፣ ሃይማኖት፣ የፆታ ፍላጎት ዝንባሌ፣ የጋብቻ ወይም የወላጅነት ሁኔታ ወይም የእርግዝና ሁኔታ ምንም ይሁን ምን ትምህርት ይሰጣል። ተማሪዎች በመደበኛነት በትምህርት ገበታቸው ላይ የመገኘት፣ በክፍል ሥራ ላይ ትጋት የተሞላበት ጥረት የማድረግ እና የትምህርት ቤት ደንቦችን እና መመሪያዎችን የመከተል ኃላፊነት እና የስቴት መስፈርቶች አሉባቸው። ተማሪዎች በተናጠልም ሆነ በቡድን፣ የሌሎች ማናቸውም ተማሪዎች ነፃና ተገቢ የሆነ ትምህርት የማግኘት መብትን ከሚጥሱ ድርጊቶች ወይም እንቅስቃሴዎች የመቆጠብ ኃላፊነትም አለባቸው።

ፖሊሲ JB/ACን ይመልከቱ - እኩል የትምህርት ዕድሎች/ከአድሎ የጸዳ (አባሪ H)።

**VIII. የሐይማኖት ነፃነት**
ድርጊቱ ሌሎችን እስካልጎዳ ድረስ፣ ተማሪዎች የፈለጉትን ሐይማኖት የመከተል ወይም ምንም ሐይማኖት ያለመከተል መብት አላቸው። ተማሪዎች በእምነቶች መካከል ያለውን ልዩነት እንዲገነዘቡ እንዲሁም አንዳቸው የሌላውን ሐይማኖታዊ እና/ወይም ሐይማኖታዊ ያልሆኑ እይታዎች እንዲያከብሩ ይበረታታሉ።

ፖሊሲ IGDAን ይመልከቱ - የተማሪ ድርጅቶች (ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች) (አባሪ M) - እና INDC - ሐይማኖት በትምህርት ቤቶች ውስጥ (አባሪ N)።

**IX. በህብረት አቤቱታ ማቅረብ (Petition)**
ተማሪዎች ከት/ቤት ሰራተኞች ጋር ያላቸውን ያለመግባባት በአክብሮት የመግለጽ መብት አላቸው። እንዲሁም ተማሪዎች በፖሊሲዎች፣ ልምዶች ወይም ሂደቶች ላይ ማሻሻያዎች ወይም ለውጦች እንዲደረጉ የትምህርት ቤት ወይም የወረዳ አስተዳዳሪዎችን የመጠየቅ መብትም አላቸው። ተማሪዎች ድምጻቸውን ማሰማታቸው፣ ሌሎችን ከመማር ማስተማር ማስተጓጎል፣ ማንንም መጉዳት፣ ንብረት ማውደም ወይም የተማሪውን የሥነ ምግባር ደንብ ወይም ህግን መጣስ አይኖርበትም።

ፖሊሲ INBን ይመልከቱ - ስለ አወዛጋቢ ጉዳዮች ማስተማር (አባሪ O)፣ IIBEB-1 - የተማሪ የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም (አባሪ C)፣ IIBEA/GAB - ሃላፊነት ያለበት የኮምፒዩተር አጠቃቀም (አባሪ B) እና JP - የተማሪ ህትመቶች (አባሪ I)።

# የጣልቃ ገብ እርምጃዎች እና የስነ ምግባር ሥነ ሥርዓቶች

## ባለብዙ ደረጃ የተማሪዎች ባህሪ ድጋፍ መመሪያ ሥነ ሥርዓት

ACPS Multi-Tiered System of Support (MTSS፣ በፍላጎት ላይ የተመሠረተ እና ሁሉን አቀፍ ለሆነ ባለ ብዙ ደረጃ የድጋፍ ስርዓት) ቁርጠኛ ነው። ይህ ስርዓት አስቀድሞ ከመለየት፣ በመረጃ ላይ የተመሠረተ ውሳኔ አሰጣጥ፣ እና ተገቢ ጥንካሬ እና የቆይታ ጊዜ ያላቸውን በማስረጃ ላይ የተመሰረቱ ልምዶችን ተግባራዊ ከማድረግ ጋር የተጣጣመ ነው። በማህበራዊ፣ በስሜታዊ ወይም በባህሪ ዕድገት መስኮች የተጨማሪ ድጋፍ ፍላጎት እንዳላቸው የሚያሳዩ ተማሪዎች ልዩ ፍላጎቶቻቸውን የሚያሟሉ አገልግሎቶች እና ጣልቃ ገብነቶች ይሰጣቸዋል።

### በርካታ-ደረጃ ያላቸው የድጋፍ ስርዓቶች
### ማህበራዊ፣ ስሜታዊ፣ አካዴሚያዊ ትምህርት (SEAL) አቀራረብ




አዎንታዊ የባህሪ ጣልቃ ገብነት እና ድጋፍ (ፒቢአይኤስ) ሁሉም ተማሪዎች የማህበራዊ የስሜታ እና የትምህርታዊ ስኬቶችን ለማስፈፀም እንዲቻላቸው የባህሪያዊ ድጋፎች እና አስፈላጊውን የማህበራዊ ባህል ለማቋቋም የሚቻልበት ንቁ የሆነ አቀራረብ ነው። አዎንታዊ የመማሪያ አካባቢን ለመፍጠር አግባብነት ስላለው የተማሪው ባህሪ ለመግለጽ፣ ለማስተማር እና ለመደገፍ የመከላከያ ስትራቴጂዎችን ይጠቀማል። በዚህ ረገድ አትኩሮት የሁሉንም ተማሪዎች የማህበራዊ እና ስሜታዊ ፍላጎቶች ለማሟላት እና የትምህርታዊ እና የማህበራዊ ውጤታቸውን ለማሻሻል በመላው ትምህርት ቤት፣ የትምህርት ክፍል እና የተናጠል ድጋፍ ስርዓቶች ማጎልበት እና ማስጠበቅ ላይ ያተኮረ ነው።

የፒቢአይኤስ ዓላማ አግባብነት ያለው ባህሪ የተለመደ እንዲሆን የሚያስችል አካባቢን ማቋቋም ነው። መዋቅሩ ተደጋጋሚ የሆኑ አሳሳቢ የባህሪ ሁኔታዎችን ለሚያሳዩ ተማሪዎች በአሰራር ላይ የተመሰረቱ ጣልቃ ገብነቶች የሚጎለብቱበት እና የሚተገበሩበት ሂደትን ያቋቁማል። እንዲሁም ትምህርት ቤት አቀፍ እና የጣልቃ ገብነት ዕቅድ ውሳኔዎችን ለመምራት የሥራ ባልደረቦቹን በመደበኛ ማሳያ እና መረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ አሰጣጥ ያሳትፋል።

አባጣገድን የሚያቋቁሙ እና የሚተገብሩ ት/ቤቶች ለሁሉም ተማሪዎች ከፍተኛ የሆነ ተሳትፎ እና አፈፃፀም የሚያስችሉ እጅግ በጣም አሳታፊ ምላሽ ሰጪ በመከላከል ላይ የተመረኮዙ እና ምርታማ የመማር ማስተማር አካባቢዎችን በተሻለ መልኩ እንዲኖራቸው ያስችላል። ፒ.ቢ.አይ.ኤስ ወደ ትምህርት ቤት አውቶብስ መዘዋወር።

#### ለ SEL የሚኖር ስርዓታዊ አቀራረብ

ከ PBIS ጋር በመሆን ተማሪዎቻችንን እና ሰራተኞቻችንን ለመደገፍ፣ ACPS የስሜታዊ እውቀታችንን በማሳደግ ተማሪዎችን እና ሰራተኞችን ለመደገፍ መምሪያ አቀፍ አቀራረብን ለመቀበል ከ Yale Center for Emotional Intelligence ጋር አጋርነት መስርቷል። RULER ለ SEL ስልታዊ አቀራረብ ነው እና ስሜታዊ የአስተውሎት መርሆዎችን በመምሪያው ውስጥ ወደሚገኝ እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ባህል ውስጥ ለማስገባት ይጠቅማል። RULER የአምስቱ የስሜታዊ አስተውሎት ክህሎቶች ምህፃረ ቃል ሲሆን የሚከተሉትን ያጠቃልላል:- መገንዘብ፣ መረዳት፣ መሰየም፣ መግለፅ እና መቆጣጠር። የእነዚህ አምስት የ RULER ክህሎቶች ዝግጅት በአራቱ መሰረታዊ መሳሪያዎቻችን ላይ የተመሰረተ ነው፡ The Charter, Mood Meter, Meta-Moment, and Blueprint. እነዚህ ክህሎቶች እና መሳሪያዎች በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ውስጥ ላሉ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ማለትም የትምህርት ቤት መሪዎች፣ መምህራን፣ ሠራተኞች፣ ተማሪዎች እና ቤተሰቦች የተዋወቁ ሲሆን አመራሮች እንዴት እንደሚመሩ፣ መምህራን እንዴት እንደሚያስተምሩ፣ ተማሪዎች እንዴት እንደሚማሩ እና ቤተሰቦች ተማሪዎችን እንዴት እንደሚደግፉ ለማሳወቅ የተነደፉ ናቸው።

#### ወደነበረበት ሁኔታ የመመለስ ስራዎች (Restorative Practices)

እንደ የፒቢአይኤስ (PBIS) አንድ ክፍል ትምህርት ቤቶች ወደነበሩበት ሁኔታ የመመለስ ስራዎችን እንደ መከላከልና እንደመፍትሄ አማራጮች ሊያካትቱ ይችላሉ። ወደነበረበት ሁኔታ የመመለስ ስራዎች በትምህርት ቤቱ ቅጥር ጊቢ ውስጥ ሰላማዊ ሁኔታ መፍጠር እና ተማሪዎች የሚያደርጉት ነገር በሌሎች ሰዎች ላይ የሚያደርሰው ችግር እንዲሰማቸውና እንዲረዱት  በማድረግ ላይ ያተኩራል። ወደነበረበት ሁኔታ የመመለስ ስራዎች (Restorative practices) እያንዳንዱ ስህተት፣ ግጭት ወይም ችግር የመማር እድል ሲሆን እነዚህ ግጭቶች ቢፈጠሩም ግንኙነቶችን ወደነበሩበት መመለስ ይቻላል በሚሉት መርሆዎች ያምናል።

ወደነበረበት ሁኔታ የመመለስ ስራዎች የማህበረሰብ ግንኙነቶችን በሁሉም ተማሪዎች እና ሰራተኞች መካከል ጠንካራና አዎንታዊ ግንኙነቶችን ለመገንባት እንደ ደረጃ 1 (Tier 1) ስራ ይጠቀማል። በተጨማሪም መከባበርን፣ መተማመንን እና ተጠያቂነትን የሚያበረታታና ለስነልቦና እና ለአካል ደህንነት አስተማማኝ የሆነ የትምህርት አካባቢ ለመፍጠር የሚያግዙ እንደ መካፈል፣ ማዳመጥ፣ መተዛዘን እና ችግሮችን መፍታት ያሉ አዎንታዊ ማህበራዊ ክህሎቶችን ያስተምራሉ እንዲሁም ያሳያሉ። ይህ የማህበራዊ ክህሎቶች ትምህርት ከፒቢአይኤስ (PBIS) በሚበረታታው የትምህርት ቤት አቀፍ የሚጠበቁ ነገሮችና ከአሜሪካ የትምህርት ቤት አማካሪዎች (American School Counselor Association (ACSA)) ብሔራዊ የትምህርት ማማከር ሞዴል (National School Counseling Model) ጋር አብሮ የሚሄድ ነው።

ወደነበረበት ሁኔታ የመመለስ ክበቦች (Restorative circles) ጥፋቶቸች፣ ግጭቶች ወይም ችግሮች በሚከሰቱበት ወቅት ተጎጂ የሆኑት ሰዎች እንዴት እንደተጎዱና

ሁኔታው እንዴት “ሊታረም” እንደሚችል ሃሳባቸውን እንዲሰጡ በማድረግ ግንኙነቶች ወደነበሩበት እንዲመለሱ ለማድረግ ጥቅም ላይ የሚውሉ የደረጃ 2 (Tier 2) ድጋፎች ናቸው።

***ወደነበረበት ሁኔታ የመመለሻ ጥያቄዎች (ፈታኝ ለሆነ ባህሪ ምላሽ ለመስጠት)***
- *ምን ተፈጠረ?*
- *በወቅቱ ምን እያሰቡ ነበር?*
- *ከዛ ጊዜ ጀምሮስ ስለ ምን አሰቡ?*
- *እርስዎ ባደረጉት ድርጊት ማን ነው የተጎዳው? በምን መንገድ?*
- *ነገሮችን ለማስተካከል ምን ማድረግ አለብኝ ብለው ያስባሉ?*

***ወደነበረበት ሁኔታ የመመለሻ ጥያቄዎች (በሌሎች ድርጊት የተጎዱትን ለመርዳት)***
- *ምን እንደተከሰተ እንዳስተዋሉ ምን አስበው ነበር?*
- *ይህ ክስተት በእርስዎና በሌሎች ላይ ምን ተጽእኖ ነበረው?*
- *ለእርስዎ በጣም ከባድ የነበረው ነገር ምን ነበር?*
- *ነገሮችን ለማስተካከል ምን መሆን አለበት ብለው ያስባሉ?*




## የባህሪያዊ ድጋፍ ደረጃዎች

**ደረጃ 1**
የፒቢአይኤስ (PBIS) አላማ በደረጃ 1 (Tier 1) ላይ የተማሪውን የባህሪ ችግር መከላከል እና ቢያንስ ከተማሪዎቹ 80 በመቶ የሚሆኑት ስኬታማንት ለማፋጠን ሂደቶች ሊቋቋሙበት የሚችሉት አዎንታዊ ባህሪ ማሳደግ ነው። እጅግ ውጤታማ የሆነ የደረጃ 1 (Tier 1) ሥርዓት በደረጃ 2 (Tier 2) እና 3 (Tier 3) ላይ በጣም ከፍተኛ መርጃዎች የሚያስፈልጋቸውን የተማሪዎች ብዛት ይቀንሳል።

*የደረጃ 1 ድጋፍ አትኩሮት ማነው?*

ሁሉም ተማሪዎች የደረጃ 1 አትኩሮት ናቸው።

*የደረጃ 1 የባህሪያዊ ድጋፍ ምን ምን ናቸው?*

- አነስተኛ ቁጥር ያላቸው በአዎንታዊነት የተገለጹ ትምህርት ቤት አቀፍ የባህሪ ግምቶች።
- የባህሪ ግምቶች በግልጽ የተቀመጡ እና የቀን ተቀን ሁኔታዎች በትምህርት ቤቱ በሞላ በሁሉም ገጽታዎች የተለዩ እና ለሁሉም ተማሪዎች ስልታዊ በሆነ መንገድ እንዲማሯቸው የሚደረጉ ናቸው።
- የሚጠበቅባቸውን ባህሪያት የሚያሳዩ ተማሪዎችን እውቅና የመስጫ ስርዓት።
- በግልጽ የተቀመጡ ተቀባይነት የሌላቸው ባህሪያት ዝርዝር እና በሥራ ባልደረቦች እንዴት መስተናገድ እንዳለባቸው።

*የድጋፍ/የግስጋሴ ቁጥጥር ድግግሞሽ*

- ከተማሪዎች የሚጠበቁ ሁኔታዎች በዓመቱ መጀመሪያ ላይ እንዲሚራቸው ይደረጋሉ።
- ቅድመ - ማስተካከያዎች እያንዳንዱ ሽግግር ወደ አዲሱ ዝግጅት ከመደረጉ በፊት ይሰጣሉ።
- የቃል እና የእይታ ማፋጠኛዎች በመጀመሪያ ላይ በተደጋጋሚ ጥቅም ላይ መዋል እና የቀን ተቀን ሥርዓቶች ሲቋቋሙ እየቀነሱ ይሄዳሉ።
- የሩብ ዓመት "መጨመሪያዎች" ከተማሪዎች ስለሚጠበቁ መደበኛ ማስታወሻዎች እንዲሁም "በቅጽበት" የሚሰጡ ማስታወሻዎች (እንደአስፈላጊነቱ) መታቀድ እና መቅረብ አለባቸው።

*ጣልቃ ገብ ማነው?*

ሁሉም አዋቂዎች አስተማሪዎች፣ አስተዳዳሪዎች፣ የድጋፍ ሥራ ባልደረቦች (ለምሳሌ ፓራ ፕሮፌሽናልስ፣ የካርቴሪያ ሥራ ባልደረባዎች፣ ጠበቂዎች፣ የቢሮ ሥራ ባልደረቦች ወዘተ)።

**ደረጃ 2**

የደረጃ 2 ተጨማሪ ድጋፎች ለደረጃ 1 ድጋፍ በአዎንታዊ መልኩ ምላሽ የማይሰጡ ተማሪዎችን ለመደገፍ ተጨማሪ ወይም ኢላማ ተኮራ ጣልቃ ገብነቶችን ለማቅረብ የተቀረፁ ናቸው። በግምት ከ15-20% የሚሆኑት ተማሪዎች የደረጃ 2 ድጋፍ ሊያስፈልጋቸው ይችላል። የደረጃ 2 ድጋፍን የሚቀበሉ ተማሮዎች ለደረጃ 1 ድጋፍ ሙሉ አቅርቦት አላቸው።

*የደረጃ 2 ድጋፍ አትኩሮት እነማናቸው?*

የደረጃ 2 ድጋፍ አትኩሮት ለደረጃ 1 ጥረቶች ምላሽ የማይሰጡ አስቸጋሪ ባህሪያትን የሚያሳዩ ተማሪዎች ናቸው። እነዚህም የሚያካትቷቸው:

- በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ፀብጫሪ/አደገኛ ላልሆኑ ጥፋቶች ሶስት ወይም ከዚያ በላይ የቢሮ ጥሪዎች፣
- ፀብጫሪ/አደገኛ ለሆኑ ጥፋቶች አንድ ወይም ከዚያ በላይ የቢሮ ጥሪዎች፣
- ከረዥም ጊዜ እግድ ወይም አማራጭ ፕሮግራም ሽግግር፣

*የደረጃ ሁለት ባህሪ ድጋፍ ምን ምን ናቸው?*

- የባህሪ ውል፤ የባህሪ ድጋፍ ዕቅድ።
- ጠቋሚ ቅጽ፣ የባህሪ ግብረመልስ ቅጽ፤ ራስን በራስ መቆጣጠሪያ ማረጋገጫ - ዝርዝር ከተመረጠ አዋቂ ጋር የገቢ/የመውጫ ማረጋገጫ።
- የማህበራዊ ብቃት መመሪያ።
- የቡድን ማማከር (ብቃት የሚያንሳቸው ቡድኖች እንደቁጣ አስተዳደር፣ የግጭት አወጋገድ፣ አደረጃጀት ወዘተ)።
- ምክር።
- የተማሪዎች መገኛ ቁጥጥር ድጋፍ ዕቅዶች።

*የድጋፍ/ግስጋሴ ቁጥጥር ድግግሞሽ*

- በአዋቂ ላይ በተመሰረተ ፍላጎት (በየቀኑ- በየሳምንቱ) የገቢ/የመውጫ ማረጋገጫ ሥርዓት።
- የየቀኑ ጠቋሚ ቅጽ።
- የብቃት ችግር ያለባቸው ተማሪዎች የማህበራዊ ብቃት ቡድን ቢያንስ በየሳምንቱ እንዲሰበሰብ ማድረግ።

*ጣልቃ ገብ ማነው?*

- ከተማሪው ጋር የሚሰሩ የትምህርት ክፍል አስተማሪዎች እና ሌሎች አዋቂዎች።
- የትምህረት ቤት አማካሪ።
- የትምህርት ቤት ሥነ አእምሮ ባለሙያ።
- የትምህርት ቤት ማህበራዊ ሰራተኛ።
- አስተዳዳሪ።

**ደረጃ 3**

ደረጃ 3 እጅግ በጣም አስቸጋሪ እና/ወይም የማያቋርጥ ችግር ያለባቸውን በግምት ከ3-5 የሚሆኑ ተማሪዎች የባህሪያዊ ፍላጎቶች ያሳካል። ደረጃ 3 ድጋፍ አንድ ባህሪ ለምን እንደሚከሰት አስመልክቶ በጣም ዝርዝር እና የባህሪ ጣልቃ ገብነት እቅድ ማጎልበቻ በጣም ጠንካራ በምርምር ላይ የተመሰረቱ ጣልቃ ገብነቶች፣ የበለጠ ድግግሞሽ እና ዝርዝር የግስጋሴ ቁጥጥር እና በጣም ብዙ የሥራ ባልደረቦች ጊዜ እና የየተማሪዎቹን ችግሮች ለማስወገድ ሃብቶችን ማስጠት አካቶ ምርምር የሚያደርግ በሥራ ላይ ያለ የባህሪ ምዘና ሂደትን ያካትታል። የደረጃ 3 ድጋፍ በተማሪው የፍላጎት ደረጃ ጥንካሬ ላይ ተመርኩዞ በተለያዩ ደረጃዎች ሊቀርብ የሚችል ነው።

*የደረጃ 3 ድጋፍ አትኩሮት ማን ነው?*

ለደረጃ 1 እና ደረጃ 2 ጥረቶች በበቂ ሁኔታ ምላሽ የማይሰጡ ጠንካራ ፍላጎቶች ያሏቸው ተማሪዎች የደረጃ 3 አትኩሮት ናቸው።

*የደረጃ 3 ባህሪ ድጋፎች ምንም ምን ናቸው?*

- ጠንካራ የደረጃ 2 ጣልቃ ገብነቶች።
- በትምህርት ቤት አማካሪ፣ በማህበራዊ ሰራተኛ ወይም የሥነ አእምሮ ባለሙያ የተናጠል ማማከር።
- በትምህርት ቤት አማካሪ፣ በማህበራዊ ሰራተኛ ወይም የሥነ አእምሮ ባለሙያ የሚመራ ጠንካራ የማህበራዊ ብቃት መመሪያ።
- በሥራ ላይ ያለ የባህሪ ምዘና/የባህሪ ጣልቃ ገብነት ዕቅድ።
- በዙሪያ ገብ አገልግሎቶች እና ድጋፍ ረገድ ከውጫዊ መስሪያ ቤቶች ጋር መመካከር እና በቅንጅት መስራት።
- የቁጥጥር ድግግሞሽን መደገፍ/ማሻሻል።
- የመጀመሪያ ስብሰባ ከአተገባበሩ 4 ሳምንታት በኋላ ይካሄዳል።
- የክትትል ስብሰባዎች ከዛ በኋላ ከ6 እስከ 8 ሳምንታት ውስጥ ቢያንስ ይካሄዳሉ።
- ስብሰባዎች እንደአስፈላጊነቱ በጣም በድግግሞሽ መካሄድ አለባቸው።
- ለእያንዳንዱ ተማሪ የተመደበው የጉዳይ ሥራ አስኪያጅ ዳታው የለውጥ አስፈላጊነትን የሚያመላክት ከሆነ መረጃ እንዲሁም ረቂቅ የጽሁፍ አስተያየቶችን ያመጣል።

*ጣልቃ ገብ ማን ነው?*

- ማህበራዊ ሰራተኛ።
- የትምህርት ቤቱ የሥነ አእምሮ ባለሙያ።
- ተባባሪ ኤጀንሲ (ዲኤስኤስ፣ ፍ/ቤት፣ የአእምሮ ጤና ወዘተ)።
- ልዩ ትምህርት፡ የተናጠል ትምህረት ፐሮግራም (የተትፕ) ቡድን።

## የጣልቃ ገብነቶች እና ያስከተሏቸው ደረጃዎች

| **የደረጃ 1 ጥሰት**<br>(እነዚህ ጣልቃ ገብነቶች በትምህርት ክፍሉ ውስጥ ስኬታማ በሆነ መልኩ በጥቅም ላይ ሲውሉ፣ ተጨማሪ የሥነ ምግባር እምጃ አያስፈልግም) | **የደረጃ 2 ጥሰቶች**<br>እነዚህ የጣልቃ ገብነት እርምጃዎች በትምህርት ቤቱ የተማሪዎች ድጋፍ ቡድን (SST) ሰራተኞች እርዳታ ጥቅም ላይ የሚውሉ ሲሆን የአስተዳደር ድጋፍን ሊያካትቱ ይችላሉ | **የደረጃ 3 ጥሰቶች**<br>(እነዚህ በትምህርት ቤቱ አስተዳደር ብቻ በብቸኝነት ይደረሳሉ) |
|---|---|---|
| • ወደነበረበት ሁኔታ የመመለሻ ክበብ<br>• የመምህር ጉባኤ ከተማሪው ጋር<br>• ከተማሪዎች ጋር የሚካሄድ የአስተማሪዎች ስብሰባ።<br>• ከጨዋታ ውጪ መደረግ።<br>• ስለአደጋው ማሳያ (የቃል ወይም የጽሁፍ)።<br>• የመቀመጫ ለውጥ።<br>• ማስጠንቀቂያ (የቃል ወይም የዕይታ)።<br>• ዳግም አቅጣጫ ማስያዝ።<br>• አግባብነት ያለው ባህሪን መከለስ።<br>• ልዩልዩ መብቶችን ማሳጣት።<br>• ዕቃዎችን መወረስ።<br>• የሥልክ ጥሪ እና ደብዳቤ ለወላጅ/ሞግዚት መስጠት።<br>• የአስተማሪዎች ስብሰባ ከወላጆች/ሞግዚቶች ጋር።<br>• የወላጅ የተማሪ እና የአስተማሪው ውል።<br>• ማማከር።<br>• እርቅ።<br>• የግጭት አወጋገድ።<br>• የአቻ ለአቻ እርቅ።<br>• የግላዊ መሳሪያዎች መወረስ።<br>• ምክር።<br>• የግለሰባዊ የሙያ እና ትምህርት ዕቅድ ክለሳ (የግሙትእክ)።<br>• የተማሪው ይቅርታ (የቃል ወይም የጽሁፍ)። | • ወደነበረበት ሁኔታ የመመለሻ ክበብ<br>• የባህሪያዊ ውል።<br>• የተወሰነ ተግባር።<br>• የማህበረሰብ አገልግሎት ስራን ማጠናቀቅ።<br>• ለጣልቃ ገብነት ድጋፍ ቡድን (የተማሪው ድጋፍ ቡድን)።<br>• በማህበረሰብ ላይ የተመሰረቱ አገልግሎቶችን ማጣቀስ።<br>• ልዩልዩ መብቶችን ማሳጣት።<br>• ተማሪዎች ለ30 ቀናት እንዲታገዱ ይደረጋል።<br>• ወደ ቢሮ መጠራት።<br>• እስር። (ከትምህርት ቤት በፊት ወይም በኋላ)<br>• የባህሪያዊ ግስጌስ ሪፖርት።<br>• የአይኢፒ ማሻሻያ።<br>• የትምህርት ክፍለ ወይም ፕሮግራም ለውጥ።<br>• የህፃናት ጥናት ስብሰባ።<br>• ማማከር።<br>• በሥራ ላይ የተመረኮዘ የባህሪያዊ ምዘና።<br>• የባህሪ ጣልቃ ገብነት ዕቅድ።<br>• አማራጭ የትምህርት አስጣጥ (አንድ ክፍል እስከ ግማሽ ቀን ያነሰ።)<br>• በትምህርት ቤት ውስጥ እገዳ(½ የትምህርት ቀን ወይም ከዚያ በላይ)<br>• የመኪና ማቆም መብትን ማጣት።<br>• አንድ ሰው ስላለፈ ተሞክሮው እና ምን ያህል እንደተለወጠ የሚያሳይ ጽሁፍ (Reflective Essay)።<br>• ተገልሎ ትምህርትን መከታተል (Independent Study)።<br>• አለአግባብ የአደንዛዥ እፅ አጠቃቀም ምክር | • የትምህርት ቤት ውስጥ ዕግድ።<br>• ከ1-5 ቀናት መታገድ።<br>• ከ6-10 ቀናት መታገድ።<br>• ወደ ማህበረሰቡ መስሪያ ቤት መላክ።<br>• አማራጭ የፕሮግራም ምደባ።<br>• ካሳ።<br>• የማስተካከያ አሰራር-የጉዳት ጥገና ሂደት።<br>• የረጅም ጊዜ ዕቅድ።<br>• መባረር።<br>• የባህሪያዊ ጣልቃ ገብነት ዕቅድ።<br>• በአሰራር ላይ የተመረኮዘ የባህሪያዊ ምዘና።<br>• የሥነ ምግባር ሂደት መስማት።<br>• አለአግባብ የአደንዛዥ እፅ አጠቃቀም ምክር |

**ማስታወሻ፡-** ይህ የመፍትሄ እርምጃዎች ዝርዝር ሁሉን አቀፍ አይደለም። የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች በተቻለ መጠን እንደየሁኔታው ለተማሪው አዎንታዊ ባህሪን ሊያመጣ የሚችለውን የመፍትሄ ሃሳብ ለመተግበር ይሞክራሉ። የስነ ምግባር ደንቡ ሲጣስ የተሰጠውን ምላሽ ሲወስን የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች የተማሪውን እድሜ፣ ተማሪውን የነበረውን ሃሳብ፣ የሁኔታዎቹን ክብደት፣ ለትምህርት ቤቱ አካባቢ የተከሰተውን የሁከት መጠን (ጥሰቱ በተከሰተበት ወቅት ወይም ከዚያ በኋላ)፣ የሁኔታው ተደጋጋሚነት (ተደጋጋሚ ከነበረ) እና ሌሎችንም ሁኔታውን ሊያከብዱ ወይም ሊያቃልሉ የሚችሉ ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ያስገባሉ። ትምህርት ቤቱ የሚሰጠው ምላሽ የግድ ለመጀመሪያው ጥፋት በተቀመጠው ዝቅተኛ ቅጣት አይጀምሩም።

## Student Behavior and Administrative Response (SBAR፣ የተማሪ ባህሪ እና አስተዳደራዊ ምላሽ)

ACPS ከቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ አዎንታዊና የመከላከያ የተማሪ ስነምግባር ፖሊሲ እና የእገዳ አማራጮች ሞዴል መምሪያ ጋር ተጣጥሞ ይሰራል። የተለያዩ የተማሪ ባህሪያትን ምድቦች ማወቅ እና መረዳት አስተዳዳሪዎች እና ሠራተኞችን የማይፈለጉ ባህሪያትን ከመከላከል እና ከማገገሚያ መነጽር አንጻር ደረጃዎችን እና ስልቶችን በመለየት ሊረዳቸው ይችላል። በሞዴል መመሪያው መሠረት አስተዳዳሪዎች የባህሪ ጣልቃ ገብነትን፣ የዲሲፕሊን ቅጣቶችን እና የማስተማሪያ ድጋፎችን ለማካተት ለተማሪ ባህሪ ምላሽ መስጠት የሚችሉባቸው ሦስት መንገዶች አሉ። የትምህርት ቤት ክፍሎች ስለ ባህሪ የሚከተሉትን እንዲያውቁ እና እንዲረዱ ይጠየቃሉ-

9. ባህሪ ተግባቦት ነው እና ተማሪዎች በባህሪያቸው የሚነጋገሩትን መልእክት መረዳት አለብን።
10. ባህሪ ባህላዊ አውድ ስላለው በአንድ ባህል ውስጥ ተቀባይነት ያለው ወይም የሚከበር ነገር በሌሎች ባህሎች ተቀባይነት ወይም አክብሮት ላይኖረው ይችላል።
11. ባህሪ ዕድገታዊ ሲሆን የተማሪዎች የውሳኔ አሰጣጥ ክህሎት ሙሉ በሙሉ አልዳበረም።
12. ባህሪ በትምህርት የሚገኝ ነው፣ እናም ተማሪዎች እንዲያዩ የምንፈልጋቸውን ባህሪዎች ማስተማር አለብን።

በቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ እንደተገለፀው የሚከተሉት የተማሪ ባህሪ ምድቦች ባህሪው በትምህርት ቤቱ የመማሪያ አካባቢ ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ መለየትን ለማገዝ እና ማህበረ-ስሜታዊ የመማር ብቃቶችን የሚያጎለብቱ ምላሾችን ለማበረታታት የተቀረጹ ናቸው።

- የአካዳሚክ እመርታን የሚያደናቅፉ ባህሪያት (BAP)፡
  እነዚህ ባህሪያት የተማሪውን ወይም የተማሪዎችን የትምህርት እድገት ያደናቅፋሉ። እነሱ በተለምዶ የተማሪውን ራስን የማስተዳደር ወይም ራስን የማወቅ ጉድለት ያመለክታሉ። አንዳንድ ጊዜ ተማሪው ባህሪው በሌሎች ላይ ምን ተጽዕኖ እንደሚያሳድር በመረዳት እገዛ ሊፈልግ ይችላል ስለዚህ በማህበራዊ ግንዛቤ ውስጥ ሥልጠናም ሊጠቀም ይችላል።
- ከት/ቤት ሥራዎች ጋር የተዛመዱ ባህሪዎች (BSO)፡
  እነዚህ ባህሪዎች በትምህርት ቤት ሂደቶች የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ውስጥ ጣልቃ ይገባሉ። እነዚህን ባህሪዎች የሚያሳዩ ተማሪዎች ራስን የማስተዳደር፣ ራስን የማወቅ ወይም የማኅበራዊ ግንዛቤ ክህሎቶችን ማዳበር ሊያስፈልጋቸው ይችላል።
- የግንኙነት ባህሪያት (RB)፡
  እነዚህ ባህሪዎች በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል አሉታዊ ግንኙነትን ይፈጥራሉ፣ ይህም አካላዊ ጉዳት አያስከትልም። የግንኙነት ባህሪያት የትምህርት ቤቱ የአየር ሁኔታ ብዙውን ጊዜ ሰዎች እርስ በእርስ እንዴት እንደሚይዙ የሚያንፀባርቅ በመሆኑ መላውን የትምህርት ቤት ማህበረሰብ ይነካል። በግንኙነት ባህሪያት ላይ ችግርን የሚያሳዩ ተማሪዎች በሌሎቹ ማህበረ-ስሜታዊ ብቃቶች ጋርም ሊቸገሩ ይችላሉ።
- የደህንነት ስጋትን የሚፈጥሩ ባህሪያት (BSC)፡
  እነዚህ ባህሪዎች ለተማሪዎች፣ ለሠራተኞች እና ለት/ቤቱ ንብረቶች ደህንነታቸው ያልተጠበቀ ሁኔታዎችን ይፈጥራሉ። የዚህ ዓይነቱ ባህሪ መሠረታዊ ምክንያቶች በማንኛውም ማህበረ-ስሜታዊ ብቃቶች ውስጥ ሊኖሩ ይችላሉ ስለዚህ አስተዳዳሪው የተማሪውን ባህሪ መሠረታዊ መነሻዎች መመርመር አለበት። በማኅበራዊ ግንዛቤ እና ውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሚሰጥ ሥልጠና ብዙውን ጊዜ የደህንነት ስጋት በሚፈጥር በማንኛውም ባህሪ ውስጥ ይመለከታል።
- ራስን ወይም ሌሎችን ለአደጋ የሚያጋልጡ ባህሪያት (BESO)፡
  እነዚህ ባህሪያት የተማሪውን ወይም የሌላውን በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ሌሎች ሰዎችን ጤንነት ወይም ደህንነት አደጋ ላይ ይጥላሉ። ወደዚህ የከፋ ደረጃ የሚደርሱ ባህርያት ብዙውን ጊዜ ውስብስብ ናቸው። ደካማ የውሳኔ አሰጣጥ ክህሎቶችን የሚያመለክቱ ቢሆኑም፣ እነዚህን ባህሪያት የሚያሳዩ ተማሪዎች በሌሎች ማህበረ-ስሜታዊ ችሎታዎች ውስጥም የእድገት ፍላጎቶች ሊኖሯቸው ይችላሉ።

## የተማሪ ባህሪ ምድቦች

| የባህሪ ምድብ | የባህሪ መግለጫ | ሊሰጥ የሚችል አስተዳደራዊ ምላሽ (አስተዳደራዊ ምላሾች በዕድገት ደረጃ መሰረት ሊለያዩ ይችላሉ) | የ MTSS ምላሽ |
|---|---|---|---|
| ምድብ ኤ<br><br>የአካዳሚክ እመርታን የሚያደናቅፉ ባህሪያት (BAP)፡<br><br>(እነዚህ ባህሪያት የተማሪዎችን የአካዳሚክ መሻሻል የሚያደናቅፉ እና በእነዚህ ብቻ ሳይገደቡ የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፡) | የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች<br>• በክፍል ውስጥ ማውራት እና ከመጠን በላይ የሆነ ጫጫታ<br>• ስራ መፍታት፤ ከመቀመጫ ወንበር ውጪ መሆን<br>• በክፍል ውስጥ መማርን የሚያስተጓጉሉ ነገሮችን መያዝ<br>• በአዳራሽ ውስጥ ከመጠን በላይ የሆነ ጫጫታ<br>• ሌሎችን ከፍሎች ማስተጓጎል<br>• መኮረጅ<br>• ከክፍል ወይም ከትምህርት ቤት ይቅርታ የማይደረግለት መዘግየት<br>የመካከለኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፡<br>• በክፍል ውስጥ በመማር ጊዜ ጣልቃ መግባት<br>• ከክፍል ውጪ በመማር ጊዜ ጣልቃ መግባት<br>• የአካዳሚክ ሃቀኝነት መጉደል<br>• ስር የሰደደ የክፍል ዝግጁነት ለማድረግ አለመቻል<br>• ከክፍል ወይም ከትምህርት ቤት ይቅርታ የማይደረግለት መዘግየት | ደረጃ 1:<br>• አዎንታዊ የባህሪ ለውጥን የሚያበረታቱ የመማሪያ ክፍል ድጋፎች እና ጣልቃ ገብነቶች<br>ደረጃ 2:<br>• በ SST የተደገፉ በአዎንታዊ የባህሪ ለውጦች ላይ ያነጣጠሩ የማስተካከያ እርምጃዎች ተከታይ ውጤቶች<br>ደረጃ 3:<br>• የእገዳ እና የት/ቤት ውስጥ እገዳ አማራጮች<br>• ከስድስት እስከ 10 ቀናት የሚደርስ እገዳ<br>• ከአራት እስከ አምስት ቀናት የሚደርስ እገዳ | ደረጃ I<br>ደረጃ II<br>ደረጃ III |
| ምድብ ቢ<br><br>ከት/ቤት ሥራዎች ጋር የተዛመዱ ባህሪዎች (BSO)፡<br><br>(እነዚህ ባህሪያት ከት/ቤቱቹ የእለት ተእለት ተግባራትን ያደናቅፋሉ እና በእነዚህ ብቻ ሳይገደቡ የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፡) | አንደኛ ደረጃ፣ መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች፡<br>• ትክክለኛ ሰነድን መቀየር<br>• በት/ቤቱ ቅጥር ጊቢዎች ውስጥ እንዲገኙ ፈቃድ የሌላቸውን ግለሰቦች ማምጣት/መፍቀድ<br>• ሃቀኛ አለመሆን/ለሰራተኛ ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ መስጠት<br>• በት/ቤቱ ቅጥር ጊቢዎች ውስጥ እያሉ የተመደቡበትን ክፍሎች ወይም የዲሲፕሊን እርምጃ ሁኔታዎችን ሪፖርት ለማድረግ አለመቻል<br>• መቆመር<br>• ማሾፍ<br>• አግባብ ያልሆነ የተማሪ አለባበስ<br>• የግንኙነት መሳሪያዎችን ተገቢ ባልሆነ መንገድ መጠቀም<br>• የት/ቤት ኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎችን ያለፈቃድ መጠቀም<br>• የቴክኖሎጂ/የኢንተርኔት ፖሊሲን ያለአግባብ መጠቀም<br>• የሌሎችን ሰዎች ንብረት ሆን ብሎ ማበላሸት፣ የብልግና ቃላት ወይም ስዕሎችን መጻፍ ወይም መሳል፣ ወይም ት/ቤቱ ላይ ወይም የግል ንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ | ደረጃ 1:<br>• አዎንታዊ የባህሪ ለውጥን የሚያበረታቱ የመማሪያ ክፍል ድጋፎች እና ጣልቃ ገብነቶች<br>ደረጃ 2:<br>• በ SST የተደገፉ በአዎንታዊ የባህሪ ለውጦች ላይ ያነጣጠሩ የማስተካከያ እርምጃዎች ተከታይ ውጤቶች<br>ደረጃ 3:<br>• የእገዳ እና የት/ቤት ውስጥ እገዳ አማራጮች<br>• ከአራት እስከ አምስት ቀናት የሚደርስ እገዳ<br>• ከስድስት እስከ 10 ቀናት የሚደርስ እገዳ | ደረጃ I<br>ደረጃ II<br>ደረጃ III |

# የተማሪ ባህሪ ምድቦች

| የባህሪ ምድብ | የባህሪ መግለጫ | ሊሰጥ የሚችል አስተዳደራዊ ምላሽ (አስተዳደራዊ ምላሾች በዕድገት ደረጃ መሰረት ሊለያዩ ይችላሉ) | የ MTSS ምላሽ |
| --- | --- | --- | --- |
| ምድብ ሲ<br><br>የግንኙነት ባህሪያት (RB)<br><br>(እነዚህ ባህሪያት በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል አሉታዊ ግንኙነትን ይፈጥራሉ፣ ይህም አካላዊ ጉዳት አያስከትልም እና የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡) | አንደኛ ደረጃ፣ መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች፡<br>• ጉልበተኝነት/ሳይበር ጉልበተኝነት<br>• ለሰራተኞች ጥያቄ ምላሽ አለመስጠት<br>• ወሲባዊ ባህርይ ያለውና ተገቢነት የሌለው አካላዊ ንክኪ<br>• ቁሶች ወይም ጽሑፎችን በኤሌክትሮኒክ መንገድ ጨምሮ መለጠፍ፣ ማሰራጨት፣ ማሳየት ወይም ማጋራት<br>• ወሲባዊ ስሜት ቀስቃሽ አስተያየቶችን ፣ ሀሳቦችን ወይም ሌሎች አስተያየቶችን በቀጥታ ወይም በኤሌክትሮኒክ መንገድ መናገር ወይም መጻፍ<br>• ጾታዊ የስነ ምግባር ጥሰት (ከርዕስ IX የወሲባዊ ትንኮሳ በስተቀር)<br>• ባልተገባ፣ ጨዋ ባልሆነ መንገድ ሌላን ሰው ማናገር<br>• ማሾፍ፣ መሳለቅ፣ በቃል ፍጥጫ ውስጥ መሳተፍ፣ በቃል ጠብ ማነሳሳት<br>• ጸያፍ ወይም የብልግና ቋንቋ ወይም የእጅ ምልክቶች (መሳደብ፣ መርገም፣ የጥላቻ ንግግር፣ የወሮበላ ምልክቶች ወይም የእጅ እንቅስቃሴዎች) መጠቀም<br>• በተጨባጭ ወይም በተገመተው ዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በብሔራዊ አመጣጥ፣ በዜግነት/በኢሚግሬሽን ሁኔታ፣ በክብደት፣ በጾታ፣ በጾታ ማንነት፣ በጾታ መግለጫ፣ በጾታ ዝንባሌ፣ በአካል ጉዳተኝነት ወይም በሕግ የተከለከለ በማንኛውም መሠረት ላይ የተመሠረተ ስድብ መጠቀም። | ደረጃ 1፡<br>• አዎንታዊ የባህሪ ለውጥን የሚያበረታቱ የመማሪያ ክፍል ድጋፎች እና ጣልቃ ገብነቶች<br>ደረጃ 2፡<br>• በ SST የተደገፉ በአዎንታዊ የባህሪ ለውጦች ላይ ያነጣጠሩ የማስተካከያ እርምጃዎች<br>ደረጃ 3፡<br>• የእገዳ እና የት/ቤት ውስጥ እገዳ አማራጮች<br>• ከአራት እስከ አምስት ቀናት የሚደርስ እገዳ<br>• ከስድስት እስከ 10 ቀናት የሚደርስ እገዳ<br>• ከ10 ተከታታይ ቀናት የሚበልጥ፣ ነገር ግን ከ365 ተከታታይ ቀናት የሚያንስ እገዳ (ችሎት ያስፈልጋል)<br>• ችሎት የሚያስፈልግ ሆኖ ከት/ቤት ለማባረር የሚሰጥ ምክረ ሃሳብ | ደረጃ II<br><br>ደረጃ III |

# የተማሪ ባህሪ ምድቦች

| የባህሪ ምድብ | የባህሪ መግለጫ | ሊሰጥ የሚችል አስተዳደራዊ ምላሽ (አስተዳደራዊ ምላሾች በዕድገት ደረጃ መሰረት ሊለያዩ ይችላሉ) | የ MTSS ምላሽ |
|---|---|---|---|
| ምድብ ዲ<br><br>የደህንነት ስጋትን የሚፈጥሩ ባህሪያት (BSC)፡<br><br>(እነዚህ ባህሪዎች ለተማሪዎች፣ ለሠራተኞች እና ለት/ቤቱ ጎብኚዎች ደህንነታቸው ያልተጠበቀ ሁኔታዎችን ይፈጥራሉ፣ እነዚህም የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፡) | አንደኛ ደረጃ፣ መካከለኛ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች፡<br>• መያዝ፣ መጠቀም ወይም ማሰራጨት<br>• ማንኛውም የአካል ጉዳት ዛቻ ወይም ንብረት ወይም ህንፃዎችን በቦምብ ለማፍረስ ወይም ለማጥፋት የሚደረግ ሙከራ<br>• ጉልበተኝነት/ሳይበር ጉልበተኝነት፡ እርምጃዎች ከተወሰዱ በኋላ ቀጣይነት የሚኖረው<br>• አውቶብስ፡ ሾፌሩን ማዋከብ፣ በአውቶቡስ ውስጥ ያሉ ሌሎች ሰዎችን ደህንነት አደጋ ላይ መጣል<br>• አደንዛዥ ዕፆች፡ የአደንዛዥ እፅ መገልገያዎችን፣ በሐኪም የሊታዘዘ መድሃኒት ወይም ተመሳሳይ መድኃኒቶችን መያዝ<br>• በራስ ወይም በሌሎች ላይ ጉዳትን የሚያስከትል ግዴለሽ ባህሪ ውስጥ መሳተፍ<br>• የሰውነት ክፍሎችን ማጋለጥ፡ ብልግና ወይም ጸያፍ<br>• የእሳት አደጋ ማስጠንቀቂያ ደወሉን በሃሰት መደወል<br>• ከእሳት ጋር የተያያዘ፡ እሳትን ለማቀጣጠል ወይም ለማቃጠል ወይም ከፍተኛ ጭስ ለማመንጨት ሊያገለግሉ የሚችሉ ዕቃዎችን መያዝ<br>• ርዕስ IX ወሲባዊ ትንኮሳን ጨምሮ ትንኮሳ ወይም ማስፈራራት<br>• በትምህርት ቤቱ አሠራር ወይም በሠራተኞች እና/ወይም በተማሪዎች ደህንነት ላይ ከፍተኛ ሁከት መፍጠር/ማነሳሳት<br>• ያለፈቃድ ከትምህርት ቤት ግቢ መውጣት<br>• ወሲባዊ ባህርይ ያለው አካላዊ ንክኪ ማድረግ የሰውነት ክፍሎችን መተሻሸት፣ መቆንጠጥ፣ ልብስ መጎተት<br>• አካላዊ ወሲባዊ ጥቃት እና/ወይም ሌላ ሰው በወሲባዊ እንቅስቃሴ ውስጥ እንዲሳተፍ ማስገደድ<br>• ተማሪን በመገፍተር፣ በመግፋት፣ በመምታት የማይታይ ጉዳት ማድረስ<br>• ገንዘብ ወይም ንብረት መስረቅ፡ አካላዊ ጉልበት ወይም የጦር መሳሪያ ተጠቅሞ ወይም ሳይጠቀም<br>• ሁከት፣ የአካል ጉዳት ወይም የንብረት ጉዳት የማስከተል አቅም ያለው ነገር መወርወር<br>• ትምባሆ፡ የትንባሆ ምርቶችን፣ የኤሌክትሮኒክ ሲጋራዎችን፣ የእንፋሎት በአፍ የሚሳቡ መሳሪያዎችን መያዝ/መጠቀም<br>• ወዳልተፈቀደ ቦታ መግባት<br>• መሳሪያ፡ ማንኛውንም የጦር መሣሪያ መያዝ ወይም መሸጥ (ጠመንጃዎችን ሳይጨምር) | ደረጃ 1፡<br>• አዎንታዊ የባህሪ ለውጥን የሚያበረታቱ የመማሪያ ክፍል ድጋፎች እና ጣልቃ ገብነቶች<br>ደረጃ 2፡<br>• በ SST የተደገፉ በአዎንታዊ የባህሪ ለውጦች ላይ ያነጣጠሩ የማስተካከያ እርምጃዎች ተከታይ ውጤቶች<br>ደረጃ 3፡<br>• የእገዳ እና የት/ቤት ውስጥ እገዳ አማራጮች<br>• ከአራት እስከ አምስት ቀናት የሚደርስ እገዳ<br>• ከስድስት እስከ 10 ቀናት የሚደርስ እገዳ<br>• ከ10 ተከታታይ ቀናት የሚበልጥ፣ ነገር ግን ከ365 ተከታታይ ቀናት የሚያንስ እገዳ (ችሎት ያስፈልጋል)<br>• ከት/ቤት ለማባረር የሚሰጥ ምክረ ሃሳብ (ችሎት ያስፈልጋል) | ደረጃ II<br><br>ደረጃ III |

# የተማሪ ባህሪ ምድቦች

| የባህሪ ምድብ | የባህሪ መግለጫ | ሊሰጥ የሚችል አስተዳደራዊ ምላሽ (አስተዳደራዊ ምላሾች በዕድገት ደረጃ መሰረት ሊለያዩ ይችላሉ) | የ MTSS ምላሽ |
|---|---|---|---|
| ምድብ ኢ<br><br>ራስን ወይም ሌሎችን ለአደጋ የሚያጋልጡ ባህሪያት (BESO)<br><br>(እነዚህ ባህሪያት የተማሪውን ወይም በት/ቤት ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ሌሎች አካላትን ጤና እና ደህንነት አደጋ ላይ ይጥላሉ፤ ከእነርሱም መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡) | • ጥቃት፡ በሌላ ሰው ላይ የአካል ጉዳት ለማድረስ ማሰብ<br>• ጥቃት እና ድብደባ፡ በሌላ ሰው ላይ የአካል ጉዳት ማድረስ<br>• የቦምብ ዛቻ፡ የቦምብ ዛቻ መሰንዘር<br>• አደንዛዥ ዕፆች፡ (ትምባሆ፣ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ንጥረ ነገሮች፣ ሕገ ወጥ ዕፆች፣ ሲንቴቲክ ሃሉሲኖጂንስ፣ ወይም ያልተፈቀደ የሐኪም መድኃኒቶች) መያዝ/ተጠቅሞ መገኘት/መጠቀም/ማሰራጨት<br>• መደባደብ/ሁከት መፍጠር፡ በተማሪዎች መካከል ወይም በሌላ ሰው ላይ ጉዳት የማያደርስ አካላዊ ጥቃት መፈጸም<br>• እሳት፡ እሳት ለማስነሳት መሞከር፣ እሳት ማስነሳትን ለመደገፍ እገዛ ማድረግ ወይም እሳት ማስነሳት<br>• ከወንጀል ቡድን ጋር የተያያዘ፡ በሚያስፈራራ ወይም በአደገኛ ባህሪ ውስጥ መሳተፍ<br>• ለጸብ መገፋፋት<br>• አካላዊ ወሲባዊ ጥቃት መፈጸም እና/ወይም ሌላ ሰው በወሲባዊ እንቅስቃሴ ውስጥ እንዲሳተፍ ማስገደድ<br>• የጦር መሣሪያዎችን ወይም ተመሳሳይ ነገሮችን መያዝ ወይም መጠቀም<br>• ሰራተኛን መምታት፡ ጉዳት ባይደርስም በሰራተኞች ላይ ሃይልን መጠቀም<br>• በሌላ ተማሪ ወይም ሰራተኛ ላይ ጥቃት ወይም ጉዳት ለማድረስ ማስፈራራት ወይም ጥቃትን ማነሳሳት<br>• የጦር መሳሪያ፡ የጦር መሳሪያ ወይም አውዳሚ መሳሪያ ይዞ መገኘት<br>• የጦር መሳሪያ፡ የጦር መሳሪያን በመጠቀም የት/ቤት ሰራተኞች፣ ተማሪዎች ወይም ሌሎችን ማስፈራራት ወይም የመጉዳት ሙከራ ማድረግ | ደረጃ 1፡<br>• አዎንታዊ የባህሪ ለውጥን የሚያበረታቱ የመማሪያ ክፍል ድጋፎች እና ጣልቃ ገብነቶች<br>ደረጃ 2፡<br>• በ SST የተደገፉ በአዎንታዊ የባህሪ ለውጦች ላይ ያነጣጠሩ የማስተካከያ እርምጃዎች ተከታይ ውጤቶች<br>ደረጃ 3፡<br>• የእገዳ እና የት/ቤት ውስጥ እገዳ አማራጮች<br>• ከአራት እስከ አምስት ቀናት የሚደርስ እገዳ<br>• ከስድስት እስከ 10 ቀናት የሚደርስ እገዳ<br>• ከ10 ተከታታይ ቀናት የሚበልጥ፣ ነገር ግን ከ365 ተከታታይ ቀናት የሚያንስ እገዳ<br>• ከት/ቤት ለማባረር የሚሰጥ ምክረ ሃሳብ (ችሎት ያስፈልጋል) | ደረጃ III |

# በትምህርት ቤት ውስጥ ያሉአሳሳቢሁኔታዎችን ማስወገድ

ከልጅዎ ጋር የሥነ ምግባር ጉዳይን አስመልክቶ ማናቸውም አሳሳቢ ሁኔታዎች ካሉ እባክዎን ከልጅዎ ጋር ከሚሰሩ ሰዎች ጋር ጉዳዩን በቀጥታ ለመወያየት ትምህርት ቤቱን ይገናኙ። አብዛኞቹ ጉዳዮች ከትምህርት ቤት አስተዳዳሪው፣ ከትምህርት ክፍል አስተማሪ ወይም ከተማሪው የድጋፍ ቡድን አባል ጋር በመተባበር በት/ቤት ደረጃ ሊወገዱ ይችላሉ።

**የወላጅ ማስታወቂያ**
- ተማሪው የሥነ ምግባር ጥሰት ከፈፀመ።
- አስተማሪ ወይም አባል ከወላጅ ወይም ሞግዚት ጋር ይናኛል።

**የወላጅ ምላሽ**
- ጥያቄዎች ካሉ፣ ወላጅ ለእርሱ የሚቀርበው ግለሰብ ማትም የትምህርት ክፍል አስተማሪን በመጀመሪያ ይገናኛል።
- ጉዳዩ ከተወገደ በምንም መልኩ መቀጠል አያስፈልግም።

**የወላጅ ምላሽ**
- ወላጅ ከአስተማሪ ጋር ጉዳዩን ይወያያል ግን አሁንም ተጨማሪ ጥያቄዎች ሉኖሩ ይችላሉ።
- የትምህርት ቤት አስተዳዳሪውን ለማብራሪያ ዓላማ ይገናኛል።
- ጉዳዩ ከተወገደ፣ በምንም መልኩ በተጨማሪ ለመቀጠል አያስፈልግም።

**የወላጅ ምላሽ**
- ወላጅ ከአስተዳዳሪ ጋር ተናግሯል ግን እስካሁንም ድረስ ተጨማሪ ጥያቄዎች አሉት።
- የት/ቤት አመራር ዋና ዳይሬክተሩን ያነጋግሩ
- ጉዳዩ ከተወገደ፣ በምንም መልኩ በተጨማሪ ለመቀጠል አያስፈልግም።

**የወላጅ ምላሽ**
- ወላጅ በጉዳዩ ላይ ከት/ቤት አመራር ዋና ዳይሬክተር ጋር የተወያዩ ቢሆንም፣ አሁንም የሚያሳስባቸው ነገር አለ
- የኃላፊውን ቢሮ ይገናኙ።

# ፍተሻና ህገወጥ ንብረቶችን መያዝ

የተማሪው ፍተሻ በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ውስጥ የሁሉንም ሰዎች ጤና ደህንነት እና በጎነት በትምህርት ቤቱ መምሪያው የማስጠበቅ ሃላፊነት እና የትምህርታዊ ተልእኮውን ከማከናወን አንፃር ተገቢ ካልሆነ ፍተሸ እና መያዝ የተማሪው ግላዊ ሙብትና ነፃነት አንፃር በተመጣጠነ መልኩ ተመርኩዞ የሚፈጠር ነው። በትምህርት ቤቱ ውስጥ ስርአትና ስነምግባረትን ለማስጠበቅ እና የተማሪዎቹንና የትምህርት ፐርሶኔሉን ጤና በጎነትና ደህንነት ለማስጠበቅ፣ የትምህርት ቤቱ ባለስልጣናት ከዚህ በታች በተቀመጡት ሁኔታዎች ስር ተማሪውን የተማሪውን ንብረቶች፣ የተማሪውን መቆለፊያዎች ወይም የተማሪውን ተሽከርካሪዎች ሊፈትሹ እና በፍለጋ ወቅት የተገኙ ማናቸውንም ህገወጥ፣ ያልተፈቀዱ ወይንም ኮንትሮባንድ ማቴርያሎች ለመያዝ ይችላሉ።

በዚህ ክፍል ውስጥ ጥቅም ላይ እንደዋለው "ያልተፈቀደ" ማለት በተማሪዎች ወይም በትምህተርት ቤቱ ፐርሶኔል ላይ ጤና ወይንም ደህንነት ላይ አደጋን የሚጋልጥ በትምህርት ቤቱ ማናቸውንም ህጋዊ አሰራር ተልእኮ ወይንም ሂደት ላይ ረብሻን የሚፈጥር ወይም አስቀድሞ ለተማሪው እንዲቀርቡ በተደረጉት የትምህርት ቤቱ ደንቦች ያልተፈቀደ ተብሎ የተገለጠ ማንኛውንም ድርጊት ይሆናል።። "የተማሪው ንብረቶች" የሚያካትቱዋቸው በነዚህም ሳይወሰን በጀርባ የሚነገቡ ቦርሳዎች ተንቀሳቃሽ ስልኮች ወይንም የኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች የእጅ ቦርሳዎች ጃኬቶች ወይንም ሌሎች የግላዊ እቃዎች ይሆናሉ።

በዚህ ፖሊሲ ውስጥ እንደቀረበው ፍተሻ እና ህገወጥ ንብረቶችን የመያዝ እርምጃን ለመተባበር ያልቻለ ተማሪ የስነምግባር እርምጃ አወሳሰድ መስረቶች ተደርጎ ይቆጠራል።

የተማሪዎቹ እና የተማሪው ንብረት ፍለጋ የሚከናወንባቸው ቦታዎች በትምህርት ቤቱ ህንፃ ወይንም በትምህርት ቤቱ ንብረት ላይ የተወሰኑ አይደሉም። ስለዚህም ፍተሸዎቹ የሚከናወኑት በትምህርት ቤቱ ስፖንሰር የተደረጉ ተግባራት በሚከናወኑባቸው ማናቸውም ቦታዎች ነው።

## የግላዊ ፍተሻዎች

የተማሪው አካል (የውጫዊ አልባሳትን ጨምሮ) እና ወይንም የግላዊ ንብረቶች ኃላፊው ተማሪወ ህገወጥ ወይንም የተከለከሉ ነገሮችን ይዟል። ወይንም ህጉን ወይንም የትምህርት ቤቱን ደንብ ጥሷል ወይም ሊጥስ ነው ብሎ ለማመን ተገቢ ጥርጣሬ ካለው የሚካሄድ እና ፍለጋው ለጥሰቱ ማስረጃ የሚያስገኝ ነው። ሁሉም የተናጠል የተማሪዎች ፍተሻ አግባብነት ባለው ጥርጣሬ ማለትም ስለተፈፀመ ጥፋት ማስረጃ የማግኘት መጠነኛ እድል ላይ ተመስርቶ መጀመር አለበት።

ፍተሻው ይፈቀድ ዘንድ፥

1. በጅማሬው ላይ ተገቢ በሆነ ጥርጣሬ ከተስተባበለ እና።

2. ፍተሻውን የሚያስተባብሉ ሁኔታዎች ጋር በአግባቡ ከተገናኘ።

ግለሰባዊ ፍተሻ በምርመራው ወቅት ትክክለኛነቱ የሚረጋገጠው፣ የትምህርት ቤቱ ኃላፊ፣ በታወቁት ሁኔታዎች አጠቃላይነት ላይ ተመስርቶ፣ ተማሪው ህገወጥ ወይም ያልተፈቀዱ ቁሳቁሶች መያዙን ወይም የትምህርት ቤቱን ደንብ ወይም ህግ ጥሷል ወይም ሊጥስ በመሆኑ ፍተሻው የጥሰቱን ማስረጃ ያስገኛል የሚል ምክንያታዊ ጥርጣሬ በሚኖራቸው ጊዜ ነው። የተወሰነው እርምጃ ከተማሪው ዕድሜ፣ ፆታ እና የተጠረጠረው ወንጀል ተፈፃሚነት አንጻር ከተግባራዊ ዓላማዎቹ ጋር ምክንያታዊ በሆነ መልኩ ተያያዥነት ሲኖረው እና ከመጠን በላይ ጥብቅ እና ጣልቃ ገብ ሳይሆን ሲቀር የትምህርት ቤት ፍተሻ ይፈቀዳል።

የተማሪዎች ተቆላፊ ሳጥኖች፣ ዴስኮች የትምህርት ቤት ኮምፒውተሮች እና ሌሎች ቴክኖሎጂዎች እና ተማሪዎች በትምህርት ቤቱ ንብረት ላይ በሚሆኑበት ጊዜ መኪናዎች ላይ ፍተሻ ሊካሄድ ይችላል።

## በስምምነት የሚደረጉ ፍተሻዎች

አንድ ተማሪ አካላዊ ፍተሻ፣ የግላዊ ንብረቶቹ እና ወይም የተሽከርካሪው ውስጣዊ ክፍል ፍተሻ እንዲደረግለት ለት/ቤቱ ኃላፊ ስምምነቱን ከገለፀ፣ የት/ቤቱ ኃላፊ አግባብነት ያለውን ጥርጣሬ ማሳየት አያስፈልገውም የተማሪውም ስምምነት ህጋዊ የሚሆነው በፍቃደኝነት እና በስምምነት ትርጓሜ እውቀት እስከተሰጠ ብቻ ነው። ተማሪዎች ፍሊጋውን የመቃወም መብታቸው ይነገራቸው እና ተማሪው ለፈለገው ፍቃዱ መስተት በመቃወሙ ለከባድ ቅጣት እራሱን እንዳጋለጠ መታየት የለበትም።

## በት/ቤት ውስጥ የህግ አፈፃፀም ኃላፊዎች ምርመራዎች

ማንኛ ውም የህግ አፈፃፀም መኮንን በትምህርት ቤቱ ቅጥር ጊቢ ውስጥ ማንኛውም ተማሪ ቃለመጠይቅ ለማድረግ ሲፈልግ የትምህርት ቤቱ ኃላፊ ወይንም ተሰያሚው ሞግዚቱን ወይንም ተሰያሚውን ለማግኘት እና ወላጅ ወይንም ሞግዚት በስብሰባው ላይ እንዲገኝ ለማድረግ የተሸለውን ጥረት ያደረጋል። ወላጅ ወይንም ሞጊዚት በስብሰበው ላይ ሊገኝ ካልቻለ፣ ኃላፊው ወይንም ሞግዚቱ በቃለ መጠይቁ በመላ ላይ መገኘት አለበት።፡

ተጨማሪ መረጃ በአባሪ ቸ ውስጥ ማግኘት ይቻላል።

# የስነምግባር እርምጃ መሰማት ሂደቶች

***በመጀመሪያ ደረጃ እግድ ካልተስማማሁስ?***
በተሰጠው እገዳ ውሳኔ የማይስማሙ ከሆነ የይግባኝ መጠየቂያ ደንዳቤ ያዘጋጁሉ። እባክዎ ከዚህ በታች የተጠቀሰውን ቅደም ተከተል ይከተሉ። ተገቢው የይግባኝ መጠየቂያ ደብዳቤ (ከዚህ በታች የተገለጸ) ካልተሞላ በስተቀር ይግባኝ እንደተጠየቀ አይቆጠርም። የይግባኝ ደብዳቤው እስከሚደርስ ድረስ ተማሪው እንደታገደ ይቆያል። በአጠቃላይ በጽሁፍ የቀረበ የይግባኝ መጠየቂያ ሲደርስ የይግባኝ ሂደቱ እልባት እስኪያገኝ ድረስ እገዳው ለጊዜው ይነሳል። ተማሪው ለራሱ ወይም ለሌሎች አደጋ የሆነ እንዲሁም ሌሎች ተማሪዎች ትምህርታቸውን እንዳይቀጥሉ ሁከት የሚፈጥር ነው ተብሎ ከተፈረጀ እገዳው ለጊዜው አይነሳም። ይህ ከሆነ የይግባኝ ሂደቱ እልባት ሳያገኝ ተማሪው ወደ ትምህርት ቤት እንዲመለስ አይፈቀድለትም።

***የአጭር ጊዜ እግዶች ይግባኝ ስነስርአት - ከ1-10 የትምህርት ቀናት***
ወላጅ/አሳዳጊ/ተማሪ ከአንድ እስከ 10 የትምህርት ቀናት ያሉ የአጭር ጊዜ እገዳ ውሳኔዎች ላይ ይግባኝ ማለት ሲፈልጉ መከተል ያለባቸው አካሄዶች የሚከተሉት ናቸው።

1. ተማሪውን ባገደው የትምህርት ቤት አስተዳዳሪ እግዱ ላይ ይግባኝ የሚጠይቁበትን ምክንያት በማብራራት ደብዳቤ ማቅረብ። እግዱ ለመጀመሪያ ለእርስዎ (አብዛኛውን ጊዜ በስልክ ሆኖ ከዚያ በመቀጠል ደብዳቤ ይላካል) ከተነገረበት ጊዜ ጀምሮ ቀን በኃላ በ24 ሰዓት ውስጥ የይግባኝ ደብዳቤውን በእጅ፣ በኢሜል ወይም በመልእክት ሳጥን ማስገባት።
2. ይግባኙ ተማሪውን ባገደው አስተዳደር ከተከለከለ፣ ለኃላፊው በፅሁፍ ለማመልከት ይችላሉ። ይይግባኝ ደብዳቤው ተማሪውን ካገደው አስተዳደር ምላሽ በተቀበሉ በ2 ቀናት ውስጥ በመልእክት በኢሜል ወይም በአካል መረከብ አለበት።
3. ይግባኝዎ በርዕሰ-መምህሩ ውድቅ ከተደረገ፣ ምላሽዎን ከት/ቤቱ ርዕሰ መምህር ምላሽ ባገኙ ሶስት የትምህርት ቀናት ውስጥ በቀጥታ ለ ACPS ዋና ርዕሰ መምህር ይግባኝ ማለት ይችላሉ። በጽሑፍ የተዘጋጀ የይግባኝ ደብዳቤ በቀጣዩ አድራሻ መቅረብ አለበት፡:

   ACPS Lead Principal
   Department of Teaching, Learning and Leadership
   1340 Braddock Place
   Alexandria, VA 22314

4. ይግባኝዎ በ ACPS ርዕሰ መምህር ውድቅ ከተደረገ፣ የተማሪ አገልግሎቶች ዋና ዳይሬክተር ምላሽ ከሰጡበት ቀን ጀምሮ ባሉት አምስት የትምህርት ቀናቶች ውስጥ የመጨረሻ ይግባኝ ለዋና ተቆጣጣሪ ቢሮው ማቅረብ ይችላሉ። በጽሑፍ የተዘጋጀ የይግባኝ ደብዳቤ በቀጣዩ አድራሻ መቅረብ አለበት፡

   Alexandria City Public Schools
   Executive Director of Student Services
   Department of Student Services and Equity
   1340 Braddock Place
   Alexandria, VA 22314

**እገዳ ከዲስፕሊን ችሎት ምከረ ሃሳብ ጋር**

***ለምን?***
እያንዳንዱ ተማሪ የአእምሮአዊ እውቀቱን ለማብቃት የሚችልበት የትምህርታዊ አካባቢን የመጠበቅ መብት አለው። ተማሪው መደበኛ ትምህርትን መካፈል በጥናቱ ትጉ መሆንና የሌሎች ሰዎች መብቶች እና ጥቅሞች በማይጣስበት መልኩ መስራት ይጠበቅበታል። ተማሪው ችግሮች እንዳይከሰቱ ለመከላከል እና ችግሮችም ከተከሰቱ ለማስወገድ ለመርዳት ጥሩ የዜግነት ግዴታን መቀበልና ማሳየት ይጠበቅበታል።

የትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪ አንድ ተማሪ የ ACPS የተማሪ ስነምግባር ጥሷል ብሎ ሲያምን የተማሪ የዲሲፕሊን ችሎቶች የሚካሄዱ ሲሆን የረጅም ጊዜ እገዳ (10 ወይም ከዚያ በላይ ቀናት) ወይም ማባረርን ጨምሮ ተጨማሪ መዘዞች ከግምት ውስጥ መግባት አለባቸው።

***ይህ እንዴት ሊከሰት ይችላል?***
በተለይ እንደ ከባድ የሚቆጠር የተማሪ ሥነ ምግባር ደንብ መጣስ ሲከሰት፣ (ማለትም በትምህርት ቤት ውስጥ መሣሪያ፣ አደንዛዥ ዕፅ ወይም አልኮል ይዞ መገኘት፣ አካላዊ አለመግባባት ውስጥ መሳተፍ)፣ ርእሰ መምህሩ ጥሰቱ የረጅም ጊዜ እገዳ ወይም

መባረርን የሚያስከትል መሆን አለመሆኑን ይወስናል። ይህ ውሳኔ ከመወሰኑ በፊት፣ ልጅዎ የፍትህ ሂደት የማግኘት መብት አለው፣ ይህም ማለት ተማሪው የሚከተሉትን ያደርጋል ማለት ነው፡

1. የደንብ ጥሰት እና ማስረጃው ይገለፀለታል።
2. ስለሁኔታው የራሱን አስተያየት የማቅርብ እድል ይሰጠዋል።
3. በውሳኔው ላይ ይግባኝ የማለት እድል ይሰጠዋል።

አንዴ ይህ ከተከሰተና ልጅዎ እንዲባረር በሚል ድጋፍ ከታገደ ወይም ለችሎት እንዲቀርብ ከተደረገ፣ የተማሪ አገልግሎቶች እና ፍትህ መምሪያ ተወካይ የችሎት ቀጠሮ ለማስያዝ ያነጋግርዎታል። የችሎቱ ቀን እና ሰዓት ለመመስረት ወላጆች በ 703-619-8036 ላይ የተማሪ አገልግሎቶች እና ፍትህ ዲፓርትመንትን በንቃት እንዲያነጋግሩ ይበረታታሉ።

***ከመሰማቱ ሂደት በፊት የተላለፉ የእግድ ቀናት አሉን?***
ተማሪዎ ሂደቱ እስኪሰማበት ድርስ ከኤሲፒኤስ ይታገዳል። በዚህ ጊዜ ውስጥ ማናቸውንም የኤሲፒኤስ ካምፓሶች እንዲማር ወይንም በማናቸውም የኤሲፒኤስ ዝግጅቶች ላይ እንዲገኝ አይፈቀድለትም።

***ሂደቱ ለምን ይሰማል?***
ሂደቱ የሚሰማው ጉልህ ጥሰቶችን ተከትሎ የሚመጡ ሁኔታዎችን ለመወሰን ነው።

***ሂደቱ ሲሰማ ምን ይከሰታል?***
በተማሪው አገልግሎቶች እና ፍትህ አስተዳደር ዲፓርትመንት ተቀናጅቶ በቀረበው፣ በችሎቱ ወቅት፣ ሁሉም የሚመለከታቸው መረጃዎች መገኘታቸውን ለማረጋገጥ የሚከተሏቸው እርምጃዎች ብዛት። ከዚህ በታች የችሎት ናሙና አጀንዳ አለ፡

1. ማስተዋወቅ
2. የአቤቱታቅሬታ አፈፃጸም ክለሳ.
3. ስለጉዳዩ በአስተዳደር የሚቀርብ
4. የተማሪው ሃሳብ ማቅረብ
5. የወላጅ/አሳዳጊ ሃሳብ ማቅረብ
6. ተጨማሪ መግለጫ
7. ማጠቃለያ
8. መዝጊያ/ ውሳኔ (አስታውሱ፤ ውሳኔ በቅሬታ አቀራረብ ሂደት ላያልቅ ይችላል።)

የስነ ስርዓት ሂደት በሚደመጥበት ወቅት አካል የተማሪው ማህደር ይታያል። ይህም የማህደር ምርመራ በእነዚህ ላይ ብቻ ባይወሰንም የሚከተሉትን ያጠቃልላል፤ የተማሪውን የአካዳሚክ ፣ ባህሪ፣ የትምህርት መከታተል/ያለ ምክንያት መቅረት ፣ የስራ ምርጫ ፕላን እና ምዘና ውጤት እና የአደጋና የስጋት ምዘና ይጨምራል።

***ሂደቱን ማን ይካፈላል?***
ከልጅዎ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር እና/ወይም የምክትል ርእሰ-መምህር፣ ወይም የተማሪ ዲን ችሎቱ ላይ ይገኛሉ። የይግባኝ ሰሚ መኮንን ተጨማሪ የትምህርት ቤት ሠራተኞችን ለመጋበዝ መብት አለው። ልጅዎ የእሱን/የእሷን በጉዳዩ ዙሪያ ያላቸውን ዕይታ የማቅረብ እድል እንዲኖራቸው ሁለታችሁም እርስዎ እና ልጅዎ በችሎቱ መገኘታችሁ አስፈላጊ ነው። ምስክሮችን አስመጥተው በልጅዎ ፋንታ እንዲያስመሰክሩ ተፈቅዶልዎታል። ከመረጡም ጠበቃ እንዲኖርዎትም ተፈቀዶልዎታል። በተጨማሪም፣ የተማሪ አገልግሎቶች እና የፍትህ መምሪያ ሂደቱን ያመቻቻል እና አስፈላጊ ከሆነም፣ ተርጓሚ ወይም አስተርጓሚ ሊኖር ይችላል።

**ከችሎቱ ሊገኙ የሚችሉ ውጤቶች ምንድን ናቸው?**
የተማሪዎች አገልግሎት እና ፍትህ አስተዳደር መምሪያ በራሱ ውሳኔ የሚሰጥባቸው የተለየዩ ውጤቶች ያሉ ሲሆን፣ እነርሱም የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፡

- አማራጭ የትምህርት ፕሮግራም ምደባ
- አማራጭ የማስተማሪያ ድጋፍ (AIS) ማእከል
- ምክር
- የፍርድ ቤት ውሳኔ
- በት/ቤት እገታ
- ከኤሲፒኢስ ት/ቤቶች መባረር
- በት/ቤት ውስጥ እገዳ (ISS)
- የግልግልና/ መልሶ የማጠናከር(ሬስቶሪቲቭ) አሰራር
- ከት/ቤት ውጭ እገዳ (OSS)
- የቤተሰብ ስብሰባ
- መልሶ መመደብ
- ወደ ትምህርት ቤት መመለስ የሙከራ መስፈርቶች ወይም ያለ መስፈርቶች
- የቃዳሜ እገዳ
- የትምህርት ቤት/ ማህበረሰብ አገልግሎት ፕሮጀክቶች
- የተማሪ ጥቅምች እገዳ
- በአስተዳዳሪ የሚሰጡ ስራዎች

የተማሪ አገልግሎቶች እና የእኩልነት ዲፓርትመንት ልጅዎን እስከ አንድ ዓመት ድረስ የማገድ እና ለአሌክሳንድሪያ ሲቲ ትምህርት ቤት ቦርድ እንዲባረሩ ምክር የመስጠት ስልጣን አለው።

**ትምህርታዊ ድጋፎች**

ተማሪዎች ከትምህርት ሲታገዱ ለት/ቤት ሥራ ተደራሽነት እና የትምህርት ቤት ሥራን እንዲያጠናቅቁ ዕድል ይሰጣቸዋል። ከእኩዮቻቸው ጋር ተመሳሳይ ፍጥነት እንዲኖራቸው፣ የመመረቂያ ጊዜያቸውን ለማስጠበቅና እና ወደ ተጨማሪ የባህሪ ስጋቶች ሊያመራ የሚችል የኮርስ ሥራ ውስጥ ወደ ኋላ መቅረት ዕድልን ለመቀነስ፣ እያንዳንዱ ተማሪ በእገዳ ወቅት ወይም ከእገዳ በኋላ ውጤት የተሰጠው የትምህርት ቤት ስራ ያገኛል።

**ለተጨማሪ ጥያቄዎች**
ማናቸውም አይነት ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎ ለተማሪ አገልግሎቶች እና የእኩልነት ክፍልን በ 709-619-8036 ያነጋግሩ።

# የስነ ምግባር ቃላት ትርጓሜ

አልኮል መጠቀም፣ ይዞ መገኘት፣ መጠቀም ወይም ማሰራጨት፡ አልኮል ተብለው የሚመደቡ አነቃቂ ወይም ንጥረ ነገሮችን ስለ መያዝ፣ ማምረት፣ መሸጥ፣ መግዛት፣ ማጓጓዝ፣ ይዞ መገኘት ወይም መጠቀም የወጡ ህጎችንና ደንቦችን ተላልፎ መገኘት ማለት ሲሆን በስነ ምግባር እርምጃ አወሳሰድ ላይ አልኮል ተጠቅሞ መገኘት በጥርጣሬ ደረጃም ሊጠቃለል ይችላል።

ዘለፋ፡ የአካል ጉዳት የማያስከትል የቃል ወይም/የንክኪ ጥቃት።

አማራጭ የትምህርት ፕሮግራሞች፡ የማታ ትምህርትን፣ የአዋቂዎች ትምህርትን ወይም ሌላ አይነት መደበኛው የትምህርት ፕሮግራም ለማይመጥናቸው ተማሪዎች ተብሎ የሚሰናዳ ፕሮግራምን በውስኑ ያጠቃልላል።

አማራጭ የማስተማሪያ ድጋፍ (AIS) ማእከል፤ ተማሪው እንደሚያሳየው አጥፊ ባህሪ ተመስርቶ ከዚህ ቀደም የተወሰደው እርምጃ ውጤታማ ካልሆነ ከመደበኛ የትምህርት ሰዓቱ ስኬጅውሉ እንዲወጣ ሊደረግ እንዲሁም በአንድ በተመረጠ ባለሞያ ሰራተኛ ስር ለአንድ ክፍል እስከ ግማሽ የትምህርት ቀን ያህል ለተወሰነ ጊዜ ሊያጠና ይችላል።

ቃጠሎ/እሳት፡ በህገ ወጥ መንገድ ሆን ብሎ በትምህርት ቤት ንብረት ላይ በእሳት ወይም በተቀጣጣይ መሳሪያ ጉዳት ማድረስ፤ ሮኬት፣ ርችት እና በቆርቆሮ ላይ የሚነድድ እሳት የእሳት አደጋን ለማድረስ እስከዋሉ ድረስ በዚህ ውስጥ ይጠቃለሉ።

ጥቃት ማድረስ ወይም መደብደብ፡- በሌላ ሰው ላይ አካላዊ ጉዳት የሚያስከትል በፈቃደኝነት የሚደረግ ድብድብ እንደ ጥቃት እና ድብደባ ይቆጠራል። አካላዊ ጥቃት ምንም ጉዳት፣ ቀላል ጉዳት ወይም ከባድ ጉዳትን ሊያካትት የሚችል ማንኛውንም አካላዊ ፍጥጫን ያካትታል፤ ነገር ግን፣ እርግጫን፣ መገፍተርን፣ መግፋትን፣ መምታት እና መደባደብን ብቻ ላያካትት ይችላል። ተጨባጭ የሆነ አስጸያፊ፣ ኃይለኛ፣ ሃይል የቀላቀለ እና ሆን ተብሎ አንድን ተማሪ ያለ ፈቃዱ መነካካት ወይም የጦር መሳሪያ ወይም ሌላ መሳሪየ በመጠቀም ሆነ ብሎ በተማሪ ላይ የአካል ጉዳት ማድረስ። በመንጋ የሚጸም ጥቃትን ይጨምራል።

ድብደባ፡ አንድ ሰው በሌላ ሰው ላይ የሚያደርሰው ህግ ውጪ የሆነ ጉዳት ወይም የሃይል ተግባር።

የጠባይ ቁጥጥር መርሐ ግብር፡ የአካል ጉዳት ያለባቸውን ተማሪዎች ወይም የሌሎች ተማሪዎችን የመማር እንቅስቃሴ በሚጎዳ ወይም ጣልቃ በሚገባ ጠባይ ላይ እርምጃ ለመውሰድ የሚሰናዳ መርሐ ግብር ማለት ነው።

በትምህርት ቤት መጓጓዣ አውቶቡስ ላይ የሚታይ ጠባይ፡ ተማሪዎች  የትምህርት ቤት መጓጓዣ አውቶቡስ ሲጠብቁ፣ ተሳፍረው ሲሄዱ ወይም ሲወርዱ በመልካም ጠባይ ላይ መገኘት አለባቸው።

የቦምብ ዛቻ፡ ተማሪዎች የቨርጂኒያን ህጎች በሚጥስ አግባብ ማንኛውም የሚፈነዳና የሚቀጣጠል መሳሪያ ይዘው መገኘት የለባቸውም። በተጨማሪም በትምህርት ቤት ቦምም እንደሚፈነዳ በመግለጽ ማንኛውንም አይነት ዛቻ ወይም ማስፈራራት ከማድረግ መቆጠብ አለባቸው።

ስርሰራ፡ ወንጀል በመፈጸም አሳብ ወደ ትምህርት ቤቱ ንብረት ወይም ህንጻ ውስጥ ለመግባት የሚደረግ ሙከራ ማለት ነው።

ትንኮሳ፡ ይህ ተግባር ተደጋጋሚ አሉታዊ ጠባዮችን በማሳየት የሚፈጸም ሲሆን የቃል ወይም ጽሁፍ ማስፈራሪያ መስጠትን፣ ስድብን፣ ስም መጥራትን፣ ተረብን እና የእነኚህን ድርጊቶች ስብጥር ያጠቃልላል።

አንድ ተማሪ በግል ወይም በቡድን በመሆን ሌሎችን በአካል ወይም በመገናኛ መሳሪያዎች እንደ ኮምፒውተር ፣ በስልክ ፣ በፔጀር፣ አስቸኳይ መልክት ማስተላለፊያ በመጠቀም ማዋከብ  ወይም ማስፈራራት አይኖርበትም ።የተከለከሉ ባህሪዎች ስለ አንድ ሰው ወይም ከእርሱ/እርሶ ጋር የሚቀራረቡ ሰዎችን ላይ ያተኮረ ስለዘር፣ ፃታ፣ ሐይማኖት፣ የአካል ወይም የሰውነት ችሎታ ፣ የወሲብ ፍላጐት ምርጫ፣ ወይም ሌሎች ባህሪያት  የሚገለፅ ንግግር።

ሳይበር ትንኮሳ፡ እንደ ኮምፒውተር ሲስተም፣ ስልክ፣ ኢንተርኔት፣ ማህበራዊ ድረገጽ ወይም ኤሌክትሮኒክ መልዕክቶችን በመጠቀም ሌላ ተማሪን ወይም ተማሪዎችን ለመጉዳት የታሰቡ አግላይና ክብርን የሚነኩ ቃላትን መጠቀም ወይም መግለጽ ማለት ነው።

የምደባ ለውጥ፡ የስነ ምግባር ሲባል፡

ከ10 ተከታታይ ቀናት ለሆነ ጊዜ አንድ ተማሪ ከትምህርት ምድብ ስፍራው ማንሳት።

ተማሪዎች ከ10 በላይ ተከታታይ ቀናት በአመት ካሳለፉ ለተከታታይ ምደባ ይጋለጣሉ።

ኩረጃ፡ መልስ ለሌሎች መስጠት፣ የቤት ስራ መቅዳት፣ ሌላ የቤት ስራን ወይም የመምህሩን መምሪያና ማቴሪያሎች መቅዳት ያጠቃልላል።

የትምህርት ቤት ባለስልጣናትን መጣስ፡ የትምህርት ቤት ባለስልጣናት በቦርዱ የተሰጣቸውን ስልጣን መሰረት በማድረግ የሚያስተላልፉትን የቃላትና የጽሁፍ መመሪያ ተማሪዎች ማክበር አለባቸው።

አጥፊ ወይም ፈንጂ መሳሪያ፡ (1) ማንኛውም ፈንጂ፣ የእጅ ቦምብ፣ መርዝ ጋዝ፣ ከአንድ አስስ በላይ የሆነ ሮኬት እና አንድ ከጉብ ያህል አንስ ተወንጫፊነት ያለው ሚሳይል ወይም ተመሳሳይ መሳሪያ (2) ለስፖርት አላማ ከሚውል ሻት ጋን እና ከዚሁ ጥይት በስተቀር ማንኛውም በፕሮጀክታይል ተወንጫፊነት የሚተኮስና ከአንድ ተኩል ኢንች በላይ መሪ ዘንድ ያለው መሳሪያ (3) ማናቸውም ሲገጣጠሙ አውዳሚ መሳሪያ ሆነው በጥቅም ላይ መዋል የሚችሉ ተገጣጣሚ ዕቃዎች። አውዳሚ መሳሪያ ሲባል ለአውዳሚነት አላማ ያልተሰሩ መሳሪዎችን ወይም በአውዳሚነት ተሰርተው በኋላ ግን ወደ ሌላ አይነት አላማ የተለወጡ መሳሪያዎችን አያጠቃልልም።

ንብረት ማውደም/ማበላሸት፡- ማለት የንብረቱ ባለቤት ወይም ጠባቂ ወይም ተቆጣጣሪ ሳይፈቅድ ሆን ብሎ እና/ወይም በተንኮል የህዝብን ወይም የግል የሆነ ንብረትን ማበላሸትና ማውደም ማለት ነው። ይህ ምድብ በትምህርት ቤቱ ግድግዳ ላይ ስዕል መሳልን ያካትታል። ተማሪዎች የትምህርት ቤቱን ህንጻ ወይም ሌላ አይነት ንብረት ሆን ብሎ ከመጉዳትና በትምህርት ቤቱ፣ በትምህርት ቤቱ አውቶቡስ ወይም በትምህርት ቤቱ ስፖንሰር የሚደረጉ ዝግጅቶች ላይ የሚገኝ ንብረትነቱ የሌላ ሰው ንብረት የሆነን ወይም በሌላ ሰው ጥበቃ ስር ያለ ማንኛቸውም ዋጋ የሚያወጣ ዕቃ ከመጉዳት መጠበቅ ይገባቸዋል።

ስርዓት ማጣት፡ ለባለስልጣን ትዕዛዝ ያለመገዛት፣ መልስ ያለመስጠት ወይም ሆን ብሎ የትምህርት ቤት መደበኛ እንቅስቃሴን ማወክ።

አለማክበር፡- በባህሪው አስፈሪ፣ ተቆጪ ወይም ንቀት የሆነ አግባብነት የሌለው ቋንቋን ወይም ባህሪን መጠቀም።

ረባሽ ስነ ምግባር/ባህሪ፡- ማንኛቸውም የትምህርት ቤት እንቅስቃሴ፣ ስራ ወይም ሒደት የሚረብሽና ለተማሪዎችም ሆነ ለሌሎች ጤንነት ወይም ደህንነት አስጊ የሆነ እንዲሁም የትምህርት ሂደቱን የሚያስተጓጉል ተግባር። በተደጋጋሚ የሚከሰት ረባሽ ስነ ምግባርን ያካትታል። ይህ ትርጓሜ ወደ ት/ቤት ሲኬድ እና ከት/ቤት ሲመለሱ ያለን ምግባር ያካትታል፤   በ Va. Code 22.1-78 መሰረት።

የረብሻ ተግባር፡ ማናቸውንም የትምህርት ቤት ተግባር ወይም ሒደት  የሚረብሽና ለተማሪዎችም ሆነ ለሰራተኞች ጤንነት ወይም ደህንነት አስጊ የሆነ ተግባር።

ህገወጥ ዕፆችን ማሰራጨት፣ መያዝ ወይም የመሸጥ ፍላጎት፡ ተማሪዎች ማሪዋና፣ ሲንተቲክ ካናዮንድስ ወይም ሌላ በመድሀኒት ቁጥጥ ድንጋጌ ምእራፍ 15.1 ርእስ 54 ስር በቨርጂኒያ ህግ ላይ የተመለከተ እጽ መያዝ፣ መሸጥና ማዘዋወር አይችሉም።

- የእጽ ጥፋት፡ ማሪዋና እና ሌሎች በአንደኛና ሁለተኛ መርሐ ግብር ላይ የተመለከቱ ሀሺሽ የሆኑ እጾችን ለማምረት፣ ማጓጓዝና ይዞ ለመገኘት የወጡ ህጎች መተላለፍ
- በማሪዋና መጠርጠርም በስነ ምግባር እርምጃ አወሳሰድ ላይ ሊካተት ይችላል
- በህገ ወጥ አግባብ እጽ ተብለው የሚቆጠሩ ነገሮችን ማምረት፣ መግዛት፣ ማብቀል፣ ማጓጓዝ ወይም ማስገባት አይፈቀድም።
- ለሌላ ሰው ተብሎ የታዘዘ መድሃኒትና እጽ መያዝ አይቻልም።
- በህገ ወጥ መንገድ ለስርጭት፣ ለሽያጭ ወይም ለሌላ አላማ እጽ መያዝ አይቻልም
- በህገ ወጥ መንገድ ለመጠቀም፣ ለስርጭት፣ ለሽያጭ ወይም ለሌላ አላማ በህግ የተከለከሉና ቀደም ሲል በተገለጸው የእጽ ምድብ ውስጥ ያልተካተቱ እጾችን መያዝ አይቻልም
- የሀሺሽ መጠቀሚያ ወይም ማጨሻ እቃዎችን በኪስ ወይም በቦርሳ ውስጥ ይዞ መገኘት አይቻልም
- በህገ ወጥ አግባብ ያልተፈቀዱ መድሃኒቶችንና ንጥረ ነገሮችን ማምረት፣ መግዛት፣ ማብቀል፣ ማጓጓዝ ወይም ማስገባት አይፈቀድም።

የኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎችን ወይም ተንቀሳቃሽ ስልኮችን ያለአግባብ መጠቀም፡- ስድብን፣ ዝልፊያን፣ በዘር ወይም በጾታ ጥቃት የሚያደርሱ ነገሮችን በጽህፈት ለመግለጽ፣ ልቅ የሆኑ አስተያየቶችን ወይም ምልክቶች ለማስተላለፍ፣ ሌላ ተማሪን ለማጥቃት፣ ለማዋረድ ወይም ሃሰት ስለ አንድ ተማሪ ወይም ሰራተኛ የሆኑ ነገሮችን ለመናገር ቴክኖሎጂን ወይም ተንቀሳቃሽ ስልክን አለአግባብ መጠቀም።

የሌሎች ሰዎችን ደህንነት አደጋ ላይ መጣል፡- የአንድ ተማሪን ወይም ሰራተኛን ጤንነት፣ ህይወት ወይም ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል ማንኛውም ባህሪ።

መገለል፡ የትምህርት ቤቱ ቦርድ በቨርጂኒያ ህግ በሌላ ትምህርት ቤት ቦርድ አማካይነት በስነ ምግባር የተባረረ ወይም ከ30 ቀናት በላይ የታገደ ተማሪን አልቀበልም የሚልበት ሁኔታ ማለት ነው።

መባረር፡ የትምህርት ቤቱ ቦርድ በትምህርት ቤት ፖሊሲ መሰረት በስነ ምግባር ያባረረው ተማሪ ለ365 ቀናት ያህል መልሶ መመዝገብ አይችልም።

ማስገደድ፡ አንዳች ዋጋ የሚያወጣን ነገር በማስፈራራት ወይም በአካላዊ ሃይል በማስገደድ ከሌላ ተማሪ ላይ ለመውሰድ ወይም ለመቀበል የሚፈጸም ተግባር ማለት ነው።

የሃሰት ክሶች፡- ሆን ብለው በሌላ ሰው ላይ የሐሰት ክስ የሚያቀርቡ ወይም የሃሰት መረጃ ወይም ውንጀላ የሚያቀርቡ ተማሪዎችም ሆነ የትምህርት ቤቱ ሰራተኛዎች የስነ ምግባር እርምጃ ይወሰድባቸዋል።

የወንጀል ክስ፡ በወንጀት ጥፋት የተከሰሱ ተማሪዎች የስነ ምግባር እርምጃ ይወሰድባቸዋል ወይም በመከላከል/ኢንተርቬሽን ተግባር ተሳታፊ እንዲሆኑ ይደረጋል።

ምንም ጉዳት ያላስከተለ ወይም አነስተኛ ጉዳት ያስከተለ (ሁለቱም ወገኖች) ፀብ ወይም ድብድብ፡ ምንም ወይም ጥቃቅን ጉዳቶች በማይኖሩበት አካላዊ ጥቃትን በሚያካትት ድብድብ ውስጥ የጋራ ተሳትፎ ማድረግ። እነዚህ የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፡- በሰውነት ላይ መቧጨር (ለምሳሌ፡ ጉልበት፣ ክርን፣ እጅ) ወይም ጥቃቅን ቁስሎች።

የጦር መሳሪያ፡- ማንኛውም በትምህርት ቤት ይዞታ ላይ ወይም በትምህርት ቤት ድጋፍ በሚዘጋጅ እንቅስቃሴ ላይ የተከለከለ መሳሪያ፣ በቨርጂኒያ ኮድ ክፍል 18.2-308.1 በተመለከተው መሰረት፣ ወይም (1) ማንኛውም መሳሪያ፣ የውድድር ማስጀመሪያ ሽጉጥ፣ የአየር ግፊት ሽጉጥን (የቀለም ጥይት፣ የብረት ብዮች፣ የአየር ጠመንጃ) ጨምሮ፣ በተቀጣጣይ ነገሮች ፍንዳታ ወይም ግፊት አማካኝነት ነጠላ ወይም በርካታ ውንጫፊዎችን ማስፈንጠር የሚችል ወይም ለዚህ የተዘጋጀ ወይም በቀላሉ ሊቀየር የሚችል፤ (2) የማንኛውም እንዲህ ያለ መሳሪያ ማህደር ወይም ማቀባበያ ክፍል፤ (3) ማንኛውም የጦር መሳሪያ ድምጽ መቀነሻ ወይም ማፈኛ፤ (4) ማንኛውም አውዳሚ መሳሪያ፤ ወይም (5) ማንኛውም በዝግ ማሸጊያ የተቀመጠ ያልተቀባበለ የጦር መሳሪያ።

የሐሰት ስራ/ማጭበርበር፡- ሌላ ሰውን ለማታለል ወይም ለመጉዳት በማሰብ የሃሰት ሰነድን መፍጠር፣ ማስተካከል ወይም መጠቀም።

ተግባራዊ የጠባይ ፍተሻ፡ ተማሪውን ወይም ሌሎች አቻ ተማሪዎችን ትምህርታቸውን መከታተል እንዳይችሉ የሚያደርጋቸው ጠባይ መነሻው ምን ሊሆን እንደሚችል ለመፈተሽ የሚደረግ ዳሰሳ ሲሆን ሒደቱ በእጅ ያለውን መረጃ ወይም አዲስ መረጃን እንደ አይኢፒ ቡድኑ ውሳኔ የመገምገም ስራን ሊያጠቃልል ይችላል።

ቁማር፡ ያልታወቀ ውጤት ባለው አንዳች ውድድር ላይ ገንዘብን ወይም ሌላ ዋጋ የሚያወጣ ነገርን በውርርድ በማስያዝ የሚፈጸም ተግባር ነው።

ከውንብድና ጋር የተያያዘ እንቅስቃሴ፡ ተማሪዎች በጄኤፍሲኢ ፖሊሲ መሰረት በተመለከተው የውንብድና ተግባር ላይ መሳተፍ የለባቸውም። የመንገድ ላይ ውንብድና ማለት አንድ ወይም ሌላ አይነት ወንጀል ስራ ለመፈጸም በማሰብ በሚቋቋምና ቢያንስ ሶስት አባላትን ያቀፈ መደበኛም ሆነ መደበኛ ያልሆነ ድርጅት፣ ማህበር ወይም ቡድን ማለት ነው።

ጥቃት፣ ማስፈራራት፡ የትምህርት አካባቢውን ሰላም በሚጎዳ አግባብ በተማሪ፣ በተማሪዎች ወይም በትምህርት ቤት ሰራተኞች ላይ የሚፈጸም ተደጋጋሚ የጥቃት ተግባር ማለት ሲሆን ማንኛውም ተማሪ በሌላ ተማሪ ወይም በትምህርት ቤቱ ሰራተኛ ላይ ወይም በበጎ ፈቃድ መምህራንና የተማሪ መምህራን ላይ በዘር፣ በጾታ፣ በአመጣጥ፣ በዜግነት ወይም በሃይማኖት ላይ ተመስርቶ በት/ቤቱ ግቢ ውስጥ ጥቃት መፈጸም አይገባውም። መከታተልን ያጠቃልላል።

የሃይል ተግባር፡ ይህ ማለት በአንድ ቡድን ወይም ህብረት ውስጥ ለመቀላቀልና ይሁንታ ለማግኘት እንዲሁም ከበሬታንና የበላይነትን ለማረጋገጥ ሲባል በጤንነትና ደህንነት ላይ ጉዳት በሚያደርስ አኳኋን በተማሪ ወይም በተማሪዎች ላይ አካላዊ ጉዳት ማድረስ ማለት ነው።

የተማሪ ቤቱ ፕሪንሲፓል ይህንን መሰል የሃይል ተግባር ሲፈጸም ጉዳዩን ለአካባቢው የጋራ ብልጽግና ባለስልጣን ያሳውቃል። ከላይ የተመለከተው ተግባር በ12 ወራት እስራትና በ2500 ዶላር የገንዘብ ቅጣት ሊያስቀጣ የሚችል ሲሆን በዚህ ፖሊሲም የስነ ምግባር እርምጃ ሊያስወስድ ይችላል። ጉዳት የደረሰበት ማንኛውም ሰው በህጉ ክፍል 18.2.56 መሰረት ለደረሰበት የአካል ጉዳት ከአጥፊው ላይ ካሳ መተየቅ ይችላል።

ሰሚው ጽ/ቤት፡ ጽ/ቤቱ የስነ ምግባር አቤቱታን በመስማት በተቆጣጣሪው ስም ውጤቱን ይወስናል፣ ለት/ቤቱ ቦርድ አስተያየት ይሰጣል፤ ተቆጣጣሪን ወክሎ በቦርዱ ስብሰባ ላይም ይገኛል። በተጨማሪም የተባረሩና የታገዱ ተማሪዎችን መረጃ ይይዛል፤ የእግድ ይግባኞችን ይወስናል፤ ለት/ቤቱ አስተዳዳሪዎች ስልጠናና ድጋፍ ይሰጣል፤ በተቆቆቀጣሪው ስም ሆኖም የሰራተኞችን ቅሬታ አቤቱታ ይሰማል።

የትምህርት ቤት ረብሻን ማነሳሳት ወይም መሳተፍ፡- የህዝብ ደህንነትን፣ ሰላምና መረጋጋትን ከባድ አደጋ ላይ የሚጥል ባህሪ፣ የሃይል መጠቀምና አመጽ፣ የሃሰት የእሳት አደጋ ማስጠንቀቂያዎችን ማስጮህና አመጽን (ሶስት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች በጋራ ሲንቀሳቀሱ) ማነሳሳትን ይጨምራል።

ተገቢ ያልሆነ ንክኪ እና/ወይም ወሲባዊ እንቅስቃሴ፡- በአንድ ተማሪ ወይም ሰራተኛ ላይ የሚፈጸም በተጠቂው አመለካከት አጸያፊ፣ ተገቢ ያልሆነ እና/ወይም ያልተፈለገ አካላዊ ንክኪ።

ተገቢ ያልሆነ ቋንቋ፡ ተገቢ ያልኑ ቃላትን ወይም የውይይት ርዕሶችን መምረጥ።

በት/ቤት ውስጥ እገዳ (ISS)፡ ተማሪው በሚፈጠረው የባህሪ ችግር ምክንያት ከመደበኛ የትምህርት ሰዓቱ ስኬጅውሉ እንዲወጣ ሊደረግ እንዲሁም በአንድ በተመረጠ ባለሞያ ሰራተኛ ስር ከግማሽ የትምህርት ቀን ወይም ከዚያም በላይ ያህል ተመድቦ ለተወሰነ ጊዜ ሊያጠና ይችላል። ፤አፀያፊ፡ ብልግና ወይም የሚያዋርድ ቋንቋ ወይም ምልክት መጠቀም። ቋንቋ የእጅ ምልክት ፣ ወይም የብልግና ፣ አፀያፊ ባህሪ ወይም ዘር የሚመለክት ባህሪ የመማርና የማስተማር ሂደቱን ላይ ተፅእኖ የሚያሳድር።

እገታ መፈጸም፡ ያለ ግለሰቡ ፈቃድ፣ ወይም አካለመጠን ያልደረሰ ልጅን ያለ አሳዳጊ ወላጅ (ወላጆች) ወይም ሕጋዊ ሞግዚት ፈቃድ በሕገ-ወጥ መንገድ መያዝ፣ ማጓጓዝ እና/ወይም ማገት። ይህ ምድብ ታጋቾችን መያዝን ያካትታል።

ያለፈቃድ አካባቢውን/ክፍልን ወይም ትምህርት ቤቱን ለቅቆ መሄድ፡- ለመውጣት ፈቃድ ማግኘት ግዴታ በሆነበት ጊዜ የትምህርት ክፍሉን፣ የትምህርት ቤቱን ህንጻዎች ወይም ቅጥር፣ አካባቢ ወይም እንቅስቃሴ ከትምህርት ቤቱ ሰራተኛ ግልጽ ፈቃድ ውጪ ለቅቆ መሄድ።

የረጅም ዘመን እገዳ፡ ማናቸውም ተማሪ ከ10 ያላነሱ የትምህርት ቀናት በትምህርት ገበታው ላይ እንዳይገኝ የሚተላለፍ ውሳኔ ማለት ነው።

ማስወገድ፡ ማለት ተማሪው ሌላ አማራጭ ሁኔታ ሳይመቻችለት ከ10 ተከታታይ ቀናት በላይ ከትምህርት ሲታገድ ወይም ተከታታይ የሆኑ የእግድ ውሳኔዎች የተላለፉበት ተማሪ በውሳኔዎቹ ድምር ከትምህርት ሲወገድ ማለት ነው።

የገለጻ ውሳኔ፡ ተማሪው ለስነ ምግብር እርምጃ ከሚያበቁት ጠባዮች ጋር እንዲሁም ከትምህርት አቀባበል ጋር ያለውን ግንኙነት ለመፈተሽ የሚደረግ ምርመራ ነው።

ሌሎች ጥሰቶች፡ ከዚህ በላይ ከተመለከተው በተጨማሪ ተማሪዎች የመማር ማስተማር ሒደቱን የሚያውኩ ወይም በፌዴራልና በግዛቱ ህጎች የተከለከሉ ድርጊቶችን መፈጸም አይችሉም።

ተያያዥነት፡ ተከታታይ የሆኑ ከ10 ቀናት በላይ እገዳን የሚያስከትሉ ቅጣቶች የምደባ ለውጥን ያስከትላሉ።

ቢፐር፣ ሞባይል ስልክ፣ የግል ፒዲኤ ወይም ተመሳሳይ የግንኙነት መሳሪያዎችን ይዞ መገኘት፡ ተማሪዎች በትምህር ቤት ውስጥ እና በትምህርት ቤቱ አውቶቡስ ውስጥ በትምህርት ላይ አብርተው የማይጠቀሙበት እስከሆነ ድረስ ቢፐር፣ ሞባይል ስልክ፣ የግል ፒዲኤ ወይም ተመሳሳይ የግንኙነት መሳሪያዎችን መያዝ ይችላሉ። ተማሪው በዚህ ሰነድ ከተፈቀደው ውጪ ሌላ ነገር ይዞ ቢገኝ ከሚወሰድበት የስነ ምግባር እርምጃ በተጨማሪ እቃውን ሊቀማና ለወላጅ ተመላሽ ሊደረግበት ይችላል።

የጦር መሳሪያና ሌሎች አደገኛ ነገሮችን መያዝ፡ ተማሪዎች ምንም እንኳን ተቀባይነት ያላቸው ነገሮች ናቸው ቢባሉም ማናቸውንም የጦር መሳሪያና ሌሎች አደገኛ ነገሮችን ይዘው መገኘት አይችሉም።

አስቀያሚ፣ ነውር ወይም ተገቢ ያልሆነ ቋንቋ ወይም እንቃስቃሴ ቋንቋ የሰውነት እንቅስቃሴ ወይም ባህሪ ይህም ነውራኛ ስድብ ተገቢ ያልሆነ ንግግር ፣ ነውር ድርጊት ወይም በዘር የሚነካ የመማር ማስተማሩን ሂደት የሚያውክ

ማስወገድ፡ ይህ ማለት በስነ ምግባር ችግር ሳቢያ ተማሪውን ከትምህርቱ ላይ ማስወገድ ወይም መለወጥ ማለት ነው።

በክፍል 16.1.305.1 መሰረት የወንጀል ፍርድ ወይም የወንጀል ክልከላ፡ ተቆጣጣሪው በክፍል 16.1.305.1 መሰረት የወንጀል ፍርድ ሪፖርት ወይም በቨርጂኒያ የወንጀል ኮድ መሰረት የወንጀል ክልከላ ሪፖርት ሲደርሰው ተማሪውን ሊያግደው ወይም ሊያባርረው ይችላል።

በቀል፡ የትምህርት ቤቱን ሰራተኞች ወይም ተማሪዎችን አንዳች ጥፋትን ሪፖርት በማድረጋቸው የተነሳ መበቀል የተከለከለ ነው።

ዘረፋ፡ በሀይል፣ በማስፈራራት ወይም በመሰል ተግባር አንዳች ዋጋ ያለውን ነገር ከሌላ ሰው ያለ ፈቃዱ ለመንጠቅ ወይም ለራስ ለመውሰድ የሚደረግ ተግባር ነው።

የትምህርት ቤት ንብረት ወይም ወሰን:- ማንኛውም በትምህርት ቤቱ ቦርድ ባለቤትነት ወይም ኮንትራት ስር ያለ ንብረት ወይም ማንኛውም በትምህርት ቤቱ ቦርድ ባለቤትነት ወይም ኮንትራት ስር ያለ ወይም በተወካይ የሚንቀሳቀስ ተሽከርካሪ። ይህ ትርጓሜ ወደ ት/ቤት ሲሔድ እና ከት/ቤት ሲመለሱ ያለን ምግባር ያካትታል፣ በቨርጂኒያ ኮድ 22.1-78 መሰረት (Va. Code 22.1-78)

ጾታዊ ጥቃት: ከአንድ ሰው ጋር ያለ ፈቃዱ ወሲባዊ ግንኙነት ለማድረግ መሞከር ወይም ማድረግ።

ወሲባዊ ትንኮሳ፡ ያልተገቡ ወሲባዊ ሙከራዎች፣ የወሲብ ውለታን መጠየቅ፣ ወሲባዊ ጠባይ ያለው ቀረቤታ፣ ንግግርና አካላዊ ንክኪ ጥሩ ያልሆነ የመማር ማስተማር ድባብን የሚፈጥር ነው።

የአጭር ጊዜ ማስወገድ፡ አንድን ተማሪ በአመት ለ10 ወይም ከዚያ በታች ለሆኑ ቀናት ወደ አማራጭ ሁኔታ መመደብ ማለት ሲሆን ተከታታይ ባልሆነ ሁኔታ በተለያየ ጊዜ የተሰጠው እገዳ ተጠራቅሞ 10 ቀናት ሲሞላም ተፈጻሚ ይሆናል።

የዋና ተቆጣጣሪው ተወካይ:- 1) የሰለጠነ የአቤቱታ ሰሚ መኮንን፣ ወይም 2)በቀጥታ ለዋና ተቆጣጣሪው ወይም ለተወካዩ ሪፖርት የሚያደርግ በትምህርት ቤቱ ተቀማጭ የትምህርት ወይም የአስተዳደር ሰራተኛ ያልሆነ በትምህርት ክፍሉ የአስተዳደር ቢሮዎች ውስጥ ተቀጣሪ ባለሙያ ሰራተኛ።

ማርፈድ:- ወደ ትምህርት ቤት ወይም ክፍል አርፍዶ መምጣት።

የቴክኖሎጂ ግልጋሎት፡ አንድ ተማሪ የሌላውን ተማሪ ንብረት በሃይል መንጠቅ አይገባውም። ተማሪዎች ቴክኖሎጂን መርሆች ማክበር አለባቸው። ይህንን መመሪያ በሚጻረር አግባብ ቴክኖሎጂና ኔትወርክን መጠቀም የተከለከለ ሲሆን ተማሪዎች በኤሲፒኤስ መመሪያዎች መገዛት አለባቸው።

ስርቆት፡ የሌላ ተማሪን ንብረት በሃይል ወይም በሌላ አግባብ ያለ ፈቃዱ መውሰድና የራስ የማድረግ ተግባር ነው።

ማስፈራራት/ዛቻ፡ ለማስገደድ ተግባር ሲሉ ተማሪዎች በሌላ ተማሪ ወይም ሰው ላይ የቃልም ሆነ የተግባር የሃይል ማስፈራሪያ ከመጠቀም መቆጠብ ይገባቸዋል። ይህ ሲባል መሳሪያን ሳያሳዩ በቃልም ሆነ በምልክትና በመልዕክቶች በሌላ ሰው ላይ የሚፈጸመውን የማስፈራራት ተግባር ያካትታል።

መተላለፍ፡ ያልተፈቀደላቸው ሰዎችና የታገዱ ተማሪዎች ያለ ምንም ጉዳይና ያለ አንዳች ፈቃድ ወደ ት/ቤቱ ቅጥር ግቢ መግባት ወይም በቅጥር ግቢው ውስጥ መቆየት አይችሉም።

አልኮል፣ ትንባሆና ሀሺሽ መጠቀም/ይዞ መገኘት፡ ተማሪዎች በትምህርት ቤትና በአውቶብስ ውስጥ እንዲሁም ከትምህርት ቤቱ ግቢ ውጪም ቢሆን አልኮል፣ ትንባሆና ሀሺሽ መጠቀም/ይዞ መገኘት አይችሉም። ይህም ጭስ አልባ ሲጋራን፣ ያልተፈቀዱ መድሃኒቶችን እና እጾችን በውስኑ ያጠቃልላል።

ተማሪው በመመሪያው ላይ የተከለከሉትን ንጥረ ነገሮች እንዲሁም አልኮል፣ ትንባሆና ሀሺሽ መግዛት፣ መሸጥ፣ መጠቀምና ይዞ መገኘት አይችልም። ይህ መመሪያ የጄኤፍሲኤፍ ፖሊሲን ያጠቃልላል።

የተከለከሉ ንጥረ ነገሮች አልኮል፣ ማሪዋና፣ እጾችን፣ ማነቃቂያዎችን እንዲሁም ማናቸውንም በመመሪያውና በተገቢ ህጎች ላይ የተመለከቱ ነገሮችንና በሐኪም ትዕዛዝ ተፈቅደው ካልሆነ በቀር ሊወሰዱ የማይገባቸውን መድሀኒቶች ያጠቃልላል። ሌሎች የሚከተሉ ውጤቶች እንደተጠበቁ ሆነው የት/ቤቱ ስፖርተኛ የሆነ ተማሪ በሐኪም ትዕዛዝ ተፈቅዶለት ካልሆነ በቀር አደንዛዥ እጽ መጠቀሙ በተቆጣጣሪውና በዳይሬክተሩ ከተረጋገጠ ለሁለት ተከታታይ አመታት ከውድድር ይታገዳል።

የጦር መሳሪያዎች፡ የጦር መሳሪያና ሌሎች አደገኛ ነገሮችን መያዝ፡ ተማሪዎች ምንም እንኳን ተቀባይነት ያላቸው ነገሮች ናቸው ቢባሉም ማናቸውንም የጦር መሳሪያና ሌሎች አደገኛ ነገሮችን ይዘው መገኘት አይችሉም። በቨርጂኒያ ኮድ ክፍል 18.2-308.1 በተመለከተው መሰረት ማናቸውም በትምህርት ቤት ውስጥ እንዳይገባ የተከለከለ መሳሪያ ወይም ማናቸውም ወደ ትክክለኛ መሳሪያ ሊለወጥ የሚችል፣ የማናቸውም መሳሪያ አጽም፣ ማናቸውም አይነት የመሳሪያ ድምጽ ማፈኛ፣ ማናቸውም አውዳሚ መሳሪያ ወይም ማናቸውም በዝግ ማሸጊያ የተቀመጠ ያልተቀባበለ የጦር መሳሪያ ይጠቃለላል።

# እገድ

የቨርጂኒያ የእውቅና ማረጋገጫ ደረጃቸውን የጠበቁ አሰራሮች (1992) ክፍል 8 ቪኤሲ 20-131-210ኤ ሀላፊው “የትምህርት ቤቱ መመሪያ ሰጪ እና አዎንታዊ የተማሪዎች አፈፃፀምን፣ አስተማማኝና ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢን ለመማርና ማስተማር ምቹ ይሆንና ሀብቶችን በተገቢ መልኩ ለመጠቀም የሚያስችል የማቅረብ ሀላፊነት አለበት” ክፍል ቢ.2 ሀላፊው “የትምህርት ቤቱ መምሪያ ተፈፃሚ እንዲሆንና በትምህርት ቤቱ አካባቢ ደህንነቱ የተጠበቀና አስተማማኝ ሁኔታን በማስጠበቅ የሚጠየቁትን ማረጋገጥ” አለበት። ክፍል 8ቪኤሲ 20-131-230ሲ.3 የትምህርት ቤቱ አስተዳደር “በአካባቢያዊ ቦርድ በተቋቋሙት መመሪያ መሰረት በትምህርት ቤቱ ንብረት ላይ ወይም በትምህርት ቤቱ ስፖንሰር በተደረጉ ተግባራት ላይ በተማሪዎቹ የሚፈፀሙ የሀይል፣ የረብሻ ወይም ህገወጥ ተግባራትን አስመጥቶ ምላሽ ለመስጠት የተቋቋሙ ስነስርዓቶችን” ያረጋግጣል

## 1. የተማሪዎች እግድና ስንብት

ተማሪው ከትምርሀት ቤት ሊታገድ ወይም ሊባረር ይችላል በቂ ምክንያት ካለ ። ነገር ግን በምንም ሁኔታ ካለምክንያት ከትምህርት መቅራት ብቻ ምክንያት ሊሆን

አይችልም። በቨርጂኒያ ህግ አንቀፅ 6.1-305.1 መሰረት ተማሪው ት/ቤት ያለው ለዋና ስራአስኪያግ(ሱፐር ኢንቲንደንት) ተማሪው ጥፋት ውሳኔ የተሰጠበት ሪፖርት ከደረሰው ተማሪው ከትምህርት ቤት መታገድ ወይም መባረር ይችላል።

በቨርጂኒያ ህግ በንዑስ ክፍል አንቀፅ 16.1-260 ስር የፍርድ ቤት ባለጉዳይ መዝጋቢ ኦፊሰር ተማሪው የዚህ ዓይነት ድርጊት ፈፅሞል ለተባለበት የትምህርት አስተዳዳር ክልል ስራ አስኪያጅ (ሱፐር ኢንቴንደንት) ተማሪው ፈፅሞል ተብሎ ስለተጠረጠረው ድርጊት፣ የቀረበው ክስ በሚፈጸምበት ማናቸውም ወቅት ድርጊቱ በአዋቂ ቢፈጸም ወንጀል እንደሚሆን የሚቆጠር ከሆነ ወይም አዋቂ ተማሪ እንደዚህ ዓይነት ወንጀል የፈፀመ ከሆነና ጉዳዩም በፍርድ ቤቱ የስልጣን ክልል ስር ከሆነ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል ። ለአስተዳዳር ክልል ስራ አስኪያጅ (ሱፐር ኢንቴንደንት) የሚላከው ሪፖርት የክስ መዝገብ መከፋቱን እና የተፈጸመውን ድርጊት አይነት ፣የሚከተሉት ጉዳዮች ደንብ መጣስ ካለ ይገልፃል፤

1.የጦር መሣሪያ ደንብ መተላለፍ ፣ በርእስ 18.2፣ ምእራፍ 7፣ አንቀፅ 4 (§ 18.2-279 et seq.) ፣ 5 (§ 18.2-288 et seq.) ፣ 6 (§ 18.2-299 et seq.) ፣ 6.1 (§ 18.2-307.1 et seq.)፣ ወይም 7 (§ 18.2-308.1 et seq.) የተጠቀሰው

2. የነፍስ ግድያ ፤ በርእስ 18.2፣ ምእራፍ 7፣ አንቀፅ 1 (§ 18.2-30 et seq.) መሰረት፤

3. ከፍተኛ ወንጀል (ፌሎኒ) ጥቃት እና የአካል ጉዳት በርእስ 18.2፣ አንቀፅ 4 (§ 18.2-2-51 et seq.)

4. የወሲብ ጥቃት ወንጀል፣ ርእስ 18.2 ፣ ምእራፍ 4፣ አንቀፅ 7 (§ 18.2-61 et seq.)

5. ስኬጅውል I ወይም II ቁጥጥር የሚደርግባቸው ነገሮችን ማምረት፣ መሸጥ፣ መስጠት፣ ማከፋፈል ወይም በእጅ ይዞ መገኘት፣ ርእስ 18.2 ፣ ምእራፍ 4፣ አንቀፅ 1 (§ 18.2-247 et seq.)

6. ማሪዋና እፅ ማምረት፣ መሸጥ፣ መስጠት፣ ማከፋፈል፣ርእስ 18.2 ፣ ምእራፍ 7፣ አንቀፅ 1(§ 18.2-247 et seq.)

7. የእሳት ቃጠሎ እና ተዛማጅ ወንጀሎች፣ርእስ 18.2 ፣ ምእራፍ 5፣ አንቀፅ 1(§ 18.2-77 et seq

8. የዘረፋ እና ተዛማጅ ጥፋቶች፣ አንቀፅ §§ 18.2-89 እስከ 18.2-93;

9. ዘረፋ፣ አንቀፅ §§ 18.2

10. የተከለከለ የመንገድ ላይ የቡድን ወንጀለኛ እንቅስቃሴ፣አንቀፅ §§ 18.2--46.2;

11. ሌሎች ወጣቶችን ለመንገድ ላይ የቡድን የወንጀል እንቅስቃሴ መመልመል፣ አንቀፅ §§ 18.2--46. 3

12. በተደራጀ ሁኔታ የጭካኔ ተግባር ማከናወን ፣አንቀፅ §§ 18.2- 42.1

ክስ የተመሰረተበት ተማሪ የሚማርበት ት/ቤት የተመለከተ መረጃ ለማግኘት አለመቻል በጉዳዪ ላይ ክስ ላለመመስረት ምክንያት አይሆንም።

አስተማሪዎች በአንዳንድ ሁኔታዎች አስቸጋሪ ባህሪ ምክንያት ተማሪዎችን ከክፍል የማስወጣት ስልጣን የዚህን ሦሊሲ ተፈፃሚነት እንደሚያስተጉጉል ተደርጎ መቆጠር የለብትም። ወልጆች/አሳዳጊዎች እገዳውን የሚመልከት ቅሬታ አቤቱታ ሊያቀርቡ ይችላሉ።የቅሬታ አቀራረብ በሚመለከት ስለአለው አሰራር በዚህ ሰንድ ተገልፃል።

## II. የአጭር ጊዜ እግድ

አንድ ተማሪ በትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ወይም አግባብ ባለው አስተዳዳሪ ከ10 የትምህርት ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ሊታገድ ይችላል። ርዕሰ መምህሩ ወይም አግባብነት ያለው አስተዳዳሪ ለተማሪው እና ለወላጅ የቃል ማስታወቂያ ከሰጠ በኋላ ተማሪውን ሊያግደው ይችላል። ስለ እገዳው እና ለእገዳው ምክንያት የሆነውን ባህርይ የሚመለከት የፅሁፍ ማስታወቂያ በ 24 ሰዓታት ውስጥ ይሰጣል። ትምህርት ቤቱ ጉዳዩን በሚመረምርበት ጊዜ ተጨማሪ መረጃ ከተገኘ፣ ደብዳቤው ሊሻሻል እና ማንኛውም የዲሲፒሊን እርምጃም ሊቀየር ይችላል።

ማንኛውም ተማሪ በሚታገድበት ወቅት፣ እገዳውን በተመለከተ የሚመለከተው ርዕሰ መምህር ወይም ተገቢው አስተዳደር ለት/ቤቱ አመራር ዋና ዳይሬክተር እግዱን ሪፖርት ማድረግ አለበት።

ከ10 ቀናት ለማይበልጥ ጊዜ ከትምህርት የታገደው ተማሪ ወላጅ ወይም አሳዳጊ የተሰጠው የቃል ወይም የፅሁፍ ማስታወቂያ እገዳው ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ ማካተት አለበት።

## III. የረጅም ጊዜ እግድ

አንድ ተማሪ ለእርሱ እና ለወላጁ/ለሞግዚቱ ስልሚወሰድበት እርምጃ እና ምክንያቱ በትምህርትቤቱ ቦርድ ወይም ኃላፊ ወይም ተሰያሚ ፊት የመሰማት መብት እንድለው አስመልክቶ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው ከ10 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ከትምህርት ቤቱ መገኛ መቆጣጠሪያ ቅፅ ላይ ሊታገድ ይችላል። የትምህርት ቤቱ ኃላፊ ወይም ተሰያሚ ውሳኔ ለሙሉ የትምህርት ቤቱ ቦርድ ይግባኝ ሊባል ይችላል። የተባለው ይግባኝ በትምህርት ቤቱ ቦርድ በ30 ቀናት ውስጥ ይወሰናል።

ማንኛውም የተባለው የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ የእገዱን እርዝማኔ መጥቀስ እና በማህበረሰብ ላይ የተመሰረተ ትምህርት፣ አማራጭ ትምህርት ወይም የጣልቃ ገብነት ፕሮግራሞች ስለመኖራቸው አስመልክቶ መረጃ ያቀርባል። የተባለው ማስጠንቀቂያ ተማሪው በእግዱ ማብቂያ ጊዜያት ወይም ላይ በትምህርት ቤቱ ቦርድ የፀደቀውን አግባብነት ያለው አማራጩ የትምህርታዊ ፕሮግራም ለመካፈል ወደ መደበኛ የትምህርት ቤተ የመቆጣጠሪያ ቅፅ ለመመለስ ብቁነት እንዳለውም መጥቀስ አለበት። ማንኛውም በማህበረሰብ ላይ የተመሰረት ፕሮግራም፣ አማራጭ ትምህርት ወይም የጣልቃ ገብነት ፕሮግራም በትምህርት ቤቱ መምሪያ የቀረበው የትምህርታዊ ፕሮግራም ክፍል ካልሆነ በተማሪው ወላጅ/ሞግዚት መሸፈን አለበት።

በዚህ ውስጥ የተደነገገ ማንኛውም ነገር የትምህርት ቤቱ ቦርድ በተባለው ቆይታ ጊዜያት አማራጭ የትምህርት ፕሮግራም በግላዊ ያሉ ተማሪዎች እንዲካፈሉ ከመፍቀድ ወይም ከመጠየቅ አይከለክለውም።

## IV. ስለ ስንብት

*ሀ. አጠቃላይ ድንጋጌ*

አንድ ተማሪ ለእርሱ እና ለወላጁ/ለሞግዚቱ ስልሚወሰድበት እርምጃ እና ምክንያቱ በትምህርትቤቱ ቦርድ ወይም ኃላፊ ወይም ተሰያሚ ፊት የመሰማት መብት እንድለው አስመልክቶ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው በኋላ ሊሰናበት ይችላል።

ከትምህርት ቤቱ የተሰናበተ ተማሪ ወላጅ/ሞግዚት ማንናውም የቃል የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ የእግዱን እርዝማኔ፣ በማህበረሰብ ላይ የተመሰረተ የትምህርት ፕሮግራሞች መገኘት፣ አማራጭ የትምህርት ፕርግራሞች ወይም ሌሎች የትምህርት አማራጮች እና ተማሪው በእግዱ ማብቂያ ላይ ወደ መደበኛ የትምህርት ገበታው የመመለስ መብት እንዳለው አስመልክቶ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል። የማንኛውም በምህበረሰብ ላይ የተመሰረተ ትምህርት ፕሮግራም ወይም አማራጭ የትምህርት ፕሮግራም ወይም የትምህርታዊ አማራጭ በትምህርት ቤቱ መምሪያ የቀረበው የትምህርታዊ ፕሮግራም አካል ያልሆነው በተማሪው ወላጅ/ሞግዚት ይሸፈናል።

በዚህ ውስጥ የተደነገገ ማንኛውም ነገር የትምህርት ቤቱ ቦርድ በተባለው ስንብት ቆይታ ጊዜያት አማራጭ የትምህርት ፕሮግራም በግላዊ ያሉ ተማሪዎች እንዲካፈሉ ከመፍቀድ ወይም ከመጠየቅ አይከለክለውም።

የትምህርት ቤቱ ቦርድ ተማሪው በስንብቱ ጊዜያት መደበኛ የትምህት ገበታው ላይ ለመመለስ ወይም አማራጭ የትምህት ፕሮግራም ላይ ለመገኘት ወይም የአዋቂ የትምህርት ፕሮግራም ላይ ለመመለስ ብቁ እንዳልሆነ ካረጋገጠ፣ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ለተማሪው ወላጅ ተማሪው ከተሰናበተበት ቀን ጀምሮ ለአንድ አመት የሚጸና ጊዜ ወደ ትምህርት ገበታው ዳግም ለመመለስ ማመልከት እንደሚችል እና ይህ ዳግም የመመለስ መብት እንዴት ይሰጥ እንደሚችል አስመልክቶ በመጥቀስ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል።

የትምህርት ቤቱ ቦርድ የተባሉት ተማሪዎች ወደ ትምህርት ገበታቸው ዳግም ለመማመልከት እና ለመግባት ስለሚችሉባቸው ሁኔታዎች ፕሮግራም በደንብ የሚያቋቁም ይሆናል። የተባለው ፕሮግራም ማንኛውንም የመጀመሪያ ደረጃ ወደ ትምህርት ገበታ ዳግም የመመለስ እድል ማመልከቻ ወደ በትምህርት ቤቱ ቦርድ ወይም በትምህርት ቤቱ ኃላፊ በሚከለስበት መልኩ መቀረፅ እና ይህ ሙብት ከተሰጠ ተማሪው ከትምህርት ገበታው ከተሰናበተበት ቀን ጀምሮ ለአንድ አመት የትምህርት ዘመን መደበኛ ትምህርቱን እንዲቀጥል ይቻለዋል። ኃላፊው የተባለውን ማመልከቻ ከለከለ፣ ተማሪው የተባለውን የትምህርተ ክልከላ ክለሳ ለትምህርት ቤቱ ቦርድ ሊያመለክት ይችላል።

**ሊ. ለስንብት የሚዳርግ ስነምግባር**
ከዚህ በታች የተጠቀሱት ውጪ ለስንብት እርምጃዎች የሚዳርጉ አስተያየቶች በሚከተሉት መወሰኛዎች ላይ ይመሰረታሉ።

- የድርጊቱ ባህሪና ከባድነት።
- የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ አደጋ ደረጃ።
- የተማሪው የስነምግባር ታሪክ የከዚህ በፊት ጥሰቶች ከባድነት እና ብዛት።
- አማራጭ የትምህርታዊ ምደባ ወይም ፕሮግራም ተገቢነት እና መገኘት።
- የተማሪው እድሜ እና የውጤት ደረጃ።
- የማንኛውም የአእምሮ ጤና የእፅ ጠንቀኝነት ወይም ልዩ የትምህራዊ ምዘናዎች።
- የተማሪው መገኛ መቆጣጠሪያ ቅፅ እና።
- ሌሎች አግባብነት ያላቸው ጉዳዮች።

አንድን ተማሪ የማሰናበት የሚደረስ ውሳኔ የተባሉት መወሰኛዎች ከግምት ውስጥ ባለመወሰዳቸው የተነሳ ሊቀለበሱ አይችሉም። በዚህ ክፍል ውስጥ ማንኛውም ነገር የትምህርት ቤቱ ቦርድ በሚከተሉት ነኡስ ክፍሎች ውስጥ ውይይት የተደረገባቸው ከዚህ በላይ ያሉትን ልዩ ልዩ የስንብት አላማዎች መሰረቶች ማናቸውም መወሰኛዎች ከግምት ውስጥ ከማስገባት አይከለክለውም።

*የጦር መሳሪያዎች*
የትምህርት ቤቱ ቦርድ ወደ ትምህርት ቤቱ ንብረት ወይም በትምህርት ቤቱ ስፖንሰር የተደረጉ ተግባራት ላይ የጦር መሳሪያ ይዞ ወይም በዚህ ፖሊሲ ውስጥ እንደተጠቀሰው የጦር መሳሪያን ያመጣ ወይም ጠመንጃ ያመጣ ወይም በትምህርት ቤቱ ንብረት ወይም የትመህርት ቤቱ ስፖንሰር የተደረጉ ተግባራት ላይ የቢቢ ጠመንጃ የመጣን ማንኛውንም ተማሪ ከአንድ አመት ላነሰ ግዜ ሊያስተናግድ ይችላል። የትምህርት ቤቱ አስተዳደር በትምህርት ቤቱ ቦርድ መሠረት ያሉትን ልዩ ልዩ መሠረቶች አንድ ልዩ ሁኔታ ፍሬ ነገሮች ተመስርቶ መወሰንና ምንም አይነት የስነ ምግባር እርምጃ ወይንም ሌላ የስንብት ቆይታ ተገቢ አይሆንም። የትምህርት ቤቱ ቦርድ ልዩ ሁኔታዎች የሚወሰኑባቸውን መመሪያዎች ሊያስተዋውቅ ይችላል። በተጨማሪም፣ የትምህርት ቤቱ ቦርድ፣ በደንቡ መሰረት፣ ለዋና ተቆጣጣሪው ወይም ለዋና ተቆጣጣሪ ተወካይ በእንደዚህ ያሉ ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ በማካሄድ ከማባረር ውጪ የሆነ የቅጣት እርምጃ ተገቢ መሆኑን መወሰን የሚችሉበትን ስልጣን ሊሰጥ ይችላል። የተለየው ሁኔታ እውነታዎች ምንም ይሁኑ ምን፣ በዚህ ፖሊሲ ውስጥ ምንም ነገር የተማሪን መባረር እንደሚፈልግ ተደርጎ መተርጎም የለበትም።

የተደበቁ መሳሪያዎችን አስመልክቶ በቨርጂኒያ ህግ ክፍል 18.2 -308 ውስጥ የተገለፁ የተተው ሁኔታዎች እንደየሁኔታው በዚህ ፖሊሲ ድንጋጌዎች ላይ ተግባራዊ ይሆናሉ። የዚህ ፖሊሲ ድንጋጌዎች በትምህርት ቤቱ መምሪያ ስፖንሰር በተደረጉ የትምህርት ስነስርዓት ወይም ሌሎች ፕሮግራሞች ክፍል የተባለውን የጦር መሳሪያ ወይም የጦር መሳሪያዎች ይዘው በተገኙ ሰዎች ወይም በትምህርት ቤቱ ውስጥ ማንኛውንም ተግባራቱን በመወጣት ላይ ያለ ማንኛውም የህግ አስፈጻሚ ሀላፊ ወይም በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢዎች መሳሪያ እንዲጠቀም የተፈቀደለት ማንኛውም ድርጅት ላይ ተግባራዊ አይሆንም።

*የአደንዛዥ እፅ ጥፋቶች*
የትምህርት ቤቱ ቦርድ የተከለከሉ ንጥረ ነገሮችን ወደ ትምህርት ቤቱ ይዘው እንዳመጡ፣ የተከለከሉ ንጥረ ነገሮችን እንዳስመሰሉ ወይም ማሪዋና ይዘው የመጡ ማናቸውንም ተማሪዎችን ያሰናብታል። የትምህርት ቤቱ ቦርድ ለሁኔታው ተገቢ የሆነ ልዩ መሰረቶች እንዳሉና ሌሎች የስነምግባር እርምጃዎች ተገቢነት ሊወስን ይችላል።

በተጨማሪም፣ የትምህርት ቤቱ ቦርድ፣ በደንቡ መሰረት፣ ለዋና ተቆጣጣሪው ወይም ለዋና ተቆጣጣሪው ተወካይ በእንደዚህ ያሉ ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ በማካሄድ ከማባረር ውጪ የሆነ የቅጣት እርምጃ ተገቢ መሆኑን መወሰን የሚችሉበትን ስልጣን ሊሰጥ ይችላል። የተለየው ሁኔታ እውነታዎች ምንም ይሁኑ ምን፣ በዚህ ፖሊሲ ውስጥ ምንም ነገር የተማሪን መባረር እንደሚፈልግ ተደርጎ መተርጎም የለበትም።

**ሐ. የትምህርት ቤቱ ቦርድ መስማት ስነስርዓት**
የትምህርት ቤቱ ቦርድ መሰማት ስነስርዓት እንደሚከተለው ይሆናል፥

1. የትምህርት ቤቱ ቦርድ -በመስማት ሂደት ውስጥ ቀጥተኛ ግንኙነት የሌላቸው ሰዎችን ለመስማት የመቆጣጠሪያ ቅፅ ተገቢነትን ይወስናል። የመሰማት ሂደቱ በትምህርት ቤቱ ቦርድ በሌላ አኳኋን ካልተገለፀ በስተቀር ግላዊ ይሆናል።
2. የትምህርት ቤቱ ቦርድ ከሀላፊውና ወይም ተወካዩ እና ተማሪው ወይም ወላጁ/ሞግዚቱ (ወይም ተወካዩ) የመክፈቻ መግለጫዎችን ሊጠይቅና በትምህርት ቤቱ ቦርድ ውሳኔ የመዝጊያ መግለጫዎችን ሊፈቅድ ይችላል።
3. ተዋዋይ ወገኖቹ በመቀጠል ማስረጃዎቻቸውን ያቀርባሉ ኃላፊው በዋነኛነት የማሰረዳት ሸክም ስላለበት ማስረጃውን በመጀመሪያ ያቀርባል። ምስክሮች በትምህርት ቤቱ የቦርድ አባላትና የሚመለከታቸው ወገኖች (ወይም ተወካዩ) ቃለመጠይቅ ሊደረግላቸው ይችላሉ። የትምህርት ቤቱ ቦርድ በብቸኛ ውሳኔው ይህንን ስነስርዓት ሊለውጥ ይችላል ግን ለሁለቱም ወገኖች ማናቸውንም ፍሬ ነገሮች ወይንም አግባብነት ያላቸው ማስረጃዎች እንዲያቀርቡ ሙሉ እድል መስጠትና ወገኖቹ መስቀለኛ ጥያቄ የማቅረብ እድል ሊሰጣቸው ይገባል። ቢሆንም ግን የትምህርት ቤቱ ቦርድ ከተማሪው መገኛ ውጪ ያሉ የተማሪውን ምስክሮች ምስክርነት፣ የወላጅ/ሞግዚት እና ተወካያቸው ምስክርነትን በትምህርት ቤቱ ቦርድ ብቸኛ ውሳኔ የተባለው እርምጃ የተማሪውን ምስክር ለማስጠበቅ አስፈላጊ ከሆነ ምስክርነታቸውን ሊቀበል ይችላል።
4. የሚመለከታቸው ወገኖች የትምህርት ቤቱ ቦርድ አስፈላጊ ናቸው ብሎ የሚቆጥራቸውን የተባሉትን ተጨማሪ ማስረጃዎች ያቀርባሉ የትምህርት ቤቱ ቦርድ የማስረጃው ተገቢነትና ተጨባጭነት ይመዝናል።
5. ወገኖቹ የሚያቀርቧቸው ኢግዚቦቶች በትምህርት ቤቱ ቦርድ በማስረጃነት ከተቀበሉና ለዚህም ማረጋገጫ ምልክት ተደርጎባቸው የዚህ መዝገብ ክፍል መሆን አለባቸው።
6. የትምህርት ቤቱ ቦርድ አስተያየቶቹን በአብላጫ ቦርድ ውድቅ ማድረግ ወይም መለወጥ ይችላል።
7. የትምህርት ቤቱ ቦርድ ውሳኔውን ምክንያቶቹን ጨምሮ ለተማሪው፣ ለወላጁ/ሞግዚቱ ኃላፊውና ዋና ኃላፊው ማስተላለፍ አለበት።

**መ. አማራጭ የትምህርት ቤት ፕሮግራም**
የትምህርት ቤቱ ፕሮግራም ከቨርጂኒያ ህግ ጋር የተገናኘ ማናቸውንም ጥሰት ለፈፀመ ወይም የትምህርት ቤቱን የቦርድ ስነስርዓት በመጣስ በጦር መሳሪያዎች አልኮል አደንዛዥ እጽ ወይም ሌሎች ሰዎች ላይ ሆን ብሎ የአካል ጉዳት በማድረስ (1) የተከሰሰ (2) ከቨርጂኒያ ህጎች የጦር መሳሪያዎች አልኮል ወይም አደንዛዥ እጽ ወይም በሌሎች ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት የዳረገ ወይም ሊዳርግ የሚችል ለትምህርት ቤቱ መምሪያ ዋና ኃላፊ መውጣት የሚያስፈልገው ጥፋት ከመፈፀም ጋር በተገናኘ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ወይም ንፁህ ያልሆነ (3) የትምህርት ቤቱን የቦርድ ፖሊሲዎች ጥሶ ከባድ ጥፋት ወይም ተደጋጋሚ ጥፋቶች የፈጸመ (4) በቨርጂኒያ ህግ መሰረት የታገደ (5) በቨርጂኒያ ህግ መሰረት የተሰናበተ ወይም በህጉ ንኡስ ክፍል አማራጭ የትምህርታዊ ፕሮግራም እንዲካፈል የተወሰነበት። የትምህርት ቤቱ ቦርድ የተባለው ተማሪ ወንጀል በመፈፀሙ ላይ ሳይመረኮዝ የተባሉትን ፕሮግራሞች እንዲካፈል

ለመጠየቅ ይችላል የትምህርት ቤቱ ቦርድ አደንዛዥ እጽ ወይም አልካል ይዞ ወይም በተጽእኖ ስር ሆኖ ወደትምህርት ቤቱ አውቶብስ ወደትምህርት ቤቱ ንብረት ወይም በትምህርት ቤቱ ስፖንሰር የሚደረጉ ተግባራት ይዞ በመገኘት በትምህርት ቤቱ ቦርድ ፖሊሲዎች ላይ ጥሰት በመፈፀም የአደንዛዥ እጽ ወይንም የአልኮል ጠንቀኝነት ወይም የሁለቱንም ምርመራ እንዲያደርግ በመርማሪ እና በተማሪው ወላጅ/ሞግዚት ስምምነት ተወስኖበት በህክምና ፕሮግራም ውስጥ እንዲሳተፍ ሊጠይቅ ይችላል።

ሀላፊው (ወይም ተሰያሚው) ማንኛውም ተማሪ በተመሳሳይ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማር ሌላ ተማሪ ላይ በቨርጂኒያ ህግ ውስጥ እንደተጠቀሰው የአካል ጉዳት የሚያስከትል ድርጊት ከፈጸመ የተባለው ተማሪ አማራጭ የትምህርት ፕሮግራም እንዲካፈል የሚጠይቅ ውሳኔ እስኪተላለፍ ድረስ የአጭር ጊዜ እግድ ሊጥል ይችላል።

በዚህ ውስጥ በጥቅም ላይ እንደዋለው "የተከሰሰ" ማለት በተማሪው ላይ አቤቱታ ወይም ማዘዣ ተመስርቶበት ወይም በእንጥልጥል ላይ ያለየክስ ሂደት ማለት ነው።

**ሠ. ሪፖርት ስለማቅረብ**

ሀ. በፌደራል ህግ ደንብ ወይም የህግ ፍልስፍና ሊጠየቅ ከሚችለው በስተቀር ሪፖርቶቹ የሚከተሉትን በሚያስከትሉ ሁሉም አደጋዎች ላይ ለሀላፊው ወይም ለተሰያሚው መቅረብ አለባቸው፥

1. በትምህርት ቤቱ አውቶብስ፣ በትምህርት ቤቱ ንብረት፣ ወይም በትምህርት ቤቱ ስፖንሰር በተደረጉ ተግባራት ላይ ድብደባ ወይም ድብደባና ግርፊያ ፈጽመው የአካል ጉዳት ያላደረሰ።
2. በትምህርት ቤቱ አውቶቢስ በትምህርት ቤቱ ንብረት በትምህርት ቤቱ ስፖንሰር በተደረጉ ተግባራት ላይ የአካል ጉዳት፣ የጾታዊ ጥቃት ሞት ተኩስ በስለት መውጋት ቆረጣ ወይም ማቁሰል በማንኛውም ግለሰብ ላይ የሚያደርስ ድብደባና ግርፋት ወይም ደግሞ ማንኛውንም ግለሰብ ሲከታተል የተገኘ።
3. በትምህርት ቤቱ አውቶቢስ በትምህርት ቤቱ ንብረት በትምህርት ቤቱ ስፖንሰር በተደረጉ ተግባራት ላይ አልኮል፣ ማሪዋና የተከለከለ እጽ፣ የተከለከለ እጽ መጠቀምን ማስመሰል ወይም አናቦሊክ ስትሮይድ የሚመለከት ማንኛውንም ተግባር የፈፀመ ወይም በተማሪዎች የታዘዙ መድሀኒቶች ላይ ስርቆት የስርቆት ሙከራ የፈፀመ።
4. በበትምህርት ቤቱ አውቶቢስ በትምህርት ቤቱ ንብረት በትምህርት ቤቱ ስፖንሰር በተደረጉ ተግባራት ላይ ተግባራት ላይ በትምህርት ቤቱ ሰራተኛ ላይ ማናቸውንም ዛቻዎች የፈፀመ።
5. በትምህርት ቤቱ ንብረት ላይ በቨርጂኒያ ህግ 22.1 -277.07 እንደተደነገገው ህገወጥ የጦር መሳሪያ ይዞ የተገኘ።
6. በትምህርት ቤቱ አውቶቢስ በትምህርት ቤቱ ንብረት በትምህርት ቤቱ ስፖንሰር በተደረጉ ተግባራት ላይ ቨርጂኒያ ህግ ክፍል 18.2 – 85 ውስጥ እንደተገለፀው ማንኛውንም ጥይት ቦምብ ፈንጂ ማቴሪያሎች ወይም የሚፈነዱ መሳሪያዎች ፈንጂ ወይም ተቀጣጣይ መሳሪያዎች ወይም የኬሚካል ባምቦች ያስከተለ ማንኛውም ህገወጥ ድርጊት።
7. የትምህርት ቤቱ ሰራተኛ ወይንም የትምህርት ቤቱ ንብረት የትምህርት ቤቱ አውቶብሶች ላይ በቨርጂኒያ ህግ ክፍል18.2 -83 ውስጥ እንደተገለፀው ማንኛውም ማስፈራሪያ ወይም ሀሰተኛ የቦምብ ማስፈራሪያ።

ለ. ዋና ሀላፊው እና ሀላፊው ወይም ተሰያሚዉ በትምህርት ቤቱ ውስጥ ተመዝግበው የሚገኙ ተማሪዎች ከባድ ጥፋት ከፈፀሙ ጥፋቱ በማናቸውም ቦታዎች ቢፈፀምም፣ የተባለው ጥፋት በዋቢ ከተፈፀመ የአደንዛዥ እጽ መቆጣጠሪያ ህግን ከጣሰ እና በበትምህርት ቤቱ አውቶቢስ በትምህርት ቤቱ ንብረት በትምህርት ቤቱ ስፖንሰር በተደረጉ ተግባራት ላይ ከተከሰተ ወይም በዚህ ፖሊሲ ንኡስ ክፍል 8 ሀ ከአንቀጽ 1-7 ባሉት ውስጥ የተገለፁትን ማናቸውንም አደጋዎች ያስከተለ አዋቂ ቀላል ጥፋት ፈፃሚ ከሆነና ተማሪው ለወላጅ/ሞግዚት ጥበቃ ከተለቀቀ ወይም 18 አመት ወይም ከዛ በላይ ሆኖ በዋስትና ከተለቀቀ ከአካባቢያዊ ህግ አፈፃፀም ባለስልጣናት ሪፖርቶች መቀበል አለበት አንድ ወጣት በህጉ ንዑስ ክፍል 16.1-260 መሠረት በአዋቂ ቢፈፀም ወንጀል ተደርጐ የሚቆጠርን ድርጊት ስለመፈፀሙ ማስታወቂያ የደረሰው ዋና ሀላፊ ወጣቱ ተመዝግቦበት ለሚገኘው የትምህርት ቤቱ ሀላፊ የተባለውን መረጃ ሪፖርት ማድረግ አለበት።

ሐ. ሀላፊው ወይም ተሰያሚው በዚህ ፖሊሲ ክፍል 7 ሀ (1-7) መሠረት ሪፖርት እንዲደረጉ ወይም የሚፈቀድ ሪፖርት ለዋና ሀላፊው ማቅረብ አለበት ዋና ሀላፊው ሁሉንም የተባሉትን ክስተቶች ለቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ በየአመቱ ሪፖርት ማድረግ አለበት።

የተባሉት አደጋዎች ሪፖርት ሲቀርብ፣ ሀላፊዎችና ዋና ሀላፊዎች በህግ አፈፃፀም ባለስልጣናት የተመዘገቡትን ማናቸውንም ጥፋቶች እስሮች ወይም ክሶች እና በተባሉት ባለስልጣናት በዚህ ፖሊሲ ንዑስ ክፍል ለ መሰረት ሪፖርት እንዲደረጉ የሚጠየቁትን በትክክል ማመላከት አለበት።

መ. ሀላፊው እና ወይም ተሰያሚውየሰነ ምግባር እርምጃ በተባለው ተማሪ ላይ በመወሰዱ ወይም በስነምግባር እርምጃው ላይ ሳይመረኮዝ በዚህ ንዑስ ክፍል ሪፖርት እንዲደረግ የሚጠየቅ ወይም ሪፖርት የሚደረግን ማንኛውም ድርጅት አስመልክቶ ለማንኛውም ተማሪ ወላጅ/ሞግዚት ያሳውቃል። የተባለው ማስጠንቀቂያ አግባብነት ካለው የተማሪው ተሳትፎ ጋር ብቻ መዛመድና ሌሎች ተማሪዎችን አስመልክቶ ምንም አይነት መረጃ ማካተት የለበትም።

ሠ. ማንኛውም ተማሪ በዚህ ንዑስ ክፍል ውስጥ እንደተገለጸው ማንኛውንም ሪፖርት የሚደረግ ክስተት ከፈፀመ የተባለው ተማሪ በተባለው ክልከላ እና ጣልቃ ገብነት ተግባራት ዋና ሀላፊው ወይም ተሰያሚው እንደአግባብነቱ እንደሚጠየቀው እንዲሳተፍ ይጠየቃል። ክልከላው እና ጣልቃ ገብ ተግባራቱ በ1994 የፌደራል የተሻሻለው የአሜሪካ ትምህርትቤቶች ህግ መሠረት የአካባቢያዊ ትምህርት መምሪያ የአደንዛዥ እፅና አልኮል ጠንቀኝነት መከላከያ እቅዶች ውስጥ መለየት አለባቸው።

ረ. በፌደራል ህግ ደንብ ወይም የህግ ፍልስፍና በሌላ አካኋን ሊጠየቅ ከሚችለው በስተቀር፣ ሀላፊው በዚህ ፖሊሲ ንዑስ ክፍል 7ሀ አንቀጽ 2-5 ስር የተዘረዘረውን ማንኛውንም ክስተት የተባለው ድርጊት ልዩ ነገር ፈጻሚ የሆነ ማንኛውም ለአካለ መጠን ያልደረሰ ተማሪ ወላጅ/ሞግዚት የወንጀል ጥፋት ተደርጐ ሊቆጠረ የሚችል ሁኔታ ወዲያውኑ ሪፖርት መደረግ አለበት በተጨማሪም ሀላፊው በህጉ ሊጠየቅ እንደሚችለው ለአካባቢያዊ ህግ አፈጻጸም ሪፖርት የተደረገን ክስተት ሪፖርት ማድረግና ወላጅ/ሞግዚቶቹን እንደአስፈላጊነቱ ለበለጠ መረጃ የአካባቢያዊ ህግ አፈጻጸም ሊያገኛቸው ይችላል።

ለዚህ ክፍል አላማዎች ወላጅ/ሞግዚት ቁጥጥር የሚያደርግበትን ወይም የሚመለከተውን ህፃን አስመልክቶ ማንኛውም ወላጅ ሌላ ግለሰብ ይሆናል።.

**ረ. የታገዱ እና ወይም የተባረሩ ተማሪዎች ዳግም ወደትምህርት ገበታቸው የመመለስ እድል**

ከኤስፒኤስ ትምህርት ቤት የታገደ ማንኛውም ተማሪ ወደመደበኛ ትምህርቱ ለመመለስ ብቁ እስኪሆን ድረስ በማንኛውም ሌላ ትምህርት ቤት ውስጥ ለመማር ብቁ አይሆንም በትምህርት ቤቱ ቦርድ ከመደበኛ ትምህርቱ ከ30 ቀናት ለበለጠ ግዜ የተባረረ ወይም የታገደ ማንኛውም ተማሪ ወይም በጋራ ብልጽግና ውስጥ የሚገኝ የግል ትምህርት ቤት ወይም በሌላ ክልል ውስጥ የሚገኝ የግል ትምህርት ቤት ወይም በዚህ የጋራ ብልፅግና በሌላ ክልል ውሰጥ የሚገኝ የግል ትምህርት ቤት ምዝገባው እንዲወጣ የተደረገ ተማሪ እግድ ከ30 ቀናት በሚበልጥባቸው ሁኔታዎች የእግዱ ቆይታ ከዚህ እግድ ቆይታ ግዜ ሊበልጥ አይችልም።

ከትምህርት ቤቱ መገኘ መቆጣጠሪያ ቅፅ የተባረረን ማንኛውንም ተማሪ ሳያካት፣ የትምህርት ቤቱ ቦርድ በቨርጂኒያ ህግ 22.1-277.06 መሠረት የአባራሪው የትምህርት ቦርድ በተባለው ተማሪ ላይ የተጣሉትን ማናቸውንም ወይም ሁሉንም ዳግም ወደትምህርት ገበታ የመመለስ ሁኔታዎች ሊቀበል ወይም ሊያነሳ ይችላል። ውድቅ አድራጊው የትምህርት ቤት ቦርድ ወደ ትምህርት ቤቱ ዳግም የመግባት እድልን አስመልክቶ ምንም አይነት ተጨማሪ ሁኔታዎች አይጥልም። የትምህርት ቤት ሃላፊ

ወይም ተሰያሚው ወደትምህርት ገበታው ዳግም የመመለስ እድልን ካለ ወላጅ/ሞግዚት ስብሰባ ካልወሰነ በስተቀር  ማንኛውም የታገደ ተማሪ የተባለው ተማሪና ወላጁ/ሞግዚቱ የተማሪውን ባህሪ ማሻሻያ ለመወያየት ከትምህርት ቤቱ ሀላፊዎች ጋር እስኪገናኙ ድረስ ወደ መደበኛ የትምህርት ፕሮግራሙ መመለስ አይችልም።

ወላጅ/ሞግዚት ይህንን ፖሊሲ ጂኢሲ ለማክበር ካልቻለ፣ የትምህርት ቤቱ ቦርድ የወጣቶችና የአገር ውስጥ ግንኙነት ፍርድ ቤት የተማሪውን ባህሪ ለማሻሻል በሚደረጉ ጥረቶች ውስጥ ሆንብሎና ተገቢ ባልሆነ መልኩ የሚቃወም ወላጅ/ሞግዚት ላይ ክስ እንዲመሰረት ሊጠይቅ ይችላል።

የተማሪው ምዝገባ እንዲነሳ ወይም ውድቅ እንዲደረግ አሰመልክቶ የሚፀናው ቆይታ ግዜ በትምህርት ቤቱ ቦርድ ወይም ዋና ሃላፊው ወይም ተሰያሚው አግባብነት ባለው የመሰማት ሂደት መቋቋም ያለበት እንዳበቃ፣ ተማሪው ወደትምህርት ገበታው ለመመለስ የትምህርት ቦርድ በድጋሚ ማመልከቻ ይጠይቃል። ወደትምህርት ገበታው የመግባት ማመልከቻ ውድቅ ከተደረገ፣ የትምህርት ቤቱ ቦርድ ቀጣይነት ያለው የማግለያ ቆይታ ግዜ ርዝማኔ እና ተማሪው ወደትምህርት ገበታው ለመመለስ የትምህርት ቦርዱን ዳግም በማመልከቻ ስለሚጠይቅባቸው ተከታይ ቀናት መለየት አለበት።

***የተባረሩ ተማሪዎችን ዳግም ወደትምህርት ገበታ መመለስ አስመልክቶ ገዢ ደንብ***
ከአሌክሳንደሪያ ከተማ የህዝብ ትምህርት ቤቶች የተባረሩና በተባረሩባቸው ግዜያት ወደመደበኛ ትምህርት ገበታቸው እንዲመለሱ ወይም አማራጭ የትምህርት ፕሮግራም እንዲካፈሉ ያልተፈቀደላቸው ተማሪዎች ከተባረሩባቸው ቀን ጀምሮ ለአንድ አመት ለሚፀና ግዜ ዳግም ወደትምህርት ገበታቸው ለመመለስ ሊያመለክቱ ይችላሉ። የማንኛውም የተባረረ ተማሪ ዳግም ወደትመህርት ገበታው የመመለስ ሂደት እንደሚከተለው ነው፥

ሀ. አንድ ተማሪ ለት/ቤት በጊዜው እንደገና እንዲገባ እድል ማግኘቱን ለማረጋገጥ፣ የመልሶ ማስገቢያ ማመልከቻ ከ 9 ወር ባላነሰ ጊዜ ውስጥ፣ እና የትምህርት ቤቱ ቦርዱ ተማሪውን የማሰናበቻ ደብዳቤ እንዲሰጠው ከወሰነበት ቀን ጀምሮ ከ 10 ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት። እንደገና ለማስገባት የተሰበሰበውን ማመልከቻ በጊዜው ማቅረብ አለመቻል በችሎቱ ውሳኔ ላይ ማዘግየት ሊያስከትል ይችላል። አቤቱታዎች በፅሁፍ መሆን አለባቸው እና በ ACPS የተማሪዎች አገልግሎት እና ፍትህ ክፍል መቅረብ አለባቸው። 18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ ማንኛውም ተማሪ በራሱ ስም ማመልከቻ ማስገባት አለበት። ተማሪው ዕድሜው ከ 18 ዓመት በታች ከሆነ፣ ወላጅ(ጆች)/አሳዳጊ(ዎች) በተማሪው ስም ሊተገበሩ ይችላሉ፣

ለ. ለንባብ የተጻፈ አቤቱታ በደረሰው በ 21 ቀናት ውስጥ፣ የ ACPS የተማሪዎች አገልግሎቶች እና ፍትህ ክፍል ችሎት ቀጠሮ ይይዛል። በችሎቱ ወቅት፣ ተማሪው እና/ወይም ወላጅ(ዎች)/ አሳዳጊ(ዎች) ተማሪው ለምን ወደ ት/ቤት እንደገና መግባት እንዳለበት፣ እና የተማሪው ባህሪ እንደተሻሻለ ትምህርት ቤቱ እንዴት እርግጠኛ መሆን እንደሚችል እና አግባብ ያልሆነ ባህሪይ በድጋሚ እንደማይኖር ለማስረዳት ተዘጋጅተው መምጣት አለባቸው። ተማሪው በተባረረበት ወቅት ድጋሚ ተመልሶ ለመግባት በትምህርት ቤቱ ቦርድ ማናቸውም ቅድመ ሁኔታዎች ከተቀመጡ፣ እነዚህ ሁሉ ሁኔታዎች የተሟሉ መሆን አለመሆናቸውን ችሎቱ ይገመግማል። የተማሪ አገልግሎቶች እና የእኩልነት ዲፓርትመንቱ ችሎቱ በተሰማ በ 7 ቀናት ውስጥ የጽሑፍ ውሳኔ ይሰጣል። ወላጅ(ጆች)/አሳዳጊ(ዎች) እና/ወይም ተማሪው የውሳኔውን ቅጂ ይቀበላሉ።

ሐ. ወላጅ(ጆች)/አሳዳጊ(ዎች) እና/ወይም ተማሪው ውሳኔውን በተቀበለ በአምስት ቀናት ውስጥ የተማሪ አገልግሎቶች እና የፍትሃዊነት መምሪያ የሰጠውን ውሳኔ ለት/ቤቱ ቦርድ ይግባኝ ማለት ይችላል። የአስተዳዳሪው ውሳኔ ቅጂ፣ የማባረር ውሳኔ ቅጂ፣ እና መባረሩን በተመለከተ የገባ ማንኛውም ቁሳቁሶች፣ እና እና ድጋሚ ለመግባት የተሰበሰበው ማመልከቻ ለቦርዱ ይቀርባል። ቦርዱ ምናልባት ተጨማሪ ቀጠሮ ሊይዝ ይችል ይሆናል፣ ነገር ግን ላያስፈልገውም ይችላል። ቦርዱ ይግባኙን ከግምት ውስጥ ባስገባ በ 21 ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ይሰጣል።

ተጨማሪ መረጃ በአባሪ F ውስጥ ማግኘት ይቻላል።

# ከአካል ጉዳት ጋር የሚኖረ ተማሪዎች ስነ ምግባር

ይህ መረጃ ከአካል ጉዳት ጋር የሚኖሩ ተማሪዎችን ስነ ምግባር አስመልክቶ በውሳኔ አሰጣጥ ረገድ መደረስ ካለባቸው ሂደቶች እና ሥነ ሥርዓቶች ጋር በተዛመደ ለኤሲፒኤስ ቤተሰቦች መረጃ ለማቅረብ የታቀደ ነው።

## ገዢ መርሆች

ከአካል ጉዳት ጋር ለሚኖሩ ተማሪዎች የኤሲፒኤስ መርህ መስፈርቶችን ለመምራት በፌደራል እና በክልል ደንቦች ውስጥ 5 ዋና ዋና መርሆች አሉ:-

1. ሁሉም ተማሪዎች በአዎንታዊ የባህሪያዊ ጣልቃ ገብነቶች እና ድጋፍ መዋቅር ውስጥ የተመሰረቱ ደህንነታቸው የተጠበቀ፣ በተገቢው ሥነ ምግባር የሚመሩ ትምህርት ቤቶች እና ሥርዓታቸውን የጠበቁ የመማሪያ አካባቢዎች ይገባቸዋል።
2. አስተማሪዎች እና የትምህርት ቤት አስተዳዶች የሥነ ምግባር ጉድለትን እና የሥነ ምግባር ችግሮችን ለመከላከል እና እነዚህ ችግሮች ሲከሰቱ ለመድረስ የሚያግዙ መሳሪያዎች ሊኖራቸው ይገባል።
3. ሥርዓታቸውን የጠበቁ እና አስተማማኝ ትምህርት ቤቶች ሊያስፈልጋቸው የሚችሉ ከአካል ጉዳተኝነት ጋር የሚኖሩ ተማሪዎች ጉዳይን እና ከአካል ጉዳተኝነት ጋር የሚኖሩ ተማሪዎች መብቶቸን ነፃ እና አግባብነት ባለው የህዝብ ት/ቤት ውስጥ ለማስጠበቅ አስፈላጊ የሆኑትን በተመጣጠነ መልኩ መድረስ።
4. የተናጠል ትምህርታዊ ፕሮግራሞችን በደንብ ከጎለበቱ የባህሪያዊ ጣልቃ ገብነት ስትራቴጂዎች መቀነሻ የትምህርት ስነ ምግባር ችግሮች ጋር መከተል።
5. የትምህርት ቤቱን ሰራተኛ የሥነ ምግባር ደንቡን የጣሰ አንድ የአካል ጉዳተኛ ተማሪ የምደባ ለውጥ ማድረግ እንዳለበት አስመልክቶ እንደየሁኔታው ለመወሰን የሚያስችሉት ማናቸውንም ልዩ ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ይወስዳል።

የተማሪው ባህሪ የተማሪውን ትምህርት ወይም የሌሎችን በሚያደናቅፍበት ጊዜ የአይኢፒ ቡድን ባህሪውን ለመድረስ አዎንታዊ የባህሪያዊ ጣልቃ ገብነቶችን ስትራቴጂዎችን እና ድጋፎችን መጠቀም ያስባል።

**የአይኢፒ በድን ከሚከተሉት አንዳቸውን ከግምት ውስጥ ያስገባል፥**
- ለተማሪው የባህሪያዊ ፍላጎቶች በልዩ ሁኔታ ተግባራዊ የሚሆኑ ግቦች እና አገልገሎቶችን ማጎልበት ወይም።
- በአሰራር ላይ የተመረኮዘ የባህሪያዊ ምዘና ማካሄድ እና የተማሪውን የባህሪያዊ ፍላጎቶች ለመድረስ የባህሪያዊ ጣልቃ ገብነት እቅድ ፍላጎትን መወሰን።

ተማሪው በአጭር ጊዜ ወይም በረጅም ጊዜ ስንብት እንዲደረግ ሊዳርጉት የሚችሉ ማናቸውም ባህሪያት ውስጥ ተሳትፎ ከተገኘ  የአይኢፒ ቡድን የተባለውን የባህሪ ጥሰት መድረስ አለበት። የአይኢፒ ቡድን ውይይቶች እና ክለሳዎች የተማሪው ባህሪ ድግግሞሽ እንዲቀንስ እና ለመከላከል እንዲቻል የተማሪውን የባህሪያዊ ችግሮች ለመድረስ የሚያስችሉ ጥረቶች ላይ ያተኩራሉ። በዚህ ረገድ ከግምት ውስጥ ሊወሰዱ የሚገቡ አግባብነት ያላቸው ድጋፎች እና አገልግሎቶች፥

- አሰራር ተኮር የባህሪያዊ ምዘና ማካናወን።
- የባህሪያዊ ጣልቃ ገብነት ዕቅድን ማጎልበት ወይም መከለስ።
- የማማከር አገልግሎት ማቅረብ።

- የማህበራዊ ብቃት ሥልጠና ማቅረብ።
- ተለማማጅ የባህሪያዊ ቴክኒክ ስልጠና (ማለትም) ባህሪው ተደጋጋሚ እንዳይሆን የሚያስችል ምትክ ብቃት ማስቻያ ትምህርት።
  - የግጭት አወጋገድ ብቃት ማቅረብ፤
  - የአቻ ለአቻ እርቅ ብቃት ማቅረብ፤

## የአጭር ጊዜ አወጋገድ

የቨርጂኒያ ደንቦች የኤኢፒ ቡድን ወደ ስነ ምግባር ጥሰት የሚዳርግ ማንኛውም ክስተት ከመከሰቱ በፊት ስለ ተማሪው የባህሪ ችግሮች የመድረስ ጠቀሜታን ያሰምሩበታል። ስለዚህም  በጣም አግባብነት ያላቸው የእርምጃ ዓነቶች የአይኢፒ ቡድንን መጥራት እና በአሰራር ላይ የተመረኮዘ የባህሪ ምዘና (ነኛው ካልተሳካ) አስፈላጊነት መወሰን እና ከአጭር ጊዜ ማስወገጃ ወይም ተከታታይ የሆኑ የአጭር ጊዜ ማስወገጃዎች በፊት የባህሪያዊ ጣልቃ ገብነት ዕቅድን ማጎልበት ወይም መከለስ። እነዚህ ንቁ እርምጃዎች የአጭር ጊዜ ማስወገጃዎች ሂደትን ለመከላከል የሚያስችሉ እርምጃዎች ያስጠብቃሉ። እነዚህ ንቁ እርምጃዎች የአጭር ጊዜ ማስወጋጃዎችን ለማካሄድ የመከላከያ እርምጃዎችን በሰነድ ያስጠብቃሉ። አስተዳዳሪው አንድን የአካል ጉዳተኛ ተማሪ ከተማሪው የዘመኑ የትምህርት ዝግጅት ወደ አማራጭ የትምህርት ዝግጅት የማስወገድ ወይም ጥልቅ እግድ ላይ የማኖር አስፈላጊነት ከግምት ውስጥ ከወሰደ ይህ እነዚህ አማራጮች አካል ጉዳተኝነት በሌለባቸው ተማሪዎች ላይ እስከሚተገበሩት አማራጮች ድረስ ሊፈፀሙ ይችላሉ።

አስተዳዳሪዎች በእያንዳንዱ ጥሰት የማስወገጃ ጊዜ እርዝማኔን ለመወሰን ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው። የአንድ ተማሪ ጥሰት የተባለው የጊዜ ቆይታ የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር እስከ 10 ቀናት ለሚጠጉ ወይም ለሚደርሱ ጊዜያት መወገድ  በተለይም የተባለው የሥነ ምግባር እርምጃ በወጥነት ካልተተገበረ ወይም አካል ጉዳተኝነት በሌለባቸው ተማሪዎች ላይ ተፈፃሚ ካልሆነ እጅግ በጣም የበዛ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። አንድ ተማሪ ባህሪውን አስመልክቶ ለሚፈፀሙ ራሳቸውን የቻሉ የሥነ ምግባር ጉድለቶች በትምህርት ዓመቱ ውስጥ ለ10 ቀናት ወይም ከዚያ በላይ ከታገደ፣ ይህ በምደባ (የኸርም ጊዜ እግድ ሥነ ሥርዓቶን ይመልከቱ) ለውጥ ተደርጎ ይቆጠራል። በትምህርት ቤት የተመሰረተ አስተዳዳሪ በልዩ የትምህርት አገልግሎት ቢሮ ውስጥ ካለ ሰራተኛ ጋር በመተባበር እርስ በእርሳቸው ዝምድና የሌላቸውን የሥነ ምግባር ጉድለት ሁኔታዎች ተከትለው በተናጠል የሚወሰዱ የአጭር ጊዜ ማስወገጃዎችን ትክክለኛነት ይወስናል። ጥሰቱ የግላዊ እና ልዩ ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ ተመሳሳይነትን የሚጋራ ከሆነ (የጋራ የሆኑ ነገሮች) ካሉት፣ የተባለው አካሄድ መኖሩን ለመወሰን አግባብነት ይኖረዋል። የተባለውን እግድ ትክክለኛነት ለመከለስ በእውነት ተባባሪ የሆነ አቀራረብን በማሻሻል፣ ወላጆች በሂደቱ ውስጥ ምክክር ሊደረግላቸው እና ስለውሳኔው ወዲያውኑ እንዲያውቁ ሊደረጉ ይገባል።

እርምጃውን አስመልክቶ የተወሰደው ውሳኔ ሰነድ በሥነ ምግባር መዛግብት ክለሳ፣ የተማሪው አይኢቢ የማናቸም የባህሪያዊ ጣልቃ ገብነት ዕቅድ ማጎልበቻ አካቶ በተደረጉ ክለሳዎች፣ ሌሎች የትምህርታዊ መዛግብት እና ከማናቸውም ሌሎች አግባብነት ያላቸው ምንጮች የተገኙ ግብአቶች የተሰበሰቡ መረጃዎችን ማጠቃለያ ማከተት አለበት። ውሳኔውን ለማድረግ ምክክር የተደረገላቸው ግለሰቦችም በሰነድ መጠበቅ አለባቸው።

የተማሪውን ባህሪ እና የተናጠሉ የሥነ ምግባር ክስተቶችን በመከለስ ይህ አካሄድ መኖር አለመኖሩን ለመወሰን፣ በትምህርት ቤት ላይ የተመሰረተ አስተዳደር፣ በሚከተሉት ረገድ ድጋፍ የሚያቀርበውን የኤስሲፒኤስ የስነ ሥርዓት አስተባባሪ ይገናኛል፥

- ለዕግድ ከዳረጉት ባህሪያት ጋር በተገናኘ ያሉትን ምክንያቶች መተንተን፤
  - ስህተቱ የት እንደተከሰተ (አካባቢ)፤
  - ከሌሎች ሰዎች ጋር የሚደጉ ግንኙነቶች፤
  - የተግባር መስፈርቶች፤
  - እነዚህን ጥሰቶች የቀሰቀሱ ክስተቶች፤
  - የእያንዳንደ የማስወገድ ርምጃ ርዝማኔ፤
  - ተከታታይ ለሆኑ የማስወገድ ርምጃዎች የዳረጉ የከዚህ በፊት ክስተቶች ውስጥ የተማሪው ባህሪ ተመሳሳይነት፤
  - ተማሪው የተወገደበት አጠቃላይ የግዜ መጠን ወይም፤
  - አንዱ የማስወገድ ርምጃ ከሌላኛው ጋር  ያለው ቅርበት፤
- የአይኢፒ ምላሽም እስከዛሬው ቀን ድረስ (ኤፍቢኤ፣ ቢአይፒ፣ ግቦች፣ ከባህሪው ጋር ተዛማጅ የሆኑ አገልግሎቶች) መከለስ እና።
- የአካሄድ ስርዓታቸው የሌሉ ውሳኔዎችን በሰነድ በመጠበቅ እና ቀጣይ እርምጃዎችን በማቋቋም ድጋፍ ማቅረብ።

## የመገለጫ ውሳኔ ክለሳ (ኤምዲአር)

የኤምዲአር ስብሰባ ተማሪው በስነምግባር ጉድለት የተነሳ ለምደባ ለውጥ ማንኛውም ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በአስር ቀናት ውስጥ ይካሄዳል። ይህም ውሳኔ በአይኢፒ ቡድን አግባብነት ያላቸው አባላት ይደረጋል። የስብሰባው አላማ ስነምግባሩ ከሚከተሉት አንዳቸው መሆኑ ይወሰናል፡

- ከተማሪው አካል ጉዳት ጋር ቀጥተኛና ጉልህ ግንኙነት ባለው ሁኔታ የተከሰተ።
- የተማሪውን ኢአይፒ ለመተግበር ትምህርት ቤቱ ተግባሩን ባለመወጣቱ የተነሳ በቀጥታ የተከሰተ።

ከሁለት አንዳቸው ጥያቄዎችን "አዎ" ብለው ከመለሱ ለስነምግባር እርምጃ አወጋገድ የሚገዛው ባህሪ የተማሪው አካል ጉዳት መገለጫ መሆኑ ይወሰናል።

***ጥያቄ ቁጥር 1፥***
በተማሪው አካል ጉዳት የተነሳ ተከስቷል የተባለው ስነ ምግባር ወይም የተባለው ስነ ምግባር ከተማሪው አካል ጉዳት ጋር ቀጥተኛና ጉልህ ግንኙነት አለውን?

የተባለው የስነምግባር ጉድለት መከሰት የአይኢፒ ቡድኖች ስኬታማ የሆኑ የመገለጫ መወሰኛዎችን ለመምራት እንዲችሉ አጠቃላይ የችግር - ማስወገጃ ክለሳ። የተባለው ስነምግባር ከተማሪው አካል ጉዳት ጋር በቀጥታ በተያያዘና ጉልህ ግንኙነት ባለው መልኩ መከሰቱን ለመወሰን፣  የአይኢፒ ቡድን የሚከተሉትን መወሰኛዎች ከግምት ውስጥ ያስገባል፥

- የተማሪውን ትምህርታዊ ፕሮግራም።
- የአካባቢያዊ መወሰኛዎች።
- የቤት ውስጥ መወሰኛዎች እና የተማሪው አእምሮአዊ አካላዊና የማጐልበቻ መሰናክሎች።
- የተማሪው የስነ ምግባር ታሪክ (በአጠቃላይ እግድ የላለፈበት ግዜያት፣ የእግዶቹ መቀራረብ እና የእያንዳንዱ እግድ እርዝማኔ።
- ከተማሪው የስነምግባር ታሪክ ጋር የተገናኘ የስነምግባር ጉድለቱ አይነት(የተናጠለ ደረጃ ከድግግሞሽ አንፃር፣ የተማሪው በሀሪ ከከዚህ በፊትና ከዘመኑ ክስተት ጋር ያለው ጉልህ ተመሳሳይነት)።
- ለተባለው የስነምግባር ጉድለት አስተዋጽኦ ያደረጉ ሌሎች መወሰኛዎች እንደ ልዩ ሁኔታዎች፣ ከአደጋው ታዛቢዎች የተገኙ መረጀዎች ወዘተ....
- የተማሪው የስነምግባር ደንብ ለቤተሰቡ መቅረቡን የሚያስረዳ ደንብ።
- በሀሪው አደገኛ እንደነበር በሌላ ሰው ላይ ጉዳት እንደዳረገ ወይም “ከባድ የአካል ጉዳት” እንደዳረገ።
- የዘመኑ የባህሪ ስትራተጂዎች ተመሳሳይ የስነምግባር ጉድለትን ለመከላከል እና በተማሪው ትምህርት ቤት ውስጥ የሚፈለገውን ባህሪ ለማስፈጸም ያለው ውጤታማነት።
- ከስነምግባር ጉድለቱ ጋር በተገናኘ የተማሪው ቢአይፒ ውጤታማነት።
- ቢአይፒው በማይኖር ጊዜ፣ የኤፍቢኤ አስተዳደር።
- የበለጠ መረጃ (ኤፍቢኤ ወይም ሌሎች የግምገማ አይነቶች) ማስፈለጋቸው።
- በጣም የቅርብ የብቁነት ማረጋገጫ ግምገማ።

***ጥያቄ ቁጥር 2፥***
የተባለው ስነምግባር የትምህርት ቤቱ ወረዳ አይኢፒን ለመተግበር ባለመቻሉ የተነሳ በቀጥታ የተከሰተ ውጤት ከነበር ?

የአይኢፒ ቡድን በስነምግባር ጉድለቱ ላይ የተማሪውን አይኢፒ ለመተግበር ባለመቻላቸው የደረሰውን ተፅእኖ ይወስናሉ። ይህም ማለት በመጀመሪያ ያልተተገበረውን ነገር መወሰንና በመቀጠል በተማሪው ባህሪ ላይ ያለውን እንደምታ መወሰን ይሆናል። የአይኢፒ ቡድን የሚከተሉትን ከግምት ውስጥ ይወስዳል።

- ከተማሪው ብቃት፣ ማህበራዊ ችሎታና ባህሪ ጋር በተገናኘ ያልተተገበረው የአይኢፒ አካባቢ እና የተተስተዋለው የስነምግባር ጉድለት እንዴት እነደሆነ።
- የአይኢፒ ቡድን ትምህርት ቤቱ የተማሪን አይኢፒ ለመተግበር አለመቻሉን መወሰን፣ አዎንታዊ ባህሪ ድጋፍ ወይም ቢአይፒ።

የአይኢፒ ቡድን የተማሪውን አይኢፒ ትምህርት ቤቱ ለመተግበር አለመቻሉን ከወሰነ፣ በትምህርት ቤት ላይ የተመሰረተ ደረጃ አነዚህን ችግሮች ለማስተካከል አስቸኳይ እርምጃዎች ይወስዳል።

**ባህሪ የተማሪው አካል ጉዳት  መገለጫ ነው.**
ቡድኑ የስነምግባር ጉድለቱ የተማሪው አካል ጉደት መገለጫ መሆኑን ከወሰነ፣ የሚከተሉት መከሰት አለባቸው፡

- የአይኢፒ ቡድን የተማሪው ወላጅ/ሞግዚት እና የትምህርት ቤቱ መምሪያ በቢአይፒ ወይም አይኢፒ ማሻሻያ ክፍልነት  ምደባውን ለመለወጥ ካልተስማሙ በስተቀር ተማሪው ከተወገደበት ምደባ ተማሪው መመለስ አለበት።
- ኤፍቢኤ ማከናወን የትምህርት ቤቱ መምሪያ ምደባው እንደተከሰተ ለውጥ የዳረገው ባህሪ ከመከሰቱ በፊት ምዘናውን አካሂዶ ካልነበረ፤
  - ኤፍቢኤ በአይኢፒ ቡድን እንደሚወሰነው ነባሩን ዳታ መከለስ ወይም አዲስ የፍተሻ ዳታ መጠቀም ወይ መገምገም ያካትታል።
  - የአይኢፒ ቡድን ኤፍቢኤ አዲስ የፍተሻ ዳታ ማግኘት ወይም ግምገማ ማካሄድ እንዳለበት አካቶ ከወሰነ፣ በመቀጠል ወላጅ/ሞግዚት በኤስፒኤስ በተገኘው ግምገማ ወይም የግምገማ ክፍል ካልተስማማ ገለልተኛ የትምህርታዊ ግምገማ እንዲደረግ የማድረግ መብት አለው።
- የተማሪውን ቢአይፒ መወሰን
  - የባህሪ ጣልቃ ገብነት እቅድ ከጐለበተ፣ ይህንን እቅድ መከለስና ባህሪውን ለመድረስ እንዳስፈላጊነቱ ማሻሻል።

**ባህሪው የተማሪው አካል ጉዳት መገለጫ አይደለም**
የአይኢፒ ቡድን የተማሪው ባህሪ የተማሪው አካለ ጉዳት መገለጫ እንዳልነበር ከወሰነ፣ የትምህርት ቤቱ ሰራተኛ ከአካል ጉዳት ጋር የሚኖሩ ተማሪዎችን አግባብነት ያላቸው ስነስርዓቶች በተመሳሳይ አካኋን ሊተገበርና ለነዚህ ስነስርዓቶች ተመሳሳይ ቆይታ ከአካል ጉዳት ጋር በማይኖሩ ተማሪዎች ላይ ተግባራዊ ይሆናል። ነገር ግን የተባሉት አገልግሎቶች የአይኢፒ ቡድን እንደሚጠየቀው በዚህ ረገድ በተደረሰው ውሳኔ ይቀርባል።

## በረጅም ግዜ ማስወገጃ እርምጃ ግዜያት የሚቀርቡ አገልግሎቶች

የአይኢፒ ቡድን ከማስወገጃው 11ኛ ቀን በፊት ወይም በተቻለው ፍጥነት የረጅም ግዜ እግድን የሚጋፈጠ ተማሪ የሚፈልጋቸውን አገልግሎቶች በመወሰን ተማሪው የሚከተለውን እንዲፈጽም ያስችሉታል፡

- በሌላ ነባራዊ ዝግጅት ቢሆንም እንኳን ባጠቃላይ የትምህርት ስነስርዓት ውስጥ መሳተፉን መቀጠል።
- በተማሪው የዘመኑ አይኢፒ ውስጥ የተገለፁትን ድጋፎችና አገልግሎቶች ውስጥ መቀበሉን በመቀጠል ተማሪው የአይኢፒ ግቦችን ለማሳካት ግስጋሴ እንዲኖረው ማስቻል እና።
- ኤፍቢኤም እና የባህሪ ጣልቃ ገብነት ድጋፎችና አገልግሎቶች የባህሪ ጥሰት በተደጋጋሚ እንዳይከሰት ለመድረስ የተቀረፁትን መቀበል።

የአይኢፒ ተጨማሪ ክፍል በረጅም ጊዜ ማስወገጃ ግዜያት ለሚቀርቡ አገልግሎቶች በሰነድ እንዲጠበቁ መጐልበት አለባቸው። ተማሪው በአጠቃላይ የትምህርታዊ ስንስርዓት ውስጥ መሳተፉን እንዲቀጥል ለማስቻል የሚቀርቡ የመመሪያ አገልግሎቶች መጠንና አይነት በሚከተለው ላይ ይመረኮዛሉ፡

- የማስወገጃው ርዝማኔ።
- ተማሪው ከዚህ በፊት የተወገደበት መጠን እና።
- የተማሪው የትምህርታዊ ፍላጐትና ግቦች።

ተማሪውን በረጅም ጊዜ ማስወገጃ ግዜያት ለማገልገል ሲባል፣ የአይኢፒ ቡድን አማራጭ የመመሪያ ቴክኒኮችን እንደ አማራጭ/ከፍተኛ ደረጃ ያላቸው ቁጥጥር የሚደረግባቸው ከፊል የትምህርት ቤት መገኛ መቆጣጠሪያ (ለምሳሌ ከትምህርት ቤት ስንበት በኋላ በሳምንት ለሁለት ሰዓታት) ወይም በቤት ውስጥ የተመሰረተ መመሪያ ከግምት ውስጥ ይወስዳል። የትምህርት ቤቱ ሰራተኛ ወደኋላ እንዳይጐተት እና በአጠቃላይ የትምህርት ስነስርዓቱ እና የአይኢፒ ግቦችና አላማዎች ላይ ግስጋሴን ለማስቻል እድል ይኖረዋል። በተጨማሪም በክልል ወይም በመምሪያ አቀፍ ፈተና ግዜያት ከትምህርት ቤቱ የተወገዱ ተማሪዎች በሁሉም አስፈላጊ ምዘናዎች ውስጥ ለመካፈል ዝግጅቶች ሊቀርብላቸው ይገባል።

## የጦር መሳሪያዎችን፣ አደንዛዥ እፆችን ወይም ከባድ የአካል ጉዳቶችን ያስከተሉ ልዩ ሁኔታዎች

የአካል ጉዳተኛ ተማሪን ከ ACPS የተማሪዎች አገልግሎቶች እና የእኩልነት አስተዳዳሪ ጋር ለመገናኘት ልዩ ሁኔታዎች ሊያስፈልጉ ይችላሉ። ቀጥለው ለተዘረዘሩት የተለዩ ሁኔታዎች የአካል ጉዳተኛ ተማሪ በተከታታይ ለ 45 የትምህርት ቀናት ተማሪው በትምህርት ቤት፣ በት/ቤት ግቢ ውስጥ፣ ወይም በት/ቤቱ ክፍል ስልጣን ስር ላሉት የት/ቤት ተግባራት በሚመደበው ተወካይ ሊመደብ ይችላል፡

- **የጦር መሳሪያዎች፡ የጦር መሳሪያ ይዞ መገኘት።**
- **አደገኛ እፆች፡ ህገወጥ አደንዛዥ እፆችን እያወቀ ይዞ መገኘት ወይም መጠቀም ወይም የተከለከሉ ንጥረ ነገሮችን መሸጥ ወይም መጠየቅ።**
- **ከባድ የአካል ጉዳት፡ በሌላ ግለሰብ ላይ ከባድ የአካል ጉዳት መዳረግ።**

የጦር መሳሪያዎችን፣ አደንዛዥ እጾችን እና ወይም ከባድ የአካል ጉዳቶችን በሚያካትቱ ሁኔታዎች፣ የትምህርት ቤቱ ተሰያሚ የተማሪው ባህሪ፣ የተማሪው አካል ጉዳት መገለጫ መሆኑን በመወሰኑ ላይ ሳይመረኮዝ በአማራጭ የትምህርታዊ ዝግጅት ላይ ቢበዛ ለ45 ከፍተኛ የትምህርት ቀናት ሊመድበው ይችላል።

## በ11ኛ ቀን ላይ የሚቀርብ ልዩ የትምህርታዊ አገልግሎቶች

አንድ የአካል ጉዳት ያለበት ተማሪ ከተማሪው የዘመን ምደባ ላይ ከትምህርት አመቱ 11ኛ ድምር ቀን ጀምሮ ከተወገደ እና በማናቸውም ተከታታየ ግዜያት ከትምህርት ገበታው ከተወገደ፣ የትምህርታዊ አገልግሎቶች መቅረብ አለባቸው። በ11ኛ ቀን በተከታታይ በአጭር ግዜ ውስጥ ለተወገድ ተማሪዎች የሚቀርቡ አገልግሎቶች የተማሪውን ግስጋሴና ትምህርቱን የማቋረጡ ተፅእኖ በመመዘን በትምህርት ቤቱ ሰራተኛ ይወሰናሉ። በትመሀርት ቤት ላይ የተመሰረተ አስተዳደር ከተማሪው አጠቃላይ ትምህርትና ልዩ ትምህርት አስተማሪዎች ጋር በመመካከር ተማሪው የማከተሉትን መቀጠል ካለበት አስፈላጊ አገልግሎቶችን ሌላም ካለ ለመወሰን፡

- ባጠቃላይ የትምህርት ቤት ስነስርአት ላይ እንዲሳተፍ እና።
- በተማሪው አይኢፒ ውስጥ የተገለፁትን ግቦች ለማሳካት ማሻሻል እንዲያሳይ።

## የትምህርት ቤቱ ቀን ክፍሎች

የትምህርት ቤቱ የቀን ክፍሎች አንድን ተማሪ ለስነምግባር አላማዎች ለማስወገድ ተማሪው ከሚወገድበት አጠቃላይ መጠን ጋር ይደመራሉ ከግማሽ ቀን ያነሰ ማንኛውም ክፍል የግማሽ ቀን የማስወገድ እርምጃ ተደርጐ ሲቆጠር ከግማሽ ቀን የበለጡ ማናቸውም ክፍሎች የሙሉ ቀን የማስወገድ እርምጃ ተደርገው ይቆጠራሉ።

## የረጅም ጊዜ የማስወገድ እርምጃ

የረጅም ጊዜ የማስወገድ እርምጃ አላማ ስነ ምግባር እርምጃው አማካኝነት ሁሉም ተማሪዎች ደህንነታቸው እንዲጠበቅና ለትምህርት ምቹ ሁኔታዎች ማስቻልና የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች/ወላጅ/ሞግዚቶች ለተማሪው አግባብነት ያላቸውን ሁኔታዎች ለመወሰን እንዲቻል ማድረግ ነው። የረጅም ግዜ የማስወገድ እርምጃዎች ከ10 ተከታታይ የትምርት ቀናት ወይም በድምሩ እንደ አካሄድ የሚቆጠሩ የትምህርት ቀናት ካሉ የምደባ ለውጥ ተደርገው ይቆጠራሉ። በምደባው ውስጥ ማንኛውም ለውጥ የመገለጫ መወሰኛ ክለሳ ለማሟላትና ለማከናወን በአይፒ ቡድን አግባብነት ያላቸው አባላት ይጠየቃል።

የረጅም ጊዜ መታገድ በሚያስፈልግበት ጊዜ የ IEP ቡድኑ ተገቢ አገልግሎቶችን መወሰን አለበት። በትምህርት ቤቱ ላይ የተመሠረተ አስተዳደር ተማሪውን ወደ ACPS የተማሪ አገልግሎቶች እና የፍትሃዊነት ዲፓርትመንት የሚያስተላልፈው ከሆነ፣ እና ማስወገዱ የቦታ ለውጥ ካለው (ከ 10 ቀናት በላይ)፣ ውጤቶቹን ለተወካዩ ለማሳወቅ የመገለጫው ውሳኔ ግምገማው (Manifestation Determination Review) በተቻለ ፍጥነት መከናወን አለበት። የመገለጫው ውጤት ዝግጁ በሚሆንበት ጊዜ ከታቀደው ስብሰባ በፊት ለ ACPS የተማሪዎች አገልግሎቶች እና የፍትሃዊነት መምሪያ መቅረብ አለበት።

ተጨማሪ መረጃ በአባሪ J ውስጥ ማግኘት ይቻላል።

# ፀብአጫሪነትን መከላከል

## በኤሲፒኤስ ውስጥ ፀብአጫሪነትን ስለመከላከል

ACPS የሁሉንም ተማሪዎች የትምህርት ስኬት እና ማህበራዊ፣ ስነ ልቦናዊ እና አካላዊ ደንነት የተጠበቀበት እና አዎንታዊ የትምህርት አካባቢ ለመፍጠር ቁርጠኛ ነው። የ ACPS የተማሪዎች አገልግሎት እና ፍትህ ክፍል በተማሪዎች መካከል ጤናማ፣ ተንከባካቢ፣ እና ኃላፊነት የሚሰማቸው ባህሪያትን የሚያስተዋውቁ ፕሮግራሞችን እና ሠራተኞችን ይደግፋል።

## ፀበአጫሪነት ምንድን ነው?

ፀበአጭጫሪነት፣ እንግልት እና ዛቻ በኤሲፒኤስ ውስጥ ቸል አይባሉም። በቨርጂኒያ ሕግ ክፍል 22.1-276.01 መሠረት ፀብአጫሪነት ተፈላጊ ያልሆነ፣ ኃይለኛ ባህሪ የሚከተሉትን ለማድረስ የሚፈፀም እንደሆነ ተገልጽዋል፥

- ኢላማ የተደረገውን ግለሰብ ለመጉዳት፣ ለማስፋራራት ወይም የማዋረድ።
- ትክክለኛ ወይም በግልጽ የሚታይ የኃይል ወይም ጥንካሬ አለመመጣጠን እና።
- በዓይነተኛነት በተደጋጋሚ ጊዜ የሚፈፀም ወይም ከባድ የስሜታዊ ጉዳት የሚያስከትል።

ፀብአጫሪነት የተለያዩ መንገዶችን እንደ፥

- **በንግግር የሚፈፀም ፀብአጫሪነት** የስም ጥሪ፣ ዛቻ መፈፀም፣ መሳደብ፣ ማስፈራራት፣ ዘርን ፆታን ሐይማኖትን፣ የአካላዊ ችሎታን፣ የፆታ መገለጫን፣ የፆታዊ ግንዛቤን ወይም ሌሎች በንግግር የሚፈፀሙ እግልቶችን አካቶ።
- **የአካላዊ ፀብአጫሪነት** መምታት፣መጎንተል፣ መትፋት፣ መቆንጠጥ፣ መግፋት ወይም የሆነን ሰው ንብረት መጉዳት።
- **ተዛማጅ ወይም ማህበራዊ ፀብ አጫሪነት፣** የሆነን ሰው ክብር ወይም ግንኙነት ለመጉዳት ታልሞ የሚፈፀም፣ ይህንን የሚያካትተው፥
  - ወሬዎችን ማናፈስ።
  - የሆነን ሰው በሕዝብ ፊት ማዋረድ ወይም ማሳፈር።
  - ሰዎች የሆነን ሰው እንዲያገሉት ማበረታታት ወይም ማግለል።
- **የሳይበር ፀብአጫሪነት** የኤሌክትሮኒክ ቴክኖሎጂዎች እንደ ተንቀሳቃሽ ስልኮች፣ ኮምፒውተሮች፣ ታብሌቶች፣ የግንኙነት መሳሪያዎች፣ የማህበራዊ ሚዲያ ሳይቶች፣ የጽሁፍ መልዕክቶች፣ ንግግሮች እና ድህረ ገፆችን በመጠቀም የሚፈፀም ማዋረድ ወይም ማሳፈር ድርጊት ነው። ይህም የሚያካትተው፥
  - የጽሁፍ መልዕክቶች እና ኢሜሎች።
  - በኢሜል የተላኩ ወሬዎች ወይም በማህበራዊ ኔትወርክ ገፆች ላይ የተለጠፉ።
  - አሳፋሪ ፎቶዎች፣ ቪዲዮች፣ ድህረ ገፆች ወይም ሀሰተኛ የኦን ላይን ፕሮፋይሎች መለጠፍ።

ፀብአጫሪነት የማያካትተው

- የተለመደ ፉገራ ወይም ልፊያ።
- የጋራ ክርክር ወይም የአቻ ለአቻ ግጭት።
- የተነጠሉ የኃይል ድርጊት፣ የማህበራዊ መተው ወይም ድብድብ .

ፀብአጫሪነት በእነዚህ ባህሪያት ኢላማ የተደረጉ ሰዎችን እነዚህ ባህሪያትን በመሰከሩ እና በተባሪው ባህሪ ውስጥ በሚሳተፉ ሰዎች ላይ ጎጂ ተጽዕኖዎች ያስከትላል። በአንዳንድ ሁኔታዎች ግን የፀብአጫሪነት ለረጅም ጊዜ የሚቆይ እና የስሜታዊ ጉዳት የማስከትል አቅም ያለው ነው።

## የፀብአጫሪነትን ሪፖርት ስለማድረግ

ኤሲፒኤስ ሁሉም የፀብአጫሪነት ሪፖርቶች ይመረምራል። የፀብ አጫሪነት ክስተት የደረሰባቸው ወይም ለመታዘብ የቻሉ ተማሪዎች ወይም የተማሪዎች ወላጆች/ሞግዚቶች ለትምህርት ቤቱ ኃላፊ ወይም ረዳት ኃላፊ የተባሉትን ክስተቶች ወዲያውኑ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው። አደጋው ሲከተል፣ የሚከተሉት እርምጃዎች ጉዳን ለመድረስ መወሰድ ይገባቸዋል:

1. ስለአደጋው እና ተሳታፊ ወገኖች የሚገልጽ ሪፖርት ማመንጨት።
2. በተሰያሚ ሳይቱ አስተዳዳሪ የሚከናወን ጥለቅ ምርመራ።
3. የሰለባው እና የጥቃት አድራሹ ወላጆች ሁለቱም ስለአደጋው እንዲያውቁ ይደረጋሉ።
4. የሥነ ምግባር እርምጃ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የሚወሰድ ሲሆን ይህም በሳይቱ አስተዳዳሪ የሚፈፀም ይሆናል።
5. የምክር ወይም ሌሎች አዎንታዊ የስነምግባር ጣልቃ ገብነቶች ያስፈልጉ እንደሆነ ለመወሰን ጎጂውን፣ ተጎጂውን እና ተጓዳኞችን ሁሉም ተማሪዎች ተካትተው ይገመገማሉ።

**መስመር ላይ ሪፖርት ማድረግ (Online reporting)**
ልጆች ላይ የተከሰቱ ጥቃቶች (bullying) በኤሲፒኤስ የሞባይል አፕሊኬሽን (ACPS Mobile App) ውስጥ በመጠቆሚያ መስመር (Tip Line) በመጠቀም ለኤሲፒኤስ (ACPS) ሪፖርት ማድረግ ይቻላል። ስምዎን ሳይገልጹ ማድረግ ጥቆማዎን ማስገባት ይችላሉ፣ ነገር ግን በተቻለ መጠን ዝርዝር መረጃዎችን መስጠት ACPS ጥቃቱን

በሚመረምርበት ወቅት ያግዘዋል። የኤሲፒኤስ የሞባይል መተግበሪየን (ACPS Mobile App) ወደ m.acps.k12.va.us በመሄድ ወይም Apple App Store ወይም Google Play መደብር ውስጥ 'Alexandria City Public Schools' ብለው በመፈለግ ስልክዎ ላይ ይጫኑ።

አሌክሳንድሪያ ሴፍ ፕሌስ (Alexandria Safe Place) 24 ሰዓት አገልግሎት የሚሰጥ የአሌክሳንድሪያ ከተማ ጥቃትንና ግጭቶችን ሪፖርት የማድረጊያ ነጻ የስልክ መስመር ነው። ለታዳጊዎች (እድሜያቸው ከ5-18 ሰሆነ) አስቸኳይ እገዛ እና ድጋፍ ለማግኘት በስልክ ቁጥር 703-746-5400 ይደውሉ። ለተጨማሪ መረጃ የአሌክሳንድሪየ ከተማ ድረ ገጽ የሆነውን www.alexandriava.gov ይጎብኙ።

ልጆች ላይ የሚደርስ ጥቃትን በተመለከተ እና እንዴት አጋር መሆን እንደሚችሉ ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት የሚከተለውን ድረ ገጽ ይጎብኙ:- www.acps.k12.va.us/bullying.

የGBA/JFHA ፖሊሲ ተመልከት - የወሲብ ጥቃት/በዘር ፣ የዘር ምንጭ፣ አካል ጉዳት፣ ሃይማኖት፣ አድሜ፣ ፃታ፣ የፃታ ማንነት፣ የፃታ መገለጫ፣ እና የፃታ ፍለጐት መገለጫ ላይ የተመሰረተ ጥቃት / ጠላትነት ስሜት የሰፈነበት፣

# አባሪዎች

| | |
|---|---|
| አባሪ A፡ | የትምህርት ልሕቀትና ፍትሃዊነት |
| አባሪ B፡ | ትክክለኛ የኮምፒውተር ሲስተም አጠቃቀም ፖሊሲ ኤልኤልቢኢኤ/ጂኤቢ |
| አባሪ C፡ | የተማሪዎች የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ፖሊሲ ኤልኤልቢኢቢ |
| አባሪ D፡ | የክብር ኮድ |
| አባሪ E፡ | የተማሪ ስነ ምግባር ፖሊሲና ደረጃ ጄኤፍሲ-አር |
| አባሪ F፡ | የተማሪ እገዳና ስንብት ፖሊሲና ደረጃ ጄጂዲ-አር/ጄጂኢ-አር |
| አባሪ G፡ | ከህግ አስፈጻሚዎች ጋር ያለው ግንኙነት ፖሊሲ ኬኤንኤጂ |
| አባሪ H፡ | እኩል የትምህርት ዕድሎች/ከአድሎ የጸዳ እና የተማሪ መዛግብት/FERPA፣ JB/AC እና JO ፖሊሲዎች |
| አባሪ I፡ | የተማሪ ሕትመቶች፣ ፖሊሲ JP |
| አባሪ J፡ | የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎችን ስነ ምግባር ማስያዝ፣ ፖሊሲ JGDA |
| አባሪ K፡ | ፍተሻ እና በቁጥጥር ስር ማዋል፣ ፖሊሲ JFG |
| አባሪ L፡ | ለተማሪዎች መድሃኒት መስጠት፣ ፖሊሲ JHCD |
| አባሪ M፡ | የተማሪ ድርጅቶች፣ ፖሊሲ IGDA |
| አባሪ N፡ | ሐይማኖት በትምህርት ቤቶች ውስጥ፣ ፖሊሲ INDC |
| አባሪ O፡ | ስለ አወዛጋቢ ጉዳዮች ማስተማር፣ ፖሊሲ INB |
| አባሪ P፡ | የውሲብ መደፈር/ በዘር ፣ ብሄራዊ ማንነት፣ የአካል ጉዳት፣ ሐይማኖት፣ አድሜ ፣ ፃታ፣ የፃታ ማንነት፣ የፃታ መገለጫ እና የውሲብ ምርጫ፣ / አስጨናቂ የስራ አካባቢ የ GBA/JFHA ፖሊሲ |
| አባሪ Q፡ | በትምህርት ቤቶች አልኮል እና ሌላ ድራግ፣ ፖሊሲ JFCF/JFCI |

# አባሪ A፡ የትምህርት ልሕቀትና ፍትሃዊነት

## ፖሊሲ አይጂቢጂ

የአሌክሳንድሪያ ከተማ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎችን ጥራቱን በጠበቀና የትምህርት ፍትሃዊነት በሰፈነበት መልካም ዜጋ እንዲሆኑና ክህሎታቸውንና የወደፊት ህልማቸውን እስከ መጨረሻው ደረጃ እንዲያሳኩ የሚያዘጋጃቸው የትምህርት አካባቢ ላይ ለማስተማር በቁርጠኝነት ይሰራል። ተማሪዎቹ ሲመረቁ ኮሌጅ ለመማር፣ ስራ ለመጀመር ወይም ራሳቸውን ችለው ለመኖር ሊመኙ ይችላሉ። ምንም እንኳን የትምህርት ፍትሃዊነት ማለት ሁሉም ተማሪዎች አንድ አይነት ተሞክሮ ወይም አንድ አይነት ውጤት ይኖራቸዋል ማለት ባይሆንም፤ በኤሲፒኤስ (ACPS) የሚሰጠው ትምህርት በእያንዳንዱ ተማሪ ለሚኖረው ፈተና፣ ፍላጎት እና ችሎታ እኩል ምላሽ ይሰጣል፣ እንዲሁም እያንዳንዱ ተማሪ ለስኬት የሚያስፈልጉት መሳሪያዎች እኩል ይሰጡታል ማለት ነው።

የትምህርት ቤቱ ቦርድ ለተማሪዎቻችን ገንቢና መልካም ህይወትን እንዲመሩ የሚያስችሉ የትምህርት ውጤቶችን እንዲያገኙ የሚያስችሉ አመራሮችንና መሳሪያዎችን ያቀርባል።

ኤሲፒኤስ (ACPS) እያንዳንዱ ተማሪ በፈታኝ ስርዓተ ትምህርት፣ በውጤታማ የትምህርት አሰጣጥ፣ በአሳታፊ ግንኙነት እንዲሁም አካላዊ፣ በስነ ልቦናዊ እና ማህበራዊ ደህንነቱን የሚያበረታታ አካባቢ ሲያገኝ ከፍተኛ የስኬት ደረጃ ላይ እንደሚደርስ ያምናል።

ኤሲፒኤስ (ACPS) ከዚህ በታች ከተመለከቱት መርሆች ጋር የሚጣጣሙ ፖሊሲዎችን፣ መመሪያዎችን እና ስራዎን ያስፈጽማል፡-

- ለእድገት ምላሽ የሚሰጡ የትምህርት ተሞክሮዎች እና ሁሉን አሳታፊ የሆኑ የትምህርት አካባቢዎች ተማሪዎች ከፍተኛ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ይረዳሉ። ኤሲፒኤስ ተማሪዎችን በትምህርታቸው የሚደግፉ የማስተማር ስልቶችን፣ ግምገማዎችንና ሌሎች መሳሪያዎችን የሚያቀርብ ሲሆን መምህራንም እነዚህን ይጠቀማሉ።
- የትምህርት ውጤት በገቢ፣ በዘር፣ በአካል ጉዳተኝነት፣ በጾታ፣ በመጀመሪያ ቋንቋ ወይም በቤተሰብ አይወሰንም።
- ለትምህርት ፕሮግራሞች፣ አገልግሎቶች እና እድሎች ያለው ተደራሽነት በኤሲፒኤስ (ACPS) ፖሊሲዎችና በአካባቢ፣ በግዛት እና በፌዴራል ህጎች ውስጥ ከተመለከቱት መስፈርቶች ውጪ በሌላ ላይ አይመሰረቱም። የኤሲፒኤስ ሰራተኞች እነዚህን ተፈጻሚ የሆኑ የኤሲፒኤስ ፖሊሲዎችን እና የአካባቢ፣ የግዛት እና በፌዴራል ህጎች ማወቅ ይጠበቅባቸዋል።
- ቤት፣ ትምህርት ቤትና ማህበረሰብ ሁሉም ለተማሪው ስኬት ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ።
- ተማሪው የመማር ክህሎቱን ከፍ ማድረግ የሚችልባቸው ፈታኝ የትምህርት ፕሮግራሞችን ቀርጾ ማቅረብ የእያንዳንዱ አስተዳዳሪ፣ መምህርና ሰራተኛ ሃላፊነት ነው።
- አስተዳዳሪዎች፣ መምህራንና ሰራተኞች በጋራ በመስራት ሁሉንም ተማሪዎች የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል የትብብር አርዓያ ይሆናሉ። እያንዳንዱ ሰራተኛ ለሁሉም ተማሪ መማርና ስኬት ሃላፊነት ያለበት ሲሆን ይህንንም ሃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችል ባህል ለመፍጠር ይተጋል።
- ሰራተኞች የፕሮግራም ሃሳቦችን በማቅረብና ከተማሪዎችና ከቤተሰቦቻቸው ጋር የትምህርት እድሎችን በተመለከተ ጥብቅ ግንኙነት በማድረግ ለእያንዳንዱ ተማሪ ስኬታማነት ይተጋሉ።
- አዎንታዊ የትምህርት ውጤት የኤሲፒኤስ ሰራተኞችና የተማሪዎች ሃላፊነት ሲሆን በዚህ ላይ ቤተሰቦችና የማህበረሰብ አባላት ተሳታፊ ይደረጋሉ።
- ተማሪዎቻችን ላይ የምንሰራው ስራ በልጁ ሙሉ ስብዕና ላይ በማተኮር ይመራል።

# አባሪ B፡ ትክክለኛ የኮምፒውተር ሲስተም አጠቃቀም ፖሊሲ

## ኤልኤልቢኢኤ/ጂኤቢ ፖሊሲ

የአሌክሳንደሪያ ከተማ የህዝብ ት/ቤቶችና ሰራተኞቹ ለመማር ማስተማር ስራና ለምርታማነት ቴክኖሎጂን፣ ወጥነትን፣ ሃላፊነትን እንዲሁም ብቃትን ይጠቀማሉ።

የት/ቤቱ ቦርድ ኮምፒውተር ሲስተምና የኢንተርኔት አገልግሎትን በመጠቀም የእያንዳንዱን ተማሪ ስኬት ለማሻሻል ጥረት የሚያደርግ ሲሆን ይህም ሲባል ሃርድዌር፣ ሶፍትዌር፣ ዳታ፣ ኮሚኒኬሽን መስመር እና የስቶሬጅ ሚዲያ፣ ሰርቨሮች፣ ማተሚያዎች እንዲሁም የኢንተርኔት ግንኙነትን መጠቀምን ያጠቃልላል።

ሁሉም የኤስፒኤስ ኮምፒውተር ኔትወርክ አጠቃቀም፡

- ቴክኖሎጂን ከትምህርት ጋር በማቀናጀት ረገድ ሙሉ በሙሉ የኤስፒኤስ ግቦችን መደገፍ።
- ለትምህርት አላማ የሚውለውን ቴክኖሎጂ በሚመለከት የተማሪና የሰራተኞችን መስፈርት መለየት።
- የተማሪዎችን፣ ሰራተኞችን፣ እና ኦፕሬተሮችን ደህንነት ለጉዳት የማያጋልጥ መሆን።
- የአገልግሎት ኪሳራን የማያመጣ።
- ያልተፈቀዱ መሳሪያዎችን የማይጠቀም መሆን አለበት።

የኮምፒውተር አጠቃቀም በጊዜ፣ በይዘትና በግልጋሎት አይነት በአግባቡ ስራ ላይ ሊውል የሚገባ ሲሆን ማንኛውም የኤስፒኤስ ኮምፒውተርን የሚጠቀም ሰው የግል መረጃ ጥበቃ አይደረግለትም።

ሰዎች የኤስፒኤስ መሳሪያዎችን ሲጠቀሙ በላዩ ላይ ላለው ማናቸውም ማቴሪያል ሃላፊነት አለባቸው። ኤስፒኤስ በኮምውተሩ ላይ የሚደረገውን ማናቸውንም እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር መብት ያለው ሲሆን ማናቸውም በኮምፒውተሩ ላይ የሚደረግ እንደ ኢሜይል ልውውጥ ወይም ፋይሎችን የመስራት፣ የማስተካከል፣ የመላክና የማጥፋት ስራ በኤስፒኤስ ሰራተኞች ቁጥጥር ሊደረግበት/ሊከፈትና ሊነበብ ይችላል።

ኤስፒኤስ የቴክሎጂ ውጤቶችን ከዚህ በታች በተመለከተው አግባብ በግል ለማስጠቀም የሚፈቅድበት አሰራር አለው። ይህም ሲባል በኤስፒኤስ ዘንድ፡-

- የቤተሰብ አባላትን ሳይጨምር ለሰራተኞችና ለተማሪዎች በኤስፒኤስ ሃርድዌር፣ ሶፍትዌር፣ ዳታ፣ ኮሚኒኬሽን መስመር እና የስቶሬጅ ሚዲያ፣ ሰርቨሮች፣ ማተሚያዎች እንዲሁም የኢንተርኔት ግንኙነት መጠቀም አይቻልም።
- ድንገተኛ መጠቀም በኤስፒኤስ ላይ የፋይናንስ ሃላፊነትን ወይም ህጋዊ ተጠያቂነትን ማስከተል የለበትም።
- ድንገተኛ መጠቀም ከሰራተኞች የየእለት ስራ ጋር መጋጨት የለበትም።
- የኤስፒኤስ የቴክኖሎጂ ሀብትን ለግል (ኢሜይል፣ ፎቶ፣ ቪዲዮ፣ ሙዚቃ፣ የድምጽ መልዕክት) መጠቀም በአነስተኛ መጠን መሆን አለበት።   እና ስነ ልቦናዊ መረጋጋት የተመለከቱ መረጃዎችን ያጠቃልላል።

ኤሲፒኤስ የግል ፋይልን ለማጠራቀም፣ ለመጠበቅ ወይም ለማስተካከል ሃላፊነት የሌለበት ሲሆን በኢንተርነኔት ደህንነት ረገድ ተማሪዎች ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ኮድ ቁጥር 22.1-70.2 ያዝዛል።

ተቆጣጣሪው ስለ ኮምፒውተር ሲስተም አጠቃቀም ተገቢውን ዝርዝር የያዘ መመሪያ ያወጣል።

ይህ መመሪያም የሚከተሉትን ያካትታል፡-

- የዲቪዥን ሰራተኞች እና ተማሪዎች የዲቪዥኑን የኮምፒውተር መሳሪያ እና የኮሚውኔኬሽን አገልግሎት ህገ ወጥ ነገሮችን ለመላክ፣ ለመቀበል፣ ለመመልከትና ለማውረድ አይችሉም። የኮፒ ራይትና ቅጂ ህጎችን ተመልከቱ። [በ www.acps.k12.va.us/policies-E ላይ ፖሊሲ EGAAAን ይመልከቱ]፤
- የዲቪዥን ኮምፒውተሮችን በመጠቀም ረገድ ይዘትን የሚያጣሩ ወይም የሚገድቡ አሰራሮችን ማቋቋም፤ ይህም የሚያካትተው (ሀ) በኮድ 18.2-374.1.1 ወይም በክፍል 18 ዩኤስሲ 2256 መሰረት የህጻናት ወሲባዊ ፊልም/ስእል ለ) በኮድ 18.2-372 ወይም በክፍል 18 ዩኤስሲ 1460 መሰረት ህገ ወጥ ተግባሮችን እና ሐ) በኮድ 18.2-390 በተመለከተው አግባብ የትምህርት ቤቱ ዲቪዥን ጎጂ ብሎ የሚፈርጃቸውን ድርጊቶች እና በሌላ አግባብም አካለመጠን ላላደረሱ ልጆች በክፍል 47 ዩኤስሲ 254 (ኤች)(7)(ጂ) መሰረት ጎጂ የሚባሉ ድርጊቶች ይካተታሉ።
- በኤሲፒኤስ ኮምፒውተሮች አጠቃቀም የቴክኖሎጂ ልኬት መመሪያ ተግባራዊ እንደሚሆን የሚገልጽ ድንጋጌ።
- የኦንላይን ድርጊቶች ቁጥጥር ሊደረግባቸው እንደሚገባ የሚገልጽ ድንጋጌ።
- ተማሪዎችና ሰራተኞች ሜይል፣ ቻት ሩም እና ሌላ አይነት ቀጥተኛ የኤሌክትሮኒክ ግንኙነት ሲያደርጉ ተገቢውን ጥበቃ የሚያደርግና የሚደግፍ ድንጋጌ።
- አካለመጠን ያላደረሱ ህጻናት ያልተፈቀደ የኦንላይን አክሰስን እንዳያደርጉ የሚከለክልና ሀኪንግና ሳይበር ቡሊይንግን የሚያግድ ድንጋጌ።
- ስለ ተማሪዎችና ሰራተኞች ግላዊ የሆነ መረጃን ከማሰራጨት የሚያግድ ድንጋጌ።
- የኤሲፒኤስ ሰራተኞች ከተማሪዎች ጋር ግንኙነት ሲደርጉ በኤሲፒኤስ ኤሌክትሮኒክ አካውንት እንዲጠቀሙ የሚያዝዝ ድንጋጌ።

የኤሲፒኤስ ኮምፒውተር ሲስተም ህዝባዊ ፎረም አይደለም።

የኤሲፒኤስ ኮምፒውተር ሲስተምን ከመጠቀም በፊት እያንዳንዱ ተማሪ፣ ሰራተኛ እንዲሁም እያንዳንዱ ተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ ሃላፊነት የተሞላ የኮምፒውተር ሲስተም አጠቃቀም ፖሊሲን መፈረም አለበት። ይህንን ፖሊሲ ያለማክበር የኮምፒተር አጠቃቀም ጥቅማ ጥቅሞችንና ድጋፎችን ያሳጣል፤ የህግ እርምጃም ያስወስዳል።

በኢንተርኔት ላይ ለሚተላለፍ ማናቸውም አይነት መረጃ መጥፋት ወይ መበላሸት የአሌክሳንደሪያ ከተማ ት/ቤቶች ቦርድ ሃላፊነት አይወስድም።

የት/ቤቱ ቦርድም በዚህ አገልግሎት ላይ በሶስተኛ ወገኖች ያለ አግባብ የሚጠየቅ ክፍያን በሚመለከት ምንም ሃላፊነት የለበትም።

ተቆጣጣሪው ይህንን ፖሊሲና አጃቢ ሰነዶችን ለቨርጂኒያ ግዛት የትምህር ዲፓርትመንት ማቅረብ አለበት።

# አባሪ C፡ የተማሪዎች የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም

## ፖሊሲ ኤልኤልቢኢቢ-1

የአሌክሳንደሪያ ከተማ የህዝብ ት/ቤቶች በተማሪዎች ዘንድ ብቃትን ለመፍጠርና ተማሪዎችን ለከፍተኛ ትምህርት፣ ብቁ ዜግነት እና የስራ ሀይልነት ለማብቃት ሲባል ቴክኖሎጂን በጤናማ እና ሃላፊነት ባለበት መንገድ መጠቀምን ይፈቅዳል።

ኤሲፒኤስ ትምህርትና ምርምርን በማጠናከርና በማበረታታት አግባብ የተረጋገጡ ማህበራዊ ሚዲያዎች በጥቅም ላይ እንዲውሉ ድጋፍ ያደርጋል። ተማሪዎቹንም ቴክኖሎጂን በጤናማ እና ሃላፊነት ባለበት መንገድ ስለ መጠቀም ያስተምራል። የኤሲፒኤስ ተማሪዎች የቴክኖሎጂ መገልገያዎችን ሃላፊነታቸውን በአግባቡ ለመወጣትና ከሌሎች ተማሪዎችና ከሰራተኞች ጋር በብቃት ግንኙነት ለማድረግ ይጠቀሙባቸዋል።

ለዚህ ፖሊሰ አላማ ማህበራዊ ሚዲያ ማለት ዌብ ሎጎን፣ ብሎግን፣ ዊኪን፣ ማህበራዊ መረቦችን፣ ኦንላይን ፎረሞችን፣ ቨርቹዋል ወርልድን እና ሌሎች ለህዝብ ክፍት ሆኑ ማህበራዊ ድረገጾችን ያጠቃልላል።

### ማህበራዊ ሚዲያን ለትምህርትና ለተገቢ ግልጋሎት መጠቀም

በዲቪዥኑ በቅድሚያ ከተፈቀዱ ውጭ የሆኑ ኦንላይም ማህበራዊ ሚዲያዎች በተቆጣጣሪው አካል በቅድሚያ ፈቃድ ካልተሰጠባቸው በቀር በትምህርት ላይ ወይም በትምህርት ቤት ውስጥ በተሰናዳ ኩነት ላይ ጥቅም ላይ ሊውሉ አይችሉም። ፈቃድ ቢሰጥም ተቆጣጣሪው አካል የአድሚኒስትሬተር አክሰስ ሊሰጠው ይገባል።

ኤሲፒኤስ የግልጽ ግንኙነትን እና ሀሳብን የመለዋወጥን ዋጋ እውቅና የሚሰጥ በመሆኑ ተማሪዎችም ቴክኖሎጂን በጤናማ እና ሃላፊነት ባለበት መንገድ ሊጠቀሙ ይገባል።

በመማር ማስተማር ላይ ፊት ለፊት እንዳይደረጉ የተከለከሉ እንደ ትንኮሳና ያልተገባ ቃል መጠቀም የመሳሰሉ ተግባራት በማህበራዊ ሚዲያ ግንኙነት ላይም ክልክል ናቸው። በተማሪዎችና መካከል ወይ ከሰራተኞች ጋርና በሰራተኞች መካከል የሚደረግ ኦን ላይን ግንኙነት በይዘትም ሆነ በድምጸቱ ተገቢ መሆን አለበት

### ማህበራዊ ሚዲያን ለግል መጠቀም

ሁሉም የኤሲፒኤስ ተማሪዎች የትምህርት ቤቶቻችን ተወካይና ሞዴል መሆናቸውንና በማህበረሰቡ ውስጥም ለሌሎች ተማሪዎች አርአያ ሊሆኑ እንደሚገባ ጠንቅቀው ማወቅ ይገባቸዋል። ተማሪዎች የሀገሪቱን ህጎች የሚጻረሩ ወይም በመማር ማስተማር ሒደቱ ላይ አሉታዊ ውጤት የሚፈጥሩ ነገሮችን ፖስት ከማድረግ ወይም በዚህ መሰል ግንኙነቶች ውስጥ ተሳታፊ ከመሆን መቆጠብ አለባቸው።

### ይህንን ፖሊሲ ያለማክበር

ይህንን ፖሊሲና መመሪያውን ያለማክበር የኮምፒውተር ተጠቃሚነትን ለማጣትና ለስነ ምግባር እርምጃዎች ሊያበቃ ይችላል።

ተቆጣጣሪው ይህንን ፖሊሲ የሚደግፍ መመሪያ ማውጣት አለበት

---

# አባሪ D፡ የክብር ኮድ

---

ኤሲፒኤስ ተማሪዎቹን፣ ፋኩሊቲውን እና አመራሩን ጨምሮ በትምህርት ዘመን ሁሉ ክብር ያለው ጠባይን ለማስጠበቅ የሚተጋ ሲሆን ህብራችን የጋራ መግባባትን ለማረጋገጥ ሲባል አክብሮትን የተመላ መግባባትን ይላበስ ዘንድ አንዳችን ከሌላችን ጋር በሚኖረን ግንኙነት ሁልጊዜም መልካ ጠባይ ሊኖረን ይገባል።

የምንተጋለት ክብር እጅግ ጠቃሚ የሆነው አንድ ይዘት ቢኖር በትምህርት ላይ የሚፈጸም የመኮረጅና ሌላ አይነት የማጭበርበር ተግባር ሲሆን በዚህ የተነሳም ተቀባይነት የሌላቸውና የክብር ኮድን የሚጥሱ ብለን ያስቀመጥናቸውን ጠባዮች ከዚህ በታች አስቀምጠናል።

## I. የክብር ኮድ አላማ

- ይህ የክብር ኮድ ከትምህርት ቤቱ ቦርድ ፖሊሲ ጋር የሚጣመር ሲሆን በፖሊሲው መሰረትም ተማሪው የመማር ማስተማሩ ሒደት ማእከል በመሆኑ ተማሪዎች ለትምህርታቸው ሃላፊነት ሊወስዱ ይገባቸዋል። ተማሪዎች ከመምህሩና ከአቻዎቻቸው ጋር በትብብር በመስራት ለውይይትና ለክፍል ስራ አስተዋጽኦ ማድረግ አለባቸው። ሁሉንም የቤት ስራ በመምህሩ ትዕዛዝ፣ የማስረከቢያ ጊዜና የግምገማ መስፈርት መሰረት ማከናወን የሚገባቸው ሲሆን የሚጠበቀው ውጤት ካልመጣ ስራዎችን በድጋሚ መከለስ ይገባቸዋል። እንደ ሒደቱ አንድ አካል ተማሪዎች የራሳቸውን እድገት በመከታተል ረገድ ንቁ ሚና ይኖራቸዋል።
- ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሒደት ተጠያቂ የሚሆኑበትን ደረጃና የሚጠበቅ ግምት ማስቀመጥ አስፈላጊ እንደሆነ እናምናለን።
- የኤስፒኤስ የትምህርት ቤት ቦርድ ፖሊሲዎችን ከአምስቱ የከፍተኛ ውጤት የኮሌጅ ተወዳዳሪነት መስፈርቶች ጋር ጎን ለጎን ለማስኬድ በምናደርገው ጥረት ተማሪዎች ከትምህርታዊ ጥፋቶች ጋር የተያያዙ ድርጊቶችን ይህም ማጭበርበርን እና ኩረጃን እንዴት ማስወገድ እንደሚገባቸው መመሪያ ሊሰጣቸው ያስፈልጋል።
- የኮሌጅና ስራ ዝግጁነትን መንፈስ በመፍጠር ረገድ የኤስፒኤስ ማህበረሰብ ተማሪዎችን በስነ ምግባር ረገድ በስራቸው ዝግጁ እንዲሆኑ ማድረግ የፋኩሊቲው እና የአመራሩ ሃላፊነት እንደሆነ ያምናል።
- በተጨማሪም ተማሪዎች በኤስፒኤስ ትምህርት ቤቶች ደረጃ የሚጠበቀውን የተጠያቂነት ደረጃ ማዳበር እንደሚገባቸው እናምናለን። እጅግ ዝግጁ የሆኑና ከኤስፒኤስ ግምት በላይ የሚሄዱ ተማሪዎችን ለማፍራት ጥረት የምናደርግ ሲሆን ይህንን ጥረት ያለመደገፍ ከስራ መሰናበትን ሊያስከትል ይችላል።

## II. ኩረጃ

የኤስፒኤስ የስነ ምግባር ደንብ እንደሚከተለው ይደነግጋል፡-

- የአሌክሳንደሪያ ከተማ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች የራሳቸውን የስራ ውጤት በማቅረብ ረገድ ታማኝ መሆን አለባቸው። ለሌሎች ሙብትም ክብር ማሳየት አለባቸው።
- ተማሪዎች ማጭበርበር፣ ወይም ሆን ብለው ከማንኛውም ፈተናና የቤት ስራ ጋር በተያያዘ ሀሰተኛ መረጃ ማሰራጨት አይገባቸውም።

## III. ማጭበርበር

- ማጭበርበር ማለት 1) የሌላን ሐሳብ እንደ ራስ አድርጎ መስረቅ ወይም መውሰድ 2) ምንጩን ሳይጠቅሱ ሌላ ማቴሪያንልን መጠቀም 3) የአእምሮ ውጤትን መስረቅና እንደ አዲስ አድርጎ ወይም አስመስሎ ማቅረብ ነው።
- ይህ ተግባር የቤት ስራዎችን መግዛት ወይም በሌላ ሰው ማሰራትን ያጠቃልላል።
- አንድ ተማሪ የራሱ ያልሆነውን ስራ የእኔ ነው ብሎ ካለ የክብድ ደንቡን የመጣስ ተደርጎ ይቆጠራል።

## IV. ኩረጃ ማለት

- ኩረጃ ማለት መልስ ለሌሎች መስጠት፣ የቤት ስራ መቅዳት፣ ፈተና ከሌላ ሰው መኮረጅ፣ የመምህሩን ማቴሪያል እና ተመሳሳይ ፈተናን ከሌላ መኮረጅ ማለት ነው።

## V. የመምህሩ ግምት

- መምህራን በማጭበርበርና በመከላከያው እንዲሁም በሚያስከትለው ውጤት ዙሪያ ተማሪዎችን እንዲያስተምሩና ዘወትር እንዲያስገነዝቡ ይጠበቃሉ።
- ማጭበርበርን ለመከላከል የቲሲ ዊልያምስን ላይብረሪ ድረ ገጽ መጠቀም ይቻላል። www.acps.k12.va.us/plagiarism

## VI. የተማሪ ማረጋገጫ

- በእያንዳንዱ አመት የእያንዳንዱ ኮርስ መጀመሪያ ላይ ተማሪዎች ከክብር ኮድ ጋር የሚስማሙ ስለመሆናቸው ማረጋገጫ ይሰጣሉ ይህም ኮዱን ያለማክበር የሚያመጣውን ውጤት የሚረዱ መሆናቸውን መግለጽንም ያጠቃልላል። ይህንን ማረጋገጫ በቃልም ሆነ በጽሁፍ ከተማሪዎች ለማግኘት የሚቻልበትን አሰራር እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ይቀርጻል፡
- በክብር ኮድ ላይ ያለው ማናቸውም ይዘት ከእያንዳንዱ ፈተና፣ ወረቀትና ሌላ ፕሮጀክት ማስረከቢያ እለት በፊት በዚህ ሰነድ ላይ የተመለከቱትን ደረጃዎች ከማሟላት አያግድም። ይህንን መሰል ማረጋገጫ ያስፈልግ እንደሆን የሚሰጥ ውሳኔ ከት/ቤቱ ፕሪንስፓል ጋር በመተባበር በአካዳሚክ ማህበረሰብ የሚሰጥ ይሆናል።

## VII. የተፈጻሚነት ቀን

ይህ የክብር ሰነድ ከጃንዋሪ 5/2015 አንስቶ ተፈጻሚ ይሆናል።

## VIII. የክብር ኮድ ስነ ስርዓቶች

የማጭበርበር ስራ ሲፈጸም ወይም ኩረጃና ፈተና መቅዳት ወይም ያለ መምህሩ ፈቃድ አስተርጓሚ ሶፍትዌር የመጠቀም ሁኔታ ሲኖር ከዚህ በታች የተመለከቱት ውጤቶች ይከተላሉ፡

***የመጀመሪያ ጥፋት***
*መምህሩ የሚከተለውን ነገር ያደር ጋል፡*

- የተፈጸመውን ተግባር በሚመለከት ከልጁ ወላጆች ጋር ተገናኝቶ ይነጋራል።
- ጉዳዩን ለሚመለከተው ዲን/ሃላፊ ያስተላልፋል።
- ጉዳዩን ለምልከታና በተፈጻሚ አሰራሮች መሰረት ለቅጣት ሲል ወደ ተገቢው የክብር ሶሳይቴ ያስተላልፋል።

*ተማሪው የሚከተለውን ነገር ያደርጋል፡*

- በፈተና ላይ ዜሮ ካገኘ ምንም አይነት የማካካሻ እድል አይኖረውም።
- ላለፈው ጊዜ እንደ ክብር ሮል የመሰለ የትምህርት ውጤት እድል ያጣል።

***ተደጋጋሚ ጥፋት***
*መምህሩ የሚከተለውን ነገር ያደርጋል፡*

- ተማሪው ለፈጸመው ተግባር ለወደፊት የሚያገኘውን የማካካሻ ክፍለ ጊዜ መከልከል የሚችል ሲሆን ተማሪው ግን ሌሎች ስራዎችን በፈተና መመዘኛ ፖሊሲዎች መሰረት ለመመልከት ይችላል።
- ከስራው ጋር በተያያዘ ተማሪው ሊያገኘው የሚችለው እድል መከልከል።
- ይህንን ጉዳይ ስለ ተማሪው በመሆን በተለያዩ ግንኙነቶችና ማመልከቻዎች ላይ ማካተት

የመጀመሪያ ጥፋት በሚለው ስር ከተመለከቱት በተጨማሪ ከዚህ የሚከተሉት ነገሮች ሊከተሉ ይችላሉ፡-

- እስከ አንድ ሳምንት ድረስ ተማሪው ከስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች ሊታገድ ይችላል። ይህም ሲባል ልምምድን፣ ውድድርን እና ሌሎች ከትምህርት ውጪ የሆኑ እንቅስቃሴዎችን ያጠቃልላል።
- ተማሪው ማንኛውንም የተማሪ ጽ/ቤት ቦታ ሊለቅቅ ይችላል።
- ተጨማሪ ጥፋት ሲፈጸም በውጤቱ ተማሪው ከስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችና ከማንኛውም የተማሪ ጽ/ቤት ቦታ መነሳትን ሊያጠቃልል ይችላል።
- አስተዳደሩ ከላይ ከተመለከቱት በተጨማሪ የስነ ምግባር እምጃዎችን ሊያካትት ይችላል።

**ይግባኞች**

የክብር ደንብን በመጣስ የተከሰሰ ተማሪ የተጣለበትን ቅጣት ለፕሪንሲፓሉ ይግባኝ ሊል ይችላል። ፕሪንሲፓሉም ጉዳዩን ሊመለከት ወይም ለሌላ ይህንን ጉዳይ ለመመልከት ስልጣን ላለው አካል ወይም ቦርድ ሊያስተላልፍ ይችላል። በትምህርት ቤቱ ደረጃ ያለው የይግባኝ ሂደት የመጨረሻ ይሆናል።

# አባሪ E፡ የተማሪ ስነ ምግባር ደረጃ

## ፖሊሲ ጄኤፍሲ-አር

ከዚህ በታች ያሉት ደረጃዎች ለሁሉም ተማሪዎች ተብለው በት/ቤቱ ቦርድ የወጡ ናቸው። ቅጣት የሚወሰነው በእያንዳንዱ ጥፋት ስር በሚቀርበው ፍሬ ነገር ላይ ተመስርቶ በቦርዱ፣ ቦርዱ በሚሰይማቸው ኮሚቴዎችና በሌሎች የት/ቤቱ ባለስልጣናት ነው።

### 1. ጥናትን መተው

ተማሪው በወጥነት ወይም በሌላ አግባብ የትምህርት ቤት ስራውን ቸል ማለት ወይም በት/ቤቱ የሚሰጡትን የመማር እድሎች መተው የለበትም።

### 2. አለባበስ

የተማሪው አለባበስ ሌሎች ተማሪዎችን ትምህርታቸውን ከመከታተል የሚያውክ ወይም የጤናና ደህንነት ስጋት ወይም ችግር የሚፈጥር መሆን የለበትም።

### 3. ያለ ምክንያት ማርፈድ ወይም መቅረት

ተማሪዎች ወላጅ ወይም ትምህርት ቤቱ ሳይፈቅድ ወይም ሌላ ምክንያት ሳይኖራቸው ከትምህርት መቅረት ወይም ማርፈድ ለባቸውም።

አንድ ተማሪ በአመት ውስጥ ለአምስት ቀናት ያህል ሲቀር፣ የዚህም ምክንያት በተማሪው ወላጅ ሳይብራራ ሲቀርና የተማሪው ወላጅ ይህንኑ አያውቅም ተብሎ ሲታሰብ የት/ቤቱ ማህበራዊ ሰራተኞች በአካል ወይም በስልክና በተለያየ የመገናኛ መንገድ ከተማሪው ወላጅ ጋር በመገናኘት ይህንን ለማሳወቅና ማብራሪያ ለማግኘት ጥረት ያደርጋሉ።

ተማሪው ከትምህርት እንዳይቀር የት/ቤቱ ፕሪንሲፓል፣ ማህበራዊ ሰራተኛ፣ ተማሪውና የተማሪው ወላጆች የጋራ ጥረት ያደርጋሉ። ተማሪው ከተደረገው ጥረት በኋላም ከትምህርት ከቀረና የት/ቤቱ ማህበራዊ ሰራተኛ የተማሪው ወላጆች መቅረቱን እንደማያውቁ ካሰበ በሚመለከታቸው የት/ቤቱ ሰራተኞችና በተማሪው ወላጆች መካከል የጋራ ውይይት ይጠራል። ከዚህም በኋላ ተማሪው ለወላጅ ሳያሳውቅ ከቀረ የትምህርት ቤቱ ፕሪንሲፓል ወይም ማህበራዊ ሰራተኛው ለፍርድ ቤት በማሳወቅ የሚከተለውን ሊያደርግ ይችላል፡-

1. ተማሪው ልጅና ቁጥጥር የሚፈልግ መሆኑን ገልጾ ለወጣቶች እና የአካባቢ ግንኙነት ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ።
2. ትምህርትን ቸል በማለት ለልጁ ወላጆች ዋራንት መስጠት።

ከ 18 አመት በታች የሆነው ተማሪ ለ10 ተከታታይ ቀናት ከትምህርት ገበታው ከቀረ የት/ቤቱ ፕሪንሲፓል በጄኢዲ ፖሊሲ መሰረት የተማሪው መንጃ ፈቃድ ይታገድ ዘንድ ወጣቶች እና የአካባቢ ግንኙነት ፍርድ ቤት አቤቱታ ያቀርባል።

### 4. የረብሻ ጠባይ

ተማሪዎች በማንኛውም የመማር ማስተማር ሒደትን በሚጎዳና ለጤናና ሰላም አዋኪ በሆነ ተግባር ውስጥ መሳተፍ አይገባቸውም።

### 5. ያልተገባ ንግግር መጠቀም

ተማሪዎች የመማር ማስተማር ሒደትን የሚጎዳና አግባብ ያልሆነ ንግግርን/ቋንቋን መጠቀም የለባቸውም።

### 6. ዛቻ/ማስፈራራት

ተማሪዎች በቃል፣ በጽሁፍ ወይም በአካላዊ ድርጊት በሌላ ሰው ላይ አንዳች የማስገደድ ተግባር ለመፈጸም በማሰብ የማስፈራራትና የዛቻ ተግባር ከመፈጸም መቆጠብ አለባቸው።

### 7. ድብደባ

ተማሪዎች የመማር ማስተማር ሒደትን የሚጎዳና አግባብ ያልሆነ ንግግርን/ቋንቋን መጠቀም የለባቸውም።

ተማሪዎች በአካል ወይም በሌላ አይነት መሳሪያ በመጠቀም በሌላ ሰው ላይ ያለ ፈቃዱ ንክኪ በመፈጸም ጉዳት ማድረስ የለባቸውም።በፈቃደኝነት የተደረገ ጥል የአካል ጉዳት ቢያመጣ እንደ ድብድብ ይቆጠራል።

ድብደባና ጥቃት ሲባል ጉዳት የሌለውን ወይም አነስተኛ ጉዳት የሚያመጣን ወይም ከባድ ጉዳት የሚያስከትን አካላዊ ጥቃትን የሚያጠቃልል ሲሆን መምታት፣ መጎተት፣ መገፍተር፣ እና መተናነቅን ያጠቃልላል።

ድብደባ ያልተገባ ሃይልን በሌላ ሰው ላይ መጠቀም ማለት ነው።

## 8. ትንኮሳ

ማንኛውም ተማሪ በተናጠልም ሆነ በቡድን በቃል ወይም እንደ ኮምፒውተር ሲስተም፣ ስልክ፣ ኢንተርኔት ወይም ኤሌክትሮኒክ መልዕክቶችን በመጠቀም የቃል ወይም ጽሁፍ ማስፈራሪያ በመስጠት፣ በስድብ፣ ስም በመጥራት፣ በመተረብና የእነኚህን ድርጊቶች ስብጥር በመፈጸም ሌላ ተማሪን ወይም ተማሪዎችን ማጥቃት/መተንኮስ የለበትም። የተከለከሉ ድርጊቶች በጾታ፣ በዘር፣ በቀለም ወይም በአመጣጥ የተመሰረቱ ትችቶች እና ስድቦችን ያጠቃልላል።

## 9. ቁማር

ማንኛውም ተማሪ በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ወይም በትምህርታዊ ተግባር ላይ በአንዳች ያልታወቀ ውጤት ባለው ውድድር ላይ ገንዘብን ወይም ሌላ ዋጋ የሚያወጣ ነገርን በውርርድ በማስያዝ በሚፈጸም ቁማር ላይ መሳተፍ የለበትም።

## 10. አልኮል፣ ትንባሆና ሀሺሽ መጠቀምና/ይዞ መገኘት፡

ተማሪዎች በትምህርት ቤትና በአውቶብስ ውስጥ እንዲሁም ከትምህርት ቤቱ ግቢ ውጪም ቢሆን አልኮል፣ ትንባሆና ሀሺሽ መጠቀም/ይዞ መገኘት አይችሉም። ይህም ጭስ አልባ ሲጋራን፣ ያልተፈቀዱ መድሃኒቶችን ከጄኤችሲዲ ፖሊሲ ጋር በተጣጣመ መልኩ ለተማሪዎች ያልተሰጡ የሃኪም ትእዛዝ እና ያለሃኪም ትእዛዝ መድሃኒቶች እና እጾችን በውስኑ ያጠቃልላል።

ተማሪው በመመሪያው ላይ የተከለከሉትን ንጥረ ነገሮች እንዲሁም አልኮል፣ ትንባሆና ሀሺሽ መግዛት፣ መሸጥ፣ መጠቀምና ይዞ መገኘት አይችልም።

ይህ መመሪያ የጄኤፍሲኤፍ ፖሊሲን ያጠቃልላል።

የተከለከሉ ንጥረ ነገሮች አልኮል፣ ማሪዋናን፣ እጾችን፣ ማነቃቂያዎችን እንዲሁም ማናቸውንም በመመሪያውና በተገቢ ህጎች ላይ የተመለከቱ ነገሮችንና በሐኪም ትዕዛዝ ተፈቅደው ካልሆነ በቀር ሊወሰዱ የማይገባቸውን መድሀኒቶች ያጠቃልላል።

ሌሎች የሚከተሉ ውጤቶች እንደተጠበቁ ሆነው የት/ቤቱ ስፖርተኛ የሆነ ተማሪ በሐኪም ትዕዛዝ ተፈቅዶለት ካልሆነ በቀር አደንዛዥ እጽ መጠቀሙ በተቆጣጣሪውና በዳይሬክተሩ ከተረጋገጠ ለሁለት ተከታታይ አመታት ከውድድር ይታገዳል።

## 11. እጽን ለመሸጥ በማሰብ ይዞ መገኘት ወይም መሸጥና ማከፋፈል

ተማሪዎች በመድሀኒት ቁጥጥር ህግ፣ ምእራፍ 15.1 ርእስ 54 ቨርጂኒያ ኮድ ላይ እንደተጠቀሰው በህገ ወጥ አግባብ ያልተፈቀዱ መድሃኒቶችንና ንጥረ ነገሮችን ማምረት፣ መግዛት፣ ማብቀል፣ ማጓጓዝ ወይም ማስገባት አይፈቀድላቸውም።

## 12. ንብረት ማውደም

ተማሪዎች እያወቁ ወይም በተንኮል መንፈስ ተነሳስተው የትምህርት ቤቱን ህንጻ ወይም ሌላ አይነት ንብረት ሆን ብሎ ከመጉዳትና በትምህርት ቤቱ ውስጥ የሚገኝ ንብረትነቱ የሌላ ሰው የሆነን ማናቸውንም ዋጋ የሚያወጣ ዕቃ ከመጉዳት መቆጠብ ይገባቸዋል።

## 13. የትምህርት ቤት ባለስልጣናትን መጣስ፡

የትምህርት ቤት ባለስልጣናት በቦርዱ የተሰጣቸውን ስልጣን መሰረት በማድረግ የሚያስተላልፉትን የቃላትና የጽሁፍ መመሪያ ተማሪዎች ማክበር አለባቸው።

## 14. የጦር መሳሪያና ሌሎች አደገኛ ነገሮችን መያዝ፡

ተማሪዎች ምንም እንኳን ተቀባይነት ያላቸው ነገሮች ናቸው ቢባሉም ማናቸውንም የጦር መሳሪያና ሌሎች አደገኛ ነገሮችን ይዘው መገኘት አይችሉም።

## 15. ስርቆት

ተማሪዎች የሌላ ተማሪን ንብረት በሃይል ወይም በሌላ አግባብ ያለ ፈቃዱ መውሰድና የራስ የማድረግ ተግባር መፈጸም የለባቸውም።

## 16. በትምህርት ቤት መጓጓዣ አውቶቡስ ላይ የሚታይ ጠባይ፡

ተማሪዎች  የትምህርት ቤት መጓጓዣ አውቶቡስ ሲጠብቁ፣ ተሳፍረው ሲሄዱ ወይም ሲወርዱ በመልካም ጠባይ ላይ መገኘት አለባቸው።

## 17. ኩረጃ

ተማሪዎች መልስ ለሌሎች መስጠት፣ የቤት ስራ መቅዳት፣ ሌላ የቤት ስራን ወይም የመምህሩን መምሪያና ማቴሪያሎች መቅዳት የለባቸውም።

## 18. መተላለፍ

ያልተፈቀደላቸው ሰዎችና የታገዱ ተማሪዎች ያለ ምንም ጉዳይና ያለ አንዳች ፈቃድ ወደ ት/ቤቱ ቅጥር ግቢ መግባት ወይም በቅጥር ግቢው ውስጥ መቆየት አይችሉም።

## 19. የውንብድና ተግባር፡

ተማሪዎች በጂኤፍሲኤ ፖሊሲ መሰረት በተመለከተው የውንብድና ተግባር ላይ መሳተፍ የለባቸውም፡

## 20. ጥቃት

ማንኛውም ተማሪ በሌላ ተማሪ ወይም በትምህርት ቤቱ ሰራተኛ ላይ ወይም በበጎ ፈቃድ መምህራንና የተማሪ መምህራን ላይ የጂኤፍኤችኤ/ጂቢኤ ፖሊሲን በመጻረር በዘር፣ በጾታ፣ በአመጣጥ፣ በዜግነት ወይም በሃይማኖት ላይ ተመስርቶ በት/ቤቱ ግቢ ውስጥ ጥቃት መፈጸም አይገባውም።

## 21. ቢፐር፣ ሞባይል ስልክ፣ የግል ፒዲኤ ወይም ተመሳሳይ የግንኙነት መሳሪያዎችን ይዞ መገኘት፡

ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ እና በትምህርት ቤቱ አውቶቡስ ውስጥ በትምህርት ላይ አብርተው የማይጠቀሙበት እስከሆነ ድረስ ቢፐር፣ ሞባይል ስልክ፣ የግል ፒዲኤ ወይም ተመሳሳይ የግንኙነት መሳሪያዎችን መያዝ ይችላሉ። ተማሪው በዚህ ሰነድ ከተፈቀደው ውጪ ሌላ ነገር ይዞ ቢገኝ ከሚወሰድበት የስነ ምግባር እርምጃ በተጨማሪ እቃውን ሊቀማና ለወላጅ ተመላሽ ሊደረግበት ይችላል።

## 22. የቴክኖሎጂ ግልጋሎት

ተማሪዎች ቴክኖሎጂን መርሆች ማክበር አለባቸው። ይህንን መመሪያ በሚጻረር አግባብ ቴክኖሎጂና ኔትወርክን መጠቀም የተከለከለ ሲሆን ተማሪዎች በኤሲፒኤስ መመሪያዎች መገዛት አለባቸው።

## 23. በክፍል 16.1.305.1 መሰረት የወንጀል ፍርድ ወይም የወንጀል ክልከላ፡

ተቆጣጣሪው በክፍል 16.1.305.1 መሰረት የወንጀል ፍርድ ሪፖርት ወይም በቨርጂኒያ የወንጀል ኮድ መሰረት በተጨማሪም በ ቪኤ ኮድ ክፍል 16.1-260 ላይ የተጠቀሰውን ጥፋትበአንድ ተማሪ ላይ የወንጀል ክልከላ ሪፖርት ሲደርሰው ተማሪውን ሊያግደው ወይም ሊያባርረው ይችላል።

24. ሌዘር ፖይንተር

ተማሪዎች ሌዘር ፖይንተሮችን ይዘው መገኘት አይችሉም።

## 25. የቦምብ ዛቻ

ተማሪዎች የቨርጂኒያን ህጎች በሚጥስ አግባብ ማንኛውም የሚፈነዳና የሚቀጣጠል መሳሪያ ይዘው መገኘት የለባቸውም። በተጨማሪም በትምህርት ቤት ቦምብ እንደሚፈነዳ በመግለጽ ማንኛውንም አይነት ዛቻ ወይም ማስፈራራት ከማድረግ መቆጠብ አለባቸው።

## 26. የወንጀል ክስ

በወንጀት ጥፋት የተከሰሱ ተማሪዎች የስነ ምግባር እርምጃ ይወሰድባቸዋል ወይም በመከላከል/ኢንተርቬሽን ተግባር ተሳታፊ እንዲሆኑ ይደረጋል።

## 27. ሌላ ምግባር

በዚህ ሰነድ ከተገለጹት ውጪ ተማሪዎች በሌላ አይነት የመማር ማስተማርን ሒደት በሚያደናቅፍ ወይም የፌዴራልና የግዛቱን ህጎች በሚጎዳ ተግባር ላይ መሳተፍ የለባቸውም።

## 28. የሃይል ተግባር

ተማሪዎች ከሃይል ተግባር መቆጠብ አለባቸው

ይህ ማለት በአንድ ቡድን ወይም ህብረት ውስጥ ለመቀላቀልና ይሁንታ ለማግኘት እንዲሁም ከበሬታንና የበላይነትን ለማረጋገጥ ሲባል በጤንነትና ደህንነት ላይ ጉዳት በሚያደርስ አኳኋን በተማሪ ወይም በተማሪዎች ላይ አካላዊ ጉዳት ማድረስ ማለት ነው። የትምህርት ቤቱ ፕሪንሲፓል ይህንን መሰል የሃይል ተግባር ሲፈጸም ጉዳዩን ለአካባቢው የጋራ ብልጽግና ባለስልጣን ያሳውቃል። ከላይ የተመለከተው ተግባር በ12 ወራት እስራትና በ2500 ዶላር የገንዘብ ቅጣት ሊያስቀጣ የሚችል ሲሆን በዚህ ፖሊሲም የስነ ምግባር እርምጃ ሊያስወስድ ይችላል። ጉዳት የደረሰበት ማንኛውም ሰው በህጉ ክፍል 18.2.56 መሰረት ለደረሰበት የአካል ጉዳት ከአጥፊው ላይ ካሳ መጠየቅ ይችላል።

## የእርምት እርምጃዎች

የትምህርት ቤቱ አስተዳደር የተማሪዎች የስነ ምግባር ደንብ ጥሰት ሲፈጸም የሚከተሉትን የእርምት እርምጃዎች ሊወስድ ይችላል። ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ እያንዳንዱ ጥፋት ሙሉ በሙሉ ታሳቢ ይደረጋል፡-

1. ካውንስሊንግ
2. ማስጠንቀቂያ
3. ተግሳጽ
4. ጥቅም መከልከል
5. የወላጅ ምክክር
6. በፕሪንሲፓል ወይም በተወካዩ የሚታዘዝ ስራ ወይም እግድ
7. ከትምህርት በፊት ወይም በኋላ ዲቴንሽን (በቅድሚያ ወላጆች እንዲያውቁት ይደረጋል)

8. በትምህርት ጊዜ በትምህርት ቤት ውስጥ ከሚሰናዱ ተግባሮች መታገድ
9. የትምህርት ቤት እገዳ
10. ከት/ቤት ውጭ መታገድ
11. ወደ አማራጭ ፕሮግራም መዛወር
12. እንደ አስፈላጊነቱ ለህግ አካል ማሳወቅ
13. እንዲባረር አስተያየት መጻፍ
14. የአልኮል ወይም የንጥረ ነገር አጠቃቀም ግምገማ
15. በአልኮል ወይም አደንዛዣዕ ዕጽ መካላከል ፕሮግራም ውስጥ ተሳትፎ ማድረግ
16. ተማሪው ቁጥጥር የሚፈልግ ታዳጊ መሆኑን በመግለጽ ለወጣቶችና ለአካባቢያዊ ፍርድ ቤት መግለጫ ማቅረብ

# አባሪ F፡ የተማሪ እገዳና ስንብት

## ፖሊሲ ጄጂዲ-አር/ጄጂኢ-አር

### I. የእገዳና ስንብት መነሻ

ከዚህ በታች የተመለከቱት የደንብ መተላለፎች ለእገዳ መንስኤዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡-

- ቃጠሎ
- የዛቻ ስጋቶች
- ድብደባ እና ጸብ
- የረብሻ ተግባር
- ያልተገባ ቋንቋ መጠቀም
- ቁማር
- አልኮልና ሌላ እጽ መጠቀም/ማሰራጨት
- ንብረት ማውደም
- የት/ቤት አካላትን ትዕዛዝ ያለማክበር
- ጦር መሳሪያ መያዝ
- ስርቆት
- የአውቶብስ ደንቦችን መጣስ
- መተላለፍ
- ውንብድና
- ትንባሆ መያዝና መጠቀም
- ወሲባዊ ትንኮሳ

ከዚህ በታች የተመለከቱት የደንብ መተላለፎች ለስንብት መንስኤዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡-

- ቃጠሎ
- የዛቻ ስጋቶች
- ድብደባ እና ጸብ
- ቁማር
- አልኮልና ሌላ እጽ መጠቀም/ማሰራጨት
- የት/ቤት አካላትን ትዕዛዝ ያለማክበር
- ጦር መሳሪያ መያዝ
- ስርቆት
- የአውቶብስ ደንቦችን መጣስ
- ውንብድና
- ወሲባዊ ትንኮሳ

### II. እገዳና ስንብትን የተመለከተ ይግባኝ

የት/ቤቱ ተቆጣጣሪ ወይም ወኪሉ ተማሪውን ለ10 ቀናት ለማገድ የሚስተላልፈው ውሳኔ ለትምህርት ቤቱ ቦርድ በፖሊሲው መሰረት ይግባኝ አይባልበትም። ለ10 ቀናት ወይም ከዚያ ያነሰ እገዳ ሲወሰን ይግባኙ ተማሪውን ያገደው አስተዳዳሪ ጋር መቅረብ አለበት። (የስነ ምግባር ችሎት ክፍልን ይመልከቱ)።

በስነ ምግባር ችሎቱ ላይ የተሰጡ ውሳኔዎችን ውሳኔው ከተነገረዎት ቀን ጀምሮ ባሉ አምስት የስራ ቀናት ውስጥ የተማሪዎች አገልግሎት፣ አማራጭ ፕሮግራሞች እና ፍትሃዊነት ሃላፊው (Chief of Student Services, Alternative Programs and Equity) ጋር ይግባኝ ማለት ይቻላል።

የእገዳ ውሳኔው ከ10 ቀናት በላይ ለሆነ ጊዜ ሲሆንና ተማሪውና የተማሪው ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ሌላ ሃላፊነት ያለበት አካል ባለበት በት/ቤቱ ቦርድ ይግባኙ በሚታይበት ወቅት ተማሪው በትምህርት ገበታው ላይ እንዳይገኝ ሊታገድ ይችላል። ተማሪው የይግባኝ መብቱን ቢጠቀምም ባይጠቀምም የት/ቤቱ ቦርድ የእገዳ ውሳኔውን ያሳውቃል።

### III. የተባረሩ ተማሪዎች ድጋሚ ምዝገባ

ከአሌክሳንደሪያ ከተማ የህዝብ ት/ቤቶች የተባረሩና በዚሁ ወቅት ወደ ትምህርት ቤት እንዳይገቡ የታገዱ ተማሪዎች ለዳግም ምዝገባ ማመልከት የሚችሉት ከአመት በኋላ ነው። የማንኛውም ተማሪ የዳግም ምዝገባ ሒደት እንደሚከተለው ይሆናል፡-

ሀ. የትምህርት ቤቱ ቦርድ የተማሪውን ዳግም ምዝገባ ይወስን ዘንድ ለዚሁ የሚርበው ማመልከቻ ከዘጠኝ ወራት ሳይቀድም ከአስር ወራት ሳይዘገይ መግባት አለበት። ማመልከቻን በጊዜ ያለማቅረብ የዘገየ የቦርድ ውሳኔን ሊያስከትል ይችላል። ማንኛውም እድሜው 18 አመት የሆነ ተማሪ በራሱ ስም ማመልከቻውን በጽሁፍ ማቅረብ ያለበት ሲሆን እድሜው ካልደረሰ ግን የተማሪው ወላጅ/አሳዳጊ ማመልከቻውን ያቀርባል።

ለ. ማመልከቻ በቀረበ በ21 ቀናት ውስጥ ጽ/ቤቱ ውሳኔ የሚሰጥ ሲሆን ውሳኔውን ለመስጠት በሚሰየመው ጉባኤ ላይ ተማሪው ወይም የተማሪው ወላጅ ተገኝቶ ተማሪው በድጋሚ መመዝገብ የሚያበቃውን ምክንያት፣ እንዲሁም ትምህርት ቤቱ ተማሪው ከዚህ ቀደም የፈጸመውን ነገር መልሶ እንደማይፈጽም የሚያረጋግጥ ማስተማመኛ ይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል። ተማሪው ዳግም እንዲመዘገብ የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎች ከነበሩ መሟላታቸውን ቦርዱ ያረጋግጣል። የቦርዱ ዳይሬክተር በ7 ቀናት ውሳኔ የሚሰጥ ሲሆን ይህንኑ ውሳኔ ተማሪው/የተማሪው ወላጆች በኮፒ እንዲያውቁት ይደረጋል።

ሐ. ወላጆች/አሳዳጊዎች የቦርዱን ውሳኔ በተሰጣቸው በሰባት ቀናት ውስጥ ይግባኝ ሊሉበት ይችላሉ። የመባረሩ ውሳኔ ኮፒ፣ እና ማናቸውም መባረሩን የተመለከቱ ሰነዶች ከይግባኝ አቤቱታው ጋር ለቦርዱ አብረው ይቀርባሉ። ቦርዱ ካስፈለገ ተጨማሪ ጉባኤ በመሰየም በይግባኙ ላዩ በ21 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል።

መ. የዳግም ምዝገባ አቤቱታ እምቢ ከተባለ ተማሪው ወይም እንደ አግባብነቱ የተማሪው ወላጅ/አሳዳጊ በየአመቱ ከላይ በተመለከተው አግባብ አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ።

# አባሪ G፡ ከህግ አስፈጻሚዎች ጋር ያለው ግንኙነት

## ፖሊሲ ኬኤንኤጂ

### በህግ አስፈጻሚ አካላት ት/ቤት ውስጥ የሚደረግ ምርመራ

አንድ የህግ አስፈጻሚ ኦፊሰር ተማሪውን በት/ቤት ግቢ ውስጥ ማነጋገር ካስፈለገው በቅድሚያ ለፕሪንሲፓሉ ማሳወቅ አለበት። ፕሪንሲፓሉ ወይም ተወካዩ በተቻለ መጠን የልጁን ወላጅ/አሳዳጊ በመገናኘት በንግግሩ ላይ እንዲገኝ ለማደስረግ ይሞክራል። የልጁ ወላጅ/አሳዳጊ በንግግሩ ላይ መገኘት ካልቻለ ፕሪንሲፓሉ ወይም ተወካዩ በንግግሩ ላይ ይገኛሉ።

### በት/ቤት ውስጥ የህግ መጥሪያ መስጠት

ህጋዊ መጥሪያ ለአንድ ተማሪ ወይም ሰራተኛ የሚሰጠው ከሆነ የት/ቤቱ ቦርድ በተቻለ መጠን መጥሪያ ሰጪው አካል መጥሪያውን ከት/ቤት ግቢ ውጪ እንዲሰጥ ያደርገዋል። ይህ ሳይሆን መጥሪያው በግቢ ውስ መሰጠት ካለበት በፕሪንሲፓሉ ጽ/ቤት ወይም በተማሪው ፋኩሊቲ ዘንድ እንዲቀመጥ ይደረጋል። በተንከባካቢ ስር ላለ ተማሪ በትምህርት ቤት ውስጥ መጥሪያ መሰጠት ካለበት ይህ ሊደረግ የሚችለው በፖሊስ አማካይነት ብቻ ነው።

### ፕሮግራም መቅረጽ

ተቆጣጣሪው በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ወይም በትምህርት ቤት በተሰናዳ ክስተት ላይ ወንጀልን ለመከላከል የሚያስችሉ ፕሮግራሞችን ከአካባቢያዊ ህግ አስፈጻሚ አካልት፣ የወጣቶች ፍርድ ቤት፣ ወላጆችና ሰራተኞች ጋር በመተባበር እንዲቀረጽ ያደርጋል። ተቆጣጣሪው የወሲብ ጥፋተኞችን ሪከርድ መዝገብ በኬኤን ፖሊሲ መሰረት ይይዛል።

### ለህግ አስፈጻሚ አካላት ሪፖርት ስለማድረግ

በፌዴራል ህግና መመሪያ ካልታዘዘ በቀር ፕሪንሲፓሉ ከዚህ በታች የተመለከቱትና ወንጀል ተብለው ሊቆጠሩ የሚችሉ ድርጊቶች ሲፈጸሙ ለህግ አስፈጻሚ አካላት ሪፖርት ማድረግ አለበት፡-

- ጉዳት ያስከተለ ድብድብ፣ ወሲባዊ ትንኮሳ፣ ሞት፣ ተኩስ፣ በጩቤ መውጋት፣ በአውቶብስ፣ በት/ቤትና ትምህርት ቤት ባዘጋጀው ዝግጅት ላይ ውስጥ ሰውን በስለት መቁረጥ ወይም መጉዳት ወይም።
- ማንኛውንም አልኮልን፣ ማሪዋናንና ሌሎች በህግ የተመለከቱ እጾችን በአውቶብስ፣ በት/ቤትና ትምህርት ቤት ባዘጋጀው ዝግጅት ላይ ይዞ ወይም ተጠቅሞ መገኘት ወይም።
- የተማሪ ንብረትን መስረቅና ለመስረቅ መሞከርን ጨምሮ በአውቶብስ፣ በት/ቤትና ትምህርት ቤት ባዘጋጀው ዝግጅት ላይ የረብሻ ተግባር መፈጸም ወይም።
- በአውቶብስ፣ በት/ቤትና ትምህርት ቤት ባዘጋጀው ዝግጅት ላይ የጦር መሳሪያንና ቦምብን፣ ፈንጂዎችና ተቀጣጣይ ነገሮችን ወይም የኬሚካል መሳሪያዎችን ይዞ የመገኘት ተግባር መፈጸም ወይም።
- በአውቶብስ፣ በት/ቤትና ትምህርት ቤት ባዘጋጀው ዝግጅት ላይ በማንኛውም ተማሪ ወይም ሰራተኛ ላይ የቦምብ ማስፈራራትን እና ዛቻን መፈጸም።

ፕሪንሲፓሉ በአውቶብስ፣ በት/ቤትና ትምህርት ቤት ባዘጋጀው ዝግጅት ላይ ጉዳት ያላስከተለም ቢሆን ማናቸውም ድብድብ ሲከሰት ለህግ አስፈጻሚ አካላት ሪፖርት ማድረግ አለበት።

# አባሪ H፡ እኩል የትምህርት ዕድሎች/ከአድሎ የጸዳ እና የተማሪ መዛግብት/FERPA

### እኩል የትምህርት ዕድሎች/ከአድሎ የጸዳ፣ JB/AC ፖሊሲዎች

የዘር፣ ቀለም፣ የትውልድ ዜግነት፣ ዜግነት፣ የአካል ጉዳት፣ ሃይማኖት፣ ፆታ፣ የፆታ ፍላጎት ዝንባሌ፣ የፆታዊ አገላለጽ፣ ለመሆን የሚፈለግ የፆታ ምርጫ ፍላጎት፣ የጋብቻ ወይም የወላጅነት ሁኔታ ምንም ይሁን ምን እኩል የትምህርት ዕድሎች ለሁሉም ተማሪዎች የሚገኙ ይሆናሉ። በተጨማሪም፣ የሁሉንም ተማሪዎች የተለያዩ ፍላጎቶች ለማሟላት ተጨማሪ የትምህርት ፕሮግራሞች የሚቀረጹ ይሆናሉ። የአሌክሳንድሪያ ከተማ ትምህርት ቤት ቦርድ በፕሮግራሞቹ እና እንቅስቃሴዎች ውስጥ በዘር፣ በቀለም፣ በብሔር፣ በትውልድ፣ በጾታ፣ በአካል ጉዳት፣ በእድሜ፣ በሃይማኖት፣ በጾታ ማንነት፣ በጾታ አገላለፅ፣ በጾታ ዝንባሌ፣ በጄኔቲክ መረጃ፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በወላጅነት ወይም እርግዝና

ሁኔታ ላይ መሰረት ያደረገ ልዩነት ወይም አድልዎ አያደርግም። የ ACPS መድልዎ-አልባ ፖሊሲዎችን በተመለከተ እባክዎን ወደ የተማሪ አገልግሎቶች እና ፍትህ ክፍል፣ 1340 Braddock Place, Alexandria, Virginia 22314 or 703-619-8036 ይምሩ።

### የተማሪ መዛግብት/FERPA፣ ፖሊሲ JO

የትምህርት ቤቱ ዲቪዥን በየአመቱ ለተማሪውና ለወላጆች በቤተሰብ ትምህር መብቶችና ነጻነቶች ህግ መሰረት ያላቸውን መብት ያሳውቃቸዋል፤ ይህም ከዚህ በታች የተመለከቱትን ያጠቃልላል፦

- የተማሪውን የትምህርት ማህደራት የመመልከትና የመመርመር መብት።
- ወላጅ/አሳዳጊ ትክክል አይደሉም፣ የተማሪውን የግል መብት ይጥሳሉ ወይም ወደተሳሳተ አቅጣጫ ይመራሉ ብሎ ያሰባቸውን የተማሪውን የትምህርት ማህደራት እንዲታረሙ የመጠየቅ መብት።
- ኤፍኢአርፒኤ ይፋ እንዲሆኑ ከሚፈቅድበት ወሰን ባሻገር በተማሪው ሪከርድ ላይ የግል ተብለው የተፈቀዱ መረጃዎች ይፋ እንዲደረጉ የመፍቀድ መብት።
- የዳይሬክተሪ መረጃ ተብሎ የተመደበ መረጃን እንዲለቀቅ የማድረግ መብት።
- ተማሪው ለመመዝገብ ባሰበባቸው ወይ በተመዘገበባቸው ተቋማት ዘንድ የሚጠየቀውን መረጃ የትምህር ቤቱ ዲቪዥን ለዚሁ የምዝገባና ዝውውር አላማ ሲል ይፋ የሚያደርግበት መብት።
- ለወታደራዊ ተቋማት ወይም መረጃ ለሚፈልጉ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የተማሪው ስም፣ አድራሻና የስልክ ቁጥር ይፋ እንዲደረግ የመጠየቅ መብት።
- የትምህርት ቤት ባለስልጣን የሚባለውን ወይም ትክክለኛ የትምህርታዊ ፋይዳን በሚመለከት ያለውን መስፈርትና መመሪያ ማወቅ እንዲሁም የትምህርቱ ቤቱን።

ከኤፍኢአርፒኤ ጋር ያለመጣጣም በሚመለከት ለዩናይትድ ስቴትስ የትምህርት ዲፓርትመንት የቤተሰብ ፖሊሲ መጣጣም ጽ/ቤት አቤቱታ የማቅረብ መብት።

---

# አባሪ 1፡ የተማሪ ሕትመቶች

---

## ፖሊሲ JP

**ሕጋዊ የትምህርት ቤት ህትመቶች ትርጓሜ**
እንደ ጋዜጦች፣ አመታዊ መጽሃፎች እና ድርሰታዊ መጽሄቶች ያሉ መደበኛ የትምህርት ቤት ህትመቶች በመደበኛው የትምህርት ክፍለ ጊዜ ሊዘጋጁ የሚችሉና በትምህርት ቦርዱ የጸደቁ የትምህርት ስርአቱ ክፍሎች ናቸው። እነዚህ ህትመቶች ለተማሪው ወይም ለጠቅላላው ህዝብ ህዝባዊ መድረክ ለማቅረብ የታሰቡ አይደሉም። ከነዚህ ህትመቶች ጋር በተገናኙ ሁሉም ሁናቴዎች፣ የትምህርት ቤቱ ቦርድ አሳታሚ ይሆናል፤ ርዕሰ መምህሩ ኢ.ርታኢ ይሆናል፤ የፋካልቲው ስፖንሰር ተባባሪ ኢ.ርታኢ ይሆናል፤ በተባባሪ ኢ.ርታኢው የተሰየሙ ተማሪዎች እንደ ረዳት ኢ.ርታኢና ጋዜጠኞች ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ።

**የተማሪ ኢ.ርታኢዎች እና ጋዜጠኞች ኃላፊነቶች**
ተማሪ ኢ.ርታኢዎች እና ጋዜጠኞች አጸያፊ፣ ስም አጥፊ ወይም የግላዊነት መብትን የሚጥስ ያልሆነ፣ ወይም ደግሞ

- የተማሪዎችን ወይም የሰራተኞችን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል ከሆነ ወይም የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎችን በከፍተኛ ሁኔታ ወደ መስተጓጎል ይመራል ተብሎ የሚታመን ከሆነ፤
- የአንድ ሕገ ወጥ ድርጊት መፈጸምን ወይም የትምህርት ቤት ፖሊሲ ወይም ደንብ መጣስን የሚደግፍ፤
- ሕገ ወጥ ምርቶችን የሚያስተዋውቅ ወይም የሚደግፍ፤ ወይም
- በዘር፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በትውልድ ዜግነት፣ በፆታ ዝንባሌ፣ በፆታ፣ በጾታ መግለጫ፣ በዘር፣ በፖለቲካ ሁኔታ፣ በትውልድ ወይም በአካል ጉዳት ላይ የተመሠረተ ጭፍን ጥላቻን፣ ጥላቻን፣ ጥቃት ወይም ትንኮሳን የሚደግፍ ያልሆነ እውነተኛ ጽሁፍ የማዘጋጀት እና የመጻፍ ኃላፊነት ይኖርባቸዋል።

**የተማሪ ህትመቶች የፋካልቲ ተባባሪ ኢ.ርታኢ ኃላፊነቶች**
የትምህርት ቤት ህትመቶች የፋካልቲ ተባባሪ ኢ.ርታኢዎች ተማሪዎችን በአሜሪካ የጋዜጣ ኢ.ርታኢዎች ማህበር የስነ ምግባር ኮዶች እንዲመሩ ማዘዝና ተማሪዎች እንዲረዱትና እንዲከተሉትም ማገዝ ይኖርባቸዋል። የፋካልቲ አባላት ተማሪዎች ትክክለኛ እና ተገቢ የጋዜጠኝነት ዘዴዎችን እንዲከተሉ መመሪያ መስጠት እና ህግን ወይም የጋዜጠኝነት ሥነ ምግባር ህግን ሊጥሱ በሚችሉ ነገሮች ላይ ከርዕሰ መምህሩ፣ ኢ.ርታኢም ከሆነው፣ ጋር ይመክራሉ። በአንዳንድ የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ አባላት አወዛጋቢ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ነገር በተማሪዎች እና በፋክልቲ አርታኢ በጥንቃቄ መመርመር ያለበት ሲሆን የርዕሰ መምህሩን (አርታኢውን) ትኩረት እንዲያገኝ መደረግ ይኖርበታል።

**የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር (አርታኢ) ኃላፊነቶች**
የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ሁሉንም ሕትመቶች በትምህርት ቤት ቦርድ ፖሊሲ መሰረት እና በእሱ/በእስዋ ፍርድና ጥንቃቄ ተመርኩዞ የማጽደቅ ኃላፊነት አለበት።

# አባሪ J: የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎችን ስነ ምግባር ማስያዝ

## ፖሊሲ JGDA

የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች ሆነው የተማሪ የሥነ ምግባር ደንብን የሚጥሱ ወይም የስነስርአት እርምጃ ሊያስወስዱባቸው በሚችሉ ምግባራት የሚሰማሩ፣ በዚህ ፖሊሲ መሰረት የዲሲፕሊን እርምጃ ይወሰድባቸዋል። በተጨማሪም፣ መደበኛዎቹን የዲሲፕሊን ሂደቶችን መከተል የግድ ነው። የትምህርት ቤት ሰራተኛ፣ በዲሲፕሊን ምክንያት የአካል ጉዳተኛ ልጅን የቦታ ለውጥ ለማዘዝ ሲወስን፣ እንደየ ጉዳዩ የሚኖሩ ማንኛቸውንም ልዩ ሁኔታዎች ከግምት ሊያስገባ ይችላል።

**I. የረጅም ጊዜ እገዳዎች፣ ማባረሮች ወይም የአጭር ጊዜ እገዳዎች በአመዳደብ ላይ የስርአተ ጥለት ለውጥ የሚፈጥሩ**
የአካል ጉዳት ያለባቸውን ተማሪዎች አሁን ካሉበት የትምህርት ምደባዎች ለማስወገድ ዓላማ፣ የምደባ ለውጥ የሚከሰተው በሚከተሉት ሁኔታዎች ወቅት ነው፡-

ማስወገዱ ከ 10 ተከታታይ የትምህርት ቀናት በላይ ሲሆን፣ ወይም በትምህርት ዓመቱ ለ 10 ቀናት ወይም ከዚያ ያነሱ ማስወገዶች ድምር ከ 10 ቀናት በላይ ሲሆን እና በሚከተሉት ምክንያቶች ስርአተ ጥለት ሲፈጥሩ፡-

- በእያንዳንዱ ማስወገድ እርዝማኔ፣
- በማስወገዶቹ መካከል ያለው ቅርበት፣
- ልጁ የተወገደበት ጠቅላላ ጊዜ፣ እና
- የልጁ ባህሪ በቀደሙ ክስተቶች ወቅት ከነበረው የልጁ ባህሪ ጋር በከፍተኛ ሁኔታ ሲመሳሰል።

የስነስርአት እርምጃው የአካል ጉዳት ላለበት ተማሪ የቦታ ለውጥ ማድረግ የሚያስከትል ከሆነ፣ የተማሪው ወላጅ/አሳዳጊ የስነስርዓት ምክረ ሃሳቡ በተሰጠበት በዛው ቀን ማስታወቂያ እንዲላክላቸውና የአካሄድ መከላከያ ቅጂ እንዲደርሳቸው መደረግ አለበት። በክፍል IV ውስጥ የተዘረዘሩ ሂደቶችን መከተል ያስፈልጋል።

**II. የአጭር ጊዜ እግድ**
የአጭር ጊዜ እገዳ በአንድ ጊዜ ለ 10 ተከታታይ ቀናት ወይም ከዚያ ላነሰ ጊዜ መታገድ ነው።

የትምህርት ቤት ባለሥልጣናት የአካል ጉዳተኛ ተማሪን አሁን ካለው/ካላት የትምህርት እቅድ በአንድ አመት በድምሩ እስከ 10 የትምህርት ቀናት ድረስ ሊያስወግዱት ይችላሉ፣ ይህም እንዲህ ያለው ማስወገድ የአካል ጉዳት የሌለባቸው ልጆች ላይ የሚተገበር ሲሆን እና ምንም ስርአተ ጥለት እስከሌለ ድረስ ለአጭር ጊዜ እገዳዎች።

**III. ተግባራዊ የስነምግባር ግምገማዎች እና የባህሪ ጣልቃ ገብነት እቅዶች**
የትምህርት ቤቱ አስተዳደር፣ ወላጅ/አሳዳጊ እና ተዛማጅነት ያላቸው የግላዊ ትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን አባላቶች አንድ መገለጫ አለ የሚለውን ከወሰኑ፣ የ IEP ቡድን የሚከተሉትን ማድረግ አለበት፡-

- ተግባራዊ የስነምግባር ግምገማዎች (FBA) ማካሄድ እና የባህሪ ጣልቃ ገብነት እቅድ (BIP) ተግባራዊ ማድረግ፣ አስቀድሞ ምንም FBA ያለተካሄደ ከነበረ፤ ወይም
- ተማሪው አስቀድሞ FBA እና BIP ያለው ከሆነ፣ ባህሪውን ለማስተካከል እንደ አስፈላጊነቱ BIP ውን ይከልሱ/ ያሻሽሉ።

**IV. የትምህርት አገልግሎቶች በስነስርአት ቅጣት ወቅት**
በአንድ የትምህርት ዘመን ውስጥ ለመጀመሪያዎቹ 10 ቀናት እግድ፣ በተመሳሳይ መልኩ እግድ ለተጣለባቸው የአካል ጉዳት ለሌለባቸው ተማሪዎች አገልግሎቶች የማይሰጡ ከሆነ፣ ACPS ለአካል ጉዳተኛ ለሆኑ ተማሪዎች የትምህርት አገልግሎቶችን መስጠት አይጠበቅበትም።

በአንድ የትምህርት ዘመን ውስጥ ከመጀመሪያዎቹ 10 ቀናት እግድ በኋላ፣ ACPS የአካል ጉዳቱን ከግምት ባስገባ መልኩ፣ ለተማሪው አስፈላጊ እስከሆነው ድረስ በእግዱ ወቅት አገልግሎቶችን ያቀርባል፣ ይህም

- በአጠቃላይ ሥርዓተ ትምህርቱ ለመግፋት እና
- በተገቢው መልኩ በተማሪው የግላዊ ትምህርት ፕሮግራም (IEP) ውስጥ የተቀመጡትን ግቦች ወደ ማሳካት ለመሄድ።

የተፈላጊ አገልግሎቶች ውሳኔ የሚደረገው የምደባ ለውጥ በሚፈጥረው የ IEP የሥነ ምግባር ቡድን ነው። የምደባ ለውጥ ላልሆነ የዲሲፕሊን ቅጣት፣ ውሳኔው የሚደረገው በትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ከተማሪው የልዩ ትምህርት መምህር ጋር በመመካከር ነው።

**V. የመገለጫው ውሳኔ**
የአካል ጉዳት ላለበት ተማሪ የቦታ ለውጥ የሚያስከትል የዲሲፕሊን እርምጃ ለመውሰድ ሲታሰብ፣ ቢቻል የዲሲፕሊን እርምጃ ለመወሰድ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በ 10 የትምህርት ቀናት ውስጥ የመገለጫ ውሳኔ ግምገማ መከናወን ይኖርበታል። ይህ ግምገማ ተገቢነት ባላቸው የግላዊ ትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን አባላቶች፣ የልዩ ትምህርት ቢሮ ተወካይ፣ ወላጅ/አሳዳጊ እና ሌሎችንም በትምህርት ቡድን ውስጥ በሚወሰነው መሰረት በማካተት መከናወን ይኖርበታል።

የግላዊ ትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድኑ የተማሪው ባህሪ የእንዲህ ያለ ተማሪ አካል ጉዳት መገለጫ እንዳልነበር ሊወስን የሚችለው፣ የሚከተለው ከሆነ ብቻ ነው፡-

- የግላዊ ትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድኑ በተማሪው ማህደር ውስጥ ያሉት መረጃዎች፣ የተማሪው IEP፣ ማንኛውም የመምህር ምልከታዎች፣ በወላጅ/አሳዳጊ የቀረበ አግባብነት ያለው መረጃን ጨምሮ ከግምት በማስገባት
- እንደሚከተለው ከወሰነ ነው፡-
  - » በጥያቄ ውስጥ ያለው ባህሪ በተማሪው የአካል ጉዳት ምክንያት እንዳልተከሰተ ወይም ቀጥተኛና አሳማኝ ግንኙነት እንዳልነበረው፣ እና
  - » በጥያቄ ውስጥ ያለው ባህሪ የትምህርት ቡድኑ የግላዊ ትምህርት ፕሮግራሙን (IEP) መተግበር ያለመቻል ቀጥተኛ ውጤት እንዳልሆነ።

መገለጫ ከተገኘ ግን፣ ተማሪው ሊኖር ከሚችለው ተቀባይነት ያለው የአጭር ጊዜ እገዳ በላይ ሊቀጣ አይችልም። የተማሪው ወላጅ/አሳዳጊ የተማሪው/ዋ ምግባር የአካል ጉዳተኝነት መገለጫ አለመሆኑን በሚገልጸው ውሳኔ የማይስማሙ ከሆነ ወይም የተማሪው ወላጅ/አሳዳጊ ከተማሪው/ዋ የቅጣት ወቅት አመዳደብ ጋር ከሚያያዝ ማንኛውም ውሳኔጋ የማይስማሙ ከሆነ የተፋጠነ የፍትህ ሂደት ችሎት ሊጠይቁ ይችላሉ። የችሎት መኮንኑን ውሳኔ ወይም የ 45 ቀን ማስወገድ ጊዜው እስኪያልቅ ድረስ ተማሪው በጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት ቅንብር ውስጥ ይቆያል።

**VI. መገለጫ እንዳልሆነ ለተወሰነ ባህሪ የሚወሰድ የዲሲፕሊን እርምጃ**

ባህሪያቱ የተማሪው/ዋ አካለ ስንኩልነት መገለጫ እንዳልሆነ ከታወቀ በኋላ የአካል ጉዳት ባለበት/ባለባት ተማሪ ላይ ልክ የአካል ጉዳት በሌለባቸው ተማሪዎች ላይ በሚወሰደው መልኩ የዲሲ ፕሊን ሂደቶቹ ተግባራዊ ይሆናሉ። የአመዳደብ ለውጥ የሚፈጥረውን ማስወገድ ተከትሎ ተማሪው/ዋ በአጠቃላይ ሥርዓተ ትምህርቱ ለመግፋት፣ ምንም እንኳን በሌላ ቅንብር ውስጥ ቢሆንም፣ እና በተገቢው መልኩ በተማሪው/ዋ የግላዊ ትምህርት ፕሮግራም (IEP) ውስጥ የተቀመጡትን ግቦች ወደ ማሳካት ለመሄድ፣ ተማሪው/ዋ አስፈላጊ የሆኑትን የትምህርት አገልግሎቶች መቀበል መቀጠል አለበት። በተጨማሪም፣ የልጁ የልዩ ትምህርትና የዲሲፕሊን መዛግብት ዲሲፕሊኑን በተመለከተ የመጨረሻ ውሳኔ ለሚወስነው ሰው እንዲገኙ መደረግ ይኖርባቸዋል።

**VII. መገለጫ እንደሆነ ለተወሰነ ባህሪ የሚወሰድ የዲሲፕሊን እርምጃ እና/ወይም አማራጭ አመዳደብ**

ባህሪያቱ የተማሪው/ዋ አካለ ስንኩልነት መገለጫ እንደሆነ የታወቀ የአካል ጉዳተኛ ተማሪ ማስወገድ በሕግ እስከተፈቀደው ድረስ እንጂ የስነስርዓት እርምጃ ላይወሰድበት ይችላል። ተማሪው/ዋ የምደባ ለውጥን ሳያካትት ወደ ሌላ አካባቢ ሊዘዋወሩ ይችላሉ ወይም የቦታ አቀራረብን ለውጥ በመከተል ወደ ሌላ ወይም ይበልጥ ጥብቅ ወደ ሆነ ምደባ ሊወሰዱ ይችላሉ። በክፍል III በቀረበው መሰረት የግላዊ ትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድኑ ተግባራዊ የስ ነምግባር ግምገማዎች (FBA) እና/ወይም የባህሪ ጣልቃ ገብነት እቅድ (BIP) ማካሄድ ወይም መከለስ።

**VIII. ለጦር መሳሪያና ለአደንዛዥ ዕጽ እንዲሁም ከባድ የአካል ጉዳት ላደረሱ የሚሆን ጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት ቅንብር**

የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች 1) በትምህርት ቤት ውስጥ፣ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ፣ ወይም ወደ/በ ትምህርት ቤት ተግባራት መሳሪያ የሚይዝ ወይም የሚኖረው፣ ወይም 2) በትምህርት ቤት፣ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ወይም በትምህርት ቤት ተግባራት ላይ እያለ ሕገወጥ መድሃኒቶች የሚይዝ ወይም የሚጠቀም ወይም ቁጥጥር የሚደረግባቸው እጾችን የሚሸጥ ወይም የሚሸጡትን ለማግኘት የሚሞክር፣ ወይም 3) በትምህርት ቤት፣ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ወይም በትምህርት ቤት ተግባራት ላይ እያለ ሌላ ሰው ላይ ከባድ አካላዊ ጉዳት የሚያደርስ በ JFCD ፖሊሲ መሰረት ሊቀጣ ይችላል፡ የጦር መሳሪያ በትምህርት ቤት እና JFCF፡ አደንዛዥ እጾች በትም ርት ቤት ወይም JGDB፡ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ከባድ የአካል ጉዳት በማድረሳቸው ቅጣት እና እስከ 45 የትምህርት ቀናት ተገቢ በሆነ ጊዜያዊ የአማራጭ ትምህርት ቅንብር ውስጥ ሊቀመጡ ይችላሉ። ይህ አማራጭ መገለጫ መኖሩ እና አለመኖሩ ሳይታይ የሚኖር አማራጭ ነው። ምንም መገለጫ ያልተገኘ ከሆነ፣ ተማሪው/ዋ አንድ የአካል ጉዳት የሌለበት ተማሪ ሊቀጣ እስከሚችለው ሊቀጣ ይችላል።

**IX. የምደባ ለውጥ ችሎት**

ከሌሎቹ የማስወገድ አማራጮች በተጨማሪ, የችሎት መኮንኑ የአካል ጉዳተኛው ተማሪ አመዳደብ ላይ ቅያሪ በማድረግ ወደ ተገቢ የጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት ቅንብር ውስጥ ከ 45 ቀናት ለማይበልጥ ጊዜ እንዲቀመጥ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፣ ይህም የችሎት መኮንኑ አሁን ባለበት ምደባ የሚቆይ ከሆነ ተማሪው በራሱ ላይ ወይም በሌሎች ተማሪዎች ላይ ከፍተኛ የሆነ ጉዳት ማስከተል የመቻል እድል አለው ብሎ ሲወስን ነው። የተጨማሪ 45 የትምህርት ቀናት ማስወገድ በችሎት መኮንኑ ሊፈቀድ ይችላል።

**X. በይግባኝ ወቅት ያለ አመዳደብ**

የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች የአካል ጉዳት ለሌለባቸው ተማሪዎች የሚያገኟቸውን የፍትህ ሂደት መብቶች የማግኘት መብት አላቸው። በተጨማሪም፣ የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች በአካል ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች ትምህርት ድንጋጌ፣ በተሻሻለው እና በማናቸውም የስቴት አካሄዶች ስር የሚገኙ የፍትህ ሂደት አካሄዶችን የማግኘት መብት አላቸው። በማንኛውም ይግባኝ ወቅት፣ የተማሪው ምደባ ወላጅ/አሳዳጊ እና የትምህርት መምሪያው በተቃራኒው ካልተስማሙ በስተቀር፣ የተማሪው/ዋ ምደባ በአካል ጉዳት ያለባቸውን ተማሪዎች በሚያስተዳድረው የቨርጂኒያ ደንብ ድንጋጌዎች መሠረት መሆን አለበት።

**XI. የአካል ጉዳተኛ እንደሆኑ ያልተለዩ ተማሪዎች**

የትምህርት ክፍሉ የዲሲፕሊን እርምጃ ያስከተለው ይህ ባህሪ ከመከሰቱ በፊት ስለ አካል ጉዳቱ ዕውቀት ያልነበራቸው ከነበረ፣ የተማሪው አካል ጉዳተኛነት ገና ያልታወቀ ሆኖ፣ የተማሪው ወላጅ/አሳዳጊ ግን የአካል ጉዳተኝነት ይኖራል የሚል ግምት ያላቸው ቢሆንም፣ የአካል ጉዳት የሌለባቸው ተማሪዎች ላይ ተፈፃሚነት ላላቸው ተመሳሳይ እርምጃዎች ተገዢ ይሆናሉ። የሚከተሉት ከሆኑ የትምህርት ክፍሉ ስለ ተማሪው አካል ጉዳተኝነት እንደሚያውቅ ተደርጎ ይወሰዳል:-

- ወላጅ/አሳዳጊ ቀደም ሲል በጽሁፍ (ወይም በቃል ወላጅ/አሳዳጊ መጻፍ ወይም የጽሁፍ መግለጫ እንዳይሰጥ የሚያደርግ የአካል ጉዳት ያለበት ከሆነ) ለትምህርት ቤቱ ሰራተኛ ተማሪው የልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች የሚያስፈልገው ስለመሆኑ ስጋታቸውን ገልጸው ከነበረ፤ ወይም
- ወላጅ/አሳዳጊ ተማሪው ለልዩ ትምህርት ያለውን ብቁነት በመደበኛ የግምገማ ሂደት እንዲገመገም የግምገማ ጥያቄ አቅርበው ከነበረ፤ ወይም
- የተማሪው አስተማሪ ወይም ሌላ የት/ቤት ሰራተኛ ስለ ባህሪ ስርአተ ጥለት ወይም አፈጻጸም ያላቸውን የተወሰነ ስጋት ለት/ቤቱ ልዩ ትምህርት ዋና ዳይሬክተር ወይም ለትምህርት ክፍሉ ሌሎች ተቆጣጣሪ ሰራተኞች ገልጸው ከነበረ።

የሚከተሉት ከሆኑ የትምህርት ክፍሉ ስለ ተማሪው አካል ጉዳተኝነት እንደማያውቅ ተደርጎ ይወሰዳል:-

- ወላጅ/አሳዳጊ የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን ወይም የተማሪውን ግምገማ መፍቀድ እምቢ ብሎ ከነበረ፣ ወይም
- ተማሪው ግምገማ የተደረገለት እና ለልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ብቁ ሆኖ ያልተገኘ ከነበረ።

የግምገማ ጥያቄው የቀረበው በተማሪው ላይ የዲሲፕሊን እርምጃ በሚወሰድበት ወቅት ከሆነ፣ ግምገማው በተፋጠነ ሁኔታ መካሄድ ይኖርበታል። ተማሪው/ዋ ለአካል ጉዳት ተማሪነት ብቁ ሆነው ከተገኙ፣ በትምህርት ክፍሉ ከተካሄደው ግምገማ እና በወላጅ/አሳዳጊ የቀረበውን መረጃ ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ለተማሪው/ዋ በዝቅተኛ ገዳቢ አካባቢ ውስጥ ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች መቅረብ አለባቸው፣ በሌላ እቅድ ውስጥ ቢሆን እንኳን፣ ከትምህርት ቤት ለታገዱና ለተባረሩ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ያለውን አሰራር በመከተል። የግምገማውን ውጤቶች በመጠባበቅ ላይ ከሆነ፣ ተማሪው በትምህርት ቤቱ ኃላፊዎች በሚወሰን የትምህርት አመዳደብ ውስጥ ይቆያል።

**XII. የአልኮል እና የአደንዛዥ ዕፅን ፖሊሲ የሚጥሱ የተወሰኑ በክፍል 504 (Section 504) ስር ያሉ ተማሪዎችን መቅጣት**
በመልሶ ማቋቋሚያ ደንብ  በክፍል 504 (Section 504) ውስጥ አካል ጉዳተኝነት እንዳለባቸው የተለዩ እና በህገወጥ መንገድ አደንዛዥ ዕጽን ወይም አልኮል መጠቀም ላይ እየተሳተፉ ሲሆን፣ የክፍሉን የአልኮልና የአደንዛዥ ዕጽ ፖሊሲዎችን በመጣስ የአካል ጉዳት ከሌለባቸው ተማሪዎች ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ሊቀጡ ይችላሉ። ተማሪው በዚህ ሁኔታ ውስጥ በልዩ ትምህርት ሂደቶች ስር ያሉ የፍትህ ሂደት ችሎት የማግኘት መብት አይኖረውም ነገር ግን ለመደበኛ ትምህርት ተማሪዎች የሚደረጉትን ጥበቃዎች ይደረጉለታል።

# አባሪ K፡ ፍተሻ እና በቁጥጥር ስር ማዋል

## ፖሊሲ JFG

ፍተሻ የግለኝነት መተላለፍን ያካትታል። የአንድ ተማሪ ፍተሻ የሚፈቀድ መሆኑና አለመሆኑ የተማሪውን ምክንያታዊ ካልሆነ ፍተሻና በቁጥጥር ስር መዋል ያለውን የግለኝነት እና የነጻነት መብት እንዲሁም የትምህርት ክፍሉ በትምህርት ቤት ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ የሁሉንም ሰዎች ጤንነትና ደህንነት የመጠበቅ እንዲሁም የትምህርት ተልዕኮውን የማከናወን ኃላፊነቶችን በማመዛዘን ላይ በመመርኮዝ ነው። በትምህርት ቤቶች ውስጥ ሥርዓትን እና ደንብን ለማስከበር እና የተማሪዎችን እና የትምህርት ቤት ሰራተኞችን ጤና እና ደኅንነት ለመጠበቅ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ሁኔታዎች ውስጥ የትምህርት ቤት ባለስልጣናት ተማሪን፣ የተማሪ ንብረቶችን፣ የተማሪ ኮመዲኖዎችን ወይም የተማሪ ተሽከርካሪዎችን ሊፈትሹ እና ማንኛውንም በፍለጋው ውስጥ የተገኙ ህገወጥ፣ ያልተፈቀዱ ወይም የኮንትራባንድ ዕቃዎች በቁጥጥር ስር ሊያውሉ ይችላሉ።

በዚህ ፖሊሲ ውስጥ ጥቅም ላይ እንደዋለው "ያልተፈቀደ" የሚለው ቃል ለተማሪዎች ወይም ለትምህርት ቤት ሰራተኞች ጤንነት ወይም ደህንነት አደገኛ የሆነን ማንኛውንም ነገር ወይም የትምህርት ቤት ሂደትን፣ የትምህርት ተልዕኮውን ወይም የትምህርት ቤት ተግባሩን የሚያስተጓጉል ወይም ለተማሪው/ዋ አስቀድሞ በሚሰጥ የትምህርት ቤት ሕግ ያልተፈቀዱ ማንኛቸውንም ነገሮች ማለት ነው። "የተማሪ ንብረቶች" የሚያካትተው፣ ግን በዚህ ብቻ የተወሰነ አይደለም፣ የጀርባ ቦርሳዎች፣ ተንቀሳቃሽ ስልኮች ወይም ሌሎች የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች፣ ቦርሳዎች፣ ጃኬቶች ወይም ሌሎች የግል እቃዎችን ነው።

አንድ ተማሪ በዚህ ፖሊሲ በቀረበው መሰረት ፍተሻዎችን እና በቁጥጥር ስር ማዋልን አለመፍቀድ ለዲሲፕሊን እርምጃ መሰረት እንደሚሆን ይቆጠራል።

የተማሪዎችን እና የተማሪን ንብረቶች ፍተሻ የሚካሄድባቸው ቦታዎች በትምህርት ቤቱ ህንጻ ወይም በትምህርት ቤቱ ይዞታ ብቻ የተገደቡ አይደሉም። ተማሪው/ዋ በትምህርት ቤት ስፖንሰር በተደረገ ተግባር ውስጥ በሚሳተፉበት ቦታ ሁሉ ፍለጋዎች ሊካሄዱ ይችላሉ።

**ግለሰባዊ ፍተሻዎች**
የትምህርት ቤቱ ኃላፊ ተማሪው ህገወጥ ወይም ያልተፈቀዱ ቁሳቁሶች መያዙን ወይም የትምህርት ቤቱን ደንብ ወይም ህግ ጥሷል ወይም ሊጥስ በመሆኑ ፍተሻው የጥሰቱን ማስረጃ ያስገኛል የሚል ምክንያታዊ ጥርጣሬ በሚኖራቸው ጊዜ የተማሪው/ዋ (የውጭ ልብስን ጨምሮ) እና/ወይም የግል እቃዎች በአንድ የትምህርት ቤቱ ኃላፊ ሊፈተሹ ይችላሉ። ሁሉም የተማሪ ግለሰባዊ ፍተሻዎች ምክያታዊ በሆኑ ጥርጣሬዎች ላይ የተመረኮዙ መሆንይኖርባቸዋል፣ ለምሳሌ፦ ስህተት መፈጸሙን የሚያረጋግጥ ማስረጃ የማግኘት መጠነኛ እድል።

የተፈቀደ እንዲሆን፣ ፍተሻው:

- በምርመራው ወቅት ምክንያታዊ በሆነ ጥርጣሬ የተረጋገጠ እና
- የፍለጋውን ትክክለኛነት ከሚያረጋግጡት ሁኔታዎች ጋር ምክንያታዊ በሆነ መልኩ የተዛመደ መሆን ይኖርበታል።

ግለሰባዊ ፍተሻ በምርመራው ወቅት ትክክለኛነቱ የሚረጋገጠው፣ የትምህርት ቤቱ ኃላፊ፣ በታወቁት ሁኔታዎች አጠቃላይነት ላይ ተመስርቶ፣ ተማሪው ህገወጥ ወይም ያልተፈቀዱ ቁሳቁሶች መያዙን ወይም የትምህርት ቤቱን ደንብ ወይም ህግ ጥሷል ወይም ሊጥስ በመሆኑ ፍተሻው የጥሰቱን ማስረጃ ያስገኛል የሚል ምክንያታዊ ጥርጣሬ በሚኖራቸው ጊዜ ነው። የተወሰነው እርምጃ ከተማሪው ዕድሜ፣ ፆታ እና የተጠረጠረው ወንጀል ተፈፃሚነት አንጻር ከተግባራዊ ዓላማዎቹ ጋር ምክንያታዊ በሆነ መልኩ ተያያዥነት ሲኖረው እና  ከመጠን በላይ ጥብቅ እና ጣልቃ ገብ ሳይሆን ሲቀር የትምህርት ቤት ፍተሻ ይፈቀዳል።

ግለሰባዊ ፍተሻ አንድ የተወሰነ ተማሪ ወይም ተማሪዎችን በብረት ፈልጎ ማግኛ እንዲቃኙ መፈለግን ሊያካትት ይችላል። አጠቃላይ ወይም ነሲባዊ የብረት ፈልጎ ማግኛ አጠቃቀም በዚህ ፖሊሲ አልተሸፈነም።

የተማሪውን ውጫዊ ልብስ ፍተሻ ሊከናወን የሚችለው አንድ የትምህርት ቤቱ ኃላፊ የትምህርት ቤቱ ደንብ ወይም ህግ ስለመጣሱ ማስረጃ ይገኛል የሚል ምክንያታዊ ጥርጣሬ በሚኖራቸው ጊዜ ብቻ ነው። የተማሪውን ውጫዊ ልብስ ፍተሻ የሚከናወን ከሆነ፣ ከተማሪው ጋር ተመሳሳይ ጾታ በሆነ የትምህርት ቤት ኃላፊ፣ ገለል ባለ ቦታ ውስጥ እና ከተማሪው ጋር ተመሳሳይ ጾታ የሆነ አዋቂ ምስክር በተገኘበት ነው የሚከናወነው።

**ሙሉ አካላዊ ፍተሻ**
ሙሉ አካላዊ ፍተሻዎች፣ የተማሪውን የውስጥ ልብሶች ጨምሮ፣ በተማሪ መብቶች ላይ ከፍተኛ የሆነ ጣልቃ መግባት ስለሚያስከትል፣ አስቸኳይ እርምጃ መውሰድ የሚያስፈልገው በአንድ ግለሰብ ወይም ሰዎች ላይ ከባድ የአካል ጉዳት ወይም ለሞት የሚዳርግ አስጊ ሁኔታ ሲኖር ብቻ የሚከናወን ሊሆን ይችላል። ሙሉ አካላዊ ፍተሻ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የትምህርት ቤቱ ኃላፊ ተገቢውን የህግ አስከባሪ ኃላፊ ማነጋገር የሚኖርበት ሲሆን፣ ፍተሻው መከናወን ያለበት በተመሳሳይ ጾታ የህግ አስፈጻሚ መኮንን እና የተመሳሳይ ጾታ ምስክር በተገኘበት ነው። የትምህርት ቤት ኃላፊዎች ሙሉ አካላዊ ፍተሻ ሊያከናውኑ የሚችሉት በአንድ ግለሰብ ወይም ሰዎች ላይ ከባድ የአካል ጉዳት ወይም ለሞት የሚዳርግ አስጊ ሁኔታን ማስቀረት አስፈላጊ ሲሆንና በበቂ ጊዜ ውስጥ የህግ አስከባሪ አካል የማይገኝ ከሆነ ብቻ ነው።  ሙሉ አካላዊ ፍተሻ የግድ በትምህርት ቤት ኃላፊ መከናወን ካለበት፣ ከተማሪው ጋር ተመሳሳይ ጾታ ባለው የትምህርት ቤት ኃላፊና ከተማሪው ጋር ተመሳሳይ ጾታ በሆነ አዋቂ ምስክር በተገኘበት መሆንይኖርበታል፣

እንዲሁም  የቅድሚያ ፍቃድ ማግኘቱ በራሱ ከባድ የአካል ጉዳት ወይም ለሞት የሚዳርግ አስጊ ሁኔታ የሚፈጥር እስካልሆነ ድረስ፣ የትምህርት ቤቱ ኃላፊ በቅድሚያ የዋና ተቆጣጣሪው ወይም የዋና ተቆጣጣሪው ተወካይ ፍቃድ ሊኖረው ይገባል።

**የኮመዲኖዎች፣ የጠረጴዛዎች እና የሌሎች በትምህርት ቤቱ የቀረቡ ማስቀመጫዎች ፍተሻ**
የተማሪ ኮመዲኖዎች፣ ጠረጴዛዎች እና ተመሳሳይ ትምህርት ቤት ያቀረባቸው የማስቀመጫ ሥፍራዎች የትምህርት ቤቱ ንብረቶች ሲሆኑ በሁሉም ጊዜያት የትምህርት ቤት ንብረት ሆነው ይቀራሉ ይሁን እንጂ ተማሪዎች ለኮመዲኖዎቻቸው ደህንነት ሙሉ ሃላፊነት ያለባቸው እና በተመደቡባቸው ኮመዲኖዎች ይዘት ሁል ጊዜም ተጠያቂ ናቸው። በመደበኝነት አጠቃላይ የኮመዲኖዎች፣ ጠረጴዛዎች፣ እና ተመሳሳይ በትምህርት ቤት የቀረቡ የማስቀመጫ ስፍራዎች ላይ አጠቃላይ ፍተሻዎች በማንኛውም ምክንያት፣ ያለ ማስጠንቀቂያ፣ ያለተማሪው ፈቃድ እና የፍተሻ ማዘዣ ሳያስፈልግ ወይም ካለምንም ምክንያት በትምህርት ቤት ባለስልጣኖች ሊካሄድ ይችላል።

**የተሽከርካሪ ፍተሻ**
ተማሪዎች በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ እንዲያቆሙ የሚፈቀድላቸው እንደ ልዩ ጥቅም እንጂ፣ እንደ መብት አይደለም። ትምህርት ቤቱ የተማሪው የመኪና ማቆሚያ ዕለታዊ ቁጥጥሮችን እና በትምህርት ቤት ንብረት ላይ የሚገኙ የተማሪ ተሽከርካሪዎችን ውጫዊ ምርመራን የማካሄድ ስልጣኑን ይዞ ይቆያል። እንዲህ ያሉት ቁጥጥሮችና ፍተሻዎች ያለ ማስጠንቀቂያ፣ ያለተማሪው ፈቃድ እና የፍተሻ ማዘዣ ሳያስፈልግ ወይም ካለምንም አሳማኝ አጠራጣሪ ጥፋት በትምህርት ቤት ባለስልጣኖች ሊካሄዱ ይችላሉ። የተማሪ ተሽከርካሪዎች ውስጣዊ ክፍል አንድ የትምህርት ቤቱ ኃላፊ ተማሪው የትምህርት ቤት ደንብ ወይም ህግ ስለመጣሱ ወይም ሊጥስ ስለመሆኑ ለማመን ምክንያታዊ ጥርጣሬ ሲኖረውና ፍተሻው የጥሰቱን ማስረጃ ያስገኛል ወይም ሌላ ህገ ወጥ ወይም ያለተፈቀዱ ነገሮች ወይም የሌሎች ህገ ወጥ ወይም የተከለከሉ እንቅስቃሴዎች ማስረጃ በተሽከርካሪው ውስጥ ይገኛል ብሎ ሲያምን ሊፈተሽ ይችላል።

**የትምህርት ቤት ኮምፒተሮች ፍተሻ**
የትምህርት ቤት ኮምፒተሮች፣ ሶፍትዌሮች እና የኢንተርኔት መዳረሶች የትምህርት ቤት ንብረቶች ናቸው። ተማሪዎች ከትምህርት ቤቱ የትምህርት ተልዕኮ እና በ IIBEA ኃላፊነት ያለው የኮምፒዩተር ስርዓት አጠቃቀም ፖሊሲ ጋር በተጣጣመ ሁኔታ  ብቻ የትምህርት ቤት ኮምፒተሮች እና ሌሎች ተመሳሳይ የትምህርት ቴክኖሎጂዎችን እንዲጠቀሙ ይፈቀዳል። የትምህርት ቤት ባለስልጣናት በማንኛውም ምክንያት፣ ያለ ማስጠንቀቂያ፣ ያለተማሪው ፈቃድ እና የፍተሻ ማዘዣ ሳያስፈልግ ወይም ካለምንም አሳማኝ ጥርጣሬ ማስፈለግ የትምህርት ቤት ኮምፒተሮችን፣ ሶፍትዌሮችን እና የኢንተርኔት አጠቃቀም መዝገቦችን ሊፈትሹ ይችላሉ።

**በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ፍተሻ**
አንድ ተማሪ ለአንድ የትምህርት ቤት ኃላፊ የሱን/የሷን አካል፣ የግል ኢቃዎች፣ እና/ወይም የተሽከርካሪውን ውስጣዊ ክፍል እንዲፈትሽ ህጋዊ ፈቃድ ከሰጡ፣ የትምህርት ቤቱ ኃላፊ ምክንያታዊ ጥርጣሬን ማሳየት አያስፈልገውም።   የተማሪ የፍቃደኝነት ስምምነት መግለጫ የሚሰራው በፈቃደኝነት እና የስምምነት መግለጫውን ትርጓሜ በመረዳትከሆነ ነው። ተማሪዎች መፈተሽ ያለመፍቀድ መብታቸው መሆኑ ሊነገራቸው ይገባል እናም አንድ ተማሪ በፍለጋው ላይ ፍቃድ ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆኑ በእሱ/በእሷ ላይ ቅጣት ሊደርስበት እንደሚችል መገንዘብ የለበትም።

**የህገ ወጥ ቁሶች በቁጥጥር ስር መዋል**
በደንብ የተካሄደ ምርመራ ህገ ወጥ ወይም ኮንትሮባንድ ቁሳቁሶችን የሚያስገኝ ከሆነ፣ እነዚህ ግኝቶች ለተገቢው ህጋዊ ባለስልጣኖች ለመጨረሻ አፈጻጸም ይላካሉ።

# አባሪ L፡ ለተማሪዎች መድሃኒት መስጠት

## ፖሊሲ JHCD

የዚህ ፖሊሲ ዓላማ በትምህርት ቤቶች አንድ ወጥ የሆነ ፣ ጥንቃቄ ያለው የመድሐኒት አሰጣጥ ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ እንዲሁም የተማሪዎችን  የጤንነት ሁኔታ በማሳደግ አንድ መልክ በማስያዝ የተማሪዎችን የአካዳሚክ ውጤታማነት መደገፍ ነው።  በተቻለ መጠን መድኃኒት የመስጠቱ ስራ በወላጆች ወይም በአሳዳጊዎች መከናወን ይኖርበታል። በJHCD-R በተገለፀው መሰረት በአንዳንድ ሁኔታዎች በሐኪም ትእዛዝ ወይም ከሐኪም ትእዛዝ ውጭ በትምህርት ጊዜ መድሐኒት ሊወሰድ ይችላል።

ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች እና በ1973 የመልሶ ማቋቋሚያ አዋጅ አንቀጽ 504  መሰረት ነፃ ተገቢነት ያለው የሕዝብ ትምህርት (FAPE) እድል እንዲያገኙ ለተፈቀደላቸው ሁሉ የመድሐኒት አሰጣጥ በተማሪው የግል የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ወይም 504 እቅድ መሰረት ይከናወናል።

**I ፤ በሐኪም ትእዛዝ የሚሰጥ መድሐኒት**
 “ፍቃድ ካለቸው ባለሞያዎች”(ዶክተሮች፣ ነርሶች፣ ወይም የዶክተር ረዳቶች፣ የዓይን እና የጥርስ ሐኪሞች) በሚሰጥ የፅሁፍ ትእዛዝ ወይም ማዘዣ መሰረት እንዲሁም መድሐኒት እንዲሰጥ ፍቃድ ስምምነት ለመስጠት  ከወላጆች የተፈረመ ፈቃድ ካገኙ የኤ ሲ ፒ ኤስ ሰራተኞች ለተማሪዎች መድሐኒት መስጠት ይችላሉ። እንደዚህ ዓይነቱ መድሐኒት መቅረብ ያለበት በመጀመሪያ በተሰጠበት የመድሐኒት መያዣ እቃ ለትምህርት ቤቱ ነርስ ወይም በርእሰ መምህሩ ለሚወከል ሰው በተማሪው ወላጅ ወይም አሳዳጊ መሰጠት ይኖርበታል። የኤ ሲ ፒ ኤስ ሰራተኞች  ፍቃድ ባለቸው ባለሞያዎች የሚሰጠውን የፅሁፍ ትእዛዝ ይከተላሉ። ራስን የማከም እና በራስ የሚወሰዱ የሐኪም ትእዛዝ የሚወሰዱ መድሐኒቶችን የስኮር፣ አስም እና /ወይም የአለርጂ ህመምተኞችን እንደየሁኔታው ይታያል።

**II፤ ከሐኪም ትእዛዝ ውጭ የሚሰጥ/ቁጥጥር የሌለባቸው መድሐኒቶች**
ፍቃድ ባለቸው ባለሞያዎች የሚሰጠውን የፅሁፍ ትእዛዝ  እንዲሁም መድሐኒቱ እንዲሰጥ ከወላጆች የተፈረመ ፈቃድ ካገኙ የኤ ሲ ፒ ኤስ ትምህርት ቤት የጤና ባለሞያዎች ወይም የሰለጠኑ የኤ ሲ ፒ ኤስ  ሰራተኞች መድሐኒቱን መስጠት ይችላሉ። የዚህ ዓይነቱ ፍቃድ የመድሐኒቱን ስም፣ የተፈቀደውን የመድሃኒት አወሳሰድ መጠን እና መድሀኒቱ የሚሰጥበትን ጊዜ የሚያሳይ መሆን አለበት። የዚህ ዓይነቱ መድሐኒት በመጀመሪያ በተሰጠበት የመድሐኒት መያዣ መሆን አለበት። የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ከወላጅ/

አሳዳጊ የተፈረመ ፈቃድ መስጫ ቅጽ ካላቸው ከሐኪም ትእዛዝ ውጭ የሚሰጡ/ቁጥጥር የሌለባቸው መድሐኒቶች ለምሳሌ አድቪል ፣ ሞርቲን እና ታይላኖል በትምህርት ቤቱ ክሊኒክ የማይገኙ ከሆነ ለአንድ ጊዜ የሚሆን በእጃቸው መያዝ ይችላሉ።

**III፤ ኤፒነፕሪን (EPINEPHRINE)**
የሙያው መስክ በሚፈቅደው አሰራር የሙያ ፈቃድ ባላቸው በሚሰጠው ትእዛዝ መሰረት ማንኛውም የትምህርት ቤቱ ነርስ ፣ የትምህርት ቤት ቦርድ ሰራተኛ ፣ የአካባቢ አስተዳደር አካል ሰራተኛ፣ ወይም የአካባቢ የጤና ዲፓርትሜንት ሰራተኛ ፈቃድ ባላው ሙያተኛ በሰጠው ትእዛዝ መሰረት ኤፒነፕሪን አሰጣጥ ስልጠና ያገኘ ኤፒነፕሪን በመያዝ የአለርጂ ህመም አናፌላክትክ (anaphylactic reaction) ለሚያጋጥማቸው ተማሪዎች መድሐኒቱን መስጠት ይችላሉ።

**IV፤ ዲሲፒሊን**
የዚህን ፖሊሲ እና በተዛማጅ ህጐች የተገለፁትን ደንቦች የሚተላለፉ ተማሪዋች በኤ ሲ ፒ ኤስ የተማሪዋች ባህሪ ህግ በተገለጸው መሰረት የሥነ ሥርዓት እርምጃ ይወሰዳል።

**V፤ ደንብ**
የ JHCD-R ደንብ ለተማሪዋች የመድሐኒት አሰጣጥ የሚመለከት መመሪያ አውጥቶል። ይህም መድሐኒት እንዴት እንደሚያዝ፣ እንደሚቀመጥ፣ ቁጥጥር፣ አመዘጋገብ እና አወጋገድ ያካትታል።

# አባሪ M፡ የተማሪ ድርጅቶች (ሁለተኛ ደረጃ)

## ፖሊሲ IGDA

በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተማሪ ድርጅቶችን አቀናጅቶ ለመስራት እና እነዚህን ድርጅቶች ከትምህርት ሰአት ውጪ በትምህርት ቤት መገናኘትን የሚፈቅድ የትምህርት ክፍሉ ፖሊሲ ነው። የዚህ ፖሊሲ ዓላማ የተማሪ ድርጅቶች ስራን የሚመራውን መስፈርት እና ሥርዓቶችን ማዘጋጀት ነው።

ከስርአተ ትምህርት ጋር የተገናኙ የተማሪ ድርጅቶች የሚከተሉትን ማድረግ አለባቸው፡-

- እንደ የመደበኛው የትምህርት ቤት ስርአተ ትምህርት ቅጥያ ማገልገል አለበት፤
- የተሳታፊዎችን ትምህርታዊ ተሞክሮ ማዳበር፤
- በትምህርት ቤቱ የትምህርት መርሃ ግብር ውስጥ ያሉትን የኮርስ ቁሳቁሶች ማሟላት እና
- ከመደበኛው ስርአተ ትምህርት ጋር ግልጽ የሆነ ግንኙነት መያዝ።

ርእሰ መምህሩ ድርጅቱ ከላይ የተጠቀሱትን መመዘኛዎች የሚያሟላ መሆኑን ይወስናል። ርእሰ መምህሩ ከላይ የተጠቀሱትን መመዘኛዎች የሚያሟሉ ድርጅቶች ፈቃድ በመስጠት በትምህርት ቤቱ እንደሚደገፉ ድርጅቶች እውቅና ይሰጣል።

**በተማሪ የተጀመሩ ድርጅቶች**
የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችም ከትምህርት ሥርዓተ ትምህርት ውጪ ያሉ የተማሪ ድርጅቶችን እንዲያደራጁና ስብሰባዎችን እንዲያከናውኑ ይፈቀድላቸዋል ይህም ከትምህርት ቤቱ ስርአተ ትምህርት ውጪ ያሉ እንቅስቃሴዎችን ለማካሄድ ሆኖ በዚህ ፖሊሲ በተጠቀሱት ደንቦች መሰረት ነው። እንደዚህ ያሉ ድርጅቶች በተማሪ የተነሳሱ እና የሚመሩ መሆን አለባቸው፣ እናም የትምህርት ቤት ሰራተኞች፣ ወላጆችና በክፍሉ ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች ያልሆኑ ማናቸውም ሌሎች ሰዎች ድርጅቶቹን ማዘዝ፣ መቆጣጠር፣ ማከናወን ወይም በርእሰ መምህሩ የተመደበ የፋካልቲው ተቆጣጣሪ እስካልተገኘ ድረስ በመደበኛነት ስብሰባዎችን መካፈልም አይፈቀድላቸውም። ከትምህርት ሥርዓተ ትምህርት ውጪ ያሉ የተማሪ ድርጅቶች በትምህርት ቤቱ እንደሚደገፉ ወይም እውቅና እንዳላቸው መወሰድ አይኖርባቸውም። በዚህ ፖሊሲ ስር እንዲህ ያሉት ድርጅቶች ስብሰባዎችን እንዲያካሂዱ ይፈቀድላቸዋል ማለት የትምህርት ክፍሉ ለነዚህ ድርጅቶች አላማ ወይም ለስብሰባዎቻቸው ይዘት ያለውን ድጋፍ አያሳይም።

**አባልነት**
በሁሉም የተማሪ ድርጅቶች ውስጥ አባል መሆን በአሁኑ ጊዜ በስፖንሰር አድራጊው ትምህርት ቤት ለተመዘገቡ ተማሪዎች ሁሉ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ እና የተገደበ መሆን አለባቸው። የተማሪ ድርጅቶች ከድርጅቱ አላማ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የትምህርት ደረጃ የአባልነት መመዘኛዎችን ሊያዘጋጁ ይችላሉ። የተማሪ ድርጅቶች በተማሪው ዘር፣ ቀለ፣ የትውልድ ሀገር፣ ወይም ሃይማኖት ምክንያት የተማሪን አባልነት አይከለክሉም። አንድ ድርጅት የአትሌቲክስ ክህሎት ላይ ወይም ንክኪ ማድረግ ተጨባጭነት ባለው ስፖርት ላይ በመመሰረት በጾታ ላይ የተመሰረተ የአባልነት መመዘኛ ሊያስቀምጥ ይችላል። ይሁን እንጂ፣ አባልነት በፆታ ማንነት፣ ጾታ መግለጫ፣ ወይም ጾታዊ ዝንዛቤ ላይ በመመርኮዝ ብቻ አይከለከልም።

**የፋካልቲ ቁጥጥር**
ርእሰ መምህሩ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የትምህርት ቤቱ ፋካልቲ አባላትን እያንዳንዱን ስርዓተ ትምህርት ተኮር የተማሪ ድርጅት እንዲደግፉ እና እንዲቆጣጠሩ ይሾማል። የፋካልቲ ድጋፍ ሰጭዎች በድርጅቱ ሁሉም እንቅስቃሴዎች ክትትል እና አመራር ላይ መሳተፍ አለባቸው እንዲሁም በሁሉም ስብሰባዎች ላይም መሳተፍ አለባቸው።

ስርዓተ ትምህርት ተኮር ያልሆኑ በተማሪ የተጀመሩ የተማሪ ድርጅቶች የፋካልቲ ስፖንሰር አይኖራቸውም። ይሁን እንጂ፣ የትምህርት ቤቱ የሙያ ሰራተኛ እያንዳንዱን የእንዲህ ያለ ድርጅት ስብሰባ ለመቆጣጠር ብቻ ተካፋይ ባልሆነ መልኩ ይሳተፋል። ድርጅቱ ለስብሰባው አንድ የሰራተኛ አባል መኖሩን የማረጋገጥ ሃላፊነት አለበት።

ACPS የአንድ የተማሪ ድርጅት ይዘት ከአንድ የትምህርት ቤቱ ሰራተኛ እምነት ጋር የሚጋጭ ከሆነ ያንን ሰራተኛ እንዲህ ባለው ስብሰባ ላይ እንዲገኝ አያስገድድም። ሃይማኖታዊ አምልኮ፣ ጸሎት፣ ወይም ሃይማኖታዊ አላማ እንዳለው የተገለጸ ስርዓተ ትምህርት ተኮር ያልሆኑ የተማሪ ድርጅቶች ስብሰባ ላይ የሚገኙ የትምህርት ቤት ሰራተኞች ተካፋይ ባልሆነ መልኩ መሳተፍ ይኖርባቸዋል።

**የተማሪ ድርጅቶች ስብሰባ**

ሁሉም የተማሪ ድርጅቶች በርእሰ መምህሩ በተሰየመው መሰረት የትምህርት ሰአት ባልሆነበት ወቅት ላይ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ የመገናኘት መብት አላቸው። ACPS በየትኛው የሃይማኖት፣ የፖለቲካ፣ የፍልስፍና ወይም በድርጅቱ ስብሰባዎች ላይ ባለ የንግግር ይዘት በመመስረት በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ከትምህርት ቤት ተቋማት ጋር እኩል የትምህርት አቅርቦትን አይከለክልም። ACPS እንደ ሌሎች የተማሪ ድርጅቶች እኩል በሆነ ሁኔታ በትምህርት ቤቱ ስብሰባዎች የማድረግ እድል ካልሆነ በስተቀር ትምህርት ተኮር ላልሆኑ የተማሪ ድርጅቶች ማንኛውም የገንዘብ ድጎማ ወይም ድጋፍ አይሰጥም።

የእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ርእሠ መምህር የተማሪ ድርጅቶችን ስብሰባዎች የአመዳደብ አሠራር መመሪያዎችን እና ደንቦችን በመቅረጽ ለዚህ አይነት ስብሰባዎች የሚገኙ ቦታዎችን እና ጊዜውን ያስቀምጣል። የትምህርት ተኮር ያልሆኑ የተማሪ ድርጅቶች የስብሰባ ጊዜ ከመደበኛ የትምህርት ጊዜ በፊት ወይም በኋላ ወይም በታወቁ የተግባር ክፍሎች ነው። እነኚህ መመሪያዎች እና ህጎች ለሁሉም ተማሪዎች እንዲገኙ ይደረጋሉ። በዚህ ፖሊሲ መሰረት ስብሰባዎች ለማካሄድ የሚፈልጉ ተማሪዎች በክፍሉ ሂደት መሰረት ለኃላፊው ማመልከቻ ማስገባት አለባቸው።

**ህግና ፖሊሲን ማክበር**

የተማሪ ድርጅቶች ከህግ፣ ከክፍሉ ፖሊሲ፣ ወይም ከትምህርት ቤት ደንቦች ጋር የሚፃረሩ ማንኛውም ድርጊት ላይ ወይም የትምህርት ቤት ስርአት ለማወክ የሚረብሽ ወይም ግልጽ በሆነ መንገድ የሚያደናፍ; ወይም ማንኛውም በማናቸውም ተማሪ ወይም ሰራተኞች ጤና፣ ደህንነት ወይም ሰላም ላይ በአሉታዊ መልኩ የሚነዱ ተግባራት ላይ መሰማራት የለባቸውም። እነዚህን ድንጋጌዎችን ማክበር አለመቻል የዲሲፕሊን እርምጃ መሰረት ሊሆን ይችላል።

# አባሪ N፡ ሐይማኖት በትምህርት ቤቶች ውስጥ

## ፖሊሲ INCD

ACPS ሃይማኖት ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ገለልተኛ መሆን ይኖርበታል። ይህም ማለት ACPS፡-

- ለየትኛውም ተማሪ የሃይማኖት ትምህርት ምንም ዓይነት ሚና ወይም ሀላፊነት አይኖርበትም፣ እና
- በማንኛውም ተማሪ ሃይማኖታዊ እምነቶች፣ በማመን፣ አለማመን ወይም ጥርጣሬ ላይ ተሳትፎ አይኖረውም።

ይህ ገለልተኛነት ACPS ተማሪዎቹ እንዲቻቻሉ እና የሃይማኖትን ልዩነት የሚያከብሩ እንዲሆኑ የማስተማር ኃላፊነቱን አይገድብም። በተጨማሪም የACPS ሃላፊነት የተማሪዎቹን እውቀት ማሳደግ እና ሃይማኖት በአንድ ህብረተሰብ ማህበራዊ፣ ባህላዊ እና ታሪካዊ እድገት ውስጥ ውስጥ የተጫወተውን ሚና አድናቆት ማሳደግ እንደሆነ ይገነዘባል።

ስለሆነም ACPS በሃይማኖታዊ እምነት እና/ወይም በሃይማኖት ልዩነቶች ላይ የተመሰረቱ እምነቶችን እንዲያውቁ እና ሁሉም ተማሪዎችና ሰራተኞች አባላት በሃይማኖታዊ እምነት እና/ወይም በሃይማኖት ልዩነቶች ላይ እንዲያተኩሩ ከማበረታታት አንጻር የሚያየው ይሆናል።

በዛህ የአክብሮት መንፈስ፣ ተማሪዎች እና ሰራተኞች ከሃይማኖታዊ እምነታቸው ጋር ተቃራኒ በሆኑ እንቅስቃሴዎች ከመሳተፍ ሊያመልጡ ይችላሉ።

# አባሪ O፡ ስለ አወዛጋቢ ጉዳዮች ማስተማር

## ፖሊሲ INB

የትምህርት ቤቱ ቦርድ ከትምህርት ዋና ዓላማዎች አንዱ ውጤታማ ዜግነት ለማግኘት እንደሆነ ይቀበላል እናም ለዚህ ስራ ውጤታማነት ዝግጅት በግለሰቦች ወይም በቡድን የተለያዩ አመለካከቶች የሚያዙባቸውን ጉዳዮችን ማጥናትን ያካትታል።

እንደነዚህ ባሉ ጉዳዮች ላይ Alexandria City Public Schools ቤቶች በአስተማሪ የተመደቡ ጉዳዩች ላይ ጥናት እንዲካሄድ መፍቀድን አላማ መሆን ይኖርበታል። ተማሪው፡-

- በትምህርት ቤቱ ውስጥ ለሚገኙ ሁሉም አስፈላጊ መረጃዎች እና ቁሳቁሶች ነፃ ተደራሽነት የመኖር፤
- ከአድልዎ እና ጭፍን ጥላቻ ነጻ በሆነ ከባቢ ውስጥ ምርምር ሊያደርግ ይገባዋል፤
- በተመደበው ጉዳይ ላይ አስተያየቶችን መፍጠር እና መግለጽ ይኖርበታል።

የተመደቡ ጉዳዮችን ማቅረብ ላይ የመምህሩ ሚና በጣም ወሳኝ ነው። የእትሙ ሁሉም ክፍሎች ለተማሪዎቹ ቀስ እየተባለ መሰጠት አለበት። ግቡ ተማሪዎች በሁሉም አስፈላጊ ጉዳዮች ላይ ግልፅ በሆነ መንገድ ማሰብ እንዲማሩ እና  ከቀረቡት ቁሳቁሶች ሁሉ እና በጉዳዩ ላይ ምርምር ሊደረግ ከሚቻለው አንጻር ውሳኔ እንዲያደርጉ ነው። አስተሳሰብን ወደ ሆነ አቅጣጫ መቀየር የትምህርት ክፍሉ አላማ ወይም አስፈላጊነት አይደለም።

አወዛጋቢ ጉዳዮችን በሚወያዩበት ጊዜ እና አስተያየትን ሲገልጹ፣ ተማሪዎች አስተያየታቸውን፣ እውነታዎቻቸውን እና ማረጋገጫዎቻቸውን ለመደገፍ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ማበረታታቱ አስፈላጊ ነው። ከአንድ አወዛጋቢ ጉዳይ፣ ችግር ወይም ውሳኔ ጋር የተዛመዱ በርካታ አስተያየቶችን እንዲመለከቱ ሊበረታቱ ይገባል - ለምን አንድ የተወሰነ ጉዳይ ብዙ አመለካከቶችን

እና አስተያየቶችን ሊያስነሳ እንደሚችል ጨምሮ። እንዲህ ያሉ ጉዳዮችን የማወዳደር እና ምንጮችን የመገምገም አሳሽ የአስተሳሰብ ክህሎቶች መዛባትን ሊያሳዩ የሚችሉ ማስረጃዎች ግምገማና ትንታኔዎች ጨምሮ ወይም ፕሮፓጋንዳ በክፍል ዘውግ ውስጥ ከአወዛጋቢ ጉዳዮች ጋር ለመጋፈጥ አስፈላጊ ናቸው።

በተገቢው ግዜ ወይም በተጠየቀ ጊዜ አስተማሪው አስተያየቱን ሊሰጥ ይችላል ነገር ግን የተሰጠው የአስተማሪው አስተያየት መሆኑ ግልጽ መደረጉ ማረጋገጥ አለበት።

የትምህርት ቤት ክፍሉ የትምህርት መርሃ ግብር በዩናይትድ ስቴትስ የፖለቲካ ስርዓት በርካታ ገጽታዎችን የሚያካትት ቢሆንም, የትምህርት ቤት ፕሮግራም ቦርድ ተማሪዎችን በግለሰብ ፓርቲ ወይም እጩ ላይ የፖለቲካ ድጋፍ እንዲሰጥ በሚያደርጉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የተማሪዎችን ተሳትፎ እንደ ማጽደቅ አይደግፍም።

# አባሪ P፡ የውሲብ መደፈር/ በዘር ፣ ብሄራዊ ማንነት፣ የአካል ጉዳት፣ ሐይማኖት፣ አድሜ ፣ ፃታ፣ የፃታ ማንነት፣ የፃታ መገለጫ እና የውሲብ ምርጫ፣ / አስጨናቂ የስራ አካባቢ

## የ GBA/JFHA ፖሊሲ

### I. ፖሊሲ መግለጫ

**የስቴትና ወይም የፌደራል ህግ መጣስ የሚፈፀም አድሎ**
የአሌክሳንደሪያ ከተማ ት/ቤት ቦርድ አስገድዶ መድፈር፣ በዘር ፣ ብሄራዊ ማንነት፣ የአካል ጉዳት፣ ሐይማኖት፣ እድሜ ፣ ፃታ፣ የፃታ ማንነት፣ የፃታ መገለጫ እና የውሲብ ምርጫ፣ ጋር የተያያዘ ከአድሎ ነፃ የሆነ የትምህርትና የስራ አካባቢ ለመፍጠርና ለመጠበቅ በቁርጠኝነት ይሰራል። በመሆኑም የአሌክሳንደሪያ ከተማ ት/ቤት ቦርድ በትምህርት ቤት ውስጥ ወይም በትምህርት ቤቱ ኋላፊነት በሚዘጋጁ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የውሲብ መደፈር እና በዘር ፣ ብሄራዊ ማንነት፣ የአካል ጉዳት፣ ሐይማኖት፣ አድሜ ፣ ፃታ፣ የፃታ ማንነት፣ የፃታ መገለጫ እና የውሲብ ምርጫ፣ ጋር የተያያዘ አድሎ በማንኛውም ተማሪ እና የት/ቤት ሠራተኛ ላይ መፈፀም ክልክል ነው።

ማንኛውም ተማሪ ወይም የት/ቤት ሠራተኛ በሌላ ተማሪም ወይም ሠራተኛን ማዋከብ በወሲብ ወይም በዘር ፣ ብሄራዊ ማንነት፣ የአካል ጉዳት፣ ሐይማኖት፣ አድሜ ፣ ፃታ፣ የፃታ ማንነት፣ የፃታ መገለጫ እና የውሲብ ምርጫ፣ ጋር የተያያዘ የማዋከብ ስራ ይህን ፖሊሲ መጣስ ነው። ከዚህ በተጨማሪ በት/ቤት በኋላፊነት ላይ ያለ የት/ቤት ሰራተኛ የወሲብ ማዋከብን ወይም በዘር ፣ ብሄራዊ ማንነት፣ የአካል ጉዳት፣ ሐይማኖት፣ አድሜ ፣ ፃታ፣ የፃታ ማንነት፣ የፃታ መገለጫ እና የውሲብ ምርጫ፣ ጋር የተያያዘ የማዋከብ ስራን በቸልተኝነት ለማለፍ ቀለል ያለ እርምጃ የሚወስድ ሰው ይህን ፖሊሲ የሚጥስ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ እላይ በተጠቀሰው እና በፌደራል ህግ ሁሉንም ተማሪዎችና የት/ቤት ሰራተኞችን ጥበቃ ካማድረግ በተጨማሪ የት/ቤት ቦርዱ በማንኛውም የሰራተኛ ቅጥር በእድሜ ምክንያት አድልዋ መፈፀም ህገወጥ ነው። እንዲሁም የት/ቤት ሰራተኞችን በእድሜ ምክንያት ማዋከብ ህገወጥ ነው። ማዋከብ የሚያጠቃልለው ለምሳሌ ስለ ግለሰቡ እድሜ አጸያፊ ወይም የንቀት አስተያየት መስጠትን ይጨምራል። ህጉ ቀላል የቀልድ ጨዋታን ፣ ያልታሰበ አስተያየትን፣ ወይም በአጋጣሚ የሚፈጠር ክስተትን የሚከለክል ባይሆንም ማዋከብ ሕገ ወጥ ይሆናል ተደጋጋሚና ወይም ከባድ ሁኖ አስጨናቂ ወይም አስቀያሚ የስራ አካባቢን የሚፈጥር ከሆነ ወይም ጥሩ ያልሆነ የቅጥር ውሳኔ ላይ የሚደረስ ከሆነ። የሚያዋክበው ሰው የተጠቂው ተቆጣጣሪ ሊሆን ይችላል ፣ በሌላ የስራ ክፍል ያለ ተቆጣጣሪ ፣ የስራ ባልደረባ ፣ ወይም ሰራተኛ ያልሆነም ሊሆን ይችላል።

የትምህርት ቤት አስተዳደሩም (1) ማንኛውንም ቅሬታ ፣ በፅሁፍ ወይም በቃል የቀረበ የወሲብ ማዋከብ ወይም በዘር ፣ ብሄራዊ ማንነት፣ የአካል ጉዳት፣ ሐይማኖት፣ አድሜ ፣ ፃታ፣ የፃታ ማንነት፣ የፃታ መገለጫ እና የወሲብ ምርጫ፣ ጋር የተያያዘ የማዋከብ ስራን ወዲያውኑ የማጣራት ፣ (2) የማዋከብ ስራውን ለማስቆም ተገቢውን አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ፣ እና(3) ይህን ፖሊሲ በሚጥስ ማንኛውም ተማሪ ወይም የት/ቤት ሰራተኛ ላይ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ እና በት/ቤት ሰራተኞች ወይም ተማሪዎች ላይ ሌላ ተጨማሪ የማዋከብ ስራ እንዳይፈጠር ለመካላከል ሌላ ተጨማሪ እርምጃ መውሰድ ።

**ሌላ አይነት የማስፈራራት፣ የማዋከብ እና/ወይም የማስጨነቅ ተግባር**
በተጨማሪም በህግ ከታገዱት የማዋከብ ወይም የአድልዎ ተግባራት ባሻገር ከማስፈራራት፣ ከማዋከብ ፣ ወይም ከሚያስጨንቅ ሂኔታ ነፃ የሆነ መልካም የባለሞያ ስራ አካባቢን/ የትምህርት አካባቢን መፍጠር የኤሲፒኤስ ዓላማ ነው። የአሌክሳንደሪያ ከተማ ትምህርት ቤት ቦርድ ደህንነቱ የተጠበቀ ፣ ጤናማ ፣ እና የባለሞያ ስራ አካባቢ ለመፍጠር በቁርጠኝነት ይሰራል። ቦርዱ እንደሚገነዘበው ከፍ ያለ የትምህርት ደረጃ ላይ ለመድረስ ሁሉም ተማሪዎች እና ሰራተኞች ለስራ ምቹ የሆነ እና መልካም የትምህርት አካባቢ መፈጠር ይኖርበታል።

ስለሆነም የት/ቤት ቦርዱ ለስራ የማያመች እና በስራ ላይ መከባበር የማይፈጥር ባህሪ በጥብቅ ይከለክላል። ሰራተኞችና ተማሪዎች አስፈሪ፣ የሚያዋርድ ወይም የሚያስጨንቅ ባህሪ፣ ስሜት የሚጐዳ ቋንቋ ወይም ተግባራት፣ ማስፈራራት፣ ማጨናነቅ ፣ መዛት፣ አድሎ ወይም የቂም በቀል ባህሪ ማሳየት አይኖርባቸውም።

### II. ትርጉሞች

**A. የወሲብ ማዋከብ**
የወሲብ ማዋከብ የሚያጠቃልለው ያልተፈለገ የወሲብ ጥያቄ፣ የወሲን ውለታ ጥያቄ፣ ከዊሲብ ፍላጐት የሚያሳይ የሰውነት እንቅስቃሴ ወይም ሌላ የቃላት ወይም የአካል መግለጫ ወይም ከወሲብ ጋር የተያያዘ ንግግር መፈፀም ማለትም (1) ይህ ድርጊት ወይም ንግግር መቀበል በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ስራ ለማግኘት ወይም በስር ለመቆየት ወይም ለትምህርት እንደ አንድ ቅድመ ሁኔታ ከተቆጠረ ወይም (2) ለዚህ ዓይነቱ ጥያቄ መቀበል ወይም በመቃወም የሚሰጥ መልስ በግለሰቡ የቅጥር ወይም የትምህርት ሁኔታ ላይ ተፅእኖ የሚያሳድር ከሆነ ወይም (3) ይህ ባህሪ ወይም ግንኙነት በአብዛኛው ወይም ባልተገባ መልኩ በግለሰቡ የቅጥር ወይም ትምህርት ላይ ተፅእኖ የሚያሳድር ከሆነ ወይም የሚያስጭንቅ ፣ የማይመች ወይም አስቀያሚ የስራ ወይም የትምህርት ሁኔታ የሚፈጥር ከሆነ (ለምሳሌ ሃብሪው ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰ የተማሪውን ወይም የሰራተኛውን የመማር ወይም የመስራት ተሳትፎ ወይም ከትምህርት ፕሮግራሙ ወይም ከስራ አካባቢ ሁኔታ የሚገድብ ከሆነ ) ።

የወሲብ ማዋከብ የሚያሳይ የብሃሪ ምሳሌዎች እላይ የተጠቀሰውን ትርጉም የሚያሞሉ የሚከተሉትን ይካትታል፤

ያልተፈለገ የውሲብ አካላዊ ግንኙነት፣ ያልተፈለገ ቀጣይነት ያለው ወይም የተደጋገመ የማሽኮርመም ወይም የወሲብ ጥያቄ ማቅረብ ወይም አስተያየት መስጠት፣ የወሲብ አባባል፣ መጥፎ አስተያየት፣ ማስፈራራት፣ ስድብ ፣ የሚያስቀይም አገላለፅ ወይም የወሲብ የሚነካ አገላለፅ ፣ የሰውነት ቀርጽ የሚመለከት የግለሰብ የሰውነት ቅርፅ ፣

የወሲብ ቀልዶች፣ ታሪኮች፣ ስእሎች፣ የአካል እንቅስቃሴዎች ወይም ስእሎች የወሲብ ሀሜቶች፣ የግለሰብ ሰውነት ወይም ልብስ በወሲብ ፍላጐት በሚያሳይ መልኩ መንካት፣ የወሲብ እቃዎችን፣ ስእሎችን፣ ካርቱን ወይም ፖስተር ማሳየት፣ እንቅስቃሴን በሚገድብ ወይም በሚዘጋ መልኩ በወሲብ በሚያስፈራ መልኩ ማሳየት ወይም የወሲብ በቀጥታ ወይም በሚጠቁም መልኩ የኤሌክትሮኒክ መልእክት መላክ።

**B. የወሲብ ጥቃት/በዘር ፤ የዘር ምንጭ፣ አካል ጉዳት፣ ሃይማኖት፣ እድሜ፣ ፃታ፣ የፃታ ማንነት፣ የፃታ መገለጫ፣ እና የፃታ ፍለጐት መገለጫ ላይ የተመሰረተ ጥቃት / ጠላትነት ስሜት**
በዘር ፣ ብሄራዊ ማንነት፣ የአካል ጉዳት፣ ሐይማኖት፣ እድሜ ፣ ፃታ፣ የፃታ ማንነት፣ የፃታ መገለጫ እና የውሲብ ምርጫ፣ ጋር የተያያዘ የማዋከብ ስራ የሚያጠቃልለው አካላዊ ወይም የቃላት የሚገለጽ ሲሆን ከግለሰቡ ዘር ፣ ብሄራዊ ማንነት፣ የአካል ጉዳት፣ ሐይማኖት፣ እድሜ ፣ ፃታ፣ የፃታ ማንነት፣ የፃታ መገለጫ እና የውሲብ ምርጫ፣ ጋር የተያያዘ ይሆናል፤ የሚከተለውን ሁኔታ ከፈጠረ፤

- (i) የሚያስጭንቅ፣ ወይም አስፈሪ ወይም የሚያበሳጭ የስራ ወይም የትምህርት ሁኔታ ወይም
- (ii) በአብዛኛው ወይም ከተገቢው በላይ በግለሰቡ ስራ ወይም ትምህርት ላይ ተፅእኖ የሚያሳድር ከሆነ
- (iii) ያለበለዚያም በከፋ ደረጃ የግለሰቡን የመስራት እድል ወይም የተማሪውን የመማር ችሎታ በትምህርት ፕሮግራሙ ከመሳተፍ ወይም ተጠቃሚ ከመሆን የሚገድበው ከሆነ

በዘር ፣ ብሄራዊ ማንነት፣ የአካል ጉዳት፣ ሐይማኖት፣ እድሜ ፣ ፃታ፣ የፃታ ማንነት፣ የፃታ መገለጫ እና የወሲብ ምርጫ ጋር የተያያዘ የማዋከብ ስራ የሚያመለክት ምሳሌዎች ከላይ የተጠቀሱትን ትርጉሞች የሚያካትት፤

- ዘር የሚያንንጥጥ አገላለፅ ያለው ስእላዊ መግለጫ( ግራፊቲ)፣
- ስያሜ መስጠት፣ ቀልዶች፣ ወይም ሃሜት ፣
- በግለሰቡ ዘር ፣ ብሄራዊ ማንነት፣ የአካል ጉዳት፣ ሐይማኖት፣ እድሜ ፣ ፃታ፣ የፃታ ማንነት፣ የፃታ መገለጫ እና የውሲብ ምርጫ፣ ጋር የተያያዘ በእርሱ ላይ ወይም በንብረቱ ላይ የማስፈራራት ወይም በዘር ላይ ፣ ብሄራዊ ማንነት፣ የአካል ጉዳት፣ ሐይማኖት፣ እድሜ ፣ ፃታ፣ የፃታ ማንነት፣ የፃታ መገለጫ እና የውሲብ ምርጫ ላይ ተመስርቶ የሚፈፀም የጭላቻ ተግባር
- በተለምዶ ከሚጠበቀው የጾታ ባህሪና መገለጫ አንፃር ያልተለመደ ባህሪ በማሳየት ምክንያት የማዋከብ ስራ እና
- በዘር ፣ ብሄራዊ ማንነት፣ የአካል ጉዳት፣ ሐይማኖት፣ እድሜ ፣ ፃታ፣ የፃታ ማንነት፣ የፃታ መገለጫ እና የውሲብ ምርጫ፣ ጋር የተያያዘ የፅሁፍ ወይም የምስል እቃዎችን በመለጠፍ ወይ በማሰራጨት እና ገለሰቦችን ማስጨነቅ ወይም ማስፈራራት

**C. ጠላትነት ስሜት የሰፈነበት፣ የሚያዋርድ ወይም የሚያስጨንቅ የስራ አካባቢ**
"ጠላትነት ስሜት የሰፈነበት ፣ የሚያዋርድ ወይም የሚያስጨንቅ የስራ አካባቢ" ማለት የከፋና በጣም የተስፋፋ ባህሪ በስራ አካባቢ በሰፋት የሚታይ እና በሰራተኛው በእርሱ ወይም በእርሶ የስራ አፈፃጸም ላይ ተፅእኖ የሚያሳድር ነው። አነስተኛ የማናናቅ ስራ ፣ ማበሳጨት እና አልፎ አልፎ የሚከሰት (በጣም ከፍተኛ ደረጃ ያልደረሰ ካልሆነ ) እንደ ጠላትነት የሰፈነበት የስራ አካባቢ በሚባለው ከፍተኛ ደረጃ የሚቆጠር አይሆንም። ባህሪው ለአንድ መልካም ሰው አስጨናቂ፣ ጠላትነት ስሜት የሰፈነበት፣ ወይም የሚያስቀይም የስራ ሁኔታ የሚፈጥር ባህሪ መሆን አለበት። ጠላትነት ስሜት የሰፈነበት አስቀያሚ ባህሪ በሚከተሉት ላይ የሚወሰንም ባይሆን የሚያካትታቸው ጉዳዮች፤ አስነዋሪ ቀልዶች፣ማንጓጠጥ፣አባባሎች፣ መጥፎ ስያሜ መስጠት፣ የአካል ድብደባ ወይም መዛት ፣ ማስፈራራት፣ መሳቂያ ማድረግ፣ ስድብ ወይም ማዋረድ ፣ አስቀያሚ ነግሮች፣ ስእሎች እና በስራ አፈፃፀም ሂደት ጣልቃ መግባት የሚያዋክበው ሰው የተጠቂው ተቆጣጣሪ ሊሆን ይችላል ፣ በሌላ የስራ ክፍል ያለ ተቆጣጣሪ ፣ የስራ ባልደረባ ፣ ወይም ሰራተኛ ያልሆነም ሊሆን ይችላል። ተጠቂው ጥቃቱ የደረሰበት ግለሰብ ብቻ ላይሆን ይችላል ሆኖም ግን በዚህ አስቀያሚ ባህሪ የተጐዳ ማንኛውም ሰው ሊሆን እንደሚችል ማስታወስ ተገቢ ነው። ከዚህ በተጨማሪ በማንኛውም የቅጥር፣ የማባረር፣ ክፍያ፣ የስራ ድልድል ፣ እድገት፣ የስራ ቅነሳ ፣ ስልጠና፣ ጥቅም እና ሌሎች ከስራ ጋር የሚያያዙ የቅጥር መስፈርቶችና ሁኔታዎችን አድሎ እንዳይኖር ህጉ ይከለክላል።

**D. ጉልበተኝነት**
"ጉልበተኝነት" ማለት ማንኛውም ለመጉዳት፣ ለማስፈራራት፣ ወይም ተጠቂውን ለማዋረድ በጉልበት የሚፈጸም የማይፈለግ ባህሪ ማለት ነው። ይህም በእርግጥ ወይም በግምት የጉልበት ልዩነት በአጥቂው/አጥቂዎች እና በተጠቂው መካከል ካለ እና ይህም በየጊዜው የሚደገም ከሆነ ወይም ከፍተኛ የስነልቦና ስቃይ የሚያሳድር ድርጊት ከሆነ ይህን ይጨምራል። "ጉልበተኝነት" ባህሪ በሚከተሉት ላይ ብቻ የሚወሰንም ባይሆን የሚያካትታቸው ጉዳዮች፤ በንግግር፣ በኤሌክትሮኒክስ መልእክት እንደ ሣይበር ቡሊንግ (ጉልበተኝነት) ወይም በእውነት ወይም በይሆናል በሚታዩ እንደ እድሜ ያሉ ልዩ መገለጫ ባህሪዎች፣ ወይም መስል ባህሪዎች አላቸው ተብለው ከሚወሰድ/ ከሚወሰዱ ከአንድ ሰው ወይም ቡድን ጋር በማመሳሰል የአካላዊ ወይም የእጅ እንቅስቃሴ አገላለፃች ይጨምራል። የሚያዋክብው ሰው የተጠቂው ተቆጣጣሪ ሊሆን ይችላል ፣ በሌላ የስራ ክፍል ያለ ተቆጣጣሪ ፣ የስራ ባልደረባ ፣ ወይም ሰራተኛ ያልሆነም ሊሆን ይችላል። "ጉልበተኝነት" የተለመዱ ቀልዶችን፣ የጉልበት ጨዋታ፣ ክርክር ወይም የእኩዮች ግጭትን አይጨምርም።

**E.የት/ቤት ሠራተኞች**
"የት/ቤት ሠራተኞች" ማለት የትምህርት ቤት ቦርድ፣ የትምህርት ቤት አስተዳደር ሰራተኞች፣ ተወካዮች፣ በጎ ፈቃደኞችን፣ ስራ ተቋራጮችን፣ ወይም ሌሎት ሰዎች በትምርህት ቤት አስተዳደር የስራ አመራር ወይም ቁጥጥር ስር ያሉትን ያጠቃልላል።

## III. የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት

በደንብ GB-R/GBA-R/JFHA-R የሚደነግገው የደንብ አፅፈጻሚ ኋላፊ እና ተቀያሪ አማራጭ የደንብ አስፅፈፃሚ ኋላፊ የአድሎ፣ የማዋከብ፣ ጉልበተኝነትን፣ እና ጠላትነት ስሜት የሰፈነበት የስራ አካባቢን ወይም በዚህ ፖሊሲ የታገደ ከስነ ስርዓት ውጭ የሆኑ ባህሪ ቅሬታዎችን ተቀብሎ፣ በመመርመር፣ ተገቢውን እርምጃ የሚወስድ እንዲመደብ ያደረጋል። የዚህ ዓይነቱ ደንቦችም እንዴት ቅሬታ እንደሚቀርብ ፣ ምርመራ ፣ እና የእነዚህ ዓይነት ቅሬታ እንዴት እንደሚዘጋ መግለፅ ይኖርበታል።

## IV. የቂም በቀል እርምጃ

የት/ቤት አስተዳደሩ የመድልዎ፣ የግልበተኝነት ፣ጠላትነት ስሜት የሰፈነበት የስራ ሁኔታ ፣ከስነ ሥርዓት ውጭ የሚሆን ባህሪ ወይም በትምህርት ቤት አስተዳዳሩ ተግባር/አሰራር ሂደት የሚመለከት ቅሬታ ባቀረቡ ተማሪዎች፣ ወላጆች ወይም ሰራተኞች ላይ የቂም በቀል እርምጃ መውሰድ ክልክል ነው።

የትምህርት ቤት አስተዳደር ለእንደዚህ ዓይነት የቂም በቀል እርምጃ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል።

## V. አማራጭ የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት የማግኘት መብት

ይህ ፖሊሲ ማንኛውንም ግለሰብ ላጋጠመው መድልዎ ፣ መዋከብ፣ ጉልበተኝነት፣ ጠላትነት ስሜት የሰፈነበት የስራ አካባቢ ወይም ከስነ ሥርዓት ውጭ የሚሆን ባህሪ መፍትሔ በሌላ መንገድ የመፈለግ መብትን በፍትህ ብሄር ክስ ማቅረብን ፣ ወይም በሌላ የውጭ አካል ቅሬታ ማቅረብን ፣ ወይም በስቴት ወይም በፌደራል ህግ መፍትሔ መንገድ መፈለግን አይከለክልም።

## VI. የመከላከል እና ፖሊሲ ማስታወቂያ

በዘር ፣ ብሄራዊ ማንነት፣ የአካል ጉዳት፣ ሐይማኖት፣ እድሜ ፣ ፃታ፣ የፃታ ማንነት፣ የፃታ መገለጫ እና የውሲብ ምርጫ፣ ጋር የተያያዘ ማዋከብን፣ ጉልበተኝነት፣ ጠላትነት ስሜት የሰፈነበት የስራ አካባቢ ወይም ከስነ ሥርዓት ውጭ የሚሆን ባህሪ የመከላከል ስልጠና በተማሪዎች የማስተዋወቂያ ስልጠና እንዲሁም በሰራተኞች በስራ ላይ ስልጠና መካተት ይኖርበታል።

ይህ ፖሊሲ (1) በትምህርት ቤት አስተዳደሩ በሚገኙ እያንዳንዱ ት/ቤት ህንፃ ውስጥ ለተማሪዎች፣ ለወላጆች፣ ት/ቤት ሰራተኞች በሚመለከቱት ግልጽ ቦታ መታየት መቀመጥ አለበጥ፣ (2) በተማሪዎች እና በሰራተኞች መመሪያ መጽሀፍ ውስጥ እና (3) የትምህርት በተጀመረበት 30 ቀናት ውስጥ ለወላጆች መላክ ይኖርበታል። በተጨማሪም ሁሉም ተማሪዎች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ሰራተኞች የደንብ አስፈፃሚ ኋላፊ የመገናኛ መረጃ በየዓመቱ እንዲያውቁት ይደረጋል።

## VII. በሐሰት መወንጀል

ተማሪዎች ወይም የት/ቤት ሰራተኞች ማዋከብ፣ ጉልበተኝነት፣ ጠላትነት ስሜት የሰፈነበት የስራ አካባቢ ወይም ከስነ ሥርዓት ውጭ የሚሆን ባህሪ በተመለከተ ሆን ብለው በሐሰት የወንጀሉ ከሆነ የስነ ስርዓት እርምጃ የሚወሰድባቸው ከመሆኑም በላይ በሲቪል ወይም በወንጀል ሊከሰሱ ይችላሉ።

# አባሪ Q፡ በትምህርት ቤቶች አልኮል እና ሌላ ድራግ

## ፖሊሲ JFCF/JFCI

ከፌደራል፣ የስቴት ወይም በየአካባቢው የሚወጡ ህግጋት እና ደንቦች በመከተል በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ተማሪዎች ባህሪ ደንብ መሰረት ህገወጥ ድራግ መጠቀም እና ተገቢ ያልሆነ አጠቃቀም የተከለከለ ነው ። ማንኛውም ተማሪ በአልኮል መጠጥ ወይም በሌላ ድራግ (AOD) ወይም ተገቢ ያልሆነ የድራግ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ተማሪዎች ባህሪ ደንብ በመጣስ የሚጠረጥር ከሆነ ማንኛውም ሰራተኛ ጉዳዮን ለሚመለከተው ለርእሰ መምህሩ ወይም ለተወካዮ ሪፖርት ማድረግ ይኖርበታል።

የትምህርት ቤቱ ቦርድ የአደገኛ እፅ አለአግባብ መጠቀም የመከላከል ፕሮግራሞች ለተማሪዎች እና ሰራተኞች ስለአልኮል ጎጂ ባህሪ፣ ህገወጥ ድረግ እና/ወይም ህጋዊ ድረግ ያለአግባብ መጠቀም እና የአደገኛ እፅ አጠቃቀም ለመቆጣጠር እርዳታ ለሚፈልጉ የጣልቃ መግባት ፕሮግራሞች እንዲኪያሄዱ ያበረታታል። ተማሪዎችን አለአግባብ ድረግ የመጠቀም ችግር ለመርዳት በተመለከተ ዋነኛው ኋላፊነት ያለው በተማሪዎችና በወላጆች ላይ ነው።

## I. አጠቃላይ

በቨርጅኒያ ህግ § 18.2-247 እንደተገለፀው አልኮል፣ ወይም ቁጥጥር የሚደረግባቸውን ድረጎች መያዝ፣ ቁጥጥር የሚደረግባቸውን ድረጎች የሚመስሉ ወይም ማሪዋና ወይም ሲንተቲክ ካናቢኖይድስ በቨርጅኒያ ህግ § 18.2-248.1፡1 በትምህርት ቤት ግቢ ንብረት ወይም የትምህርት ቤት እንቅስቃሴ በሚካሄድባቸው ቦታዎች ይዞ መገኘት ክልክል ነው።

### A. መባረር

በቨርጅኒያ ህግ § 18.2-248.1፡1 እንደተገለፀው አልኮል፣ ወይም ቁጥጥር የሚደረግባቸውን ድረጎች መያዝ፣ ቁጥጥር የሚደረግባቸውን ድረጎች የሚመስሉ ወይም ማሪዋና ወይም ሲንተቲክ ካናቢኖይድስ በትምህርት ቤት ግቢ ንብረት ወይም የትምህርት ቤት እንቅስቃሴ በሚካሄድባቸው ቦታዎች ይዞ መገኘት ተማሪ መታገድ/መባረር በሚለገፀው ፖሊሲ JGD/JGE መሰረት ከትምህርት ቤት ሊባረር ይችላል። የሱፐር ኢንቴንደንቱ ጉዳዮ በሚመለከት በተገኘው እውነታ እና እነዚያ ልዮ ሁኔታዎች የተፈጠሩ መሆኑ እና ሌላ ዓይነት እርምጃ ተገቢ ስለመሆኑ ሊወሰን ይችላል። በቨርጅኒያ ህግ ታይትል 22.1፣ ምእራፍ 14፣ አንቀፅ 3 መሰረት የዚህ ዓይነቱ የስነስርዓት እርምጃ ሊወሰድ ይችላል።

### B. ለወላጅ እና ለአካባቢው የህግ አስከባሪ ሪፖርት የማድረግ ግዴታ

የደንብ መተላለፍ እና ያለአግባብ እፅ መጠቀም ሪፖርት ማድረግ ህግ በተመለከተ በፖሊሲ CLA መሰረት ርእሰ መምህሩ የፖሊሲውን መጣስ ለወላጅና ለአካባቢው የህግ አስከባሪ ኋይል ሪፖርት ማድረግ ይኖርበታል።

## II. የአካል ጉዳት ያላቸው ተማሪዎች

A. የአካል ጉዳት ያላቸው ተማሪዎች የዚህ ፖሊሲ ክፍል I ዝርዝር ሁኔታዎች ይመለከታቸዋል እናም ልክ ምንም ጉዳት እንደሌላቸው ተማሪዎች እኩል ቅጣት ሊቀበሉ ይችላሉ የታየው ደንብ መጣስ ተማሪው ባለው ጉዳት ምክንያት የተፈጠረ ችግር አለመሆኑን የሚመለከተው የገምጋሚ ኮሚቴ እስከ ወሰነ ድረስ። የመደበኛው የስነስርዓት እርምጃ አወሳሰድ ከመከተል በተጨማሪ በJGDA ፖሊሲ የተቀመጠው የአካል ጉዳት ያላቸው ተማሪዎች የስነስርዓት እርምጃ ዝርዝር አፈፃፀም በስራ ላይ ይውላል።

B. የድረግ ህግ በመተላለፍ የአካል ጉዳት ያላቸው ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ማስወጣት ተጨማሪ ሥልጣን

1. እላይ በንዑስ ክፍል A ከተሰጠው ሥልጣን በተጨማሪ የአካል ጉዳት ያለው ተማሪ ያለ ወላጅ ፈቃድ ከትምህርት ቤት ሊወጣና ለአርባ አምስት(45) ቀናት ላልበለጠ ጊዜ በጊዚያዊነት በሌላ የትምህርት ፕሮግራም ሊመደብ ይችላል በትምህርት ቤት ውስጥ ባለበት ወቅት፣ በግቢ ወስጥ ባለበት ሰዓት በስቴቱ ኋላፊነት ወይም በአካባቢው የትምህርት ተቋማት፤ በሚካሄድ ዝግጅት ተማሪው አውቆ ከያዘ ወይም ህገወጥ እፅ ከተጠቀመ ወይም ከሸጠ ወይም ቁጥጥር የሚደረግበትን ድረግ እንዲሸጥለት ከፈለገ። ይህ ምርጫ አለ ምንም እንኳን የችግሩ መገለጫ ቢኖርም ። የማስወጣት አሰራር የአካል ጉዳት በሌለው ተማሪ ላይ ተፈፃሚ ከሚሆነው በላይ የበለጠ መሆን አይገባውም።

2. የአስራ-አራት (45) የትምህርት ቀናት ማገድ በሚመለከት “ሕገወጥ ድረግ” እና “ ቁጥጥር የሚደረግበት እፅ” በሚከተለው ትርጎሜ አለው፤

   a. ቁጥጥር የሚደረግበትን መድሐኒት ማለት መድሐኒት ወይም ሌላ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ድረጎች በሕግ (21 U.S.C. 812(C) በክፍል 202(c) V በዝርዝር ሠንጠረዥ I ፣ II፣ III፣ IV ወይም V የተካተቱ ድረጎች ናቸው።

   b. ሕገወጥ መድሐኒት (ድረግ) ማለት ቁጥጥር የሚደረግባቸውን ነገሮች ነገር ግን ቁጥጥር የሚደረግባቸውን በሕጋዊ መንገድ የተገኘና በጤና ባለሞያ ትእዛዝ ወይም በሕግ በተገለፀው ወይም በሌላ የፌደራል ሕግ በተገለፀው መሰረት የሚወስድ መድሐኒትን አይጨምርም።

**Alexandria City Public Schools**
1340 Braddock Place • Alexandria, VA 22314 • 703-619-8000

www.acps.k12.va.us @ACPSk12 and @ACPSespanol /ACPSk12 and /ACPSespanol